# መንግሥትና ፡ የሕዝብ ፡ አስተዳደር።

**ተጻፈ፡**
**ከነጋድራስ ፡ ገብረ ፡ ሕይወት ፡ ባይከዳኝ ።**

መዠመሪያ ፡ በልዑል ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ተፈሪ፡ መኰንን ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ የካቲት ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፲፪ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ታተመ ።

ሁለተኛ ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ፡ በ፴፩ኛው ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ ም ▪ በንግድ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ

**አዲስ ፡ አበባ፤ኢትዮጵያ ።**

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# መንግሥትና፡የሕዝብ፡አስተዳደር።

ተጻፈ፡

ከነጋድራስ ፡ ገብረ ፡ ሕይወት ፡ ባይከዳኝ ።

መዠመሪያ ፡ በልዑል ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡
ተፈሪ፡ መኰንን ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ የካቲት ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፲፮ ፡
ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ታተመ ።

ሁለተኛ ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኀይለ
፡ ሥላሴ፡

በ፳፩ኛው ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ ም -
በንግድ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ።

**አዲስ ፡ አበባ፤ኢትዮጵያ ።**

## ማውጫ

መቅድም። ....................................................11
፩ኛ፡ ምዕራፍ። ....................................................13
፪ኛ፡ ምዕራፍ። ....................................................15
፫ኛ፡ ምዕራፍ። ....................................................21
፬ኛ፡ ምዕራፍ። ....................................................29
፭ኛ፡ ምዕራፍ። ....................................................40
የሥራን፡ ሚዛንና፡ የዋጋን፡ ትርጒም፡ ከሦስት፡ ትንንሽ፡ ክፍል፡ ይከፍሏል። .......................... 40
መዠመሪያ፡ ክፍል።.......................... 40
ሁለተኛ፡ ክፍል።.......................... 50
ሦስተኛ፡ ክፍል ።.......................... 51
፮ኛ፡ ምዕራፍ። ....................................................57
የለውጥና፡ የንግድ፡ ማስረጃ። .......................... 57
መልሱ፡ አጭር፡ ነው።.......................... 66
መዠመሪያ። .......................... 67
ሁለተኛ። .......................... 69
ሦስተኛ። .......................... 70
፯ኛ፡ ምዕራፍ። ....................................................75
፰ኛ፡ ምዕራፍ።....................................................95
፱ኛ፡ ምዕራፍ። ....................................................100
፲ኛ፡ ምዕራፍ። ....................................................104

፲፩ኛ፡ ምዕራፍ። ........................................................112

፲፪ኛ፡ ምዕራፍ። ........................................................118

፲፫ኛ፡ ምዕራፍ። ........................................................126

፲፬ኛ፡ ምዕራፍ። ........................................................129

፲፭ኛ፡ ምዕራፍ። ........................................................137

፲፮ኛ፡ ምዕራፍ። ........................................................146

ስለደራሲው በጥቂቱ .............................................. 163


NIGUSS DIGITAL LIBRARY

## ነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ፡ (፲፰፻፸፰ -- ፲፱፻፲፪ ዓ.ም )።



ነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ በ፲፰፻፸፰ ዓ.ም ትግራይ ውስጥ፣ ዓድዋ አካባቢ ማይ መሻም በተባለ ስፍራ ተወለዱ። አባታችው ሻለቃ ባይከዳኝ ገብረዝጊ የንጉሰ ነገሥት አፄ ዮሐንስ ፬ኛ ባለሟል ስለነበሩ በንጉሰ ነገሥቱ የመጨረሻ ዘመቻ (የመተማ ዘመቻ) ተሳትፈው በጦርነቱ ላይ ስለሞቱ ሕፃኑ ገብረሕይወት ከእናቱ ጋር መኖር ጀመረ። ከንጉሰ ነገሥት አፄ ዮሐንስ ፬ኛ ሞት በኋላ ትግራይ ውስጥ በሰፈነው አለመረጋጋትና በወቅቱ በአገሪቱ ተከስቶ የነበረው ረሀብ አካባቢውን አስጨንቆት ስለነበር ገብረሕይወት ገና በሰባት ዓመቱ ከሌሎች ጓደኞቹ ጋር ሆኖ ወደ ኤርትራ ተሰደዱ። ኤርትራ ውስጥ ምፅዋ አካባቢ ይገኝ ወደነበረ በአንድ የስዊድን

ሚሲዮን ትምህርት ቤት ገብተው መማር እንደጀመሩ ከዕለታት አንድ ቀን ወደ ምፅዋ ወደብ ሄዱ። በወቅቱም በወደቡ ላይ መልህቋን ጥላ ወደነበረች መርከብ ውስጥ ገብተው መርከቧን ማየት ይጀምራሉ። የመርከቧ መነሻ ሰዓት ሲደርስ ገብረሕይወት ከጓደኞቹ ተነጥሎ ቀረ። የመርከቧ ካፒቴን የገብረሕይወትን ተደብቆ መቅረት ያወቀው ብዙ ከተጓዙ በኋላ ስለነበር ምንም ማድረግ ሳይችል ቀረ። መርከቧ ከማረፊያ ቦታዋ ስትደርስ ካፒቴኑ ገብረሕይወትን ለአንድ ኦስትሪያዊ ሀብታም ቤተሰብ በጉዲፈቻ እንዲያሳድገው ሰጠው።

ኦስትሪያዊው ቤተሰብም ገብረሕይወትን ተቀብሎት በዚያው መኖር ጀመረ። ከጥቂት ጊዜ በኋላም ትምህርት ቤት ገባ። በትምህርት አቀባበሉ ቀልጣፋና ጎበዝ የነበረው ታዳጊው ገብረሕይወት ብዙ ጊዜ ሳይፈጅበት ጀርመንኛ ቋንቋን አቀላጥፎ መናገር ቻለ። ከዚያም ወደ ጀርመን ሄዶ እንዲማር ስለተወሰነ ወደ በርሊን ዩኒቨርሲቲ ገብቶ የሕክምና ትምህርት አጥንቶ ተመረቀ። በወቅቱ የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገሥት የነበሩት ዳግማዊ አፄ ምኒልክ በመታመማቸው ንጉሰ ነገሥቱ ከጀርመን መንግሥት ሦስት ሃኪሞች እንዲመጡላቸው ጠይቀው ነበር። የጀርመን መንግሥትም ጥያቄውን ተቀብሎ ወደ ኢትዮጵያ የሚላኩ ሐኪሞችን ሲመርጥ ሐኪም ገብረሕይወት ባይከዳኝ አንዱ መሆን ቻለ። ይህን እድል በማግኘቱም አሳዳጊዎቹን አመስግኖ ተሰናበተ። ገብረሕይወት ከሌሎች ሁለት ሐኪሞች ጋር በመሆን ወደ ኢትዮጵያ መጣ።

እነ፡ ገብረሕይወት፡ ኢትዮጵያ፡ ሲደርሱ፡ ንጉስ፡ ነገሥት፡ ዳግማዊ፡ አፄ፡ ምኒልክ፡ ታመው፡ ስለነበር፡ የተቀበሏቸው፡ እቴጌ፡ ጣይቱ፡ ነበሩ። እቴጌዋም፡ ከገብረ፡ ሕይወት፡ ጋር፡ የመጡትን ጀርመናውያን ሐኪሞች ተቀብለው ገብረሕይወት ‹‹ችሎታ አይኖረውም›› በሚል ጥርጣሬ የሕክምና ስራ እንዳይሰሩ ከልክለዋቸው ነበር ይባላል። ገብረሕይወት ኢትዮጵያን የለቀቀው ገና የሰባት ዓመት ልጅ ሳለ ስለነበር የኢትዮጵያን ባሕልና ቋንቋ ረስቶት ነበር። ደጃዝማች ይገዙ በሃብቴ ለገብረሕይወት አማርኛ የሚያስተምረው ሰው መደቡለት። በሰባት ወራት ውስጥም አማርኛን በሚገባ አቀላጥፎ መናገር ቻለ። አቀላጥፎ መናገር ብቻም ሳይሆን ከጥሩ ዝርው ስነ-ጽሑፍ ፀሐፊዎች መካከል አንዱ እስከመሆን ያደረሰውን

ችሎታ አሳይቶበታል። ከገብረሕይወት መጻሕፍት መረዳት እንደሚቻለው ገብረሕይወት የአማርኛ ቋንቋን እጅግ ተራቅቆ ጽፎበታል።

ንጉሰ ነገሥት ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ከሕመማቸው ካገገሙ በኋላ ደጃዝማች ይገዙ በሃብቴ እና ነጋድራስ ኃይለጊዮርጊሥ ወልደሚካኤል (በኋላ ቢትወደድ) ለንጉሰ ነገሥቱ ስለገብረሕይወት ነገሯቸው። ንጉሰ ነገሥቱም ስለገብረሕይወት በሰሙት ነገር ተደስተው ገብረሕይወትን አስጠሯቸው። ስለትምህርታቸው ከጠየቋቸውና ካነጋገሯቸው በኋላም የራሳቸው የግል ፀሐፊና አስተርጓሚ አድርገው ሾሟቸው። ገብረሕይወት ገና በሕፃንነታቸው የትውልድ ቀያቸውን ለቀው በመሄዳቸው ከወላጆቻቸው ጋር ተረሳስተው ይኖሩ ነበር። ንጉሰ ነገሥት ዳግማዊ አፄ ምኒልክም ይህንን ችግር ተመልክተው አዋጅ አስነግረው ከወላጆቻቸውና ከዘመዶቻቸው ጋር እንዲገናኙ አድርገዋል።

ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ከሕመማቸው ጨርሰው ሊድኑ ባለመቻላቸው ግንቦት ፲ ቀን ፲፱፻፩ ዓ.ም ልጅ ኢያሱ ሚካኤል የዙፋናቸው ወራሽ መሆኑን በአዋጅ አሳወቁ። ይህንን ሐሳባቸውን ለውጭ መንግሥታት ለማሳወቅ በፈለጉ ጊዜም ወደ ውጭ መንግሥታት በተላከውና በደጃዝማች መሸሻ ወርቄ በተመራው የልዑክ ቡድን ውስጥ ገብረሕይወት አባል ነበር። የልዑክ ቡድኑም የተላከበትን ተግባር አከናውኖ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሷል።



# ግርማዊ፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ቀዳማዊ፡ ኃይለ፡ ሥላሴ።

ተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ሐምሌ ፲፮ ፡ ቀን ፡ ፲፰፻፹፬ ዓ.ም ፡ ከአባታቸው ፡ ከልዑል ፡ ራስ መኰንን ፡ እና ፡ ከእናታቸው፡ ከወይዘሮ ፡ የሺእመቤት ፡ ኤጀርሳ ፡ ጎሮ ፡ በተባለ ፡ የገጠር ፡ ቀበሌ ፡ ሐረርጌ ፡ ውስጥ ፡ ተወለዱ።

(ቀ.ኃ.ሥ.) ከጥቅምት ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፫ እስከ መስከረም ፪ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ነበሩ።



## ጳውሎስ፡ መናመኖ፡

ይህንን፡ የነጋድራስ፡ ገብረ፡ ሕይወትን፡ መጻሐፍ፡ ለመዠመሪያ፡ ጊዜ፡ ለማሳተም፡ ያሰቡበት፡ ምክንያቱ፡ ከዚህ፡ ቀጥሎ፡ ከተጻፈው፡ ደብዳሴ፡ ጋር፡ መጽሐፉን፡ ስላገኙት፡ ነው።

## ይድረስ።

ለልዑል፡ ጌታዬ፡ የኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡ አልጋ፡ ወራሽ፡ ተፈሪ፡ መኰንን፤መድኅኔ፡ ዓለም፡ ጤና፡ ይስጥልኝ፡ ብዬ፡ እጅ፡ እነሣለሁ።

በልዑልነትዎ፡ ፊት፡ የማቀርበው፡ ይህ፡ መጽሐፍ፡ ነጋድራስ፡ ገብረ፡ ሕይወት፡ ለኢትዮጵያ፡ መንግሥትና፡ ለሀገሩ፡ ሕዝብ፡ ዋና፡ ምክር፡ እንዲሆን፡ አስቦ፡ ካራት፡ ዓመት፡ በፊት፡ የጻፈው፡ ነው። ነገር፡ ግን፡ ብዙ፡ ሥራ፡ ነበረበትና፡ ጊዜ፡ ካለማግኘቱ፡ የተነሣ፡ ባንድነት፡ ሳይሰበስበው፡ ስለ፡ ሞተ፡ እኩሉ፡ በርሳስ፡ ጽሕፈት ፥ እኩሉ፡ በቀለም፡ ጸሕፈት፡ እየሆነ፡ ተበታትኖ፡ አገኘሁት።

እኔም፡ የወዳጄ፡ የነጋድራስ፡ ገብረ፡ ሕይወት፡ ድካም፡ በከንቱ፡ እንዳይቀር፡ ብዬ፡ ለመንግሥቱና፡ ለሕዝቡም፡ ትልቅ፡ ጥቅም፡ የሚገኝበት፡ መሆኑን፡ ዐውቄ፡ ከየተበታተነበት፡ ሰብስቤ፡ ባንድ፡ መዝገብ፡ ውስጥ፡ ጻፍሁት።

ነጋድራስ፡ ገብረ፡ ሕይወት፡ በትምርቱና፡ በዕውቀቱ፡ በጣም፡ የተመሰገነ፡ ነበረ። በታዘዘውም፡ ሥራ፡ ላይ፡ በጣም፡ ትጉህ፡ እንደ፡ ነበረ፡ ጌታዬ፡ ልዑልነትዎም፡ ያውቁታል። ነገር፡ ግን፡ በሰው፡ ላይ፡ ሞትን፡ የሚያኽል፡ ዕዳ፡ አለና፤ሰው፡ ሁሉ፡ ያሰበውን፡ ለመፈጸም፡ ባለመቻሉ፡ እጅግ፡ ያሳዝናል። ደግሞም፡ ዕውቀት፡ የሚሉትን፡ ሀብት፡ ለማንም፡ ሰው፡ ማውረስ፡ የማይቻል፡ ስለ፡ መሆኑ፡ የነጋድራስ፡ ገብረ፡ ሕይወት፡ ዕውቀት፡ እንዲያው፡ በከንቱ፡ መቅረቱ፡ ለወዳጆቹ፡ ሁሉ፡ በጣም፡ ያሳዝናል። ነጋድራስ፡ ገብረ፡ ሕይወት፡ ሲሞት፡ ዕድሜው፡ ገና፡ ፴፩፡ ዓመት፡ ነበረ። እስከ፡ ፸ና፡ እስከ፡ ፲፡ ዓመት፡ ቈይቶ፡ ቢሆን፡ አሳቡ፡ እየተደላደለ፡ ዕውቀቱ፡ እየሰፋ፡ ለመንግሥቱና፡ ለሕዝቡ፡ የሚጠቅም፡ ብዙ፡ ሥራ፡ ይሠራ፡ ነበረ። ነገር፡ ግን፡ በላይ፡ እንደ፡ ተናገርሁት፡ በሰው፡ ላይ፡ ሞትን፡ የሚያኽል፡ ዕዳ፡ አለና፡ በልጅነቱ፡ እንዲህ፡ ለመሆን፡ ደረሰ።

ኣሁንም፡ ለዕውቀቱና፡ ለሰውነቱ፡ መታሰቢያ፡ የሚሆን፡ ይህን፡ መጽሐፍ፡ ጽፎልኝ፡ ስለ፡ ሞተ፡ እግዚአብሔር፡ ለነፍሱ፡ ዕረፍት፡ ይስጣት። ለኛም፡ ለመጻሐፉ፡ አንባቢዎች፡ ያገራችንን፡ የኢትዮጵያን፡ ፍቅር፡ በልቡናችን፡ ያሳድርብን።

**ልዑል፡ ሆይ።**

ነጋድራስ፡ ገብረ፡ ሕይወት፡ የጻፈውን፡ ይህን፡ መጽሐፍ፡ ተበታትኖ፡ አግኝቼ፡ ባንድነት፡ ከሰበሰብሁት፡ በኋላ፡ የልዑል፡ ጌታዬም፡ አሳብዎ፡ ሁሉ፡ የኢትዮጵያ፡ ልጆች፡ ፍጹም፡ ዕውቀት፡ የሚያገኙበትን፡ ሥራ፡ ለመሥራት፡ እንደሆነ፡ ዐውቄ፤በጎንዘብዎና፡ በጽሕፈት፡ ማተሚያዎ፡ አሳትመው፡ ለኢትዮጵያ፡ ልጆች፡ እንዲያድሉት፡ ብዬ፡ ከዚህ፡ ደብዳቤዬ፡ ጋራ፡ መጽሐፉን፡ እንዳቀርብልዎ፡ ቍርጥ፡ አሳብ፡ አደረግሁ።

**ልዑል፡ ሆይ።**

የነጋድራስ፡ ገብረ፡ ሕይወት፡ ስሙ፡ እንዳይጠፋ፡ ማሰብዎንማ፡ በገንዘብዎ፡ ልጁን፡ ከትምርት፡ ቤት፡ አግብተው፡ በማስተማርዎ፡ ተረድተነዋል። ደግሞም፡ ልጁን፡ ቢያስተምሩለት፡ ጥቅሙ፡ ለልጁ፡ ብቻ፡ ነው። ይህን፡ መጽሐፉን፡ ቢያሳትሙለት፡ ግን፡ አስቀድሞ፡ ለስሙ፡ መታሰቢያ፡ ይሆናል። ቀጥሎም፡ ለመንግሥትዎና፡ ለሕዝብዎ፡ ሁሉ፡ ትልቅ፡ ጥቅም፡ የሚያስገኝ፡ ነውና፡ ለማሳተሙ፡ ፈቃድዎ፡ እንዲሆን፡ አጥብቄ፡ እለምንዎታለሁ።

መስከረም፡ ፲፡ ቀን፡ ፲፱፻፲፡ ዓመተ፡ ምሕረት፡
ፈቃደኛዎና፡ ታዛዥዎ፡ ጳውሎስ፡ መናመኖ።

# መቅድም።

የዚህ፡ ዓለም፡ ነገር፡ እጅግ፡ ይገርማል። ሰው፡ ከዚህ፡ ቦታ፡ መጣ፡ ሳይባል፡ ይወለዳል በህም፡ ዓለም፡ ጥቂት፡ ጊዜ፡ ሲታገል፡ ቈይቶ፡ በሱ፡ ፈንታ፡ የሚታገሉትን፡ አዲሶች፡ ሰዎች፡ ተክቶ፡ ያልፋል፤ይረሳልም። ሰው፡ ለምን፡ እንዲፈጠር፡ ለምንስ፡ እንዲሞት፡ እንዲህ፡ ነው፡ ለማለት፡ ግን፡ ሥራችን፡ አይደለም። ሰው፡ ሁሉ፡ ለራሱ፡ የሃይማኖት፡ ካህናት፡ አሉትና፡ ከነዚያ፡ ይጠይቅ። እንደዚሁም፡ ደግሞ፡ ሕዝቦች፡ ይወለዳሉ፤ይሞታሉም፤ ያልፋሉም፤ይረሳሉም። ሕዝቦች፡ ከተፈጠሩ፡ ዠምሮ፡ እስኪያልፉ፡ ድረስ፡ ምንም፡ ሕዝቦቹ፡ ዘራቸውና፡ ቋንቋቸው፡ ልዩ፡ ልዩ፡ ቢሆን፡ አስማምቶ፡ የሚያስኬደው፡ ሥርዐት፡ ግን፡ መሠረቱ፡ አንድ፡ ነው። ሕዝቦቹ፡ ሁሉ፡ የሚፈጠሩ፡ በዚህች፡ ምድር፡ ላይ፡ ነው። ሁሉም፡ ምድር፡ የምትሰጠውን፡ ሲሳይ፡ ለማግኘት፡ ይጥራሉ። ቢያገኙ፡ ይበላሉ፤ይጠጣሉ፤ይለብሳሉ፤ ይመቻቸዋልም። ቢያጡም፡ ይራባሉ፤ይጠማሉ፤ይታረዛሉ፤ይቸግራሉም።

ሕዝቦችን፡ ሁሉ፡ የሚፈጥር፡ አንድ፡ አምላክ፡ ነው። ይህም፡ አምላክ፡ የምንለው፡ የሕዝቦች፡ ፈጣሪ፡ ሕዝቦቹን፡ ሁሉ፡ ትክክል፡ አድርጎ፡ ፈጥሮ፡ ላኗኗራቸውና፡ ለልማታቸው፡ የሚያስፈልጋቸውን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ከሁሉ፡ ፈቃድና፡ ሥልጣን፡ ጋራ፡ በጃቸው፡ ሰጥቷቸዋል። ስለዚህ፡ ማናቸውም፡ ሕዝብ፡ ቢለማም፡ ቢጠፋም፡ በገዛ፡ እጁ፡ ነው። ሕዝብ፡ የሚጠፋበት፡ አንዳንድ፡ ጊዜ፡ ምክንያት፡ ቢገኝ፡ ያውም፡ ምክንያት፡ ባንዳንድ፡ ሰው፡ ቢመካኝ፡ ነገሩ፡ ትክክል፡ አይሆንም። የልማትን፡ መንገድ፡ ለማግኘት፡ የሚጥር፡ ሕዝብ፡ ቢገኝ፡ ባንዳንድ፡ ክፉ፡ ሰው፡ ምክንያት፡ ሊጠፋ፡ አይችልም። እንዲሁም፡ ደግሞ፡ የልማትን፡ መንገድ፡ ለማግኘት፡ የማይጣጣር፡ ሕዝብ፡ ባንዳንድ፡ ደጎና፡ ሰው፡ ኃይል፡ ልማት፡ ሊያገኝ፡ አይችልም። ደግሞም፡ ማናቸውም፡ ሕዝብ፡ የሚለማበት፡ መንገድ፡ አንድ፡ መንገድ፡ ብቻ፡ ነው። ማናቸውም፡ ሕዝብ፡ የሚጠፋ፡ ይህንን፡ የልማት፡ መንገድ፡ ትቶ፡ በሌላ፡ መንገድ፡ የሄዶ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ነው።

የሕዝብ፡ አስተዳደር፡ ትምርት፡ ሲባል፡ ሕዝቦች፡ የሚለሙበትንና፡ የሚጠፉበትን፡ መንገድ፡ የሚያሳይ፡ ትምርት፡ ነው። ስለዚህ፡ አንባቢ፡ ሆይ፡ ይህን፡ በፊትህ፡ የተዘረጋውን፡ መጽሐፍ፡ አንብበኸ፡ ለመረዳት፡ ከፈለግኸ፡ ከሥር፡ እስከ፡ ጫፉ፡ በርጋታ፡ አንብበኸ፡ ነው፡ እንጂ፡ አንዱን፡ መሥመር፡ ወይም፡ አንዱን፡ ምዕራፍ፡ አንብበኸ፡ አትፍረድ። እስከ፡ መጨረሻው፡ ዝለቀው፤ከዚያ፡ በኋላ፡ ፍረድ፤እስከ፡ መጨረሻው፡ ለማንበብ፡ ፈቃድኸ፡ ካልሆነ፡ ግን፡ ነገሩ፡ ምንም፡ እንደ፡ ሆነ፡ አትረዳውምና፡ ጊዜኸ፡ በከንቱ፡ ይባክንብኻል፤ስለዚህ፡ ባትምረው፡ ይሻልኻል።

# ፩ኛ፡ ምዕራፍ።

እስቴር፡ ሶምሎ፡ የሚባል፡ የጀርመን፡ ሊቅ፡ እንዲህ፡ ይላል፤ እያንዳንዱ፡ ሰው፡ ሌላውን፡ ሰው፡ ሁሉ፡ አጥቅቶ፡ ለብቻው፡ እንደ፡ ፈቃዱ፡ እንዲኖር፡ ይወዳል። መንግሥት፡ ግን፡ በግዛቱ፡ ውስጥ፡ የሚኖሩትን፡ ኀይለኞች፡ ሁሉ፡ ርስ፡ በርሳቸው፡ እንዲተፋፈሩ፡ የግድ፡ ይላቸዋል። የመንግሥት፡ ጥረቱ፡ ሕዝቡን፡ ሁሉ፡ አስማምቶ፡ በመካከላቸው፡ ሰላም፡ ለማድረግ፡ ነው። ስለዚህም፡ መንግሥት፡ የተሻለውን፡ ሥርዐት፡ እያወጣ፡ ያወጣውንም፡ ሥርዐት፡ እንዳይፈርስበት፡ ባለቤቱ፡ ይጠብቃል። ሥርዐት፡ አውጪውም፡ ዳኛም፡ መንግሥት፡ ራሱ፡ ነው።

ከዳኝነቱ፡ በቀር፡ ሕዝቡን፡ ከፍ፡ ወዳለው፡ የዕውቀትና፡ የሀብት፡ ደረጃ፡ እንዲደርስ፡ የማስተዳደሪያ፡ ደንብ፡ እያወጣ፡ ባወጣውም፡ ደንብ፡ ሕዝቡን፡ በሥርዐት፡ ያስተዳድራል። ሕዝቡንም፡ ማስተዳደር፡ ማለት፡ ጥንት፡ የቈየውን፡ የሕዝብ፡ ጥቅም፡ እንዳይጠፋ፡ መጠበቅ፡ ነው። ሌላውንም፡ ኣዲስ፡ ጥቅም፡ አዘጋጅቶ፡ አውጥቶ፡ በግድ፡ ማስፈጸም፡ ነው። የሕዝቡ፡ ዕውቀትና፡ ሀብት፡ ሲያድግ፡ የመንግሥቱ፡ ሀብትና፡ አሳብም፡ ይሰፋል። የሕዝብ፡ አሳብና፡ ሀብት፡ ሲሰፋ፡ መንግሥት፡ አሳቡን፡ ለማስፈጸም፡ የበለጠ፡ ኀይል፡ ያገኛል።

እንግዲህ፡ እንደ፡ ሊቃ፡ ቃል፡ ከሄድን፡ ዘንድ፤በመንግሥቱ፡ ውስጥ፡ የሚያድር፡ ሕዝብ፡ ዕውቀት፡ የሌለውና፡ ድኻ፡ የሆነ፡ እንደ፡ ሆነ፡ መንግሥቱ፡ ኀይል፡ ሊያገኝ፡ አይችልም። እንኳን፡ በውጭ፡ አገር፡ ሊታፈር፡ የገዛ፡ ሕዝቡም፡ ቢሆን፡ አያፍሩትም። ባገሩ፡ ውስጥ፡ ሽፍታና፡ ወንበዴ፡ ሌባም፡ ይበዛበታል። ሕዝቡ፡ ዕውቀት፡ ሲያድርበት፡ ግን፡ መንግሥት፡ ዐዋቂዎች፡ ሠራተኞችንና፡ ሹማምቶችን፡ ያገኛል። ሕዝቡም፡ ሲበለጽግ፡ መንግሥት፡ በግብር፡ የሚያገኘው፡ ገንዘብ፡ እየበዛ፡ ይሄዳል። ባገሩ፡ ውስጥ፡ ወደ፡ ቀኝና፡ ወደ፡ ግራ፡ መንገድና፡ የምድር፡ ባቡር፡ ቢያሠራ፡ በግዛቱ፡ ውስጥ፡ ሽፍታና፡ ወንበዴ፡ የተነሣበት፡ እንደ፡ ሆነ፡ በፍጥነት፡ ሊያጠፋው፡ ይችላል። ስለዚህም፡ መንግሥት፡ ኀይል፡ ለማግኘት፡ የፈለገ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ሕዝቡ፡ እንዲበለጽግና፡ እንዲማር፡ መጣር፡ ያስፈልገዋል።

ሊቀኍ፡ እንደሚለው፡ ሕዝቦች፡ በላያቸው፡ ባሉት፡ ነገሥታት፡ ውስጥ፡ ሲያድሩ፡ አስተዳደራቸው፡ ስለ፡ ሁለት፡ ነገር፡ ነው። መዠመሪያ፡ ሕዝበ፡ ለመንግሥት፡ የሚገባውን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ እንዲፈጽምለት፡ ይገባል።

ሁለተኛም፡ መንግሥት፡ ሕዝቡ፡ የሚያስፈልገውን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ እንዳያጣ፡ ከሽፍታና፡ ከወንበዴ፡ ከሌባም፡ እንዲጠብቀው፡ ይገባዋል።

መንግሥት፡ ሥርዐቱንና፡ ደንቡን፡ ያወጣል። ሥርዐቱንና፡ ደንቡን፡ ካወጣ፡ በኋላ፡ ግን፡ በገዛ፡ ዐዋጁ፡ ጸንቶ፡ በዚያው፡ ባወጣው፡ ሥርዐትና፡ ደንብ፡ ሕዝቡ፡ ይሄዳል።

በያንዳንዱም፡ መንግሥት፡ የሚያድሩ፡ ብዙ፡ ልዩ፡ ልዩ፡ ነገዶች፡ ይኖሩ፡ ይሆናል። ስለ፡ ሆነ፡ መንግሥት፡ አንዱን፡ ነገድ፡ አጥቅቶ፡ ሌላውን፡ ነገድ፡ ለመጥቀም፡ ሥራው፡ አይደለም። አስተካክለን፡ ካሰብን፡ ዘንድ፡ መንግሥት፡ መቆሙ፡ ለሕዝቡ፡ ሁሉ፡ ጥቅም፡ ነው። መንግሥት፡ ሕዝቡን፡ ሁሉ፡ በትክክል፡ ለመጥቀም፡ ካላሰበ፡ መንግሥት፡ በዙፋኑ፡ ሊቆም፡ አይችልም። ላንዱ፡ ነገድ፡ ወይም፡ ለጥቂት፡ ሰዎች፡ ብቻ፡ ማድላት፡ ለመንግሥት፡ የሚገባ፡ ሥራው፡ አይደለም።

ባንድ፡ መንግሥት፡ ውስጥ፡ የሚያድረው፡ እያንዳንዱ፡ ሰው፡ ለብቻውም፡ እየሆነ፡ እየተባበረም፡ ለጥቅሙ፡ ሲል፡ የሚሠራው፡ ሥራ፡ ብዙ፡ ነው። ነገር፡ ግን፡ ያንዱ፡ ሰው፡ ወይም፡ የማኅበሩ፡ ጥቅም፡ ለሌላው፡ ሰው፡ ወይም፡ ለማኅበሩ፡ ጕዳት፡ ሊሆን፡ ይችላል። አሁን፡ ለምሳሌ፡ አንድ፡ ነገር፡ አመለክታለሁ፤ነጋዴ፡ የሆነ፡ ሰው፡ በኤሮፓ፡ አገር፡ የተሠራ፡ ሸማ፡ ያለቀረጥ፡ እንዲገባ፡ ቢፈቀድለት፡ ዋጋው፡ አንሶ፡ በገበያ፡ ብዙ፡ እየተሸጠለት፡ ብዙ፡ ጥቅም፡ ባገኘበት፡ ነበር። በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ሸማ፡ እየሠራ፡ የሚያድር፡ ሸማኔ፡ በኤሮፓ፡ የተሠራ ሸማ፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ እንዳይመጣ፡ ጭራሹን፡ ቢከለከልለት፡ ወይም፡ ደግሞ፡ ቀረጡና፡ ዋጋው፡ በዝቶ፡ በገበያ፡ ቢሸጥ፡ የኢትዮጵያ፡ ሸማኔ፡ ዋጋው፡ ቅሉ፡ በብዙ፡ ቢሸጥለት፡ እጅግ፡ አድርጎ፡ ይጠቀምበት፡ ነበር።

ደግሞም፡ ሌላ፡ ምሳሌ፡ ባመጣ፡ አይከፋም። ባንድ፡ መንግሥት፡ የሚያድሩ፡ እያንዳንዱ፡ ሰዎች፡ ወይም፡ ማኅበሮች፡ ጥቅማቸው፡ ልዩ፡ ልዩ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ግልጽ፡ ነው። ማገጃም፡ ባይኖር፡ ይህ፡ ልዩ፡ ልዩ፡ የሆነ፡

ጥቅማቸው፡ ርስ፡ በርሱ፡ እየተጋጨ፡ ሁሉም፡ ይጐዱ፡ ነበር። ነገር፡ ግን፡ አጋጁ፡ መንግሥት፡ ነውና ፥ በውስጡም፡ ያሉትን፡ ጥቅማቸው፡ ልዩ፡ ልዩ፡ የሆነ፡ ሰዎችንና፡ ማኅበሮችን፡ በዚያው፡ ባወጣው፡ ደንብ፡ አስማምቶ፡ ያሳድራቸዋል።

ሕዝብ፡ የሚጠቀምበት፡ የማስተዳደሪያ፡ ደንብ፡ እንዴት፡ ያለ፡ እንደ፡ ሆነ፡ በቍርጥ፡ መወሰን፡ አይቻልም።

ዛሬ፡ ደግ፡ የተባለው፡ ደንብ፡ የሕዝቡ፡ ዕውቀትና፡ ሀብት፡ ሲሰፋ፡ ጥቂት፡ ዘመን፡ ቈይቶ፡ የማይጠቅም፡ ሆኖ፡ ይገኛል። እንዲሁም፡ ዕውቀት፡ ላሳቸው፡ ሕዝቦች፡ ደግ፡ የሆነው፡ ደንብ፡ ዕውቀት፡ ለሌላቸው፡ ሕዝቦች፡ ትልቅ፡ ጒዳት፡ ይሆንባቸዋል።

ማናቸውም፡ ዐይነት፡ ደንብ፡ ለዘወትር፡ የሕዝብ፡ ጥቅም፡ አይሆንም። የሚጠቅምበት፡ ጊዜ፡ አለው። አንዱንም፡ ሕዝብ፡ የሚጠቅም፡ ደንብ፡ ሌላውንም፡ ሕዝብ፡ ሁሉ፡ ሳይጠቅም፡ አይቀርም፡ አያሰኝም። ስለዚህ፡ ቀጥሎ፡ የተጻፈውን፡ ቃል፡ ለመናገር፡ ይቻለናል፤ደንብ፡ ሁሉ፡ ምንም፡ ቢጠቅም፡ በተለየ፡ ጊዜያት፡ ውስጥና፡ ስተለየ፡ ሕዝብ፡ ብቻ፡ ነው።

ስለዚህም፡ ጸሓፊው፡ መልካሙ፡ የሕዝብ፡ ኣስተዳደር፡ እንዴት፡ ነው፡ ያለ፡ እንደ፡ ሆነ፤በዚሁ፡ መጽሐፍ፡ ውስጥ፡ ለማሳየት፡ መጣሩ፡ የኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡ ሕዝቡን፡ ለመጥቀም፡ ከፈለገ፡ ዘንድ፡ መልካሙን፡ ያስተዳደር፡ መንገድ፡ ማሳየት፡ ሳንምር፡ ግን፡ ሰው፡ የተፈጠረ፡ ለምን፡ እንደ፡ ሆነ፡ ማወቅ፡ ያስፈልጋል። ተፈጥሮም፡ ምን፡ እንዳገኘ፤የተፈጠረበትንስ፡ ነገር፡ ያገኘው፡ በስንት፡ ዘመንና፡ ድካም፡ እንደ፡ ሆነ፡ ባጭሩ፡ እንመልከት።

# ፪ኛ፡ ምዕራፍ።

ሰው፡ ሲፈጠር፡ ከፍ፡ ያለ፡ አእምሮ፡ ተሰጠው፤ከፍ፡ ያለው፡ ኣእምሮውም፡ ላይ፡ በጊዜ፡ ብዛት፡ ዕውቀት፡ ጨምሮበት፡ የምድር፡ ጌታ፡ ሆነ። ይህንን፡ ዕውቀቱንና፡ ጌትነቱን፡ ግን፡ ሰው፡ ባንድ፡ ጊዜ፡ አላገኘም።

ከተፈጠረበት፡ ዝምሮ፡ እስከ፡ ዛሬ፡ ድረስ፡ ባለፈው፡ ዘመን፡ ውስጥ፡ ብዙ፡ ጊዜ፡ በትጋት፡ ታግሎ፡ ነው፡ ያገኘው።

ሰው፡ ከተፈጠረ፡ ዝምሮ፡ እስከ፡ ዛሬ፡ ድረስ፡ ስንት፡ ዘመን፡ እንዳለፈ፡ ለይተን፡ ለመናገር፡ አይቻለንም። ስለ፡ ሆነ፡ ግን፡ የኤሮፓ፡ ሊቃውንት፡ ከ፻፶ሺ፡ ዓመት፡ በፊት፡ በምድር፡ ላይ፡ ሰው፡ እንደ፡ ነበረ፡ የሚበቃ፡ ምስክር፡ አግኝተናል፡ ይላሉ።

በዳንማርክ፡ ነገር፡ ውስጥ፡ ትልልቅ፡ ረግረጎች፡ አሉ፤እነዚሁም፡ ረግረጎች፡ በያመቱ፡ ዐፈር፡ እየተጨመረባቸው፡ ከታች፡ እየደረቀ፡ ወደ፡ ላይ፡ ያብጣሉ። በያመቱ፡ ስንት፡ ዐፈር፡ እንደ፡ ተጨመረባቸው፡ ቢለካ፡ በስምንት፡ ሺሕ፡ ዓመት፡ ውስጥ፡ ሦስት፡ ክንድ፡ እንዲያብጡ፡ በሒሳብ፡ ተገኘ። ከእነዚህም፡ ረግረጎች፡ በታች፡ ከበሰበሱ፡ ብዙ፡ ዛፎች፡ መካከል፡ ሰው፡ ከደንጊያ፡ ያበጀው፡ መጥረቢያ፡ ተገኘ። ከአባይ፡ ወንዝም፡ ውሃ፡ ጋራ፡ በያመቱ፡ የሚሄደው፡ ዐፈር፡ ምስር፡ ሲደርስ፡ በወንዙ፡ ውስጥ፡ ይረጋል። ከእንደዚህም፡ ያለ፡ ምክንያት፡ የተነሣ፡ በአባይ፡ ወንዝ፡ በታች፡ ያለው፡ መሬት፡ በያመቱ፡ ይወፍራል። በያመቱ፡ ስንት፡ ዐፈር፡ እንደ፡ ተጨመረበት፡ ተለክቶ፡ ታውቋል።

በምስርም፡ አገር፡ ከአባይ፡ ወንዝ፡ ውስጥ፡ በታች፡ የሸክላ፡ ስባሪ፡ ስለ፡ ተገኘ፡ የወንዙ፡ መሬት፡ በያመቱ፡ ስንት፡ እንዲወፍር፡ ታይቶ፡ በዚያው፡ ቢታሰብ፡ ሌላውስ፡ ይቅርና፡ በምስር፡ አገርም፡ ቢሆን፡ ፲፩ሺ፡ ዓመት፡ ከክርስቶስ፡ ልደት፡ በፊት፡ በሥራ፡ የሠለጠነ፡ ሕዝብ፡ የነበረ፡ ይመስላል፡ ይላሉ።

ከየባሕሩም፡ ውስጥ፡ የዕንቍ፡ ትሎች፡ የሚባሉ፡ ትንንሽ፡ አውሬዎች፡ አሉ። ምሥጥም፡ በየበረሓው፡ ትልልቅ፡ ይሳ፡ እንደሚሠራ፡ የዕንቍ፡ ትሎችም፡ ከየወንዙ፡ ውሃ፡ ጋራ፡ ወደ፡ ባሕር፡ የሚሄደውን፡ ዐፈር፡ እየተቀበሉ፡ በባሕሩ፡ ውስጥ፡ ወይም፡ ከባሕሩ፡ ዳር፡ በዚያው፡ ዐፈር፡ ቤቶቻቸውን፡ ይሠሩበታል።

እነዚህም፡ ትሎች፡ የሚሠሩት፡ ቤት፡ በያመቱ፡ እያደገ፡ በዘመናት፡ ብዛት፡ ከባሕሩ፡ መካከል፡ ወይም፡ ከባሕሩ፡ ዳር፡ ትልልቅ፡ ደሴትና፡ አገር፡ ይሆናል። በአሜሪካም፡ አገር፡ ፍሎሪዳ፡ በሚባለው፡ ወረዳ፡ የባሕር፡ ጠረፍ፡ እንደነዚህ፡ ያሉት፡ የዕንቀ፡ ትሎች፡ ቤቶች፡ ተገኝተው፡

በያመቱ፡ ስንት፡ ቊመት፡ እንደሚጨምሩ፡ ታይቶ፡ ቢታሰብ፡ ከተመሠረተ፡ ዠምሮ፡ እስከ፡ ዛሬ፡ ድረስ፡ ፻፵፭ሺ፡ ዓመት፡ አልቻለ፡ ይባላል።

እንሆም፡ ከነዚህ፡ የዕንቅ፡ ትሎች፡ ቤት፡ ውስጥ፡ በላዩ፡ ላይ፡ ትሎቹ፡ ቤቶቻቸውን፡ ሠርተውበት፡ የሰው፡ ዐጥንት፡ ተገኘ፡ ይላሉ። ሰውም፡ ዱሮ፡ የውሃ፡ መቅጃ፡ መሣሪያ፡ ሳይኖረው፡ ለውሃ፡ እንዲቀርበው፡ ሲል፡ እንዳውሬ፡ ከወንዙ፡ ዳር፡ ጕድጓድ፡ እየቈፈረ፡ ይኖር፡ እንደ፡ ነበረ፡ ያስረዳል። እንሆም፡ ያንዳንዱ፡ ወንዞች፡ መሬት፡ ውሃው፡ በያመቱ፡ እየበላው፡ ወደ፡ ታች፡ ሲሰጥም፡ ሰው፡ ሲኖርበት፡ የነበረው፡ ጕድጓድ፡ ፪፻፡ ክንድ፡ የሚያኽል፡ ወደ፡ ላይ፡ ቀረ። ወንዙም፡ በያመቱ፡ ወደ፡ ታች፡ የሚሰጥመው፡ ልክ፡ ስንት፡ እንደ፡ ሆነ፡ ስለ፡ ታየ፡ ጕድጓድ፡ ከተቈፈረ፡ ቀን፡ ዠምሮ፡ እስከ፡ ዛሬ፡ ድረስ፡ ብዙኅ፡ እልፍ፡ ዘመናት፡ አልቻለ፡ ይባላል።

ከእንደዚህ፡ ያለውም፡ ጕድጓድ፡ ውስጥ፡ ብዙ፡ ያጥንት፡ ምልክትና፡ በሰው፡ እጅ፡ የተሠራ፡ የደንጊያ፡ መሣሪያ፡ ተገኘ። ከዚህ፡ ሁሉ፡ ምርማሪ፡ የተነሣ፡ የኤሮፓ፡ ሊቃውንት፡ ሰው፡ ከተፈጠረ፡ ዠምሮ፡ እስከ፡ ዛሬ፡ ድረስ፡ ቢያንስ፡ ፻፶ሺ፡ ዓመት፡ አልፋል፡ ይሳሉ። እንደ፡ መጽሐፍ፡ ቅዱስ፡ ቃል፡ የሆነ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ግን ፥ ዓለም፡ ከተፈጠረ፡ ዝምሮ፡ እስከ፡ ዛሬ፡ ድረስ፡ ከ፯ሺ፡ ፬፻፹፡ ዓመት፡ የሚበልጥ፡ ይመስላል።

ይህንን፡ ግን፡ የኤሮፓ፡ የሃይማኖት፡ ሊቃውንት፡ ሲተረጕሙት፡ በእግዚአብሔር፡ ዘንድ፡ ፩፡ ቀን፡ የሚባለው፡ በሰው፡ ዘንድ፡ ሺሕ፡ ዓመት፡ ነውና፡ እግዚአብሔር፡ ዓለምን፡ የፈጠረ፡ በ፮፡ ቀን፡ ነው፡ ቢባል፡ በ፮፡ ክፍል፡ እንደ፡ ማለት፡ ያኽል፡ ነው። እስራኤላውያንም፡ ከክርስቶስ፡ ልደት፡ በፊት፡ ያለፈውን፡ ዘመን፡ አሳጥረው፡ ቢቈጥሩት፡ ይህንን፡ ባያስተውሉ፡ ነው፡ እንጂ፤ሰው፡ ከተፈጠረ፡ ዠምሮ፡ እስከ፡ ዛሬ፡ ድረስ፡ ብዙኅ፡ እልፍ፡ ዘመናት፡ እንዳለፈ፡ ምንስ፡ ምስክር፡ ቢገኝም፡ የቅዱስ፡ መጽሐፍን፡ ቃል፡ አያስነቅፍም፡ ይላሉ።

ከዚህ፡ በላይ፡ የተጻፈውን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ እውነት፡ ይሁን፡ ይሁን፡ ለመከራከር፡ ግን፡ ለኛ፡ ኣያስፈልግም። እኛ፡ ይህንን፡ አጭር፡ ቃል፡

መጻፋችን፡ የሕዝብ፡ አስተዳደር፡ መሠረት፡ ምን፡ እንደ፡ ሆነ፡ ለማሳየት፡ ነውና፡ እንዲህ፡ ያለ፡ ክርክር፡ ባሳባችን፡ አይገባም።

ከላይ፡ የተጻፈውን፡ የሊቃውንት፡ ሐሳብ፡ ማስታወቃችን፡ ቀጥሎ፡ የተጻፈውን፡ ቃል፡ በፍጹም፡ ለማስረዳት፡ ስንል፡ ነው።

ሰው፡ ከተፈጠረ፡ ዠምሮ፡ እስከ፡ ዛሬ፡ ድረስ፡ ያለፈውን፡ ዘመን፡ የኤውሮፓ፡ ሊቃውንት፡ በ፪፡ ትልልቅ፡ ክፍል፡ ይከፍሉታል። መገዠመሪያው፡ ርግጠኛ፡ ታሪክ፡ የሌለው፡ ዘመን። ሁለተኛውም፡ ታሪኩ፡ የታወቀ፡ ዘመን፡ ይባላል። ይህም፡ ርግጠኛ፡ ታሪክ፡ የሌለው፡ ዘመን፡ ለብቻው፡ እንደ፡ ገና፡ በሦስት፡ ክፍል፡ ይከፈላል።

አንደኛው፡ የደንጊያ፡ ዘመን።

ሁለተኛው፡ የመዳብ፡ ዘመን።

ሦስተኛው፡ የብረት፡ ዘመን።

የኤውሮፓ፡ ሊቃውንት፡ መሬትን፡ እየቈፈሩ፡ ሲመረምሩ፡ ከሁሉ፡ በታች፡ የሰውን፡ ዐጥንትና፡ ከደንጊያ፡ የተበጀ፡ የሰውን፡ መሣሪያ፡ ኣገኙ፡ ይባላል። ይህም፡ በመዠመሪያ፡ ዘመን፡ የሰው፡ መሣሪያ፡ ሁሉ፡ ከደንጊያ፡ ብቻ፡ የተበጀ፡ እንደ፡ ነበረ፡ ያስረዳል። በዚያ፡ ጊዜ፡ የሰው፡ ኑሮ፡ ካውሬ፡ ኑሮ፡ እጅግ፡ የተሻለ፡ አይመስልም። የቤት፡ ሥራ፡ አልታወቀም፡ ነበረ። ሰው፡ በጕድጓድና፡ በዋሻ፡ ውስጥ፡ ሲኖር፡ ነበር። ከዚያ፡ ቀጥሎ፡ ከመሬት፡ የሚገኙት፡ መዳብና፡ ዚን፡ ታወቁ። ሰውም፡ እነሱን፡ ባንድነት፡ አቅልጦ፡ ብሮንስ፡ የሚባለውን፡ ጠንካራ፡ ቈርቈሮ፡ ሠራባቸው። የቤቱንም፡ መሣሪያ፡ ሁሉ፡ ከዚሁ፡ ከብሮንስ፡ አበጀ። የብሮንስንም፡ ሥራ፡ ካወቀ፡ ወዲህ፡ ደኅና፡ ቤት፡ መሥራት፡ ለመደ። በዚያ፡ ጊዜም፡ ሲኖርባቸው፡ የነበሩ፡ የቤቶች፡ ፍራሾችና፡ ብዙ፡ የቤት፡ መሣሪያ፡ መሬቱ፡ ቢቈፈር፡ ከመሬት፡ በታች፡ ተገኝተው፡ ብሮንስ፡ ከታወቀ፡ ወዲህ፡ የሰው፡ ኑሮ፡ እየተሻለ፡ እንደ፡ ሄደ፡ ያስረዳሉ። ከዚያም፡ የብረት፡ ሥራ፡ ታውቆ፡ መሣሪያው፡ ጠንክሮለት፡ ሰው፡ በፍጹም፡ የምድር፡ ጌታ፡ ለመሆን፡ በቃ።

ርግጠኛ፡ ታሪክ፡ የሌለውም ፥ የደንጊያ፡ የብሮንስ፡ የብረት፡ ዘመን፡ ተብሎ፡ በ፫፡ ደረጃ፡ መከፈሉ፡ መሣሪያ፡ እየተሻሸለሊት፡ በጊዜው፡ ብዛት፡ ሰው፡ በኑሮው፡ እንዴት፡ እየተመቸው፡ ዕውቀቱም፡ እንዴት፡ እየሰፋለት፡

እንደ፡ ሄደ፡ ለማስረዳት፡ ነው። ነገር፡ ግን፡ ሰው፡ መሣሪያው፡ ደንጊያ፡ ሆኖ፡ ብሮንስን፡ እስኪያውቅ፡ ድረስ፡ ስንትና፡ ስንት፡ ዘመን፡ በመካከሉ፡ እንዳለፈ፡ በርግጡ፡ ለመናገር፡ ለማናቸውም፡ ሊቅ፡ አይቻለውም። ስለ፡ ሆነ፡ ግን፡ ሰው፡ በላይ፡ ከተጠራው፡ ካንዱ፡ ደረጃ፡ ወዳንዱ፡ ደረጃ፡ እስኪወጣ፡ ድረስ፡ ብዙ፡ ብዙ፡ ሺሕ፡ ዘመናት፡ እንዳለፉ፡ ጥርጥር፡ የሌለው፡ ነገር፡ ይመስላል። የምድሩ፡ መልክና፡ ኣየር፡ እየተለዋወጠበት፡ ሰው፡ ከተፈጠረ፡ ወዲህ፡ ያገኘው፡ መከራ፡ ብዙ፡ ነው። አንድ፡ ጊዜ፡ መቅ፡ የነበረው፡ አየር፡ ነፋሱ፡ ተለውጦ፡ የበረዶ፡ ሜዳና፡ ኩረብታ፡ ሲሆን፤ አንድ፡ ጊዜም፡ መሬት፡ ተናውጦ፡ ባንድ፡ ወገን፡ አንዱ፡ አገር፡ ሰምጦ፡ ባሕር፡ ሲሆን፤በሌላው፡ ወገንም፡ ባሕር፡ የነበረው፡ ቦታ፡ ውሃው፡ ሸሽቶበት፡ እንደ፡ እሳት፡ የሚያቃጥል፡ በረሓ፡ ሲሆን፡ በዚህ፡ ዓለም፡ ላይ፡ እየተመላለሰ፡ የወረደበት፡ መዓት፡ ብዙ፡ እንደ፡ ነበረ፡ ይመስላል።

አሁን፡ ለምሳሌ፡ ባፍሪቃ፡ ውስጥ፡ ያለው፡ ሰሐራ፡ የሚባለው፡ ትልቅ፡ በረሓ፡ ቀድሞ፡ ባሕር፡ የነበረው፡ ነው። ዛሬም፡ ለም፡ የሆነው፡ ኤሮፓ፡ ዱሮ፡ አትክልት፡ የማያበቅል፡ የበረዶ፡ አገር፡ ነበር። በሰሜን፡ አሜሪካ፡ ያለው፡ ግሬንላንድ፡ የሚባለውም፡ አገር፡ በዛሬው፡ ዘመናችን፡ በበረዶ፡ ተሸፍኖ፡ ዘወትር፡ የሚኖረው፡ አገር፡ ነው፡ ነገር፡ ግን፡ ልዩ፡ ልዩ፡ አታክልት፡ መልቶበት፡ እንደ፡ ነበረ፡ የሚመሰክሩ፡ የደኖች፡ ትራፊ፡ ዛሬውንም፡ ቢሆን፡ ከበረዶው፡ በታች፡ ተቀብረው፡ ይገኛሉ።

እንደዚሁም፡ በህንድኩሽና፡ በታውሩስ፡ መካከል፡ ያለው፡ በምሥራቅ፡ የሂማሊያ፡ ተራሮች፡ በምዕራብም፡ ያራራትና፡ የካውካዝ፡ ተራሮች፡ የወሰኑት፡ አገር፡ መልኩና፡ አየሩ፡ የቀድሞው፡ ከዛሬው፡ ልዩ፡ እንደ፡ ነበረ፡ ይመስላል። የዛሬው፡ የኤውሮፓ፡ ሕዝቦችና፡ ህንዶች፡ ሺናውያንም፡ የሴም፡ ዘር፡ የሆኑትም፡ ሕዝቦች፡ ሁሉ፡ ቀድሞ፡ በዚያው፡ አገር፡ ውስጥ፡ ባንድነት፡ ሲኖሩ፡ ነበሩ።

ብዙ፡ ሺሕ፡ ዓመታትም፡ ከክርስቶስ፡ ልደት፡ በፊት፡ ከዚያው፡ ኣገር፡ የእሳትና፡ የውሃ፡ መዓት፡ እየተለዋወጠ፡ እንደ፡ ወረደበት፡ የዛሬው፡ የመሬቱ፡ መልክ፡ ያስታውቃል። ያገሩ፡ ተራሮች፡ ከልዩ፡ ልዩ፡ መሬትና፡ ደንጊያ፡ መደራረብ፡ የተነሣ፡ እንደ፡ ትልልቅ፡ ቀልል፡ ሁነው፡ የቆሙ፡ ናቸው። በዚያውም፡ አገር፡ ውስጥ፡ ያለው፡ ሜዳ፡ ቢመረመር፡ በፊት፡ ብዙ፡ ተራራና፡ ብዙ፡ ጉብታ፡ ኑሮበት ፥ በኋላም፡ ወንዛወንዙ፡ በዐፈርና፡

ውሃ፡ በሰበሰበው፡ ደንጊያ፡ በአሸዋም፡ በዐቧራም፡ ተመልቶ፡ የተደለደስ፡ ሁኖ፡ ተገኘ። ይህ፡ ሁሉ፡ የሆነው፡ መቼም፡ ዋናው፡ ምክንያት፡ በመሬት፡ መነዋወጥና፡ በውሃም፡ በእሳትም፡ ነው። በዚያው፡ አገር፡ ውስጥ፡ ሲኖሩ፡ የነበሩ፡ ነገዶች፡ ሁሉ፡ አንዳንዳቸው፡ ወደ፡ ሺን፡ አገርና፡ ወደ፡ ህንድ፡ አገር፡ ግድም፡ አንዳንዳቸውም፡ ወደ፡ ኤሮፓና፡ ወደ፡ አፍሪቃ፡ ግድም፡ ተሰደው፡ ሌሎች፡ አገሮች፡ አቅንተው፡ ሰፍረውበት፡ ኖሩ።

እነዚህም፡ ሕዝቦች፡ ሁሉ፡ መከራውን፡ የተቀበሉት፡ ባንድነት፡ ሳሉ፡ ነውና፤ምንም፡ ቋንቋቸውና፡ ባሕርያቸው፡ በጊዜ፡ ብዛት፡ ቢለዋወጥና፡ ቢለያይ፤ይህን፡ የተቀበሉትን፡ መከራ፡ አልረሱትም፡ ነበር። ምንም፡ እንኳ፡ ባይጠራና፡ ቃሉ፡ ባይተካከል፡ በተረቶቻቸውና፡ በመጻሕፍቶቻቸው፡ ውስጥ፡ የዚያው፡ መከራ፡ መታሰቢያ፡ ምልክት፡ ሳይገኝ፡ አይቀርም። አሁን፡ ለምሳሌ፡ በኦሪት፡ ውስጥ፡ የጥፋት፡ ውሃ፡ ተብሎ፡ የተጻፈው፡ የኖኅ፡ ታሪክ፡ የዚያ፡ ጊዜ፡ መከራ፡ መታሰቢያ፡ ነው። ይህም፡ የሆነበት፡ ዘመን፡ በጣም፡ ሩቅ፡ አይደለም። የኤሮፓ፡ ሊቃውንት፡ እንደሚገምቱት፡ ከኖኅ፡ ት፡ ወዲህ፡ ቢያንስ፡ ቢያንስ፡ ፲፩ሺ፡ ዓመት፡ እጅግም፡ ቢበዛ፡ ፲፯ሺ፡ ዓመት፡ አልፋል፡ ይላሉ።

በሰው፡ ላይ፡ የወረደው፡ መዓት፡ ይህ፡ ብቻ፡ ሆኖ፡ አይደለም፤ነገር፡ ግን፡ ኦሪትን፡ ያስተማሩ፡ አይሁዳውያን፡ የዱሮ፡ አባቶቻቸው፡ ከተቀበሉት፡ መከራ፡ ሁሉ፡ ትዝ፡ ያላቸው፡ ይህ፡ ከላይ፡ የተጠራው፡ ብቻ፡ ስለ፡ ሆነ፤የጥፋት፡ ውሃ፡ ብለው፡ በክርስቲያኖች፡ ሁሉ፡ የሃይማኖት፡ መጽሐፍ፡ ውስጥ፡ ጽፈው፡ ስለ፡ አቈዩልን፡ እስከ፡ ዛሬ፡ ድረስ፡ አልተረሳም።

ዘመናቱ፡ እየራቀ፡ ወሬው፡ ቢረሳ፡ ነው፡ እንጂ፡ ከዚህ፡ የከፋ፡ መዓት፡ በምድር፡ ላይ፡ እየተመላለሰ፡ ወርዶ፡ እንደ፡ ነበረ፡ በያገሩ፡ ብንሄድ፡ የመሬቱ፡ መልክ፡ ይነግራል። እስቲ፡ አሁን፡ ለምሳሌ፡ ሩቅ፡ ሳንሄድ፡ በኢትዮጵያችን፡ ውስጥ፡ ያለውን፡ የፈንታሌንና፡ የመታሐራን፡ በረሓ፡ እንመልከት። ከፈንታሌ፡ ተራራ፡ ውስጥ፡ የተተፋ፡ የእሳት፡ ጐርፍ፡ ሜዳውን፡ ሁሉ፡ መልቶታል።

ይህም፡ የእሳት፡ ጐርፍ፡ በርዶ፡ አሁን፡ በመካከሉ፡ የምድር፡ ባቡር፡ ተዘርግቶበታል። በፈንታሌም፡ ዙሪያ፡ ያለው፡ የበረደው፡ የእሳት፡ ጐርፍ፡

ከመሬት፡ ውስጥ፡ ከተተፋ፡ ወዲህ፡ እጅግ፡ ብዙ፡ ዘመን፡ አላለፈም። ዛሬ፡ በፈንታሌ፡ ግድም፡ የሚኖሩት፡ የከረዩና፡ ያዳል፡ ነገዶች፡ ግን፡ የጥቀሩን፡ ደንጊያ፡ ብዛት፡ አይተው፡ ይገረማሉ። ግን፡ ነገሩ፡ ምን፡ እንደ፡ ሆነ፡ እንዲህስ፡ የሆነው፡ መቼ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ታሪኩን፡ አይተው፡ አያውቍትም፤ ነገሩ፡ ተረስቷል። እንደዚሁም፡ በያገሩ፡ ከዚህ፡ የሚበልጥ፡ ብዙ፡ ነገር፡ ይገኛል። ነገር፡ ግን፡ እንደዚህ፡ የሆነበት፡ ምክንያት፡ ምን፡ እንደ፡ ሆነ፡ በዘመናት፡ ብዛት፡ ተረስቶ፡ ኑሮ፡ ሊቃውንት፡ እየመረመሩ፡ የመሬቱ፡ መልክ፡ ልዩ፡ ልዩ፡ የሆነበትን፡ የያንዳንዱ፡ አገር፡ አየር፡ ለብቻው፡ የሆነበቱ፡ ሁሉ፡ በምን ምክንያት፡ እንደ፡ ሆነ፡ ራሳቸው፡ መርምረው፡ ተረድተው፡ ደግሞ፡ ለዓለም፡ ሕዝቦች፡ ለማስረዳት፡ ይጣጣራሉ።

እውነትም፡ የኤውሮፓ፡ ሊቃውንት፡ ስለዚሁም፡ ነገር፡ ብዙ፡ ደከመዋል። ድካማቸው፡ ግን፡ ከንቱ፡ አልሆነም። ታሪክ፡ ሳይጻፍ፡ የነበሩ፡ ሰዎችና፡ ሕዝቦች፡ ምንስ፡ ስማቸውና፡ ሞያቸው፡ በርግጥ፡ ሳይታወቅ፡ ኑሯቸውም፡ እንዴት፡ እንደ፡ ነበረ፡ በዘመናቸውም፡ የሆነው፡ የአየርና፡ የመሬት፡ መለዋወጥ፡ በምርምር፡ ተለይቶ፡ ታውቋል።

የኤሮፓም፡ ሊቃውንት፡ በሚነግሩኝ፡ መንገድ፡ ከሄድን፡ ዘንድ፡ ሰው፡ የዛሬውን፡ ዕውቀትና፡ የኑሮ፡ ምቹነት፡ ያገኘ፡ ካንዱ፡ ደረጃ፡ ወዳንዱ፡ ደረጃ፡ እየወጣ፡ ነው፡ እንጂ፡ ባንድ፡ ጊዜ፡ አይደለም።

# ፫ኛ፡ ምዕራፍ።

የሰውም: አስተዳደር፡ ከጥንት፡ ከመሠረት፡ እንዴት፡ እንደ፡ ነበረና፡ እንዴትስ፡ እየተለዋወጠ፡ እንደ፡ ሄደ፡ በፍጹም፡ እንድንረዳው፡ ትልቍ፡ ያሜሪካ፡ ሊቅ፡ ካሬ፡ እንደ፡ ጻፈው፡ ለምሳሌ፡ አንድ፡ ሰው፡ ከነሚስቱ፡ ለብቻው፡ ተለይቶ፡ ሌላ፡ አጋዥ፡ ሳይኖረው፡ መሣሪያም፡ አልባ፡ ሆኖ፡ ወዳንድ፡ የባሕር፡ ደሴት፡ መሰደዱን፡ እናስብ።

በመካከልም፡ መሰናክል፡ ነገር፡ ካላገኘው፡ የሱና፡ የልጆቹ፡ የልጅ፡ ልጆቹም፡ ኑሮ፡ በዘመናት፡ ብዛት፡ እንዴት፡ እየተለዋወጠና፡ እየሰፋም፡ እንዲሄድ፡ በተራ፡ አስተውለን፡ እናስብ።

ይህ፡ የምናስበው፡ ሰው፡ ከነሚስቱ፡ ባንድ፡ ሰፊ፡ አገር፡ ውስጥ፡ ብቻውን፡ ሲሆን፡ መሣሪያም፡ ሳይኖረው፡ ትዳሩ፡ በመዠመሪያ፡ እንዴት፡ ያለ፡ ኑሮ፡ ኑሮት፡ ይሆን። መቼም፡ ደሴቱ፡ ሰፊ፡ ነውና፤እሱ፡ ግን፡ ሁለት፡ ራሱን፡ ብቻ፡ ነውና፡ የሄደ ፥ የሚመቸውን፡ አይቶ፡ ለትዳሩ፡ የሚሆነውን፡ ቦታና፡ መሬት፡ ሳይመርጥ፡ ኣይቀርም። ፍሬያማውን፡ መሬት፡ እንዳያቀና፡ ግን፡ ትልልቅ፡ ዛፎችና፡ ቁጥቋጦ፡ መልተውበታል። ወይም፡ ደግሞ፡ ትልልቅ፡ ረግረግ፡ ይሆንበታል። ዛፎቹንም፡ ለመቁረጥ፡ ቡቃዮቹንም፡ ለመንቀል፡ ረግረጎቹንም፡ ለማድረቅ፡ ጉልበትና፡ መሣሪያ፡ ያጣል።

ደግሞም፡ የደኑና፡ የረግረጉ፡ አየር፡ ከነከታቴውም፡ ለጤናው፡ የማይመቸው፡ ይሆናል። በእጁም፡ የሚነቅለው፡ ቁጥቋጦ፡ ወዲያው፡ እንደ፡ ነቀለው፡ ተመልሶ፡ እንዳይበቅልበት፡ ያስፈራዋል። ስለዚህም፡ በተራራው፡ አግድመት፡ ያለው፡ ገላጣ፡ መሬት፡ ዛፍና፡ ብዙ፡ ቁጥቋጦ፡ የለበትም። ውሃም፡ አይቆምበትም፤ረግረግም፡ አይሆንምና፤ከዚያው፡ ላይ፡ የሚበቃውን፡ መሬት፡ አይቶ፡ መሬቱንም፡ ባንድ፡ በትር፡ ምሶ፡ ፍሬ፡ ይተክልበታል። ይህም፡ የተከለው፡ ፍሬ፡ በመከር፡ ጊዜ፡ ዕጥፍ፡ ሆኖ፡ ይገባለታል።

ይህንንም፡ ፍሬ፡ በሁለት፡ ደንጊያ፡ መካከል፡ አድርጎ፡ ይፈጨዋል። ባንድ፡ ደንጊያም፡ ላይ፡ እንደ፡ ቍጣ፡ ዐይነት፡ ኣድርጎ፡ ጋግሮ፡ ይበላዋል። የተከለው፡ ፍሬ፡ እስቲበቅልለት፡ ድረስ፡ ግን፡ ሥራ፡ ፈቶ፡ ዝም፡ ብሎ፡ አይቀመጥም፡ ይሆናል። ዐውቆ፡ የበቀለውን፡ የደን፡ ፍሬ፡ ለመሰብሰብ፡ አውሬውንም፡ ለመያዝ፡ ወይም፡ ለመግደል፡ ወዲያና፡ ወዲህ፡ ሲመላለስ፡ ይቈያል። እንዲህና፡ እንዲህም፡ ሲል፡ ለራሱና፡ ለሚስቱ፡ የሚሆን፡ የዕለት፡ ምግብ፡ ያገኛል። ይህም፡ ሲሆንለት፡ ኑሮው፡ እየተሻለ፡ ይሄዳል። የሚመቸውንም፡ አንድ፡ ደንጊያ፡ አይቶ፡ መጥረቢያ፡ እንዲሆንለት፡ በሌላ፡ ደንጊያ፡ ይስለዋል። በብዙ፡ ድካምም፡ ዛፎቹን፡ ይጥልበታል። ነገር፡ ግን፡ በጊዜ፡ ብዛት፡ የመዳብን፡ ዐፈር፡ ያገኛል፤ኣቀላሰጠንም፡ እሱው፡ ራሱ፡ ኣስቦ፡ ይማራል። በዚሁም፡ ባዲስ፡ ዕውቀቱ፡ በጥቂት፡ ድካም፡ የተሻለ፡ መጥረቢያ፡ ለማበጀት፡ ይችላል፤ከመዳብም፡ አንደኛ፡ መናኛ፡ ዶማ፡ ያበጃል።

በዶማውም፡ መሬቱን፡ አጥብቆ፡ ወደ፡ ውስጥ፡ ዘለቃ፡ ይቈፍረዋል፤ መሬቱም፡ ደኅና፡ ሁኖ፡ ስለ፡ ተቈፈረ፡ የሚዘራውንም፡ ፍሬ፡ ፀሓይ፡ ያደርቀዋል፡ ጐርፍም፡ ይወስደዋል፡ ተብሎ፡ እንደ፡ ዱሮው፡ አያስፈራም።

መከሩም፡ የተዘራውን፡ ሦስት፡ እጅ፡ አዝሎ፡ ሳይገባ፡ አይቀርም። ከዚያም፡ ቀጥሎ፡ ምን፡ ያለበትን፡ ዐፈር፡ ያገኛል። ዚኑንና፡ መዳቡንም፡ ባንድነት፡ አጋጥሞ፡ ቢያቀልጠው፡ ብሮንስ፡ ይሆንለታል። ከብሮንስም፡ ከዱሮ፡ የበለጠ፡ መሣሪያ፡ ያበጃል። ሥራውም፡ በዚህ፡ ምክንያት፡ ከዱሮው፡ ይልቅ፡ በጣም፡ ይቀልለታል።

ያንን፡ በፊት፡ በማይረባ፡ መሣሪያ፡ ሲቈፍረው፡ የነበረውንም፡ መሬት፡ ከእንግዲህ፡ ወዲህ፡ አጥብቆ፡ ሊቈፍረው፡ ይችላል። ከፍሬያማውም፡ መሬት፡ ቡቃያ፡ ከነበረበቱ፡ ጥቂቱን፡ በዚሁ፡ ባዲሱ፡ መሣሪያ፡ ያቀናዋል፤መሬቱንም፡ በደኅና፡ ይቈፍረዋል። ቡቃያው፡ እንደ፡ ገና፡ በቅሎ፡ የዘራውን፡ ፍሬ፡ እንዳይውጥበት፡ አያስፈራውም፤በዚሁ፡ መካከል፡ መቼም፡ ልጆች፡ ይወልዳል፤ልጆቹም፡ ለሥራ፡ ይደርሳሉ። የሱ፡ ጉልበትና፡ የልጆቹ፡ ጉልበት፡ ይተባበራል። ከመተባበራቸውም፡ የተነሣ፡ የበለጠ፡ ኃይል፡ ያገኛሉ። የሚያስፈልጋቸውንም፡ ነገር፡ ሁሉ። መሬት፡ በሆዷ፡ እንደ፡ ያዘች፡ ተረድተውታል። ለመሣሪያም የሚሆናቸውን፡ ነገር፡ ከመዳብና፡ ከዚን፡ የበለጠ፡ ሌላ፡ ነገር፡ እንዲያገኙ፡ ይመረምራሉ። እንሆም፡ የብረት፡ ዐፈር፡ ያገኛሉ፤ያቀልጡታልም። እንዲሁም፡ ሆኖ፡ ከሚወጣው፡ ብረት፡ ምንም፡ እንካ፡ ጨርሶ፡ ለጊዜው፡ ባያምር። እውነተኛ፡ ብረት፡ ያገኛሉ። ወዲያው፡ ዶማና፡ መጥረቢያ፡ ያበጁና፡ ሥራቸውን፡ ከዱሮ፡ ይልቅ፡ በበለጠ፡ ይሠሩበታል።

እንግዲህም፡ ይህ፡ መዠመሪያ፡ ስደተኛው፡ ሰውዬ፡ ከልጆቹ፡ ጋራ፡ ሁኖ፡ በተራራው፡ አግድመት፡ የነበረውን፡ ትልቀኑን፡ ጥድ፡ ጥሎ፡ እርሻውን፡ ያሰፋል። በብረቱም፡ ዶማ፡ መሬቱን፡ በጣም፡ እስከ፡ ውስጡ፡ ድረስ፡ ዘለቃ፡ ይቈፍረዋል። የላይኛውንም፡ ዐፈር፡ ከታችኛው፡ ዐፈር፡ ጋራ፡ ያደባልቀዋል።

ልጆቹም፡ ልጆች፡ ይወልዳሉ፤የልጅ፡ ልጆቹም፡ ያድጉለታል፤ከዚያም፡ በኋላ፡ ከልጆቹና፡ ከልጅ፡ ልጆቹ፡ ጋራ፡ ሁኖ፡ ብቻውን፡ ሳለ፡ ለመሥራት፡

ያልቻለውን፡ አሁን፡ ግን፡ ቤተ፡ ሰቦቹን፡ ይዞ፡ ብዙ፡ ሥራ፡ ለመሥራት፡ ይችላል።

ቤተ፡ ሰቡም፡ እየበዛ፡ ሲሄድ፡ እያንዳንዱ፡ ሰው፡ የሚያገኘው፡ ምግብ፡ እየበዛ፡ የያንዳንዱም፡ ድካም፡ እያነሰ፡ ይሄዳል። ቤተ፡ ሰቦቹም፡ ከበዙ፡ ዘንድ፡ ሥራውን፡ ይከፋፈሉታል። አኩሌቶቹ፡ የእርሻን፡ ሥራ፡ ይሠራሉ፤አኩሌቶቹም፡ ደግሞ፡ ብረትና፡ መዳብ፡ ዚንም፡ የሚገኝበትን፡ ዐፈር፡ እያቀለጡ፡ ልዩ፡ ልዩ፡ የሆነ፡ ደጎና፡ ደጎና፡ መሣሪያ፡ ይሠራሉ። አኩሌቶቹ፡ ግን፡ ደግሞ፡ የተበላሹትን፡ መሣሪያዎች፡ እያሻሻሉ፡ ያድሳሉ።

ለእንክርዳድ፡ መንቀያ፡ የሚሆናቸውንም፡ ራሳቸው፡ መርምረው፡ አንድ፡ አዲስ፡ ዐይነት፡ ዶማ፡ ይሠራሉ። ይህንንም፡ አዲስ፡ መሣሪያ፡ ይዘው፡ ትንንሾቹም፡ ልጆች፡ ቢሆኑ፡ እንክርዳዱን፡ በመንቀላቸው፡ ማለፊያ፡ አድርገው፡ ሥራውን፡ ይረዳሉ። ሰዎቹ፡ እንደዚህም፡ በመተባበራቸው፡ ትዳራቸው፡ እየሰፋ፡ እነሱም፡ እየበረቱና፡ እየተጠቀሙ፡ ይሄዳሉ።

እንግዲህም፡ በሥራና፡ ባሳብ፡ እየተረዳዱ፡ የጠነከረ፡ መሣሪያ፡ አብጅተዋልና፡ ከተራራው፡ አግድመት፡ በታች፡ ወዳለው፡ ቁጥቋጦ፡ ወደ፡ በዛበት፡ መሬት፡ እርሻቸውን፡ ለማስፋት፡ ይወርዳሉ። ወርደውም፡ ቍጥቋጦውን፡ በእሳት፡ ያቃጥሉታል። ከዚያም፡ በኋላ፡ ትልልቆቹን፡ ዛፎች፡ በመጥረቢያ፡ ይጥላሉ። በጊዜም፡ ብዛት፡ ራሳቸው፡ መርምረው፡ በሬውን፡ ለማሠራት፡ ያስባሉ። በሬውም፡ በጒልበቱ፡ እንዲረዳቸው፡ የሚረዳበትን፡ መሣሪያ፡ አስበው፡ ያወጣሉ፡ ይህነንም፡ መሣሪያ፡ በጠፍር፡ አጋጥመው፡ ከበሬው፡ ዐንገት፡ በዕንጨትና፡ በጠፍር፡ ያስሩታል፤ከዚያም፡ በኋላ፡ ያርሱበታል። እንሆ፡ እንደዚህ፡ ያለው፡ መሣሪያ፡ ባልሠለጠኑት፡ ሕዝቦች፡ እስከ፡ ዛሬ፡ ድረስ፡ ይኖራል።

እንሆም፡ ዱሮ፡ በዶማ፡ ዐሥር፡ ሰዎች፡ ሲቈፍሩ፡ ይውሉበት፡ የነበረውን፡ የእርሻ፡ መሬት፡ ኋላ፡ ግን፡ አንድ፡ ሰው፡ በሁለት፡ በሬ፡ አርሶት፡ ይውል፡ ዝመር። እንደዚህም፡ ሲሆን፡ እርሻቸው፡ ከዱሮው፡ በጣም፡ የተሻለ፡ እኽል፡ የሚያበቅልና፡ የሰፋም፡ ይሆናል። የሰዎቹም፡ ቅጥር፡ እየበዛ፡ ይሄዳል። ሰመሣሪያና፡ በእኽል፡ በልብስም፡ ሀብታቸው፡ ይበዛል። የሚኖሩበትም፡ ቤት፡ በጊዜ፡ ብዛት፡ የተሻለ፡ ይሆናል።

ያ፡ በደሴት፡ የገባው፡ የመዠመሪያው፡ ሰው፡ ከነሚስቱ፡ እንደ፡ አውሬ፡ በጕድጓድ፡ ወይም፡ በዋሻ፡ ውስጥ፡ ይኖር፡ ነበር። ከዚያ፡ በኋላ፡ ግን፡ ዐውቆ፡ የወደቀውን፡ ዕንጨት፡ ሰባስቦ፡ አንዲት፡ ጐዦ፡ ሠራ። የመዠመሪያው፡ ቤት፡ መቼም፡ መስኮትና፡ የጢስ፡ መውጫ፡ አልነበረውምና፡ ሰውዬው፡ በብርድ፡ እንዳልሞት፡ ሲል፡ በጢስ፡ ውስጥ፡ ታፍኖ፡ ይኖር፡ ነበር።

ነፋሱም፡ ሲበረታበት፡ መዝጊያውንም፡ ለመዝጋት፡ የግድ፡ እየሆነበት፡ በጢሱ፡ ውስጥ፡ በጨለማ፡ ሥራ፡ እየፈታ፡ ሲቀመጥ፡ ነበረ። ይህ፡ ኑሮ፡ ግን፡ ለጤናው፡ እጅግ፡ የሚስማማው፡ አልነበረም። ልጆቹና፡ የልጅ፡ ልጆቹ፡ ካደጉና፡ ለሥራ፡ ከደረሱ፡ በኋላ፡ ከእነሱ፡ ጋራ፡ በኅብረት፡ ተጋግዞ፡ ደኅና፡ መሣሪያ፡ አውጥቶ፡ ኀይሉ፡ ሲሰፋለት፡ አይቶ፡ ጥዱንና፡ ዝግባውን፡ ቈርጦ፡ ፈልጦ፡ የተሻለ፡ ቤት፡ ሠራ። የሚኖርበትም፡ ቤት፡ እየተሻለ፡ ስለ፡ ሄደ፡ ቤተ፡ ሰቦቹ፡ እየተመቻቸው፡ ይበዛሉ። ከመብዛታቸውም፡ የተነሣ፡ ባሕርያቸውና፡ ሞያቸውም፡ ይለያያል። እኩሌቶቹ፡ በእርሻ፡ የሠለጠኑ፡ ይሆናሉ። ያውሬኝና፡ የከብትን፡ ቆዳ፡ እየፋቀ፡ ልብስ፡ ያበጃሉ። እኩሌቶቹም፡ መሣሪያውን፡ በማበጀት፡ ይሠለጥናሉ። ከዚህም፡ ሥራ፡ መከፋፈል፡ የተነሣ፡ የያንዳንዱ፡ ሰው፡ ድካም፡ እየተቃለለ፡ ይሄዳል። በዚህ፡ ሥራ፡ ብዛት፡ ገንዘብ፡ እየተረፋቸው፡ ስለ፡ ሄደ፡ ለክፉ፡ ቀን፡ እንዲሆነን፡ እያሉ፡ ትርፉን፡ ያከማቻሉ።

እርሻቸውም፡ ብዙ፡ ፍሬ፡ ከማይሰጠው፡ አግድመት፡ ወደ፡ ፍሬያማው፡ ሜዳና፡ የወንዝ፡ ዳር፡ እየሰፋ፡ ሲሄድ፡ ሰዎቹም፡ ደኑን፡ መንጥረው፡ ረግረጉንም፡ አድርቀው ፣ እየዘሩ፡ ከዱሮው፡ በጣም፡ የተሻለ፡ መከር፡ ያገኛሉ። ለከብትም፡ መሰማሪያ፡ የሚሆን፡ አይተው፡ ደኅና፡ ግጦሽ፡ ይለያሉ።

እንሆም፡ በጥቂት፡ ድካም፡ ከዱሮው፡ የበለጠ፡ ሥጋና፡ ወተት፡ ቅቤም፡ ቆዳም፡ ለማግኘት፡ ይሆንላቸዋል።

በበታቹ፡ ያለው፡ ሜዳ፡ የተሻለ፡ የእርሻ፡ መሬት፡ ስለ፡ ተገኘበት፡ ያ፡ ዱሮ፡ ሲታረስ፡ የነበረው፡ የተራራው፡ አግድመት፡ የእርሻ፡ መሬት፡

ለፍየልና። ለበግ፡ መሰማሪያ፡ እንዲሆን፡ ይለቀቅና፡ ወደ፡ አዲሱ፡ የእርሻ፡ መሬት፡ ይወረዳል።

ይህም፡ ሁሉ፡ ነገር፡ እስኪሆን፡ ድረስ፡ ብዙ፡ ትውልዶች፡ አልፈዋል።

አዲሶቹ፡ ትውልዶች: አባቶቻቸውና፡ አያቶቻቸው፡ ባከማቹት፡ ሀብትኛ፡ ዕውቀት፡ ተጠቅመው፡ ነበርና፡ ለወደ፡ ፊት፡ የበለጠ፡ ጥቅም፡ እንዲያገኙ፡ ራሳቸው፡ መርምረው፡ ለማግኘት በመጣጣር፡ ይሆንላቸዋል።

እንሆ፡ ነፋስና፡ ውሃ፡ እንኳ፡ ሳይቀሩ፡ እንዲያገለግሏቸው፡ አድርገው፡ ድካማቸውን፡ ከቀድሞው፡ ያቃልላሉ። ዘበነፋስ፡ የሚዘወር፡ ወፍጮኛ፡ በውሃ፡ የሚዘወር፡ የዕንጨት፡ መቅረጫ፡ መጋዝ፡ ያበጃሉ።

የዕንጨት፡ ከሰልም፡ የሚነድበትን፡ የብረት፡ ማቅለጫ፡ ሽክላ፡ ያበጃሉ።

እንሆም፡ ዱሮ፡ ብዙ፡ ቀን፡ የሚደከምበትን፡ ጥቅም፡ ባንድ፡ ቀን፡ ለማግኘት፡ ይቻላቸዋል። ሕዝቡም፡ በዝቶ፡ የደሴቱን፡ ተራራና፡ ሜዳ፡ ሁሉ፡ እያቀና፡ ይመሳዋል።

የሰዎቹም፡ ቊጥር፡ ሲበዛ፡ ሥራቸውና፡ ሞያቸው፡ ዐይነቱ፡ በጣም፡ የተለያየ፡ ይሆናል፤አራሾች፡ ሰፊዎች፡ ቤት፡ ሠሪዎች፥ብረት፡ ህይሪዎች፡ እየተባሉ፡ ሞያ፡ ሞያቸውን፡ ይይዛሉ። ረግረጎች፡ በሰው፡ ብልኅት፡ ይደርቃሉ።

እንሆም፡ በዱሮዎቹ፡ ሰፈሮችና፡ ባዲሶቹ፡ ሰፈሮች፡ መካከል፡ መንገድ፡ ይጠረጋል። ወይም፡ ደግሞ፡ ከነከታቴው፡ የዱሮዎቹ፡ አሮጌዎቹ፡ ሰፈሮች፡ በደኅና፡ ነው፡ ይሠራሉ። እንሆም፡ ካንዱ፡ ሰፈር፡ ወዳንዱ፡ ሰፈር፡ እየወጡ፡ በእኽል፡ ወይም፡ በበግ፡ ጠጕር፡ የተሻለ፡ ዶማም፡ ማረሻም፡ ልብስም፡ የብርድ፡ ልብስም፡ ሌላም፡ ደግሞ፡ ልዩ፡ ልዩ፡ የሆነ፡ መሣሪያና፡ ዕቃ፡ ይለዋወጣሉ። በነዚህም፡ ሥራ፡ የለውጥ፡ ንግድ፡ ይጀመራል።

ምቾትም፡ ሲገኝ፡ ሕዝቡ፡ በጣም፡ ይበዛል። ሀብቱና፡ ኀይሉም፡ እያደገ፡ ይሄዳል። እያንዳንዱም፡ ሰው፡ በዛሬው፡ ኑሮውና፡ ባለፉት፡

ትውልድ፡ ኑሮ፡ እንደ፡ ምን፡ እንደ፡ ነበረ፡ እያሰበ፡ መንፈሱ፡ ለሥራ፡ ይተጋል።

ለዝናቡና፡ ለፀሓዩም፡ መመከቻ፡ ልብስና፡ ቆብ፡ ኣበጅቷልና፡ እንዳለፉት፡ ትውልዶች፡ ከሥራው፡ አይተጓጐልም።

በዱሮ፡ ጊዜ፡ ለመከር፡ የሚሆን፡ ደጎና፡ መሣሪያ፡ አልነበረምና፡ የመከሩ፡ ጊዜ፡ አጭር፡ ስለ፡ ሆነ፡ ደጎና፡ ሆኖ፡ ከሰቀለው፡ እኸል፡ ጊዜ፡ እየተላለፈበት፡ ግማሹ፡ በስብሶ፡ ይቀር፡ ነበር።

አሁን፡ ግን፡ በጊዜ፡ ብዛት፡ ትንሽና፡ ትልቅ፡ ማጭድ፡ የዕንጨትና፡ የብረት፡ መንሽም፡ ስለ፡ ተበጀ ፥ የመከሩም፡ ሥራ፡ ይፋጠናል። ከዚያም ቀጥሎ፡ የሚያጭድ፡ መኪና፡ ይሠራል። እነዚህም፡ መሣሪያዎች፡ ሁሉ፡ የሰውን፡ ድካም፡ ያቀላሉ። ሌላውን፡ ደግሞ፡ የጐደጐደውን፡ መሬት፡ ለመምላት፡ በዝናብ፡ የሚናደውንም፡ መሬት፡ እንዳይናድ፡ ማገጃ፡ ተሠራ። ላራሹ፡ ጊዜ፡ ይሰጡታል፤ከመመራመሩም፡ ብዛት፡ የተነሣ፡ በጊዜ፡ ብዛት፡ አህያና፡ ፈረስም፡ ለምደውለት፡ የጋሪ፡ መንገድ፡ ተበጀለት። ጋሪና፡ ፈረስ፡ አህያም፡ ሰውን፡ ያገለግሉ፡ ዠመር። በነዚህም፡ ርዳታ፡ ሰው፡ ከሰልና፡ ሌላ፡ ልዩ፡ ልዩ፡ የሆነ፡ መሣሪያ፡ ከሩቅ፡ ስፍራ፡ እያመላለሰ፡ የኖራ፡ አቀላሰጥም፡ ዐወቀና፡ ለጥቅሙ፡ አደረገው። ኖራውንም፡ ለሥራው፡ እንደሚመች፡ አድርጎ፡ ያበጀዋል። ኖራውንም፡ አቃጥሎ፡ ከእርሻው፡ ፀፈር፡ ጋራ፡ ሲደባልቀው፡ እርሻው፡ ከዱሮው፡ ይልቅ፡ ይለሰልስለትና፡ ከቀድሞው፡ ይበልጥ፡ መልካም፡ አድርጎ፡ እኸል፡ ያበቅልለታል።

የሰውም፡ ቍጥር፡ እንደ፡ ገና፡ እየበዛ፡ ሀብቱም፡ እያደገ፡ ይሄዳል። ሰውም፡ ረግረጉን፡ በጥቂት፡ ድካም፡ የሚያደርቅ፡ በውሃና፡ በእሳትም፡ የሚንቀሳቀስ፡ ዕቃውንም፡ በፍጥነት፡ የሚያመላልስ፡ አንድ፡ መኪና፡ አስቦ፡ ያወጣል ። እሱም፡ ለጉዳዩ፡ ካንዱ፡ ወዳንዱ፡ ቦታም፡ የሚሄድበት፡ ከፈረስ፡ ጋሪ፡ የተሻለ፡ ሌላ፡ ነገር፡ አስቦ፡ ይሠራል ። ይህም፡ የሚሻለው፡ የምድር፡ ባቡር፡ ነው ።

ከዚህም፡ በቀር፡ ሌላ፡ ጥቅም፡ የሚሆነውን፡ መሣሪያና፡ ሌላ፡ ልዩ፡ ልዩ፡ የሆነ፡ ብልኀት፡ ያወጣል። ያንንም፡ የታየውን፡ አሳቡንና፡ ምኞቱንም፡ ለመፈጸም፡ አይሳነውም፤መሣሪያም፡ አያንሰውም፤ቦታም፡ አይርቀውም ።

የምድር፡ ባቡርና፡ መርከ ብ፡ የዓለምን፡ አራት፡ ማእዝኖች፡ ያቀርቡለታል ።

እንሆ፡ በዚህ፡ ምሳሌ፡ እንደምናየው፡ ሰው፡ በመዠመሪያ፡ የምድር፡ ተገዢ፡ ሁኖ፡ ዐውቃ፡ የሰጠችውን፡ ስጦታ፡ ሲቀበል፡ የነሳችውንም፡ ሲያጣ፡ ነበረ ። በጊዜ፡ ብዛት፡ ግን፡ ጌታዋ ፡ ሆነ፤ነፋስና፡ ውሃም፡ ተገዙለትና፡ ተመችቶት፡ እየተባዛም ፡ ሄደ ። ሰው፡ በመዠመሪያ፡ ያውሬን፡ ሥጋና፡ ዐውቆ፡ የበቀለውን፡ የደን፡ ፍሬ፡ ሲመገብ፡ ደካማውንና፡ በሽተኛውን፡ ልጁን፡ የደከመውንም፡ ሽምግሎ፡ ወይም፡ ታሞ፡ የማይድን፡ ወይም፡ የዱር፡ ፍሬ፡ ለመሰብሰብ፡ የማይችለውን፡ አባቱንና፡ ወይም፡ ወንድሙን፡ ለወደ፡ ፊት፡ እንዳያስቸግረኝ፡ ብሎ፡ ፈርቶ፡ ከበረሓ፡ እየጣለ፡ ባውሬ፡ ሲያስፈጀው፡ ይኖር፡ ነበር ። እርሻ ፡ ከተዠመረ፡ በኋላ፡ ግን፡ ርኅራኄ፡ ገባና፡ ጭከና፡ እያነሰ፡ ሄደ ። ሰውም፡ መሬቱ፡ ረቂቅ፡ ሁኖ፡ በመዠመሪያ፡ ያለብዙ፡ ድካም፡ ሲያርሰው፡ ከነበረው፡ የተራራ፡ አግድመት፡ ወርዶ፡ ደንና፡ ረግረግ፡ ወደ፡ በዛበት ፥ መሬቱም፡ ወፍራም፡ ወደ፡ ሆነበ ት፡ ሜዳና፡ የወንዝ፡ ዳር፡ ወርዶ፡ ከጊዜ፡ ብዛት፡ በኋላ፡ ባገኘውም፡ ዕውቀት፡ ደኑን፡ መንጥሮ፡ ረግረጉን፡ ኣድርቆ፡ መሬቱንም፡ አለስልሶ፡ መከሩ፡ ከበዛለት፡ በኋላ፡ ወንድሙ፡ ሲታመምና፡ ሲሽመግልም፡ ሊራራለት፡ እንዲገባው፡ ተረዳ ። ከዕውቀቱ፡ የተነሣ፡ በጊዜ፡ ብዛት፡ በምድር፡ ላይ፡ ችጋር፡ እያነሰ፡ ሄደ ። ሀብትና፡ ምቾትም፡ ሰፋ ። ሞትና፡ በሽታም፡ እያነሰ፡ ሰውም፡ እየበዛ፡ ይሄድ፡ ዠመር ። ርኅራኄም፡ ኣድሮበት፡ ተፋቅሮ፡ ተባበረ። ከመተባበሩም፡ የተነሣ፡ ኃይል፡ አግኝቶ፡ የምድር፡ ጌታ፡ መሆን፡ በቃ።

በመካከሉ፡ ግን፡ ዕንቅፋትና፡ መሰናክል፡ ነገር፡ ካላገኘው፡ ሰው፡ ይህን፡ ከላይ፡ በተጻፈው፡ ምሳሌ፡ ያሳየነውን፡ መንገድ፡ ተከትሎ፡ ቢሄድ፡ በዘመናቱ፡ እስከ፡ ፍጻሜው፡ በደኅና፡ እንዲደርስ፡ የታወቀ፡ ነገር፡ ነው። ካውሬ፡ አደንም፡ ወደ፡ እርሻ፡ ሲመለስ፡ ደኅና፡ መሣሪያም፡ ካወጣ፡ በኋላ፡ መጥፎውን፡ መሬት፡ ትቶ፡ ደኅናውን፡ መሬት፡ አቅንቶ፡ ሲያርስ፡ ዕውቀቱም፡ ሲሰፋ፡ እየተመቸውና፡ እየበዛ፡ እንዲሄድ፡ ርግጥ፡ ነው። የዚህ፡ ዓለም፡ ሕዝቦች፡ ሁሉ፡ በመካከሉ፡ ዕንቅፋት፡ ባያገኛቸው፡ ይህንን፡ ከላይ፡ የተጻፈውንና፡ ያሳየነውን፡ መንገድ፡ ተከትለው፡ ሊሄዱ፡ ነበር። ዛሬም፡ የዕውቀታቸውና፡ የሀብታቸው፡ ደረጃ፡ ከፍና፡ ዝቅ፡ ያለ፡ ሁኖ፡

ባሕርያቸውና፡ ልማዳቸው፡ የመለያየቱ፡ ምክንያት፡ አጭር፡ ነው። ከመረመርነውም፡ ዘንድ፡ በቶሎ፡ እንረዳዋለን። ማናቼውም፡ ሕዝብ፡ መቼም፡ ይህንን፡ ከላይ፡ በምሳሌ፡ ያሳየነውን፡ መንገድ፡ ተከትሎ፡ ወደ፡ ፍጻሜው፡ መድረስ፡ የሚችል፡ በመካከሉ፡ መሰናክል፡ ነገር፡ ያላገኘው፡ እንደ፡ ሆነ፡ ነው። እንደሚያገኘውም፡ መሰናክል፡ መጠን፡ የሚደርስበት፡ የዕውቀትና፡ የሀብት፡ ደረጃ፡ ከፍ፡ ወይም፡ ዝቅ፡ ያለ፡ ይሆናል። ስለዚህም፡ ነገር፡ ሕዝብን፡ ሀብትና፡ ዕውቀት፡ እንዳያገኝ፡ ሊከለክል፡ የሚችል፡ መሰናክል፡ ሁሉ፡ እንዴት፡ ያለ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ልንመረምር፡ ይገባናል።

# ፬ኛ፡ ምዕራፍ።

ሰው፡ መቼም፡ እርሻን፡ ባይዠምርም፡ ቢሆን፡ ያውሬን፡ ሥጋና፡ የደንን፡ ፍሬ፡ እየበላ፡ ተባዝቶ፡ ነበረ። መሬት፡ ሲቈፍርና፡ እርሻንም፡ ማረስ፡ ቢዠምር፡ አልፎ፡ አልፎ፡ በየተራራው፡ ጥግ፡ ሰፈረ፤በያለበትም፡ ይሠራ፡ ዠመር። ነገር፡ ግን፡ በያንዳንዱ፡ ወገን፡ ውስጥ፡ ባለው፡ ሕዝብ፡ ርስ፡ በርሳቸው፡ እየተለዋወጡ፡ የተሻለ፡ ኑሮ፡ ለማግኘት፡ ይችሉ፡ ነበር።

ዛሬ፡ እንደምናየው፡ ይህን፡ ያኽል፡ ድኽነት፡ በምድር፡ ላይ፡ አይሰፋም፡ ነበረ። ካየርና፡ ከመሬት፡ ክፋት፡ የሚበልጥ፡ በምድር፡ ላይ፡ ለሕዝቦቹም፡ ኑሮ፡ ዕንቅፋት፡ የሚሆን፡ ሌላ፡ ነገር፡ አለ። ርሱም፡ ሽፍታና፡ ጦርነት፡ ነው። በገዛ፡ እጃቸው፡ ሠርተው፡ ለመብላት፡ የማይወዱ፡ ጥቂቶች፡ ሰዎች፡ ይኖሩ፡ ይሆናል። ከነዚህም፡ ሥራ፡ ከማይወዱ፡ ሰዎች፡ ውስጥ፡ አንዱ፡ የጒልበትና፡ የዕውቀት፡ ብልጫ፡ ይኖረዋል። የቀሩትንም፡ ይሰበስባቸዋል፤ዋናቸውም፡ ሁኖ፡ ለራሱና፡ ለሚከተሉት፡ ጓደኞች፡ የሚበቃ፡ ምግብ፡ ከሌሎቹ፡ ይቀማል።

ኣራሾች፡ ግን፡ የሰፈሩት፡ በየተራራው፡ ጥግ፡ ኣልፈው፡ ኣልፈው፡ ነበርና፡ ሰፈራቸው፡ ስለ፡ ተራራቀ፡ ደኅና፡ መንገድም፡ ስለሌላቸው፡ ባንድነት፡ ሁነው፡ ለቀማኞቹ፡ መመከት፡ አይቻላቸውም፡ ነበር።

ስለዚህም፡ ነገር፡ የወንበዴው፡ ወገኖች፡ ሥራ፡ ፈቶችም፡ ይበዛሉ። እሱም፡ ጥቂት፡ ቈይቶ፡ የብዙ፡ ወገን፡ ቆሮ፡ ገዢ፡ ይሆናል። ለሱና፡ ሥራ፡

ለሌላቸው፡ ተከታዮቹም፡ ምግብ፡ የሚሆን፡ ቈፋሪዎቹና፡ አራሾቹ፡ ለፍተው፡ ካገኙት፡ ህብት፡ ከፍለው፡ እንደ፡ ግብር፡ እንዲሰጡት፡ የግድ፡ ይላቸዋል።

መቼም፡ ሰው፡ ለፍቶ፡ ሠርቶ፡ የግድ፡ ሲሆንበት ፥ ባንድም፡ ነገድ፡ ውስጥ፡ ሥራ፡ የማይወዱና፡ በሌሎች፡ ሰዎች፡ ድካም፡ የሚመገቡ፡ ሰዎች፡ ሲበዙ ፥ ከሠራተኛው፡ በላተኛው፡ መብዛቱ፡ ነውና፤ሕዝቡና፡ ሀብቱ፡ በቶሎ፡ እንዳይበዛ፡ ዕንቅፋት፡ ይሆናል። ይህም፡ እስከ፡ ዛሬ፡ ድረስ፡ ባገራችን፡ ሕዝብ፡

ውስጥ፡ ሲደረግ፡ ይኖራል።

አራሾቹ፡ ግን፡ ምንም፡ ግብሩና፡ ጕዳቱ፡ ቢበዛባቸው፡ በቀስታ፡ ከተራራው፡ ጥግ፡ ወደ፡ ሜዳው ፥ ከሜዳውም፡ ረግረግ፡ ወደ፡ ሆነው፡ እወንዙ፡ ዳር፡ ድረስ፡ እርሳቸውንና፡ ንብረታቸውን፡ ያሰፋሉ። በቀን፡ ብዛትም፡ ሌላ፡ ነገድ፡ ወደሚያርሰውና፡ ን፡ ወደሚያሰማራበት፡ አገር፡ ስፍራ፡ ይደርሳሉ።

ይህም፡ ሌላ፡ ወገን፡ ደግሞ፡ እንደዚሁ፡ ለብቻው፡ ቆሮ፡ ገዢ፡ ወጥቶበት፡ ይሆናል። እነዚህም፡ ሁለት፡ ቆሮዎች፡ ጎረ፡ ቤቶች፡ ሲሆኑ፡ እኔ፡ እበልጥ፡ እኔ፡ እበልጥ፡ ሲሉ፡ ርስ፡ በርሳቸው፡ ይቀናናሉ።

አንዱም፡ ያንዱን፡ ዜጎች፡ ለማስገበር፡ ይፈልጋል፤በዚህም፡ በመቀናናታቸው፡ ምክንያት፡ ጦርነት፡ ይነሣል።

የያንዳንዱ፡ ቆሮ፡ አሳብ፡ መቼም፡ ለመቀማት፡ ነው። ነገር፡ ግን፡ ይህነን፡ እውነተኛውን፡ ኣሳባቸውን፡ ሸፍነው፡ ስም፡ ብቻ፡ ለመፈለግ፡ የተነሡ፡ ያስመስሉታል። አንዱም፡ ቆሮ፡ በሌላው፡ ቆሮ፡ አገር፡ ላይ፡ አደጋ፡ ይጥላል። ባለጋራውም፡ እንዲደክምለት፡ ገባሮቹን፡ በብዙ፡ ይገድልበታል፤ቤታቸውንም፡ ያቃጥላል፤እርሻቸውንም፡ ያጠፋል። ቆሮዎቹ፡ ግን፡ በመዠመሪያ፡ ርስ፡ በርሳቸው፡ ለመጋደል፡ አይፈላለጉም፡ ነበር። ያንዱም፡ ቆሮ፡ ገባር፡ የጌታውን፡ ጠላት፡ የሆነውን፡ ቆሮ፡ ለመግደል፡ አይደፍርም፤ቢማርከውም፡ እንኳ፡ በብዙ፡ ትሕትና፡ ያገለግለዋል።

ገባሮቻቸውን፡ እያስተራረዱ፡ ቆሮዎቹ፡ ርስ፡ በርሳቸው፡ በፍቅር፡ ለመላላክ፡ አይመለሱም። ይልቁንም፡ የሥጋ፡ ዝምድና፡ ይኖራቸው፡ ይሆናል። በዚህም፡ ምክንያት፡ የተሸነፈው፡ ቆሮ፡ ገባሮቹ፡ ያነን፡ በብዙ፡ ድካም፡ ያቀኑትን፡ ሜዳና፡ የወንዝ፡ ዳር፡ ትተው፡ ለመመከት፡ ይመቻቸዋልና፡ ዱሮ፡ ወደ፡ ነበሩበት፡ ስፍራ፡ ወደ፡ ተራራው፡ ጥግ፡ ይሸሻሉ። እንሆም፡ ያ፡ በብዙ፡ ድካም፡ የቀና፡ ሜዳ፡ ተመልሶ፡ እንደ፡ ጥንቱ፡ ደን፡ ይሆናል። በድካም፡ ብዛትም፡ ያደረቁት፡ የወንዙ፡ ዳር፡ ረግረግ፡ ተመልሶ፡ ምድረ፡ በዳ፡ ይሆናል።

ከሁለት፡ ወይም፡ ከሦስት፡ ዓመት፡ በኋላ፡ ግን፡ በሁለቱ፡ ቆሮዎች፡ መካከል፡ ዕርቅ፡ ይደረጋል። ሸሽተውም፡ የነበሩት፡ ገባሮች፡ ወደ፡ ዱሮ፡ ቦታቸው፡ ተመልሰው፡ ይገባሉ። ሥራውንም፡ አንድ፡ ብለው፡ እንደ፡ ገና፡ ይዠምራሉ። በጦርነቱ፡ ውስጥ፡ ብዙ፡ ሰዎች፡ ሙተውባቸው፡ ስላነሱ፡ ጕልበት፡ አጥሯቸዋልና፡ መሬቱን፡ በቶሎ፡ እንደ፡ ጥንቱ፡ ለመመለስ፡ ይቸግራቸዋል። ዳሩ፡ ግን፡ በጊዜ፡ ብዛት፡ እንደ፡ ጥንቱ፡ ይሆንላቸዋል። ጥቂት፡ ጊዜ፡ በሰላም፡ እንደ፡ ኖሩ፡ ግን፡ ማንኛው፡ ቆሮ፡

ጠቅላይ፡ ገዢ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ቍርጡ፡ እንዲታወቅ፡ እንደ፡ ገና፡ ትልቅ፡ ጦርነት፡ ይነሣል። አንዱም፡ ቆሮ፡ በጦርነቱ፡ ከሞተ፡ ወይም፡ ከተማረከ፡ በኋላ፡ ቀሪው፡ ቆሮ፡ ዋና፡ ገዢ፡ ሁኖ፡ የሁለቱን፡ ነገዶች፡ ግብር፡ ይቀበላል። የማዕርጉንም፡ ስም፡ ለይቶ፡ ትንሽ፡ ንጉሥም፡ ትብሎ፡ ይቀመጣል። እንደዚህ፡ ያለውም፡ ጦርነት፡ የሚደረገው፡ በእነዚህ፡ በሁለቱ፡ ቆሮዎች፡ መካከል፡ ብቻ፡ አይደለም። በሌሎቹ፡ ቆሮዎች፡ መካከልም፡ ቢሆን፡ እንደዚሁ፡ ነው።

በጊዜ፡ ብዛትም፡ በያገሩ፡ ትንንሽ፡ ነገሥታት፡ ይቆማሉ። ኣንዱም፡ ያንዱን፡ አገር፡ ሊጠቀልል፡ ሲፈልግ፡ በመካከላቸው፡ እየተመላለሰ፡ ጦርነት፡ ይሆናል። የቀናውም፡ አገር፡ ተመልሶ፡ እንደ፡ ገና፡ ይጠፋል። ከአራሾቹም፡ እኩሌቶቹ፡ በጦርነቱ፡ ይሞታሉ። እኩሌቶቹም፡ ይሸሻሉ። በሸሹበትም፡ ስፍራ፡ ደግሞ፡ ረኃብና፡ በሽታ፡ ይፈጃቸዋል። ያንዱን፡ ትንሽ፡ ንጉሥ፡ አገር፡ ሌላው፡ እየጠቀለለው፡ ይሄዳል። በጊዜ፡ ብዛትም፡ ትልልቅ፡ ነገሥታት፡ ይወጣሉ። በውስጣቸውም፡ በግዳይና፡ በዘረፋ፡ የበለጠውን፡ እያዩ፡ ራስ፡ ደጃዝማች፡ እያሉ፡ ይሾማሉ፤የነገሡበትንም፡ አገር፡ ለነርሱ፡ ያካፍላሉ፤የቀረው፡ ሁሉ፡ የነዚህን፡ ማዕርግ፡ እያየ፡ ስምና፡

ሹመት፡ አገኛለሁ፡ እያለ፡ በሕዝቡ፡ ውስጥ፡ ያለው፡ እያንዳንዱ፡ ሰው፡ በግዳይና፡ በዘረፋ፡ እንዲመሰገን፡ ይጥራል። ጦርነቱም፡ ከዱሮ፡ የባሰ፡ ይሆናል።

ከዚህ፡ በኋላ፡ ብዙ፡ አገሮች፡ ባንድ፡ ጊዜ፡ ከልማት፡ ወደ፡ ጥፋት፡ ይወድቃሉ። ከተሞቻቸውና፡ መንደሮቻቸውም፡ ይቃጠላሉ። በሁከትም፡ ምክንያት፡ ሕዝቡ፡ ደኸይቶ፡ ከሠራተኛው፡ በላተኛው፡ በዝቶ፡ ለንጉሡ፡ ስለ፡ ክብር፡ የሚገባለት፡ ገንዘብ፡ ጥቂት፡ ነውና፤ባገሩ፡ ውስጥም፡ ሽፍታ፡ ቢነሣ፡ ሰራዊቱ፡ በፍጥነት፡ የሚሄድበት፡ የተበጀ፡ መንገድና፡ የምድር፡ ባቡር፡ ስለሌለው፡ ሽፍታ፡ ያለበትንና፡ የተነሣበትን፡ አገር፡ በፍጥነት፡ ሊረዳው፡ አይችልም። ንጉሡ፡ በገዛ፡ እጁ፡ በሾማቸው፡ መኳንንት፡ ምሉ፡ ሥልጣን፡ የለውምና፡ ምንም፡ እነርሱ፡ ባንድ፡ ንጉሥ፡ ውስጥ፡ ቢያድሩ፡ ቢገዙም፡ ርስ፡ በ

ርሳቸው፡ መዋጋትን፡ አይተዉም። ይልቁንም፡ ጉልበት፡ ሲሰማቸው፡ ንጉሥን፡ አጥፍተው፡ ራሳቸው፡ ለመንገሥ፡ ያስባሉ። በእንደዚህ፡ ያለ፡ ምክንያት፡ ጦርነት፡ ይነሣል፤በጦርነቱም፡ ብዙ፡ ሰው፡ ይሞታል፤አገሩም፡ ከልማት፡ ወደ፡ ጥፋት፡ ይደርሳል። ሁከትና፡ ቅሚያ፡ ጦርነት፡ ሲበዛ፡ ሕዝቡ፡ ደክሞ፡ ሠርቶ፡ ጥሪ፡ የሰበሰበውን፡ ሁሉ፡ እንዲቀሙት፡ ያውቃልና፡ በእንደዚህ፡ ያለ፡ ሁከት፡ ተስፋ፡ ቈርጦ፡ የጠፋውን፡ መሬት፡ እንደ፡ ገና፡ ለማቅናት፡ አይጣጣርም። ስለዚህ፡ ድኽነትና፡ ስደት፡ በሽታና፡ ሞት፡ ባገሩ፡ ሁሉ፡ ይበዛል። የሰውም፡ ኀይልና፡ ሀብት፡ እየገደለ፡ ይሄዳል። ሰውም፡ የምድሪቱ፡ ጌታ፡ መሆኑ፡ ቀርቶ፡ ችጋረኛና፡ ተገዢዋ፡ ይሆናል። ከእንደዚህ፡ ያለ፡ ባርነት፡ ለመውጣትም፡ እንደ፡ ገና፡ ብii፡ ድካም፡ ያስፈልገዋል። እንሆ፡ የዚህ፡ ዓለም፡ ሕዝቦች፡ የዕውቀታቸውና፡ የሀብታቸው፡ ደረጃ፡ ከፍና፡ ዝቅ፡ ያለ፡ መሆኑ፡ ምክንያቱ፡ ከጦርነት፡ የተነሣ፡ ነው። ጦርነቱንም፡ የሚያነሡ፡ ነገሥታቱና፡ አለቆቹ፡ ሁሉ፡ ልባቸው፡ ሀብት፡ እንደ፡ ፈለገ፡ አይገልጹም። ነገር፡ ግን፡ ስም፡ ለመፈለግና፡ ለማግኘት፡ ወይም፡ ሃይማኖትን፡ ለማስፋት፡ ወይም፡ የተጠቃውን፡ ለመርዳት፡ አስመስለው፡ ይነሣሉ። የጦርነቱ፡ ሁሉ፡ ፍጻሜና፡ ምኞት፡ ግን፡ መዝረፍና፡ ማስገበር፡ ነው። ይህንንም፡ ስላልነ፡ ዕውቀታቸው፡ የሰፋ፡ ነገሥታትም፡ ቢሆኑ፡ መዝረፍን፡ አይትዉም። ኣዘራረፋቸው፡ ግን፡ የዕውቀት፡ አዘራረፍ፡ ነው፤ማለት፡

ከባላገሩ፡ ቤት፡ መዝረፍና፡ መቀማትን፡ ትተው፡ ድል፡ ካደረጉት፡ መንግሥት፡ የጦር፡ ኪሳራ፡ የሚሉት፡ ገንዘብ፡ ጠቅልለው፡ ባንድነት፡ ይቀበላሉ። ያ፡ ድል፡ የሆነው፡ መንግሥት፡ ይህንን፡ የሚከፍለውን፡ ገንዘብ፡ የሚሰበስበው፡ ከገባሮች። ነው። የዚህ፡ የዕውቀት፡ አዘራረፍ፡ ግን፡ አንድ፡ ደግነት፡ አለው፤ማለት፡ የጦርነቱ፡ መከራ፡ ወይም፡ ዕዳ፡ ጠላት፡ ከደረሰባቸው፡ ኣገሮች፡ ላይ፡ ብቻ፡ አይወድቅም። ነገር፡ ግን፡ የዚያ፡ ድል፡ የሆነው፡ መንግሥት፡ በመላው፡ ሕዝብ፡ እንደ፡ ሀብቱና፡ እንደ፡ ድኽነቱ፡ መጠን፡ አዋጥቶ፡ ይከፍለዋል። እነዚህ፡ ዐቅምና፡ ዕውቀት፡ ያላቸው፡ ነገሥታት፡ ዐቅም፡ ከሌለው፡ ንጉሥ፡ አገር፡ ሊቀሙ፡ ሲፈልጉ፡

ይህም፡ ዐቅም፡ የሌለው፡ ንጉሥ፡ ዕውቀት፡ አንሶት፡ ሕዝቡን፡ ቢበድል። ዕውቀት፡ ያላቸው፡ ነገሥታት፡ ዝም፡ ብለው፡ ቢያዩት፡ ዕውቀታቸው፡ የሚዋረድባቸው፡ ያስመስሉታልና፡ ሕዝቡን፡ የሚረዱ፡ ኣስመስለው፡ ንጉሥን፡ ሽረው፡ አገሩን፡ ይቀሙታል። እንደዚህ፡ የመሰለ፡ ከጥቂት፡ ዓመት፡ በፊት፡ ስለ፡ ኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ያዘኑ፡ መስለው፡ ጎረ፡ ቤቶቻችን፡ የሆኑት፡ ነገሥታት፡ ርስ፡ በርሳቸው፡ የተዋዋሉትን፡ ውል፡ ስናይ፡ እንደዚህ፡ ያለውን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ልንረዳው፡ እንችላለን።

እንግዲህ፡ ጦርነት፡ ሁሉ፡ ፍጻሜው፡ ዘረፋና፡ ቅሚያ፡ እንደ፡ ሆነ፡ በግልጽ፡ ተረዳነው። ዘረፋና፡ ቅሚያም፡ ሲበዛበት፡ ሕዝቡ፡ ደኅናውን፡ መሬት፡ እየተወ፡ ለመመከት፡ ወደሚመቸው፡ ስፍራ፡ ይሰደዳል። ስለዚህ፡ ሕዝቡ፡ የሥራው፡ ሥራ፡ እየተመላለሰ፡ ሲፈርስበት፡ የዕውቀትን፡ ዋና፡ ደረጃ፡ በቶሎ፡ ለማግኘት፡ አይቻለውም። ይህ፡ ነገር፡ እውነት፡ መሆኑ፡ ተተካክሎ፡ እንዲገባን፡ የኢትዮጵያን፡ ታሪክ፡ ባጭር፡ ረድፍ፡ እንመልከተው።

ያገራችን፡ የኢትዮጵያ፡ ታሪክ፡ ሊቃውንት፡ እንደሚነግሩን፡ የኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡ ዋና፡ ከተማው፡ ዱሮ፡ አኩስም፡ መሠረተ፡ መንግሥት፡ የሆነው፡ ኣባቶቻችን፡ ስለ፡ መረጡት፡ ነው፡ እንጂ፡ ምናልባት፡ ከሌሎቹ፡ አውራጃዎች፡ የተሻለ፡ ሆኖ፡ አይደለም። የአኩስምን፡ መሬት፡ ያየ፡ የዛሬ፡ ዘመን፡ ሰው፡ እንደዚህ፡ ባለ፡ ጭንጫና፡ ሙቀት፡ የበዛበት፡ ውሃም፡ ያነሰበት፡ ብዙ፡ እኽል፡ የማይበቅልበት፡ አገር፡ ላይ፡ አኩስምን፡ የሚያኽል፡ ከተማ፡ እንዴት፡ ተዠመረ፡ ብሎ፡ ይገረም፡ ይሆናል፤አስተውሎ፡ ካሰበ፡ ግን፡ ነገሩን፡ ያገኘዋል።

በአኵስም፡ ዙሪያ፡ ራቅ፡ ብሎ፡ ያለው፡ አገር፡ ሁሉ፡ ዛፍና፡ ቁጥቋጦ፡ የበዛበት፡ አገር፡ ነው። ጥቂት፡ ራቅ፡ ብለን፡ ወደ፡ ሽሬና፡ ወደ፡ ተከዜ፡ ወደ፡ ወርዒ፡ ብንጓዝ፡ ከዚያ፡ ትልልቅ፡ የቈላ፡ ዛፍና፡ በክረምት፡ ረግረግ፡ የሚሆን፡ ብዙ፡ ሜዳ፡ እናገኛለን። ደኑ፡ ስላልተመነጠረ፡ ሜዳውም፡ ስላልቀና፡ የዚያ፡ ጊዜ፡ ንዳድና፡ ሌላው፡ በሽታ፡ ከዛሬ፡ ይልቅ፡ ያን፡ ጊዜ፡ ይበዛ፡ እንደ፡ ነበረ፡ አይጠረጠርም። አባቶቻችንም፡ በዚያ፡ ጊዜ፡ ደኅና፡ መሣሪያ፡ አልነበራቸውም፤በቊጥራቸውም፡ ጥቂቶች፡ ነበሩና፡ ያነን፡ ደንና፡ ሜዳ፡ ለማቅናት፡ አልተቻላቸውም። ስለዚህ፡ የአኩስምን፡ መጥፎ፡ መሬት፡ ለመምረጥ፡ የግድ፡ ሆነባቸውና፡ ከተማቸውን፡ በዚህ፡ ላይ፡ መሠረቱት።

በኋላ፡ ግን፡ እየበዙ፡ ሲሄዱ፡ ኀይላቸውም፡ እያደገ፡ ሄደና፡ ደንና፡ ረግረግ፡ የማያግዳቸው፡ ሆነ፡ ወደ፡ ግራና፡ ወደ፡ ቀኝም፡ እየተመለከቱ፡ እርሻቸውን፡ አሰፉና፡ ወርዒንና፡ ተከዜንም፡ ተሻገሩ። እንዲህ፡ እያሉም፡ የዛሬዋን፡ ኢትዮጵያ፡ የሚበዛውን፡ ሕዝብ፡ ኣቀኑት። እንደዚሁም፡ ቀጥራቸውና፡ ሀብታቸው፡ እየበዛ፡ ስለ፡ ሄደ፡ ጉልበት፡ ተሰማቸው። ካገራቸውም፡ ውጭ፡ የታወቊ፡ ሕዝቦች፡ ሆኑ። ልጆቻቸውና፡ የልጅ፡ ልጆቻቸውም፡ ያባቶቻቸውንና፡ ያያቶቻቸውን፡ ሞያ፡ አይተው፡ ለሥራ፡ እንዲተጉ፡ ሐውልት፡ እያቆሙ፡ ደንባቸውንና፡ ሥራቸውን፡ እየጻፉ፡ ለኋለኞቹ፡ ትውልዶች፡ መታሰቢያ፡ ይተዉላቸው፡ ዠመር። የእንደዚህ፡ ያሉትንም፡ ሐውልቶች፡ ትራፊ፡ ዛሬም፡ ቢሆን፡ በአኵስም፡ ከተማ፡ እናገኛለን። እነዚህም፡ ሐውልቶች፡ የቆሙበት፡ ዘመን፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዋና፡ ብልጽግናውንና፡ የበለጠ፡ ኃይል፡ ያገኘበት፡ ዘመን፡ እንደ፡ ነበረ፡ ያስረዳል። መሰናክልም፡ በመካከሉ፡ ባያገኘው፡ እስከ፡ ዛሬ፡ ድረስ፡ ከፍ፡ ወዳለው፡ የዕውቀትና፡ የሀብት፡ ደረጃ፡ ይደርስ፡ ነበር። ይህም፡ የሀብትና፡ የዕውቀት፡ ደረጃ፡ መሰናክል፡ የሆነው፡ ጦርነት፡ ነው።

አኵስምን፡ የመሠረቱና፡ ያከስምን፡ መንግሥት፡ ወደክብር፡ ያደረሱ፡ አባቶቻችንም፡ እንደ፡ ቀድሞ፡ ሌሎች፡ ሕዝቦች፡ ሁሉ፡ ብዙ፡ አማልክት፡ ያመልኩ፡ ነበር። በኋላ፡ ግን፡ የእስራኤል፡ ሃይማኖት፡ ተሰማ። ይህም፡ የእስራኤል፡ ሃይማኖት፡ ተሰበከና፡ በጊዜ፡ ብዛት፡ በአኵስም፡ መንግሥት፡ ተከታዮች፡ ውስጥ፡ ተገኘ። የዚህም፡ ያዲሱ፡ ሃይማኖት፡ ተከታዮች፡ እየበዙ፡ ሄዱና፡ አንድ፡ ትልቅ፡ ወገንም፡ ሆኑ። በዚህም፡ የኢትዮጵያ፡

ሕዝብ ፥ የአሕዛብና፡ የእስራኤል፡ ወገን፡ ተብሎ፡ ከሁለት፡ ተለያየ። የሁለቱም፡ ሕዝብ፡ ወገን፡ አለቆች፡ የኢትዮጵያ፡ ጠቅላይ፡ ገዢ፡ እኔ፡ ልሁን፡ እኔ፡ ልሁን፡

ሲሉ፡ በመቀናናት፡ ጦርነት፡ ገጠሙ። በጊዜ፡ ብዛት፡ ግን፡ የእስራኤል፡ ወገን፡ የሆኑት፡ አለቆች፡ ድል፡ አድርገው፡ ኢትዮጵያን፡ ጠቅልለው፡ ለመግዛት፡ በቁ። በዚሁ፡ ጦርነት፡ ምክንያት፡ ግን፡ ተከማችቶ፡ የነበረው፡ ብዙ፡ ሀብትና፡ ብዙ፡ ሰው፡ ጠፋ። ለምቶ፡ የነበረው፡ ብዙ፡ አገር፡ ተመልሶ፡ ረግረግና፡ ምድረ፡ በዳ፡ ሆነ። ይህንም፡ ረግረግና፡ ምድረ፡ በዳ፡ ወደ፡ ዱሮው፡ ልማቱ፡ ለመመለስ፡ ብዙ፡ ዘመናትና፡ ብዙ፡ ድካም፡ አስፈለገ። በጊዜ፡ ብዛት፡ ግን፡ በብዙ፡ ድካም፡ እንደ፡ ገና፡ ቀና። ጥቂት፡ ዘመናት፡ ቈይቶ፡ ደግሞ፡ ከክርስቶስ፡ ልደት፡ በኋላ፡ ባገሩ፡ ሌላ፡ ትልቅ፡ ሁከት፡ ተነሣ። ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ በኢየሩሳሌም፡ ሁኖ፡ የክርስቲያንን፡ ሃይማኖት፡ መሠረተ። ሐዋርያቶቹም፡ በዓለም፡ ሁሉ፡ ወንጌሉን፡ ይሰብኩ፡ ዠመር። በኢትዮጵያም፡ አዲሱ፡ ሃይማኖት፡ ተሰማ፤ብዙም፡ የሆኑ፡ ሰዎች፡ አዲሱን፡ ሃይማኖት፡ በቶሎ፡ ተከተሉ። የአኵስም፡ ንጉሥ፡ አዲሱን፡ ሃይማኖት፡ በትልቅ፡ ውዴታ፡ ተቀበለው። ነገር፡ ግን፡ በግዛቱ፡ ውስጥ፡ አዲሱን፡ ሃይማኖት፡ አንቀበልም፡ የሚሉ፡ ሰዎች፡ ነበሩና፡ ተነሡበት። እነሱም፡ ፈላሾች፡ ናቸው፤እንሆም፡ ከዚሁ፡ ምክንያት፡ የተነሣ፡ በሀገሩ፡ ሁከትና፡ ችጋር፡ በሽታ፡ ገባና፡ ብዙ፡ ሰው፡ ሞተ። ሲታረስም፡ የነበረው፡ ደኅና፡ መሬት፡ እንደ፡ ገና፡ ተመልሶ፡ ተበላሸ። የነዚህም፡ የሁለቱ፡ ሃይማኖት፡ አለቆች፡ ጦርነት፡ ገጠሙና፡ አንድ፡ ጊዜ፡ የክርስቲያኑ፡ ኣለቃ፡ ሌላ፡ ጊዜ፡ የፈላሻው፡ ኣለቃ፡ ድል፡ ሲያደርግ፡ ጦርነቱ፡ ብዙኅ፡ መቶ፡ ዓመታት፡ ቈየ። የኢትዮጵያም፡ ሕዝብ፡ ከፍ፡ ወዳለው፡ የዕውቀትና፡ የሀብት፡ ደረጃ፡ እንዳይደርስ፡ ዋና፡ መሰናከል፡ የሆነው፡ ይህ፡ ነው። በጊዜ፡ ብዛት፡ ግን፡ ፈላሾች፡ ድል፡ ሆኑ፤ የክርስቶስም፡ የወንጌል፡ ቃል፡ ተሰብኮ፡ እየሰፋ፡ ሄደና፡ የኢትዮጵያ፡ ሃይማኖት፡ ሆነ። ባገሩም፡ ሰላም፡ ኀባ። እንሆም፡ ሕዝቡ፡ እንደ፡ ገና፡ በዛ። አገሩም፡ እየለማ፡ ሄደ፤መጥፎውንም፡ መሬት፡ እየተወ፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ እርሻውን፡ ወደ፡ ደቡብ፡ አሰፋ፤አኵስምም፡ የክርስቲያን፡ ዋና፡ ከተማ፡ ሁና፡ ቀረች። የቤተ፡ መንግሥቱ፡ ከተማ፡ ግን፡ በኤረር፡ ተሠራ።

ይህ፡ አሁን፡ በቅርቡ፡ ዐፄ፡ ምኒልክ፡ እንደ፡ ገና፡ ያቀኑትም፡ አገር፡ ሁሉ፡ ዱሮ፡ በኢትዮጵያውያን፡ እጅ፡ ሁኖ፡ የለማ፡ እርሻ፡ ነበረ።

በአሩሲ፡ በከንባታ፡ በያገሩም፡ ሁሉ፡ እስከ፡ ዛሬ፡ ድረስ፡ የዱሮ፡ ቤተ፡ ክርስቲያንና፡ የሐበሻ፡ ቤቶች፡ ፍራሽ፡ የሚገኘው፡ ምክንያቱ፡ ይህ፡ ነው። በኤረርም፡ ነገሥታት፡ ጊዜ፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ኑሮው፡ እንደ፡ አከስም፡ ጊዜ፡ እንኳ፡ ባይሆን፡ ከፊተኛው፡ ዘመን፡ ተሽሎ፡ ነበረ። ነገር፡ ግን፡ እንደ፡ ገና፡ ደግሞ፡ ሁከት፡ ተነሣ። ግራኝ፡ የሚባል፡ የእስላሞች፡ መሪ፡ ሁኖ፡ ባገሩ፡ ላይ፡ አደጋ፡ ጣለበት። ዐሥራ፡ አምስት፡ ዓመት፡ ሙሉም፡ በሰው፡ ላይ፡ ሞት፡ በቤቱም፡ ላይ፡ እሳት፡ አወረደበት። መከረኛውም፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ያቀናውን፡ ፍሬያማውን፡ መሬት፡ ትቶ፡ ዱሮ፡ ወደ፡ ነበረበት፡ ብዙ፡ እኸል፡ ወደማይበቅልበት፡ አገር፡ ለመመከት፡ ወደሚመቸው፡ ወደየተራራውና፡ ወደየገደሉ፡ ጥግ፡ ተመለሰ። ይህ፡ ዛሬ፡ ዳር፡ አገር፡ የሚባለውም፡ አገር፡ ሁሉ፡ በጋላና፡ በሻንቅላ፡ በእስላም፡ እጅ፡ ገባ።

እነዚህም፡ ጋሎች፡ የዕውቀታቸው፡ ደረጃ፡ ዝቅ፡ ያለ፡ ሁኖ፡ የእርሻን፡ ሥራ፡ አለመዱም፡ ነበርና፡ አገሩ፡ ተመልሶ፡ ረግረግና፡ ደን፡ ሆነ። ከዐሥራ፡ አምስት፡ ዓመት፡ በኋላ፡ ግን፡ ግራኝ፡ ድል፡ ሆኖ፡ ሞተ፤የእስላሞች፡ ኃይል፡ ፈጽሞ፡ እንኳ፡ ባይጠፋ፡ ለጊዜው፡ ተሰበረ። በዚሁ፡ ሥራ፡ አምስት፡ ዓመት፡ ውስጥ፡ በችጋርና፡ በጦር፡ በበሽታም፡ ሲል፡ የሚበዛው፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ አለቀ። የተወለዱት፡ ሕፃናትም፡ ከመንገላታት፡ ብዛት፡ የተነሣ፡ ሳያድጉ፡ ሞቱ፡ ። ግራኝ፡ ድል፡ ከሆነ፡ ወዲህም፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዐቅም፡ አንሶት፡ ዱሮ፡ ቀንቶ፡ የነበረውን፡ አገር፡ ሁሉ፡ በቶሎ፡ እንደ፡ ገና፡ ለማቅናት፡ አልተቻለውም። ከዚያ፡ በኋላ፡ ዋናው፡ የኢትዮጵያ፡ ከተማ፡ ጐንደር፡ ሆነ። ከከተማውም፡ ወደ፡ ምሥራቅና፡ ወደ፡ ምዕራብ፡ ወደ፡ ሰሜንና፡ ወደ፡ ደቡብ፡ መንገድ፡ ተኸረጋ፤በትልልቆች፡ ወንዞች፡ ድልድይ፡ ተሠራ፤ስለዚህ፡ ግራኝ፡ የዘራው፡ መርዝ፡ ፈጸሞ፡ ጠፍቶ፡ ቢሆን፡ የሕዝቡ፡ ሀብትና፡ ዕውቀት፡ እንደዚያ፡ ጊዜ፡ አዠማመሩ፡ እስከ፡ ዛሬ፡ ድረስ፡ በጣም፡ ይሰፋ፡ ነበር። ነገር፡ ግን፡ ግራኝ፡ ብዙ፡ ዓመታት፡ አገሩን፡ ሲያጠፋ፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ሥራውን፡ ትቶ፡ ኑሮው፡ ሁሉ፡ በጦርነት፡ ነበር፤በዚያ፡ ጊዜ፡ የተለመደው፡ መዝረፍና፡ መቀማት፡ የሕገበ፡ ባሕርይና፡ ልምድ፡ ሆኖ፡ እስከ፡ ዛሬ፡ ድረስ፡ ቀረ።

ሰጐንደር፡ ነገሥታት፡ ጊዜም፡ በያገሩ፡ ሽፍታ፡ አልታጣም፡ ነበርና፡ በየወረዳው፡ ሁሉ፡ ትልልቅ፡ ሽፍቶች፡ ተነሥተው፡ ለጐንደር፡ ነገሥታት፡ አንገዛም፡ አሉ፤ከነዚሁ፡ ሽፍቶች፡ አንዱ፡ ትግሬው፡ ሚካኤል፡ የጐንደርን፡ ዐፄ፡ ገድለው፡ የኢትዮጵያን፡ መንግሥት፡ አንድነቷን፡ ፈጽመው፡ አጠፉት። ከዚያ፡ ወዲያ፡ በትግሬ፡ በስሜን፡ በጐዣም፤በወሎም፤ በበጌምድርም፡ በሸዋም፡ ራሳቸውን፡ የቻሉ፡ መሳፍንት፡ ወጡ። ከነዚህም፡ ያንዱን፡ አገር፡ አንዱ፡ እጠቀልላለሁ፡ ሲል፡ ርስ፡ በርሳቸው፡ ይዋጉ፡ ነበር። የኢትየጵያም፡ ሕዝብ፡ ከጦርነት፡ ብዛት፡ የተነሣ፡ ሥራ፡ ጠልቶ፡ ባሕሪው፡ ዘረፋና፡ ሰውን፡ መግደል፡ ወደደ። ከዚያ፡ ወዲህ፡ ፍሬያማውን፡ መሬት፡ የሚያርሰው፡ ጠፋ፤ሕዝቡ፡ በሞላው፡ ከድኽነት፡ ጎባ፤ከድኽነት፡ ብዛትም፡ የተነሣ፡ በኤረር፡ ነገሥታት፡ ጊዜ፡ ቀንቶ፡ የነበረውን፡ መሬት፡ ከጋሎችና፡ ከእስላሞች፡ እጅ፡ አስጥሎ፡ እንደ፡ ገና፡ ማቅናት፡ አቃተው። ኢትዮጵያም፡ ብዙ፡ ዘመናት፡ በሁከትና፡ በድኽነት፡ ከኖረች፡ በኋላ፡ ዐፄ፡ ቴዎድሮስ፡ ተነሥተው፡ በየወረዳው፡ ነው፡ የነበሩትን፡ መሳፍንት፡ ሁሉ፡ አሸንፈው፡ ለኢትዮጵያ፡ አንድነቷን፡ መለሱላት። ባገሩም፡ ሰላምና፡ ዕረፍት፡ መግባት፡ ቢዠምር፡ ሥራን፡ መውደድ፡ ተዠመረ። ቴዎድሮስም፡ በኢትዮጵያ፡ ደቡብ፡ ያለውን፡ አገር፡ እንደ፡ ገና፡ ለማቅናት፡ አሰቡ። የሸዋንም፡ ንጉሥ፡ ኀይለ፡ መለኮትን፡ ድል፡ አድርገው፡ ልጃቸውን፡ ምኒልክን፡ ከነመኳንንቶቻቸው፡ ከማረኩ፡ በኋላ፡ ሰአዳና፡ በሜጫ፡ በጉድሩ፡ በጐዣም፡ አድርገው፡ የደረሱበትን፡ ኣገር፡ ሁሉ፡ እያስገበሩ፡ ወደ፡ በጌምድር፡ ተመለሱ። ነገር፡ ግን፡ አሳባቸውን፡ ስመፈጸም፡ አልሆነላቸውም፡ ነበር። የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ከጦርነት፡ ብዛት፡ የተነሣ፡ ባሕሪው፡ ቅሚያንና፡ መዝረፍን፡ ወዶ፡ ነበርና፡ ይህንን፡ ባሕሪውን፡ ባንድ፡ ጊዜ፡ ለማስተው፡ ለብርቱው፡ ቴዎድሮስ፡ እንኳ፡ የማይቻል፡ ነገር፡ ሆነ። በያገሩም፡ ቀማኞችና፡ ሽፍቶች፡ በዙባቸው። ከመናደድም፡ ብዛት፡ የተነሣ፡ ጨካኝ፡ ሆኑ። ሕዝቡም፡ ጠልቷቸው፡ ለባዕድ፡ አሳልፎ፡ ሰጣቸው። ርሳቸውም፡ ውርደትን፡ ጠልተው፡ በገዛ፡ እጃቸው፡ ሞቱ። ያፄ፡ ቴዎድሮስ፡ ሥራ፡ ግን፡ አልጠፋም፡ ነበር፤የትግሬው፡ ዐፄ፡ ዮሐንስ፡ ወርሰው፡ እሰፉት፡ እንጂ። አዘቦና፡ ወለጋ፡ ሐረርጌና፡ አሩሲ፡ እንደ፡ ገና፡ ተመልሰው፡ በኢትዮጵያውያን፡ እጅ፡ ገቡ። ነገር፡ ግን፡ በኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ላይ፡ ሌላ፡ የውጭ፡ ጠላቶች፡ ተነሡ። እነሱም፡ ደርቡሾችና፡ ጣሊያኖች፡ ናቸው። እነዚህም፡ የውጭ፡ ጠላቶች፡ ባገሩ፡ ሁከት፡ ዘሩበት፤ጣሊያኖች፡

የትግሬውን፡ ንጉሠ፡ ነገሥትና፡ የሸዋውን፡ ንጉሥ፡ ልብ፡ ለያዩ። የትግሬንም፡ መኳንንት፡ ርስ፡ በርሳቸው፡ እንዳይስማሙ፡ አደረጉ። ከዚህም፡ የተነሣ፡ ጠብ፡ ባገሩ፡ ተዘራ። ደርቡሾችም፡ በመተማ፡ ወጥተው፡ ደምቢያንና፡ ጐንደርን፡ አጠፉ። ዐፄ፡ ዮሐንስም፡ በሁለት፡ የውጭ፡ ጠላቶቻቸው፡ መካከል፡ ተከበው፡ ተጨነቁ። ባገራቸውም፡ ውስጥ፡ የሸዋው፡ ንጉሥ፡ ዐፄ፡ ምኒልክ፡ ተነሡባቸው። በብስጭትም፡ ተስፋ፡ ቈርጠው፡ ነበርና፡ ሞታቸውን፡ ሲፈልጉ፡ ከደርቡሾች፡ ጋራ፡ ለመዋጋት፡ ወደ፡ መተማ፡ ወረዱ፤የፈለጉትንም፡ ሞት፡ ለዘለዓለም፡ በማይረሳ፡ ዠግንነት፡ በጦርነት፡ ውስጥ፡ አገኙት። የኢትዮጵያም፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ አልጋ፡ በሸዋው፡ ባላባት፡ ባፄ፡ ምኒልክ፡ ተወረሰ። ዐፄ፡ ምኒልክም፡ ጣሊያኖችን፡ በዐድዋ፡ ላይ፡ ድል፡ ካደረጉ፡ በኋላ፡ እግዚአብሔር፡ በኢትዮጵያ፡ ሰላም፡ አወረደባት። በኤረር፡ ነገሥታትም፡ ጊዜ፡ የኢትዮጵያ፡ ግዛት፡ የነበረ፡ አገር፡ ሁሉ፡ እስከሉግና፡ ቦረና ፥ ባኮ ፥ ከፋ ፥ ማጂ ፥ ጊሚራ ፥ ገምቤላ፤ተመልሶ፡ በኢትዮጵያውያን፡ እጅ፡ ገብቶ፡ ይቀና፡ ዠመር። ከኻያ፡ ዓመት፡ ወዲህ፡ የበለጠ፡ ፈጽሞ፡ ሰላም፡ ሆነ። ሕዝቡም፡ ሥራን፡ ይወድ፡ መር፤ሀብቱም፡ ኣድጎ፡ ተመችቶት፡ እየተባዛ፡ ሄደ።

እንሆ፡ ከዚህ፡ በላይ፡ በተጻፈው፡ አጭር፡ የኢትዮጵያ፡ ታሪክ፡ ንድፍ፡ እንደምናየው፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ሀብቱና፡ ዕውቀቱ፡ ሊያድግ፡ ሲዠምር፡ ዘወትር፡ ባገሩ፡ አዲስ፡ ሁከትና፡ ጦርነት፡ ይነሣል። ስለዚህም፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ አቅንቶት፡ የነበረውን፡ ደጎና፡ መሬት፡ እየተወ፡ ሁከትና፡ ጦርነት፡ በተነሣ፡ ቍጥር፡ ለመመከት፡ እንዲመቸው፡ ሲል፡ ዱሮ፡ ወደ፡ ነበረበት፡ ወደ፡ መጥፎው፡ መሬት፡ ይመለስ፡ ነበር። አሁን፡ ግን፡ ሰላም፡ ስላገኘ፡ እንደ፡ ገና፡ ነቃና፡ ሀብቱም፡ እያደገ፡ ይሄድ፡ ዠመር።

የሌሎቹንም፡ ሕዝቦች፡ ታሪክ፡ አስተውለን፡ ብንመረምር፡ ሁከት፡ ካሳገኛቸው፡ ቀጥራቸውም፡ እንዲበዛ፡ ቍጥራቸው፡ ከበዛ፡ ዘንድ፡ በዕውቀታቸውና፡ በሀብታቸው፡ እየተረዳዱ፡ ኀይላቸው፡ እንዲያድግ፤ ኀይላቸውም፡ ሲያድግ፡ መጥፎውን፡ መሬት፡ ትተው፡ ደጎናውን፡ መሬት፡ እንዲያርሱ፡ በግልጽ፡ እንረዳዋለን።

ዛሬም፡ ቢሆን፡ ወደ፡ ወለጋ፡ ወይም፡ ወደ፡ ጊሚራ፡ ብንሄድ፡ ሕዝቦቹ፡ ገላጣውን፡ መሬት፡ እየተዉ፡ በተራራው፡ ላይ፡ ወይም፡ በየተራራው፡ ጥግ፡ እየመረጡ፡ እንደሚሰፍሩ፡ እናያለን። በየተራራው፡

በታች፡ ያለው፡ ዱር፡ ግን፡ ከዚህ፡ ቀደም፡ ብዙ፡ ሰው፡ ያልገባበት፡ ስለ፡ ሆነ፡ አልፎ፡ አልፎ፡ የተመነጠረው፡ ደን፡ ይታያል። ሰውም፡ እየበዛ፡ ሲሄድ፡ ለወደ፡ ፊት፡ ደኑም፡ ሁሉ፡ ሳይመነጠር፡ አይቀርም። ይልቁንም፡ በጊዜ፡ ብዛት፡ ደኑ፡ ፈጽሞ፡ እንዳይጠፋ፡ የሚያስፈራ፡ ነው። ዐፄ፡ ምኒልክም፡ ቢሆኑ፡ ያዲስ፡ አበባን፡ ከተማ፡ ሲመሠርቱ፡ አስቀድመው፡ በእንጦጦ፡ ዠመሩ። የዛሬው፡ ያዲስ፡ አበባ፡ ከተማ፡ ግን፡ ጥንት፡ ዝኆን፡ የሚታደንበት፡ በረሓ፡ ነበር፡ ይላሉ። ከተማውም፡ የቀናው፡ ያፄ፡ ምኒልክ፡ ሰራዊት፡ ከበዛ፡ በኋላ፡ ነው።

ወደ፡ ጐዣምና፡ ወደ፡ በጌምድር፡ ወደ፡ ትግሬም፡ ወደ፡ ላስታና፡ ወደ፡ ወሎም፡ ብንሄድ፡ የዚህን፡ መንገድ፡ ዛሬም፡ ቢሆን፡ ተመስክሮ፡ እናገኘዋለን። ከኻያ፡ ስድስት፡ ዓመት፡ በፊት፡ ከጦርነት፡ ብዛት፡ የተነሣ፡ በነዚህ፡ በኢትዮጵያ፡ አውራጃዎች፡ አስቀድሞ፡ ከብቱ፡ በበሽታ፡ አለቀ። ሰዉም፡ በጦርነት፡ በበሽታና፡ በረኃብ፡ ተቀሠፈ። የቀረውም፡ ጥቂቱ፡ ወደ፡ ሸዋ፡ ተሰደደ። በያገሩ፡ የቀሩትም፡ ሰዎች፡ ደኅናውን፡ መሬት፡ ለማረስ፡ ዐቅም፡ አጥተው፡ የወንዙን፡ ዳርና፡ ደኅናውን፡ ሜዳ፡ እየተዉ፡ በየተራራው፡ ጥግ፡ በዶማ፡ እየቈፈሩ፡ ይዘሩ፡ ነበሩ። በኋላ፡ ግን፡ ከእነዚህ፡ ችጋር፡ ከገባባቸው፡ ኣገሮች፡ ብዙ፡ ሰው፡ ወደ፡ ሐማሴንና፡ ወደ፡ ሸዋ፡ እየተሰደደ፡ ሠርቶ፡ ለበሬና፡ ለላም፡ መግዣ፡ የሚሆን፡ ገንዘብ፡ አግኝቶ፡ እየተመለሰ፡ እንደ፡ ገና፡ ያባቱን፡ መሬት፡ አቀና። ዐፄ፡ ምኒልክም፡ በብዙ፡ ረዱት። በዚሁ፡ ምክንያት፡ ሕዝቡ፡ ዐቅም፡ ኣግኝቶ፡ ዛሬ፡ የወንዙን፡ ዳርና፡ ሜዳውን፡ ያርስ፡ ዠመር፤ሁሉን፡ ግን፡ ጨርሶ፡ አላለማውም፤ወደ፡ ፊት፡ ግን፡ እንደ፡ ዛሬው፡ ሰላም፡ ከቈየለት፡ ዘንድ፡ ሁከትና፡ ጦርነት፡ እንደ፡ ገና፡ ካልተነሣበት፡ ሕዝቡ፡ ሳይበዛ፡ አይቀርምና ፥ በጊዜ፡ ብዛት፡ አገሩ፡ እንደ፡ ዱሮ፡ ሳይለማ፡ አይቀርም።

# ፫ኛ፡ ምዕራፍ።

## የሥራን፡ ሚዛንና፡ የዋጋን፡ ትርጒም፡ ከሦስት፡ ትንንሽ፡ ክፍል፡ ይከፍሏል።

### አርእስት።

የአይሁዶችና፡ የክርስቲያኖች፡ የሃይማኖት፡ መጽሐፍ፡ በኦሪት፡ ዘፍጥረት፡ ፩፡ እስከ ፳፰፡ እንደሚያስተምረን፡ እግዚአብሔር፡ ሰው፡ ዓለምን፡ እንዲገዛ፡ ፈጠረው። አለውም፡ ብዙ፡ ተባዙ፡ ምድርንም፡ ምሏት፡ ግዟትም። እውነትም፡ የሰው፡ ጥረቱ፡ ምድርን፡ ለመግዛት፡ ነው። በመዠመሪያ፡ ግን፡ ተገዢዋ፡ እንደ፡ ነበረ፡ ከዚህ፡ ቀደም፡ ተረድተነዋል፤ ጌታዋ፡ የሆነ፡ በጊዜ፡ ብዛት፡ ነው። መሣሪያዎችና፡ ሌላም፡ ብዙ፡ ነገር፡ አግኝቶ፡ ተጣጥሮም፡ ተባዝቶም፡ የምድር፡ ጌታ፡ ለመሆን፡ በቃ። እነዚህንም፡ በጊዜ፡ ብዛት፡ ያገኛቸውን፡ መሣሪያዎች፡ ከፍና፡ ዝቅ፡ አድርጎ፡ ይገምታቸው፡ ዠመር። እንዴት፡ ባለ፡ ሐሳብ፡ እንደ፡ ገመታቸው፡ ለመረዳት፡ የፈለግን፡ እንደ፡ ሆነ፡ ግን፡ ወደ፡ ቀድሞው፡ ምሳሌያችን፡ እንመለስ።

## መዠመሪያ፡ ክፍል።

ያ፡ ለምሳሌ፡ ወደ፡ አንድ፡ ደሴት፡ ተሰደደ፡ ያልነው፡ ሰውዬ፡ እደሴቱ፡ ውስጥ፡ እንደ፡ ገባ፡ በዙሪያው፡ የደን፡ ፍሬና፡ አበባ፡ ወፎችና፡ የደን፡ አራዊት፡ በያይነቱ፡ ከበውት፡ ይኖሩ፡ ነበር። የነዚህም፡ ሁሉ፡ ጌታ፡ ለመሆን፡ በመዠመሪያ፡ ዐቅም፡ አላገኘም፡ ነበር። በኑሮው፡ ሁሉ፡ እንዳልተሳካለትና፡ እንዳልሆነለት፡ እናያለን፤ሚዳቋዪቱ፡ በሩጫዋ፡ ስታመልጠው ፥ ወፉም በክንፉ፡ ሲበርበት ፥ ዓሣውም፡ ወደ፡ ውሃው፡ ውስጥ፡ ሲጠልቅበት ፥ የዛፉም፡ ፍሬ፡ ሲደርቅበት፡ ለምግቡ፡ የሚሆን፡ ነገር፡ አጥቶ፡ ጥቂት፡ ጊዜ፡ መቸገሩ፡ አይቀርም። ያ፡ ለምግቡ፡ የሚሆነው፡ ነገር፡ ሁሉ፡ በዙሪያው፡ ሳለ፡ ስደተኛው፡ ሰውዬ፡ በረኃብ፡ ሲቸገር፡ ይኖር፡ ነበር። መጥረቢያ፡ ቢኖረው፡ ዛፉን፡ ቈርጦ፡ ዕንጨቱን፡ ፈልጦ፡ ደኅና፡ ቤት፡ ለመሥራት፡ አይሳነውም፡ ነበር። ነገር፡ ግን፡ መጥረቢያ፡

ስላልኖረው፡ በጕድጓድ፡ ለመኖር፡ ግድ፡ ሆነበት። በመጀመሪያ፡ ዶማ፡ ስላልኖረው፡ የደኑን፡ ፍሬ፡ እየለቀመ፡ ሲመገብ፡ ነበር። በኋላ፡ ግን፡ ቀስትና፡ ጀልባ፡ በድንጋይና፡ በእሳት፡ አበጅቶ፡ ለምግቡ፡ የአውሬና፡ የዓሣ፡ ሥጋ፡ ይመገብ፡ ዠመር። ነገር፡ ግን፡ ይህ፡ ምግብ፡ እንደ፡ ዛፉ፡ ፍሬ፡ በፍጥነት፡ የማይገኝ፡ ስለ፡ ሆነ፡ በርሱ፡ ዐይን፡ ከፍሬው፡ ይልቅ፡ ሥጋው፡ ተወደደ፤ስለዚህ፡ ስደተኛው፡ ሰውዬ፡ ሥጋውን፡ እስኪያገኘው፡ ድረስ፡ ዕንቅፋት፡ የሚሆነው፡ ነገር፡ ብዙ፡ ነበርና፡ አስቀድሞ፡ ይህን፡ ሁሉ፡ ማሸነፍ፡ ያስፈልገዋል። ዋጋውም፡ በጥቂት፡ ድካም፡ ከሚለቀመው፡ የዛፍ፡ ፍሬ፡ ይበልጥበታል። አንባቢው፡ ግን፡ እንዲህ፡ ብሎ፡ ይጠይቅ፡ ይሆናል። ሰውዬው፡ ፍሬውንና፡ ሥጋውን፡ ያገኘው፡ በገዛ፡ እጁ፡ ነው፤ ከሌላ፡ ሰው፡ አልገዛውም፡ ቢባል፡ ስለዚህ፡ የሥጋው፡ ዋጋ፡ ከፍሬው፡ ዋጋ፡ እንዲበልጥ፡ በምን፡ ዐወቀው፡ ይሆን፤የዚህ፡ ጥያቄ፡ መልሱ፡ ግን፡ አጭር፡ ነው። ሰውዬው፡ የደኑን፡ ፍሬና፡ ሥጋውን፡ ምንም፡ ከሌላ፡ ሰው፡ ባይገዛው፡ ሥርቶና፡ ለፍቶ፡ ነው፡ እንጂ፡ በከንቱ፡ አላገኘውም። ይህም፡ ሥራው፡ ዋጋ፡ መሆኑ፡ ነው። የደኑን፡ ፍሬ፡ ለመልቀም፡ እዛፉ፡ ላይ፡ ከመውጣት፡ በቀር፡ ሌላ፡ ድካም፡ አልነበረበትም፤ሥጋው፡ የሆነ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ግን፡ እንደ፡ ፍሬው፡ በቀላል፡ ድካም፡ አይገኝም። ሥጋውን፡ ለማግኘት፡ ግን፡ አስቦ፡ ቀስት፡ አበጅቶ፡ አጨማመት፡ ተምሮ፡ በሜዳና፡ በዳገት፡ በቀልቀለት፡ ሩጦ፡ ሁል፡ ጊዜም፡ አይቀናውም፡ ይሆናል። በቀስቱም፡ አውሬን፡ ለመግደል፡ አዘጋገቡና፡ አወራወሩም፡ የብዙ፡ ጊዜ፡ ትምርት፡ ያስፈልገዋል። ባዘገበ፡ ቍጥር፡ ሁልግዜ፡ አውሬ፡ አይገድልም፤ ዓሣ፡ ለመልቀምም፡ አስቦ፡ ጀልባና፡ መረብ፡ አበጅቶ፡ ጀልባውንም፡ ማዕበል፡ እንዳይሰብርበት፡ ያስፈራው፡ ነበር። መረቡንም፡ በጣለው፡ ቍጥር፡ ዓሣ፡ አይዝለትም። አንዳንድ፡ ቀንስ፡ ባዶ፡ እጁን፡ ይገባ፡ ይሆናል፤ ስለዚህ፡ የአውሬና፡ የዓሣ፡ ሥጋ፡ እስኪያገኝ፡ ድረስ፡ አስቀድሞ፡ መሰናከል፡ የሆነውን፡ ብዙ፡ ነገር፡ ማሸነፍ፡ ያስፈልገዋልና፡ ከፍሬው፡ ይልቅ። ሥጋው፡ ይወደድበታል። በእንደዚህ፡ ያለ፡ ምክንያት፡ የማናቸውም፡ ነገር፡ ዋጋ፡ ሲገመት፡ ያ፡ ነገር፡ እስኪገኝ፡ ያለው፡ ድካም፡ ሁሉ፡ እንደ፡ መገመት፡ ያኽል፡ ነው። ስለዚህ፡ አንባቢ፡ ሆይ፡ አስተውል። ማናቸውም፡ ነገር፡ እስኪገኝ፡ ድረስ፡ መሰናከሉ፡ ድካሙ፡ እያነሰ፡ ሲሄድ፡ የዚያ፡ ነኀር፡ ዋጋው፡ እያነሰ፡ ይሄዳል። ማናቸውንም፡ ነገር፡ ለማግኘት፡ መሰናከሉ፡ ድካሙ፡ ከበዛ፡ ዘንድ፡ የዚያ፡ ነገር፡ ዋጋ፡ እየበዛ፡ ይሄዳል።

ማለት፡ በምሳሌ፡ ብንተረጕመው፡ ሰውዬው፡ ቀስት፡ ሳይሠራ፡ የአውሬን፡ ሥጋ፡ ሲፈልግ፡ አውሬውን፡ በሩጫው፡ ይዞ፡ መግደል፡ ያስፈልገው፡ ነበር። ስለዚህ፡ የአውሬው፡ ሥጋ፡ ዋጋው፡ ውድ፡ ነበር። ቀስት፡ ካበጀ፡ በኋላ፡ ግን፡ ድካሙ፡ ቀለለና፡ የአውሬው፡ ሥጋ፡ ዋጋ፡ ቀለለለት። ደግሞም፡ በኋላ፡ ጠመንጋን፡ አበጀ። የአውሬን፡ ሥጋ፡ ለማግኘት፡ ድካሙ፡ ፈጽሞ፡ ቀለለ። እንሆም፡ የአውሬው፡ ሥጋ፡ ዋጋው፡ በጣም፡ ዝቅ፡ አለ። ዛሬም፡ ቢሆን፡ ባገር፡ ያለው፡ ጠመንዣ፡ ሁሉ፡ ጠፍቶ፡ እንደ፡ ገና፡ ሰው፡ ወደ፡ ቀስት፡ ቢመለስ፡ የአውሬው፡ ሥጋ፡ ዋጋው፡ እንደሚወደድ፡ የታወቀ፡ ነው፤ከዚያም፡ በኋላ፡ ቀጥሎ፡ ቀስት፡ ሁሉ፡ ካገር፡ ጠፍቶ፡ የአውሬን፡ ሥጋ፡ ለማግኘት፡ እንደ፡ ቀድሞ፡ ሩጦ፡ መያዝ፡ የሚያስፈልግበት፡ ጊዜ፡ ቢመጣ፡ የአውሬው፡ ሥጋ፡ እንደ፡ ገና፡ በጣም፡ በተወደደ፡ ነበር። በእኽልም፡ በልብስም፡ በሌላም፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ቢሆን፡ እንደዚሁ፡ ነው። ዕውቀት፡ ሲበዛ፡ ማናቸውንም፡ ለኑሮ፡ የሚያስፈልገውን፡ ነገር፡ ለማግኘት፡ መሰናክሉና፡ ድካሙ፡ ያንሳልና፡ የዕቃ፡ ሁሉ፡ ዋጋ፡ ያንሳል። ዕውቀት፡ ቢያንስ፡ ግን፡ ኑሮ፡ የሚያስፈልግ፡ ማናቸውም፡ ነገር፡ ሁሉ፡ መሰናክሉና፡ ድካሙ፡ ከበዛ፡ ዘንድ፡ የዕቃውም፡ ዋጋ፡ እየበዛ፡ ይሄዳል።

አንባቢው፡ ግን፡ ይህ፡ ነገር፡ በቶሎ፡ አይገባውምና፡ እንዲህ፡ ብሎ፡ እንደ፡ ገና፡ ይጠይቅ፡ ይሆናል፤ዐፄ፡ ምኒልክ፡ ከነገሡ፡ ወዲህ፡ በኢትዮጵያ፡ ዕውቀት፡ እየበዛ፡ ሄደ። የእኽል፡ ዋጋ፡ ግን፡ ከዱሮ፡ ይልቅ፡ ዛሬ፡ ተወደደ፤ዱሮ፡ ባንድ፡ ብር፡ አንድ፡ ዳውላ፡ ጤፍ፡ ይሸመት፡ ነበር። ዛሬ፡ ግን፡ አንድ፡ ዳውላ፡ ጤፍ፡ ዋጋው፡ ዐሥር፡ ብር፡ ሆነ። ስለዚህ፡ ዕውቀት፡ ሲበዛ፡ የሁሉም፡ ነገር፡ ዋጋ፡ ያንሳል፡ የተባለው፡ ሐሰት፡ አይሆንምን፤የዚህ፡ መልስ፡ እንዲህ፡ ነው። ኣንባቢ፡ ሆይ፡ አንተ፡ ብትሳሳት፡ ነው፡ እንጂ፡ የጤፍ፡ ዋጋ፡ ከዱሮው፡ ዋጋ፡ አነሰ፡ እንጂ፡ አላደገም። ከዚህ፡ ቀደም፡ ማናቸውም፡ አንዳች። ነገር፡ እስቲገኝ፡ ድረስ፡ ያለው፡ መሰናክልና፡ ድካም፡ ዋጋ፡ ሲገመት፡ ያ፡ ነገር፡ እስቲገኝ፡ ድረስ፡ ያለውን፡ መሰናክልና፡ ድካም፡ ሁሉ፡ እንደ፡ መገመት፡ ያኽል፡ ነው፡ ብለን፡ ነበር።

እንግዲህ፡ ዋጋ፡ ማለት፡ የሥራ፡ መለኪያ፡ ማለት፡ ነው። እንግዲያስ፡ አንባቢ፡ ሆይ፡ አስተውል። ብርኽን፡ ይዘኽ፡ ጤፍ፡ ለመሸመት፡ ወደ፡

ገበያ፡ ብትሄድ፤ባለጤፍ፡ አራት፡ ቀና፡ ወይም፡ ሁለት፡ ቀና፡ ይልኻል። ምነው፡ ዱሮ፡ አንድ፡ ዳውላ፡ ሲሸመት፡ አልነበርምን፡ ብለሽ፡ ብትጠይቀው፤ባለጤፉ፡ የቀድሞ፡ ዘመንን፡ ገበያ፡ የሚያውቅ፡ ሽማግሌ፡ ከሆነ፡ እንዲህ፡ ብሎ፡ ይመልስልኻል። ወዳጄ፡ ሆይ፡ ዱሮ፡ እንጂ፡ አንድ፡ ብር፡ ለማግኘት፡ ብዙ፡ ድካም፡ ያስፈልግ፡ ነበር። ያውም፡ ቢገኝ፡ በነጋዴዎች፡ እጅ፡ ነበር። እነዚህም፡ ነጋዴዎች፡ ብሯን፡ ለማግኘት፡ ሲሉ፡ በደንከሊ፡ ኣገርና፡ በአውሳ፡ በረሓ፡ ያለውን፡ መከራ፡ ሁሉ፡ ሲቀበሉ፡ ነበር። ሽፍታና፡ በሽታም፡ ብዙ፡ ሰውና፡ ከብትም፡ ያስቀርባቸው፡ ነበር። ዛሬ፡ ግን፡ ብርን፡ ለማግኘት፡ ይህን፡ ሁሉ፡ ድካም፡ አያስፈልግም፤ዱሮ፡ አንድ፡ ብር፡ ለማግኘት፡ ሲደከም፡ የነበረውን፡ ድካም፡ ዛሬ፡ ሠላሳ፡ ብር፡ ያተርፍበታል። የእርሻው፡ ድካም፡ ያው፡ እንደ፡ ዱሮው፡ ነው፤ድካሙም፡ አላነሰውም። እንግዲህ፡ ባንድ፡ ብር፡ አንድ፡ ዳውላ፡ ስለ፡ ተሸመተ፡ ዛሬ፡ ዳውላውን፡ በሠላሳ፡ ብር፡ እንደ፡ መሸመት፡ ያኽል፡ ነው። ዛሬም፡ ቢሆን፡ አራት፡ ቀና፡ ጤፍ፡ ባንድ፡ ብር፡ ብታገኝ፡ መልካም፡ ነው፤ጤፉ፡ በጣም፡ ረክሶልኻል። እንደ፡ ዱሮ፡ ሒሳብስ፡ ባንድ፡ ብር፡ ፩፡ ቀና፡ ትኩል፡ ብቻ፡ መሸመት፡ ይገባኽ፡ ነበር፤እንግዲህ፡ አንባቢ፡ ሆይ፡ በዚሁ፡ ምሳሌ፡ መጠራጠርኽን፡ ተረድተኽ፡ ትሄድ፡ ይሆናል፡ እንጂ፡ ምን፡ ሌላ፡ ምክንያት፡ ታመጣ፡ ይሆን። ነገር፡ ግን፡ ሌላ፡ ምሳሌ፡ ማስረጃ፡ ባሳይኽ፡ ዋጋ፡ ማለት፡ የሥራ፡ መለኪያ፡ ማለት፡ ነው፡ እንጂ፡ ሌላ፡ ትርጓሜ፡ ይኖረዋል፡ ብለኽ፡ አትጠራጠርም።

አሁን፡ ወዳንድ፡ አገር፡ መንደር፡ ብንሄድ፡ በዚያም፡ አንድ፡ በርኖስ፡ ሰፊና፡ አንድ፡ ገበሬ፡ ሲገበያዩ፡ ብናይ ፥ ባለበርኖሱ፡ ስድስት፡ ቀን፡ የደከመበትን፡ በርኖሱን፡ ለገበሬው፡ ሲሸጥ፡ ስድስት፡ ቀን፡ የተሠራበትን፡ እኽል፡ ይፈልጋል። ማለት፡ የበርኖሱ፡ ሺያጭ፡ የበጉን፡ ጠጕር፡ ቈርጦ፡ ነድፎ፡ ፈትሎ፡ በርኖሱን፡ ሠርቶ፡ እስቲጨርስ፡ ድረስ፡ ስድስት፡ ቀን፡ የፈጀበት፡ እንደ፡ ሆነ፡ ገበሬውም፡ ይህነን፡ በርኖስ፡ ለመግዛት፡ ቢፈልግ፡ አርሶ ፥ ጐልጕሎ፡ ዐርሞ፡ ዐጭዶ ፥ ወቅቶ፡ በስድስት፡ ቀን፡ ሒሳብ፡ ያገባውን፡ እኽል፡ ለባለበርኖሱ፡ ይሰጣል። እንግዲያስ፡ ዋጋ፡ ማለት፡ የሥራ፡ መለኪያ፡ ማለት፡ ነው። ይህ፡ ሳይቀር፡ ባለበርኖስ፡ ዐሥር፡ ቀን፡ የደከመበትን፡ በርኖስ፡ ስድስት፡ ቀን፡ ለተደከመበት፡ እኽል፡ መለወጥ፡

የግድ፡ ሲሆንበት፡ ሥራው፡ የማይጠቅም፡ እንደ፡ ሆነ፡ ይረዳና፡ አራሽ፡ ይሆናል።

አራሹም፡ እንዲሁ፡ ዐሥር፡ ቀን፡ የለፋበትን፡ ጤፍ፡ ስድስት፡ ቀን፡ ለተለፋበት፡ በርኖስ፡ መለወጥ፡ የግድ፡ ሲሆንበት፡ ሥራው፡ የማይጠቅም፡ እንደ፡ ሆነ፡ አይቶ፡ እርሻውን፡ ትቶ፡ በርኖስ፡ ሠሪ፡ ይሆናል፤በሌላም፡ ሥራ፡ ሁሉ፡ እንደዚሁ፡ ነው። ብረት፡ ሠሪና፡ ሸክላ፡ ሠሪም፡ ሌላም፡ ሠራተኛ፡ ሁሉ፡ እንደ፡ ሥራው፡ መጠን፡ ዋጋውን፡ ካላገኘ፡ የዱሮ፡ ሥራውን፡ ትቶ፡ እንደ፡ ድካሙ፡ መጠን፡ ዋጋ፡ የሚያገኝበትን፡ ሌላ፡ ሥራ፡ ይፈልጋል። ተጠራጣሪው፡ አንባቢ፡ ግን፡ ደግሞ፡ እንደዚህ፡ ይል፡ ይሆናል።

አንጠረኛው ፥ ብረት፡ ሠሪው ሸማኔው፡ ገበሬው ፥ ርሱ፡ ራሱ፡ ገበያ፡ ኣይሄድም፤ነገር፡ ግን፡ ሁሉን፡ ነገር፡ ወደ፡ ገበያ፡ ወስዶ፡ ዋጋውን፡ ከፍና፡ ዝቅ፡ የሚያደርገው፡ ነጋዴ፡ ነው። ነጋዴው፡ አይሠራም፤ዕቃውን፡ ግን፡ ዋጋውን፡ ከፍና፡ ዝቅ፡ እያደረገ፡ እንደ፡ ወደደ፡ ይሸጣል። የዕቃውን፡ ዋጋ፡ ዝቅ፡ የሚያደርግ፡ ሌላ፡ ባላንጣ፡ ነጋዴ፡ ርሱ፡ የሚሸጠውን፡ ዕቃ፡ ሲሸጥ፡ ያየ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ንግዱን፡ ያቆማል፤ወይም፡ ጨርሶ፡ ሥራውን፡ ለመተው፡ ያስባል። ባላንጣ፡ እንደሌለው፡ ሲያይ፡ ግን፡ ዕቃውን፡ ሁሉ፡ ብርቅ፡ አድርጎ፡ ከፍ፡ ያለ፡ ዋጋ፡ ይፈልግበታል። ስለዚህ፡ ዋጋ፡ የሥራ፡ መለኪያ፡ መሆኑን፡ እንግዲህ፡ በምን፡ እንረዳው። ለዚህም፡ መልስ፡ አለው፤በርኖስ፡ ሠሪና፡ ኣራሹ፡ ሸማኔውም፡ ጎረ፡ ቤቶች፡ የሆኑ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ዕቃቸውን፡ እንደየሥራቸው፡ መጠን፡ እንዲለዋወጡ፡ የታወቀ፡ ነው። ቤቶቻቸው፡ የእኩል፡ ቀን፡ ያኽል፡ የተራራቁ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ግን፡ አራሹ፡ ስድስት፡ ቀን፡ የተደከመበትን፡ በርኖስ ፥ ወይም፡ ሸማ፡ መግዛት፡ ሲፈልግ፡ ከዚያ፡ ሄዶ፡ በርኖሱን፡ ወይም፡ ሸማውን፡ ገዝቶ፡ እስኪመለስ፡ ድረስ፡ ያንድ፡ ቀን፡ ሥራ፡ ይፈታል። ስለዚህ፡ በርኖሱን፡ ወይም፡ ሸማውን፡ ይዞ፡ ከቤቱ፡ ሲገባ፡ ያ፡ በርኖስ፡ ወይም፡ ሸማ፡ ስድስት፡ ቀን፡ የፈጀበት፡ ጤፍና፡ ያንድ፡ ቀን፡ መንገድ፡ ድካም፡ ይፈጅበታል።

የበርኖሱ፡ ጌታና፡ ሸማኔውም፡ ቢሆኑ፡ እንደዚሁ፡ ስድስት፡ ቀን፡ የተደከመበትን፡ ጤፍ፡ ሲፈልጉ፡ እስከ፡ አራሹ፡ ቤት፡ ድረስ፡ ሄደው፡ በስድስት፡ ቀን፡ ድካም፡ በርኖስና፡ ሸማ፡ ስድስት፡ ቀን፡ የተደከመበትን፡

ጤፍ፡ ለውጠው፡ ወደ፡ ቤታቸው፡ እስኪመለሱ፡ ድረስ፡ የሰባት፡ ቀን፡ ድካም፡ ይሆንባቸዋል።

ስለዚህ፡ ዋጋ፡ የሥራ፡ መለኪያ፡ ነውና፤ጤፉን፡ እቤታቸው፡ ካጕቡት፡ በኋላ፡ ሌላ፡ ከጎረ፡ ቤት፡ መጥቶ፡ በበርኖስ፡ ወይም፡ በሸማ፡ ለውጡኝ፡ ቢላቸው፡ ሰባት፡ ቀን፡ የተደከመበት፡ ሸማ፡ ወይም፡ በርኖስ፡ አምጣ፡ ይሉታል። እንደዚሁም፡ ገበሬው፡ ስድስት፡ ቀን፡ በተለፋበት፡ ጤፍ፡ የገዛውን፡ በርኖስ፡ ሌላ፡ ጎረ፡ ቤት፡ መጥቶ፡ በጤፍ፡ ለውጠኝ፡ ቢለው፡ ያ፡ ገበሬ፡ ስድስት፡ ቀን፡ የለፋበትን፡ ጤፍ፡ የገዛበትን፡ አንድ፡ ቀን፡ ያስብና፡ ሰባት፡ ቀን፡ የተለፋበትን፡ ጤፍ፡ አምጣ፡ ይለዋል። አራሹ፡ በርኖስ፡ ለመግዛት፡ ርሱ፡ ራሱ፡ ባይሄድ፡ ነገር፡ ግን፡ ልጁን፡ ወይም፡ ሚስቱን፡ ልክ፡ ያው፡ ነው፤ከቤት፡ ይረዱት፡ የነበረውን፡ ሥራ፡ ይፈቱበታል፤ያነን፡ ለማምጣት፡ አንድ፡ ቀን፡ ሥራ፡ ፈተው፡ ውለው፡ ርሱ፡ ሠርቶ፡ ካገባው፡ እኽል፡ ይመገባሉ። ነገር፡ ግን፡ የነዚህ፡ ሁሉ፡ ቦታ፡ የተራራቀና፡ የሦስት፡ ቀን፡ መንገድ፡ የሚያውል፡ የሆነ፡ እንደ፡ ሆነ፡ የፈለጉትን፡ ነገር፡ ለማምጣት፡ ሦስት፡ ቀን፡ ይለፋ፡ ይሆንን፡ እንዲህ፡ አይደለም፤ነገር፡ ግን፡ በመካከላቸው፡ ተላላኪዎች፡ የሚሆኗቸው፡ ሌሎች፡ ሰዎች፡ ይገኛሉ። እነዚህም፡ ተላላኪዎች፡ ስድስት፡ ቀን፡ የተደከመበት፡ ጤፍ፡ ይህው፡ ሂደው፡ ዘጠኝ፡ ቀን፡ የተደከመበትን፡ በርኖስና፡ ሸማ፡ ገዝተው፡ ይመለሳሉ። ከዚያ፡ ወዲያ፡ ሸማውና፡ በርኖሱ፡ ፲፪፡ ቀን፡ የተደከመበት፡ ተብሎ፡ ይታሰባል፤ሌላ፡ ጎረ፡ ቤት፡ መጥቶ፡ በጤፍ፡ ለውጡኝ፡ ያላቸው፡ እንደ፡ ሆነ፡ ፲፬፡ ቀን፡ የተደከመበትን፡ ጤፍ፡ አምጣ፡ ይስታል፤ርሱም፡ በዚያው፡ ስሌት፡ ገዝቶ፡ ይሄዳል። ተላላኪዎቹም፡ የስድስት፡ ቀን፡ ድካም፡ ጤፍ፡ በ፫፡ ቀን፡ ሥራ፡ ትርፍ፡ ያገኛሉ። እነዚህ፡ ተላላኪዎች፡ ጥቂቶች፡ የሆኑ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ለጊዜው፡ መልካም፡ ትርፍ፡ ያገኛሉና፡ የቀሩት፡ አራሾች፡ ይህንን፡ ትርፍ፡ ተመልክተው፡ እርሻቸውን፡ ትተው፡ ተላላኪዎች፡ ይሆናሉ። ቈይቶ፡ የተላላኪዎች፡ ቍጥር፡ በዝቶ፡ የላኪዎች፡ ቍጥር፡ ያነሰ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ግን፡ ተላላኪዎች የድካማቸውን፡ ዋጋ፡ እንደ፡ ፊተኛው፡ ሊያገኙ፡ አይችሉም። ዋጋቸው፡ እያነሰ፡ ይሄዳልና፡ የተላላኪዎች፡ ሥራ፡ እንደማይጠቅም፡ አይተው፡ ሌላ፡ ሥራ፡ ለመፈለግ፡ ይሄዳሉ። ተላላኪዎች፡ ቊጥራቸው፡ በመጠን፡ የሆነ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ዋጋቸውንም፡ እንደ፡ ድካማቸው፡ መጠን፡ ያገኛሉ። እነዚህ፡ ተላላኪዎች፡

የምንላቸው፡ ሰዎች፡ ነጋዴዎች፡ ናቸው። ስለዚህ፡ ነጋዴ፡ ያንዱን፡ ዕቃ፡ ዋጋ፡ ከፍና፡ ዝቅ፡ ቢያደርግ፡ ለጊዜው፡ ነው፡ እንጂ፡ የዕቃው፡ ዋጋ፡ ውሎ፡ አድሮ፡ በተሠራበት፡ ሚዛን፡ መግባቱ፡ አይቀርም። ነጋዶችም፡ የዕቃውን፡ ዋጋ፡ ከፍ፡ ዝቅ፡ ቢያደርጉ፡ የመንገዱንና፡ የርቀቱን፡ ሚዛንና፡ ድካም፡ ሲያስተካክሉ፡ ነው፡ እንጂ፤ዋጋና፡ ሥራ፡ በትክክል፡ ይሄዳል። ከገበሬው፡ ቤት፡ እስከ፡ ባለበርኖሱ፡ ቤት፡ የሚወስድ፡ መንገድ፡ ገደልና፡ ጐርፍ፡ ቢኖርበት፡ የተላላኪ፡ ድካሙ፡ ብዙ፡ ነውና ፥ ዋጋው፡ ይበዛል። መንገዱ፡ ግን፡ ገደሉ፡ ደለደል፡ ወንዙም፡ ድልድይ፡ ቢሠራበት፡ የተላላኪው፡ ድካም፡ ያንሳልና፤ዋጋውም፡ ያንሳል። ከዚሁም፡ የትሻለ፡ ሆኖ፡ መንገዱ፡ ጋሪ፡ እንደሚያስኬድ፡ ሁኖ፡ ቢጠረግም፡ የግድ፡ የበለጠ፡ ድካሙ፡ ይቀላል፤ዘጠኝ፡ ተላላኪዎች፡ ተሸክመው፡ የማይችሉትን፡ ዕቃ፡ ወይም፡ እኸል፡ በጋሪ፡ አንድ፡ ፈረስ፡ ጐትቶ፡ ያመጣዋል። እንደዚህ፡ የሆነ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ባለሸማና፡ ባለበርኖስ፡ ጤፍ፡ ሲፈልጉ፡ ባሰጤፉም፡ በርኖስና፡ ሸማ፡ ሲፈልግ፡ እንደ፡ ዱሮው፡ ለተላላኪ፡ ብዙ፡ ዋጋ፡ አይሰጡም።

የምድር፡ ባቡር፡ ከተሠራ፡ በኋላ፡ ግን፡ የተላላኪው፡ ዋጋ፡ ፈጽሞ፡ ጥቂት፡ ይሆናል።

ስለዚህ፡ ዕውቀት፡ ሲበዛ፡ ለኑሮ፡ የሚያስፈልገውን፡ ማናቸውንም፡ ነገር፡ ለማግኘት፡ መሰናክሉ፡ ያንሳል። የማናቸውም፡ ዋጋ፡ ሁሉ፡ ዝቅ፡ ይላል። ዕውቀት፡ እያነሰ፡ ሲሄድ፡ ግን፡ ለኑሮ፡ የሚያስፈልገው፡ ዕቃ፡ ሁሉ፡ ይወደዳል። እንደዚህም፡ ባንድ፡ አገር፡ ውስጥ፡ የተሠራው፡ የጋሪ፡ መንገድና፡ የውሃ፡ ድልድይ፡ ሲበላሽ፡ በቶሎ ያልታደሰ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ባለበርኖሱ፡ ጤፍ፡ ሲፈልግ፡ ባለጤፉም፡ በርኖስ፡ ሲፈልግ፡ እንደ፡ ፈለጉት፡ በጋሪ፡ ሊመጣላቸው፡ አይችልም፤በሰው፡ ሸክም፡ ሊያመጡ፡ ግድ፡ ይሆንባቸዋል። ሰው፡ ግን፡ የፈረስ፡ ጋሪን፡ ያኸል፡ ለመሸከም፡ አይችልምና፡ አንድ፡ ጋሪ፡ ባንድ፡ ቀን፡ የሚጐትተውን፡ እስኪያመላልስ፡ ድረስ፡ ዘጠኝ፡ ቀን፡ ያስፈልገዋል። ከዚህ፡ የተነሣ፡ ጠፉ፡ ለባለበርኖሱ፡ በርኖሱ፡ ም፡ ለባለጤፉ፡ ይወደድበታል። ስለዚህም፡ ባንድ፡ ነገር፡ ውስጥ፡ ዕውቀት፡ ሲበዛ፡ የነጋዴው፡ ጥቅም፡ ያንሳል፤የሠራተኛው፡ ጥቅም፡ ግን፡ እንዲያድግ፡ ግልጽ፡ ነው። ባንድ፡ ነገርም፡ ውስጥ፡ ዕውቀት፡ ሲበዛ፡ ሠራተኞች፡ አይራራቁም፤በየመንደሩ፡ በየመንገዱ፡ በየወረዳው፡ ዕቃው፡ ሁሉ፡ ኣጠገብ፡ ላጠገብ፡ በያይነቱ፡ ይሠራልና፡ ለመለዋወጥ፡ ሩቅ፡

መንገድ፡ መሄድ፡ ኣያሳስባቸውም፤ስለዚህ፡ የተላላኪው፡ ነጋዴ፡ ዋጋ፡ ይቀራል።

የዕቃ፡ ሁሉ፡ ዋጋ፡ ዕውቀት፡ ሲበዛ፡ እያደረ፡ ዝቅ፡ እያለ፡ መሄዱ፡ በምን፡ ምክንያት፡ እንደ፡ ሆነ፡ ለመረዳት፡ እስቲ፡ እንደ፡ ገና፡ ተመልሰን፡ እንመርምር።

ያ፡ ለምሳሌ፡ ወደ፡ ባሕር፡ ደሴት፡ ተሰደደ፡ ያልነው፡ ሰው፡ መዠመሪያውን፡ ቀስት፡ ሲያበጅ፡ አስቀድሞ፡ በእግሩ፡ ሩጦ፡ አውሬን፡ ይዞ፡ ገድሎ፡ ኸማቱን፡ አበጅቶ፡ ነው። የመዠመሪያው፡ ቀስት፡ ከተበጀ፡ በኋላ፡ ግን፡ ሁለተኛውን፡ ቀስት፡ ለማበጀት፡ የፊተኛውን፡ ያኸል፡ ኣያደክመውም። እንግዲህ፡ አውሬንም፡ ለመግደል፡ እንደ፡ ፊተኛው፡ ሩጦ፡ ለመያዝ፡ አያሳስበውም፤ፊት፡ ባበጀው፡ ቀስት፡ ይገድላል። እንግዲህ፡ ቀስት፡ በመዠመሪያ፡ እስኪሠራ፡ ድረስ፡ ውድ፡ ነው፤ከተሠራ፡ በኋላ፡ ግን፡ በገዛ፡ እጁ፡ ዋጋው፡ ዝቅ፡ ይላል።

በሌላም፡ ነገር፡ ሁሉ፡ እንደዚሁ፡ ነው። አሁን፡ ከሰል፡ የብረትን፡ ዐፈር፡ ለማቅለጥ፡ የሚያስፈልግ፡ ስለ፡ ሆነ፡ በመዠመሪያ፡ ይወደዳል፤ የብረቱ። ዐፈር፡ ቀልጦ፡ መጥረቢያና፡ ዶማ፡ ከተሠራ፡ በኋላ፡ ግን፡ ብዙ፡ ከሰል፡ ለማግኘት፡ ድካሙ፡ ያንሳል።

ብዙም፡ ከሰል፡ ከተገኘ፡ በኋላ፡ ብዙ፡ የብረት፡ ዐፈር፡ ኣቅልጦ፡ ብዙ፡ መጥረቢያና፡ ዶማ፡ ያለብዙ፡ ድካም፡ ለመሥራት፡ ይቻላል። በዚህ፡ ምክንያት፡ መሣሪያ፡ ሁሉ፡ በገዛ፡ እጁ፡ ዋጋው፡ ይረከሳል፤መሣሪያም፡ ሲረክስ፡ ለሰው፡ ሁሉ፡ ኑሮ፡ የሚያስፈልግ፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ይረከሳል።

ጋሪውም፡ ቢሆን፡ እንደዚሁ፡ ነው። የመዠመሪያው፡ ጋሪ፡ እስኪበጅ፡ ድረስ፡ እጅግ፡ ያስቸግራል። ዕንጨቱ፡ ያለበት፡ ስፍራ፡ ሩቅ፡ ነውና፤ መሸከሙም፡ ያቅታልየመ መሪያው፡ ጋሪ፡ ከተሠራ፡ በኋላ፡ ግን፡ ለሁለተኛው፡ ጋሪ፡ የሚሆን፡ ያለብዙ፡ ድካም፡ ይመጣል፤ስለዚህ፡ የሌሳው፡ጋሪ፡ ዋጋ፡ ዝቅ፡ ይላል።

ለኑሮውም፡ የሚያስፈልግ፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ሲረክስ ፥ ሰው፡ በዓለም፡ ላይ፡ ሙሉ፡ ጌትነት፡ ማግኘቱ፡ ነውና፡ ይከብራልከዚህም፡ ጌትነቱ፡ የተነሣ፡ ድካም፡ ያንሳል፤እንግዲህ፡ ዕውቀት፡ እየበዛ፡ ሲሄድ፡ የዕቃው፡

ሁሉ፡ ዋጋ፡ እያደረ፡ እንዲረከስ፡ ከዚህ፡ ቀድሞ፡ የሰማነው፡ ቃል፡ ፈጽሞ፡ ያስረዳናል።

ነገር፡ ግን፡ ሌላ፡ ማስረጃ፡ ነገር፡ ብንጨምር፡ ይሻላል። ባንድ፡ መንደር፡ የሚኖሩ፡ ሰዎች፡ ጠመንዣና፡ መጥረቢያ፡ ዶማም፡ ሲኖራቸው፡ መሣሪያቸው፡ ትክክል፡ ነውና፤አንዱ፡ ባንድ፡ ቀን፡ የሠራውን፡ ዕቃ፡ ሲለውጥ፡ ያ፡ የሚቀበለው፡ ዕቃ፡ አንድ፡ ቀን፡ የተሠራ፡ እንዲሆን፡ የታወቀ፡ ነው። ዱሮ፡ ደኅና፡ መሣሪያ፡ ሳይኖር፡ ሰዎቹ፡ የሚኖሩበት፡ ሥራው፡ ብዙ፡ የሚያደክም፡ ኑሯል፤ዛሬ፡ ግን፡ ደኅና፡ መሣሪያ፡ ተገኝቷልና፡ ቤትም፡ ሆነ፡ ወይም፡ ሌላ፡ ሥራ፡ ያለብዘ፡ ድካም፡ በፍጥነት፡ ሊሠራ፡ ይችላል። እንግዲህ፡ ያ፡ የዱሮ፡ ቤትና፡ ሥራ፡ አዲሱ፡ መሣሪያ፡ ከተገኘ፡ ወዲህ፡ ይረክሳል። ዋጋ፡ የሥራ፡ መለኪያ፡ ነው፡ ስለ፡ ተባለ፡ ዕቃ፡ ሁሉ፡ ሲገመት፡ ዱሮ፡ በተቃራበት፡ አይደለም። ነገር፡ ግን፡ በዚያው፡ በተገመገመበት፡ ጊዜ፡ ተርቶ፡ ቢሆን የሥራው፡ ድካም፡ ስንት፡ እንደ፡ ሆነ፡ እየታሰበ፡ ነው። የሥራውን፡ አቀለጣጠፍ፡ በዚህ፡ ያሳያል። አንድ፡ ሰው፡ መቶ፡ ኪሎ፡ ዕቃ፡ ሰባት፡ ኪሎ፡ ሜትር፡ የሚያኽል፡ መንገድ፡ በሰዓት፡ ሊጐትት፡ ይችላልን፤አንድ፡ ፈረስ፡ ግን፡ ፱፻፡ ኪሎ፡ ዕቃ፡ በሰዓት፡ ሊጐትት፡ ይችላል። እንዲህ፡ ያንድ፡ ፈረስ፡ ኀይል፡ የ፱፡ ሰው፡ ኃይል፡ ስለ፡ ሆነ፤ሰው፡ ግን፡ በዕውቀቱ፡ ፈረሱን፡ አልምዶ፡ እንዲያገለግለው፡ ያደርጋል፤በዚሁም፡ ዕውቀቱ፡ ሥራው፡ ይፋጠንለታል።

ከዚያም፡ ቀጥሎ፡ ራሱ፡ አስቦ፡ ባቡር፡ ይሠራል፤የባቡርም፡ ኃይል፡ ከሁሉ፡ የበለጠ፡ ስለ፡ ሆነ፡ እንሆም፡ ስድስት፡ ሰዎች፡ በሰበሰቡት፡ ከሰል፡ መቶ፡ ፈረሶች፡ የማያንቀሳቅሱትን፡ ሸክም፡ ባንድ፡ ጊዜ፡ ለመሳብ፡ ይችላል። ዕውቀት፡ የሌለው፡ ሕዝብ፡ ግን፡ ይህንን፡ የመሰለ፡ ርዳታ፡ ሊያገኝ፡ አይችልም። ስለዚህም፡ በመኪና፡ የተሠራውን፡ ዕቃ፡ ሁሉ፡ ሲገምት፡ ያንን፡ ነገር፡ እስኪያገኝ፡ ድረስ፡ ስንት፡ ድካም፡ እንዲያስፈልገው፡ ገምቶ፡ በዚያው፡ ዋጋውን፡ ይሰጣል። ብዙው፡ ነገር፡ ግን፡ በዕውቀት፡ ሥራ፡ እንጂ፡ በጕልበት፡ ሥራ፡ የማይገኝ፡ ይሆናል።

አሁን፡ በኢትዮጵያችን፤ብርጭቆ፡ ጠርሙስ፡ ማንቄርቄሪያ፡ ሳሕን፡ ለመሥራት፡ አይቻልም። ይህም፡ ነገር፡ ሁሉ፡ በኤሮፓ፡ አገር፡ ያለብዙ፡ ድካም፡ ይሠራል። ያገራችን፡ ሰው፡ ግን፡ ብዙ፡ ቀን፡ የደከመበትን፡ ነገር፡ ይሰጥበታል። አንድ፡ ባላገር፡ ለልብስ፡ አንድ፡ ጣቃ፡ አቡጀዲድ፡ ሲገዛ፡

ከስድስት፡ ብር፡ እስከ፡ ፲፡ ብር፡ ይሰጥበታል። ስድስት፡ ብር፡ ግን፡ ያንድ፡ ዳውላ፡ ካራት፡ ቀና፡ ጤፍ፡ ዋጋ፡ ነው፤ጣቃው፡ አቡጀዲድ፡ በኤሮፓ፡ አገር፡ ባንድ፡ አፍታ፡ ይሠራል። አንድ፡ ዳውላ፡ ካራት፡ ቀና፡ ጤፍ፡ ግን፡ እስኪገኝ፡ ድረስ፡ ለኢትዮጵያው፡ ባላገር፡ ብዙ፡ ቀን፡ ይፈጅበታል። ስለዚህ፡ አቡጀዲዱን፡ ለመሥራት፡ የሚበቃ፡ ዕውቀት፡ ስለሌለው፡ ባንድ፡ አፍታ፡ ለተሠራ፡ ነገር፡ ብዙ፡ ቀን፡ የደከመበትን፡ ሥራ፡ ይሰጥበታል። በገዛ፡ አገራችንስ፡ ቢሆን፡ ይኸው፡ ኣይደለምን፤ያናጢ፡ ሥራ፡ ከዕንጨት፡ ተሸካሚው፡ ሥራ፡ ይልቅ፡ ይወደዳል፤ዕውቀት፡ ከጕልበት፡ ይከበራልና፡ ከቤት፡ ከዳኙ፡ ሥራ፡ ይልቅ፡ የሣር፡ ዐጫጁ፡ ሥራ፡ ይረክሳል።

በዚህ፡ ምክንያት፡ ዋጋ፡ የሥራ፡ መለኪያ፡ ነው፡ ስለ፡ ተባለ፡ የሠሩትን፡ ዕቃ፡ የሚለዋወጡ፡ ሠራተኞች፡ በየሥራቸው፡ የሚረዳቸው፡ ዕውቀት፡ ሚዛኑ፡ ትክክል፡ እንዲሆን፡ ያስፈልጋል። ማለት፡ ባለበርኖሱ፡ ሥራውን፡ ሁሉ፡ በመኪና፡ ሲሠራ ፥ አራሹም፡ እንዲሁ፡ በመኪና፡ ካላረሰ፡ ከለውጡ፡ ላይ፡ አራሹ፡ ይጐዳል፤ባለበርኖሱ፡ ግን፡ ይጠቀማል። አራሹም፡ በመኪና፡ ሲያርስ፡ ባለበርኖሱ፡ ይጐዳል። አራሹ፡ ግን፡ ይጠቀማል። ዕውቀታቸውም፡ ከፍ፡ ያለ፡ ሕዝቦች፡ ዕውቀታቸው፡ ዝቅ፡ ያለውን፡ ሕዝቦች፡ በንግድ፡ የሚበልጡበት፡ ምክንያት፡ ይህ፡ ነው። ስለዚህም፡ ሕዝቡ፡ እንዳይጐዳ፡ የሚፈልግ፡ መንግሥት፡ ሁሉ፡ አውራ፡ ጥረቱ፡ ትምርት፡ እንዲበዛ፡ ነው። የማናቸውም፡ ሕዝብ፡ ዕውቀቱ፡ እያደገ፡ ከሄደ፡ ዘንድ፡ እንዳይጐዳ፡ ርሱ፡ ራሱ፡ ይመክታል። ትምርት፡ ሳይገባ፡ ግን፡ የማናቸውንም፡ አንድ፡ ነገር፡ ደንብም፡ እንለውጣለን፡ ቢሉ፡ ሕዝቡ፡ ትልቅ፡ ጥቅም፡ አያገኝበትም። ይልቁንም፡ ግራ፡ ነገር፡ ይሆንበታል። ሰው፡ የተፈጠረ፡ የምድር፡ ጌታ፡ ሆኖ፡ በዓለም፡ ሊኖር፡ ነው። ጌትነቱም፡ ሲሰፋ፡ የሚያስፈልገውን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ በጥቂት፡ ድካም፡ ያገኛል። ሰው፡ በዓለም፡ ላይ፡ ጌታ፡ የሆነው፡ ግን፡ በዕውቀቱ፡ ብቻ፡ ነው። በጕልበትማ፡ ቢሆን፡ አህያና፡ ግመል፡ ይበልጡት፡ የለምን፤ስለዚህ፡ ዕውቀት፡ የሌለው፡ ሕዝብ፡ ለኑሮው፡ የሚያስፈልገው፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ይወደድበታልና፤ሊመቸው፡ አይችልም። ሰው፡ ፈጽሞ፡ የሚመቸው፡ መሰናክልን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ አሸንፎ፡ የምድር፡ ጌታ፡ ሁኖ፡ በዓለም፡ ከኖረ፡ ወዲያ፡ ነው።

ስለዚህም፡ ዕውቀት፡ የሌለው፡ ሕዝብ፡ ሁሉ፡ ለብቻው፡ መንግሥት፡ ቢኖረውም፡ ባይኖረውም፡ ዕውቀት፡ ያላቸው፡ ሕዝቦች፡ ይገዙታል።

እንሆም፡ አንጠረኛው፡ የእሳት፡ አንዳጁን፡ ድካም፡ አናጢው፡ የዕንጨት፡ ተሸካሚውን፡ ድካም፡ በጥቂት፡ ዋጋ፡ እንደሚገዛው ፥ እንደዚሁም፡ ዕውቀት፡ ያላቸው፡ ሕዝቦች፡ ዕውቀት፡ የሌላቸውን፡ ሕዝቦች፡ ድካም፡ በትንሽ፡ ዋጋ፡ ይገዙታል። ብዙ፡ ፈረንጆች፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ አገር፡ ድኻ፡ ሆነው፡ መጥተው፡ በቶሎ፡ በልጽገው፡ የኢትዮጵያን፡ ሰው፡ በሎሌነት፡ የሚያሳድሩ፡ ስለዚሁ፡ ዕውቀታቸው፡ ነው። ዕውቀት፡ ዓለምን፡ እንዲገዛ፡ የማይነቃነቅ፡ ዘለዓለማዊ፡ ደንብ፡ ነው።

# ሁለተኛ፡ ክፍል።

ዋጋ፡ ማለት፡ የሥራ፡ መለኪያ፡ ነው፡ ብለን፡ ነበር። መሬት፡ በሰው፡ እጅ፡ አይሠራም፤ነገር፡ ግን፡ ዋጋ፡ ያወጣል። ደግሞ፡ አንዱ፡ መሬት፡ ጥቂት፡ ዋጋ፡ ሲያወጣ፡ ሌላው፡ መሬት፡ ደግሞ፡ ሦስት፡ እጅ፡ አብልጦ፡ ዋጋ፡ ያወጣል። የዚህ፡ ነገር፡ ምክንያቱ፡ ምንድን፡ ይሆን፤መልሱ፡ አጭር፡ ነው።

ዋጋ፡ የሥራ፡ መለኪያ፡ ነው፡ ስለ፡ ተባለ፡ ኣስቀድሞ፡ ሁለት፡ ነገር፡ ያስፈልጋል። አንዱ፡ የሠሩትን፡ ሥራ፡ የሚለዋወጡ፡ ሠራተኞች፡ በየሥራቸው፡ የሚሠሩበት፡ ዕውቀት፡ ሚዛኑ፡ አንድ፡ እንዲሆን፡ መሬት፡ እኩል፡ ሆኖ፡ ለሰው፡ ሁሉ፡ እንዲከፋፈል፤መሬት፡ ግን፡ በዘመናት፡ ቀጥራቸውበተወሰነ፡ ሰዎች፡ እጅ፡ ተይዞ፡ እንደ፡ ሞኖፖል፡ ሆኗል። እነዚህም፡ ሰዎች፡ መሬቱን፡ ሲሸጡ፡ ከነሱ፡ በቀር፡ ሌላ፡ ሰው፡ እንደነሱ መሬት፡ እንደሌለው፡ አይተው፡ ስለ፡ መሬቱ፡ የሞኖፖል፡ ዋጋ ፥ በመሬቱ፡ ላይ፡ ለሠሩት፡ ቤትና፡ ሌላ፡ የእጅ፡ ሥራ፡ ሁሉ፡ እንደ፡ ሥራቸው፡ መጠን፡ ዋጋ፡ ይቀበሉበታል። ዳሩ፡ ግን፡ በመሬቱ፡ ላይ፡ የተሠራው፡ የሰው፡ ሥራ፡ ሲገመት፡ ባለመሬቱ፡ ሥራውን፡ ሲያሠራ፡ የከሰረበትን፡ ዋጋ፡ አያገኝም። ዕውቀት፡ በዝቶ፡ መሣሪያ፡ እየበዛ፡ ስለ፡ ሄደ፡ ቤቱንና፡ ሌላውን፡ ሥራ፡ ሁሉ፡ ለመሥራት፡ እንደ፡ ዱሮ፡ አያደክምምና፤ ይረክስበታል። በዚሁም፡ ባለመሬቱ፡ ስለ፡ ተጐዳ፡ ባንድ፡ ወገን፡ ይጠቀማል። ሰው፡ በዓለም፡ እየበዛ፡ ሲሄድ፡ ብዙ፡ ምግብ፡ ያስፈልገዋልና። የሚታረሰውን፡ መሬት፡ የያዘ፡ ሰው፡ ብቻውን፡ ስለ፡ ሆነ፡ የሞኖፖሉን፡ ዋጋ፡ ከፍ፡ ያደርገዋል። በዚሁም፡ ነገር፡ ለኑሮ፡

የሚያስፈልገው፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ይወደዳል። ስለዚህም፡ ባንድ፡ አገር፡ ውስጥ፡ ያለው፡ መሬት፡ በጥቂቶች፡ ሰዎች፡ እጅ፡ ብቻ፡ የሆነ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ለሕዝቡ፡ ትልቅ፡ ጕዳት፡ ይሆናል።

በዚህ፡ ምክንያት፡ ዋጋ፡ የሥራ፡ መለኪያ፡ የሚሆነው፡ ሞኖፖል፡ ላልሆነ፡ ነገር፡ ብቻ፡ ነው። ያንዱም፡ መሬት፡ ዋጋ፡ ከሌላው፡ መሬት፡ ዋጋ፡ ከፍና፡ ዝቅ፡ የሚል፡ ያንዱ፡ ሞኖፖል፡ ካንዱ፡ ሲበልጥ፡ ነው። ሞኖፖል፡ ግን፡ ከዓለማዊ፡ ሕግ፡ የወጣ፡ ነገር፡ ነውና፡ የሕዝብን፡ አስተዳደር፡ ታሪክ፡ ስንመረምር፡ ከዓለም፡ ሕግ፡ ጋራ፡ አይስማማልንም። ከዓለም፡ ሕግ፡ ጋራ፡ ካለመስማማቱ፡ የተነሣ፡ ሞኖፖል፡ የበዛበት፡ አገር፡ ሁሉ፡ ሕዝቡ፡ ድኽነት፡ እንደ፡ በዛበት፡ እናያለን።

ሰው፡ የተፈጠረ፡ የዓለም፡ ጌታ፡ ሊሆን፡ ነው፤ኣርነት፡ ካልሆነ፡ የተፈጠረለትንም፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ለማግኘት፡ እንደ፡ ባልንጀራው፡ በትክክል፡ ደንብ፡ ካልተበጀለት፡ የምድር፡ ጌታ፡ ሆኖ፡ በዓለም፡ ሊኖር፡ አይችልም ። ሰው፡ ሲፈጠር፡ ጌታና፡ ድኻ፡ ህኖ፡ አልተፈጠረም ። ድኽነትና፡ ጌትነት፡ የተለየ፡ በሰው፡ ዕውቀት፡ ነው ። ስለዚህ፡ ዜጎቹን፡ ለማስተካከል፡ የሚጥር፡ መንግሥት፡ ሁሉ፡ የሕዝቡን፡ ሀብት፡ እንዲያበዛ፡ የታወቀ፡ ነው ። ሀብትም፡ ማለት፡ ምን፡ እንደ፡ ሆነ፡ ቀጥሎ፡ የተጻፈው፡ ሦስተኛው፡ ክፍል፡ ያስረዳናል ።

# ሦስተኛ፡ ክፍል ።

## *ስለሀብት፡ ትርጕም፡ ማስረጃ ።*

ያ፡ ምሳሌ፡ ወደ፡ አንድ፡ ደሴት፡ ተሰደደ፡ ያልነው፡ ሰው፡ በመዠመሪያ፡ ሀብት፡ አልነበረውም ። ቀስት፡ ካበጀ፡ በኋላ፡ ግን፡ ሀብት፡ አገኘ ። ይህ፡ ቀስት፡ ህብት፡ የሆነበት፡ ምክንያቱ፡ ግን፡ ምን፡ ይሆን፤ ዕንጨቱንና፡ ያውሬውን፡ ዥማት፡ ብርታት፡ አጋጥሞ፡ በክንዱ፡ ጕልበት፡ ፈንታ፡ እንዲያገለግሉት፡ ስላደረገ፡ ነው ። ኣስቀድሞ፡ ምግቡን፡ በእጁ፡ ጕልበት፡ ብቻ፡ ሲያገኝ፡ ነበረ ። በኋላ፡ ግን፡ ቀስት፡ አጋዥ፡ ሆኖት፡ በዕውቀት፡ ብዛት፡ የበለጠ፡ ምግብ፡ አገኘ ። ቀስትም፡ ሀብት፡ የሆነው፡ ስለዚህ፡ ዕውቀቱ፡ ነው ። ጥቂትም፡ ቈይቶ፡ ስደተኛው፡ ሰውዬ፡ ጀልባ፡ ኣበጀ ። በዚሁም፡ ምክንያት፡ ጀል ባው፡ በውሃ፡ ላይ፡ ስላገለገለው፡ ሀብቱ፡

እያደገ፡ ሄደ ። በጀልባውም፡ በላዩ፡ ላይ፡ ዕንጨት፡ አቊሞ፡ ጀልባው፡ ቶሎ፡ እንዲሄድለት፡ ቆዳ፡ ዘረጋበት ። ነፋሱም፡ ይህን፡ ቆዳ፡ ስለ፡ ገፋ፡ የጀልባውም፡ አካሄድ፡ ተፋጠነ ።

በዚሁም፡ ምክንያት፡ ነፋሱም፡ ስደተኛውን፡ ያገለግለው፡ ነበርና፡ የስደተኛው፡ ሀብት፡ ከዱሮው፡ ይልቅ፡ እንደ፡ ገና፡ አደገ ። መሬት፡ በዕንጨቷና፡ ባውሬው፡ ዥማት፡ በውሃና፡ በነፋስም፡ ልትገዛለት፡ ስለ፡ ዠመረች፡ ስደተኛው፡ ሰው፡ ብልጽግናው፡ ወደ፡ ፊት፡ እየበዛ፡ ሄደ ።

ቀስቱንና፡ ጀልባውን፡ ወድቀው፡ አግኝቷቸው፡ ሞያቸውን፡ ግን፡ ለይቶ፡ ሳያውቅ፡ በቀር፡ በእጁ፡ ስለ፡ ገቡ፡ ሀብት ፡ ይሆኑት፡ ኑሮ፡ ይሆን፤ አይሆኑትም ። በመሣሪያው፡ ሥራውን፡ ለይቶ፡ ዐውቆ፡ ካልተጠቀመበት፡ መሣሪያው፡ በእጁ፡ ስለ፡ ገባ፡ ሀብት፡ አይሆነውም ። የፎቶግራፍን፡ ሥዕል፡ ማንሻ፡ ዕቃ፡ ላንድ፡ ሕፃን፡ ቢሰጡት፤ወይም፡ መጻሕፍትን፡ ማንበብ፡ ለማያውቅ፡ ሰው፡ መጽሐፍ፡ ቢሰጡት፡ ሀብት፡ እንደማይሆነው፡ እንደዚሁም፡ ሀብት፡ የሚሆን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ በማያውቅበት፡ ሰው፡ እጅ ፡ ሲገባ፡ ለሰውዬው፡ ሀብት፡ አይሆነውም።

መሬት፡ ለሰው፡ ጥቅም፡ የሚሆነውን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ በሆዷ፡ ይዛለች፤ ሰውም፡ የተፈጠረ፡ ጌታዋ፡ ለመሆን፡ ነው ። ስለዚህ፡ እንደ፡ ሀብት፡ ሆኖ፡ የሚቈጠር፡ ይህነን፡ ጌትነት፡ እንዲያገኝ፡ ሰውን፡ የሚረዳ፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ዛሬ፡ የዓለምን፡ ብዙ፡ ሺ፡ መርከቦች፡ የሚያንቀሳቅሳቸው፡ የደንጊያ፡ ከሰል፡ ነው ። ይህም፡ የደንጊያ፡ ከሰል፡ ዱሮም፡ ቢሆን፡ በእንግሊዝ፡ አገር፡ ነበረ ። ለእንግሊዝ፡ ሕዝብ፡ ሀብት፡ መሆን፡ የገዠመረው፡ ግን፡ ባቡር፡ ተሠርቶ፡ ከሰሉ፡ ለባቡር፡ ሥራ፡ የሚጠቅም፡ መሆኑ፡ ከታወቀ፡ በኋላ፡ ነው ። ከዚያ፡ በፊት፡ የደንጊያውን፡ ከሰል፡ በእንግሊዝ፡ አገር፡ እንደ፡ ሀብት፡ የሚቈጥረው፡ አንድም፡ ሰው፡ አልነበረም ። ባቡርና፡ መርከብ፡ ከተሠራ፡ በኋላ፡ ግን፡ የእንግሊዝ፡ አገር፡ አንዱ፡ ዋና፡ ሀብቱ፡ ከሰሉ፡ ሆነ ። ባገራች ንስ፡ ቢሆን፡ እንደዚሁ፡ አይደለምን፤ባዲስ፡ አበባ፡ ከተማ፡ ያለው፡ ደንጊያ፡ ሁሉ፡ ዱሮ፡ በዚያ፡ ሲኖሩ፡ ለነበሩት፡ ለጉለሌ፡ ጋሎች፡ ሀብት፡ አልሆናቸውም፡ ነበር ። ዐማሮች፡ መጥተው፡ የደንጊያ፡ ቤት፡ ሥራ፡ ከተመረ፡ በኋላ፡ ግን፡ በቦታው፡ ደንጊያ፡ ያለው፡ ሰው፡ እንደ፡ ሀብት፡ ይቈ ጥረው ፡ ዠመር ። ፈረንጆችም፡ ሳይመጡ፡ ያ፡ በቶሎ፡ የሚፈለጠው፡ ነጭ፡ ብሓ፡ ድንጋይ፡ እንደ፡ ሀብት፡ ሲቈጠር፡ ያ፡ በብዙ፡

ድካም፡ የሚፈለጠው፡ ጥቀሩ፡ ባሪያ፡ ድንጋይ፡ የሚቀርበው፡ ሰው፡ አላገኘም፡ ነበረ ። ፈረንጆች፡ መጥተው፡ ጥቍሩንም፡ ደንጊያ፡ ለመፍለጫ፡ መሣሪያና፡ የሚበቃ፡ ዕውቀት፡ ከተገኘ፡ በኋላ፡ ግን፡ በጥቅር፡ ደንጊያ፡ የተሠራ፡ ቤት፡ የሚጠነክር፡ ስለሆነ፤ጥቀሩ፡ ደንጊያ፡ ያለበት፡ ቦታ፡ ነጩ፡ ደንጊያ፡ ካለበት፡ ቦታ፡ ይልቅ፡ ተወደደ ። ስለዚህም ፡ ማናቸውም፡ ነገር፡ አጠቃቀሙን፡ ካላወቍበት፡ ሀብት፡ እንዳይደለ፡ በግልጽ፡ እንረዳዋለን ።

ሰው፡ ሁሉ፡ ሌላውን፡ ሰው፡ ሀብታም፡ ነው፡ ሲል፡ ግን፡ ይህንን፡ አያስብም ። በሰውም፡ አፍ፡ ሀብታም፡ ነው፡ መባል፡ የሚገባው፡ ያለው፡ ገንዘቡ፡ ሌላው፡ ሰው፡ ከያዘው፡ ገንዘብ፡ ይበልጣል፡ እንደ፡ መባል ፡ ያኽል፡ ነው ። ይህ፡ ቃል፡ ግን፡ የሀብት፡ ሙሉ፡ ትርጉም፡ አይደለም ። ለሀብት፡ ሁለት፡ ዐይነት፡ አለው ። ኣንዱ፡ ዐይነት፡ ርግጠኛ፡ ሀብት፡ ይባላል ። ሁለተኛውም፡ የብልጫ፡ ሀብት፡ ይባላል ። ቤት ፥ አልጋ ፥ ድስት፡ ያለው፡ ሰው፡ ይህ፡ ቤት፡ አልጋ ፥ ድስቱ፡ ርግጠ ኛው፡ ሀብቱ፡ ፡ ነው ። ጎረ፡ ቤቱም፡ ከዚህ፡ የበለጠ፡ ነገር፡ ቢያገኝ፡ ለሰውዬው፡ ቤቱ፡ ኣልጋው፡ ድስቱ፡ እንደ፡ ዱሮው፡ ያገለግሉታልና፡ ያውም፡ ርግጠኛ፡ ሀብት፡ መሆናቸው፡ አይቀርም ።

በምሳሌ፡ ለማስረዳት ፥ ወልደ፡ ማርያም፡ ቤት፡ አልጋ፡ ድስት፡ ቢኖረው፡ ገብረ፡ ማርያም፡ ደግሞ፡ ከነዚህ፡ ከተቈጠ ሩት፡ በላይ፡ ትርፍ፡ አንድ፡ ጠረጴዛ፡ ቢኖረው ፥ ጠረጴዛው፡ ለገብረ፡ ማርያም፡ የብልጫ፡ ሀብቱ፡ ነው ። ይህም፡ የብልጫ፡ ሀብት፡ የሆነው፡ ጠረጴዛ፡ የሚገመተው፤ ወልደ፡ ማርያም፡ ቢፈልገው፡ እስኪያገኘው፡ ድረስ፡ በሚፈጅበት፡ ድካም፡ ነው፤ማለት፡ ጠረጴዛውን፡ እስኪያገኘው፡ ድረስ፡ ለወልደ፡ ማርያም፡ የሚያስፈልገው፡ ድካም፡ ያንድ፡ ቀን፡ ሥራ፡ ብቻ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ገብረ፡ ማርያም፡ ያገኘው፡ የብልጫ፡ ሀብት፡ ጥቂት፡ ነው ። ጠረጴዛውን፡ እስኪያገኝ፡ ድረስ፡ ለወልደ፡ ማርያም፡ የሚያስፈልገው፡ ድካም፡ ያሥር፡ ቀን፡ ሥራ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ግን፡ ገብረ፡ ማርያም፡ ያገኘው፡ የብልጫ፡ ሀብቱ፡ ከፍ፡ ይላል ። የዋጋን፡ ነገር፡ ስንመረምር፡ እንደ፡ ተረዳነው፡ አሁንም፡ ቢሆ ን፡ የሀብት፡ መለኪያ፡ ሥራ፡ ነው ።

ለሰው፡ የሚያስፈልገውን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ምድር፡ በሆዷ፡ ይዛለች ። በዚህም፡ በምድር፡ ላይ፡ ባለው፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ሰው፡ አንዳች፡ ሌላ፡ ነገር፡ ሊጨምርበት፡ ዐቅም፡ የለውም ። ማናቸውንም፡ ነገር፡ ሲፈልግ፡

አንቀሳቅሶ፡ ማጋጠም፡ ብቻ፡ ነው ፡ ያለበት ። ማንቀሳቀስና፡ ማጋጠም፡ የሚሆነው፡ በሥራ፡ ነው ። ስለዚህም፡ የሰው፡ ዕውቀትና፡ ገንዘቡ፡ ሥራ፡ ብቻ፡ ነው ። አንዱም፡ ሰው፡ ባልንጀራውን፡ በሀብት፡ የሚበልጠው፡ ትርፍ፡ ሥራ፡ ሲገባለት፡ ነው ። ጎብረ፡ ማርያም፡ ከወልደ፡ ማርያም፡ በሀብት፡ የበለጠው፡ የጠረጴዛውን፡ ዕንጨት፡ ስላገኘ፡ አይደለም ። ዕንጨቱ፡ ከደን ፡ ተቈርጦ፡ መጥቶ፡ ተጠርቦ፡ ተጋጥሞ፡ ጠረጴዛ፡ ሁኖ፡ ከቤቱ፡ ገብቶ፡ ስላገለገለው፡ ነው፡ እንጂ፤ዕንጨትንማ፡ ምድር፡ ዐውቃ፡ በያገሩ፡ ታበቅለው፡ የለምን ።

ሰው፡ ኑሮው፡ ከምድር፡ ጋራ፡ ሲታገል፡ ነው፤እሱ፡ ጌታዋ፡ ለመሆን፡ ሲጥር፡ እሷ፡ ኣልገዛም፡ ስትለው፡ ዘወትር፡ ዕረፍት፡ አልባ፡ ሲታገል፡ ይኖራል። ይህም፡ የሰው፡ ትግል፡ ሥራ፡ ይባላል ። ሁለት፡ ሰዎች፡ ሲታገሉ፡ አንዳቸው፡ ባለጋራውን ፡ አንድ፡ ጊዜ፡ በሚያስጥል፡ ስፍራ፡ የያዘውና፡ የጣለው፡ እንደ፡ ሆነ፡ ከዚያ፡ በኋላ፡ ድካሙ፡ ይቀልለታልና ፥ ጥቂት፡ መጫን ፡ ብቻ፡ ነው፡ ያለበት።

ባለጋራውም፡ ሊወድቅ፡ እግሩን፡ ከለቀቀ፡ ወዲያ፡ ተከትሎት፡ በላዩ፡ ከመውደቅ፡ በቀር፡ ሌላ፡ ልፋት፡ የለበትም ። በሰውም፡ ኑሮ፡ እንደዚሁ፡ በሥራው፡ የሚያገኘው፡ ጥቅም፡ በመዠመሪያ፡ ጥቂት፡ ነው ። ቈይቶ፡ ግን፡ ጥቅሙ፡ እያደረ ፡ ይቀጥላል ። አንዳች፡ ነገር፡ በመዠመሪያ፡ ከተሠራ፡ ወዲያ፡ የዚያ፡ ነገር፡ ዐይነት፡ ሁለተኛ፡ ሲሠራ፡ አያቅትም። እንዲሁም፡ አንዳች፡ ነገር፡ ከተመረ፡ በኋላ፡ ፍጻሜው፡ ቀላል፡ ነው ። የተማሰውን፡ ጕድጓድ፡ ለማስፋት፡ ምን፡ ያቅታል ። የብረት ፡ ዐፈርስ፡ ቀልጦ፡ ብረቱ፡ ከተለየ፡ በኋላ፡ መጥረቢያ፡ ለመሥራት፡ ምን፡ ይቸግራል ። እንደዚሁም፡ ጕድጓድ፡ ተምሶ፡ ርጥቡ፡ ዕንጨት፡ ተቈርጦ፡ ከቀረበ፡ ወዲያ፡ ከሰልን፡ ለማግኘት ፡ ምን፡ ትልቅ፡ ድካም፡ ያስፈልጋል ። በዚህ፡ ምክንያት፡ ማናቸውም፡ ሥራ፡ ከተሠራ፡ ወዲያ፡ የሚከተለውን፡ ሥራ፡ ያቀላል ። የሰው፡ ጥረቱ፡ ምድርን፡ ለመግዛት፡ ነው ። ስለዚህም፡ አንድ፡ ሥራ፡ በሆነለት፡ ቍጥር፡ ለዚሁ ጌትነት፡ ይቃረባል ። ከዚያም፡ ወዲያ፡ ይህነን፡ ጌትነት፡ ለማግኘት፡ ድካሙ፡ ይቃለልለታል። ሀብትም፡ ማለት፡ የዚሁ፡ ጌትነት፡ መለኪያ፡ ነውና፤አንዱ፡ ሀብት፡ ከተገኘ፡ በኋላ፡ መሰናከል፡ ነገር፡ ካልመጣ፡ የበለጠ፡ ሀብት፡ ይከተለዋል ። ተጣጥሮ፡ አንዲት፡ ላም፡ የገዛ፡ ሰው፡ ባመቱ፡ ጥጃ፡ ትወልድለታለች ። ሀብቱም፡ ሁለት፡ እጅ፡ ይሆናል ።

ጥጃዋንም፡ በመልካም፡ ያሳደጋት፡ እንደ፡ ሆነ፡ እሷም፡ ላም፡ ትሆንለታለች ። እናቷ፡ ደግሞ፡ ስትወልድ፡ እሷም፡ ትወልድለታለች ። እንሆም፡ የሰውዬው፡ ሀብት፡ ከመዠመሪያው፡ አራት፡ እጅ፡ በለጠ ። ከብቶቹም፡ በያመቱ፡ ይበዙለታል፤በሮቹም፡ ያድጉለታል። በነዚህም፡ በሮች፡ ጉልበት፡ መሬትን፡ አርሶ፡ ብዙ፡ እኽል፡ ያገኛል ።

እኽልም፡ ሲተርፈው፡ ትርፉን፡ ለብረት፡ ሠሪው፡ ሰጥቶ ፡ ከዱሮው፡ የበለጠ፡ ማረሻ፡ ይገዛል ። በዚሁም፡ በደኅናው ፡ ማረሻ፡ ያርስና፡ ከጥንቱ፡ የበዛ፡ እኽል፡ ያገኛል ። ባዲሱም ፡ ትርፍ፡ ለራሱና፡ ለልጆቹ፡ ልብስም፡ የዝናብ፡ ልብስ፡ ይባዛል ። እንሆም፡ በብርድና፡ በዝናብ፡ ጊዜም፡ ቢሆን፡ ከሥራው ፡ አይተጓጐልም፤ከዱሮው፡ አብልጦ፡ ይሠራል፡ እንጂ፤ ከእርሻውም፡ የሚያገኘው፡ ከዱሮው፡ ይልቅ፡ የበለጠ፡ ይሆናል ። በትርፉም፡ ዐረብያ፡ ሠረገላ፡ ይገዛል ። ባረብያውም፡ በፍጥነት፡ ወደገበያ፡ ብዙ፡ እኽል፡ ይዞ፡ ይሄድና፡ ሽጦ፡ የሚያስፈልገውን፡ ብዙ፡ ነገር፡ ገዝቶ፡ ባንድ፡ ጊዜ፡ ይዞ፡ ይመለሳል ። ለማረስም፡ ከዱሮ፡ ይልቅ፡ ጊዜ፡ ያገኛል። ስለዚህም፡ በእርሻ፡ የሚገኘው፡ ትርፉ፡ ሌላ፡ መሬት፡ ባይጨምር፡ እያደረ፡ ያድግለታል ።

እንሆም፡ ማናቸውም፡ አንድ፡ ዐይነት፡ ሀብት፡ ሲገኝ፡ መሰናከል፡ ነገር፡ ካልመጣ፡ የሚበልጥ፡ ሌላ፡ ሀብት፡ ይከተለዋል ። ይህም፡ የሚሆነው፡ ለያንዳንዱ፡ ሰው፡ ብቻ፡ አይደለም፥ለመንግሥትም፡ እንጂ፤ ለመንግሥትም፡ ጥቅም፡ የሚሆን ፡ አንድ፡ ጊዜ፡ ከተሠራ፡ ዘንድ፡ የበለጠ፡ ጥቅም፡ የሚያመጣ ፡ ሌላ፡ ነገር፡ ይከተለዋል ።

አሁን፡ ድንገት፡ መንግሥት፡ ተጣጥሮ፡ ፩፡ ወረዳ ፡ ውስጥ፡ ፩፡ የጋሪ፡ (ሠረገላ)፡ መንገድ፡ ቢያበጅ፤አራሹም ፡ የብረት፡ ሠሪውም፡ የልብስ፡ ሪውም፡ የሠፉትን፡ ሥራ ፡ ለመለዋወጥ፡ ሲፈልጉ፡ በቶሎ፡ ለመገናኘት፡ ይችላሉ። በዚሁም፡ እየሥራቸው፡ ለመሥራት፡ ከዱሮው፡ ይልቅ፡ ጊዜ፡ ያገኛሉ ። ከሥራቸውም፡ የሚያገኙት፡ ትርፍ፡ ይበዛል ። ስለዚህም፡ ለመንግሥት፡ የሚገባለት፡ ግብር፡ ያድጋል። በዚሁም፡ ባንድ፡ ወረዳ፡ ሌላ፡ የጋሪ፡ (የሠረገላ)፡ መንገድ፡ ይበጅበታል። በዚሁም፡ በሁለተኛው፡ የበለጠ፡ አዲስ፡ ትርፍ፡ ይገኝበታል ። በሁለቱም፡ ወረዳዎች፡ ያገኘውን፡ አዲስ፡ ትርፍ፡ ኣጋጥሞ፡ መንግሥት፡ የምድር፡ ባቡር፡ ሲሠራ፡ በሁለት፡

ፊት፡ ይጠቀምበታል። መገዠመሪያ፡ በባቡሩ፡ ኪራይ ፡ ከጋሪው፡ መንገድ፡ ግብር፡ ይልቅ፡ ይጠቀምበታል። ሁለተኛ፡ ዱሮ፡ ጋሪ፡ ሲጐትቱ፡ የነበሩ፡ በየወረዳው፡ ያሉ፡ ሠራተኞች ፡ ፈረሶቻቸውና፡ በቅሎዎቻቸው፡ በሮቻቸው፡ ሳይደክሙ፡ ያውም፡ ከዱሮ፡ የበለጠ፡ የፈለጉትን፡ ሥራ፡ ሁሉ፡ በፍጥነት ፡ ያገኙታል ። ሰዎቹም፡ ከብቶቻቸው፡ ዱሮ፡ በመንገድ፡ ሲያባክኑት፡ የነበረው፡ ጒልበት፡ ሌላ፡ ሥራ፡ ይሠራበታል ። በዚሁም፡ ዱሮ፡ ያልነበረ፡ አዲስ፡ ትርፍ፡ ይገኝበታል ። ከዚሁም፡ ትርፍ፡ ኣንድ፡ ክፍል፡ ግብር፡ ለመንግሥት፡ ይገባለታል ። መንግሥትም፡ በዚሁ፡ አዲስ፡ ግብር፡ የበለጠ፡ ሌላ፡ ትርፍ ፡ ያገኝበታል ። በሌላም፡ ነገር፡ ሁሉ፡ እንደዚሁ፡ ነው ። ለትምርት፡ ቤት፡ ገንዘብ፡ ቢወጣና፡ ሕዝቡ፡ ቢማር፡ ተምሮም ፡ በማናቸውም፡ ሥራ፡ ይሠለጥንና፡ የመንግሥት፡ ግብርም፡ ያድጋል ። በዚሁም፡ ቢሆን፡ መንግሥት፡ የበለጠ፡ ጥቅምና ፡ ትርፍ፡ ያገኝበታል፡ እንጂ፡ አይጐዳበትም ። ለሕዝቡ፡ በሽተኞች፡ ማስታመሚያ፡ ቤት፡ ቢሠራም፡ ባልጠነከረ፡ በሽታ ፡ ብዙ፡ ሰው፡ ይሞት፡ ነበር ። ታሞ፡ ከዳነ፡ ወዲያ፡ ሠርቶ ፡ የሚያገባው፡ ግብር፡ ከታመመበት፡ ገንዘብ፡ ይልቅ፡ ሳይበልጥ፡ አይቀርም፤ወይም፡ ደግሞ፡ ሳይወልድ፡ ሊሞት፡ የነበረው፡ ከዳነ፡ ወዲያ፡ ሁለት፡ ወይም፡ ሦስት፡ ቢወልድ፡ እነዚያም፡ ልጆች፡ በጒልበትና፡ በሥራ፡ በግብር፡ ያገለግላሉ ። ይህም፡ ለመንግሥት፡ እጅግ፡ የበለጠ፡ ጥቅሙ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ባገሩ፡ ውስጥ፡ ያሉትን፡ ሠራተኞች፡ ቢያሠለጥንና፡ ቢያቃርብ፡ ቢያተጋቸውም፡ ወይም፡ ለጤናቸውና፡ በደኅና፡ አኗኗር ፡ እንዲኖሩለት፡ ቢጥር፡ ገንዘብም፡ ቢያወጣ፡ ዋናውን፡ ሳያጠፋ፡ በየቀኑና፡ በየወሩ፡ በያመቱ፡ ብዙ፡ ወለድ፡ በሚሰጥ ፡ በታመነ፡ ባንክ፡ ገንዘቡን፡ አደራ፡ እንዳስቀመጠ፡ ያኸል ፡ ነው ። ስለዚህ፡ ባንዱ፡ ሀብት፡ የበለጠ፡ ሀብት፡ ይገኛል ፡ ብንል፡ የተተካከለ፡ ቃል፡ ነው ። ሀብትም፡ ማለት፡ የተከማቸ፡ ሥራ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ለእንግዴሁ፡ ተረድተነዋል። ሰው፡ የሚሠራውን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ኣንቀሳቅሶ፡ ከማጋጠም፡ በስተቀር፡ ሌላ ፡ ለመሥራት፡ አይችልም። ነገር፡ ግን፡ መሰናክለን፡ ሁሉ ፡ ታግሎ፡ ካሸነፈ፡ ወዲያ፡ የሚፈልገውን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ምድር ፡ ትሰጠዋለች። ሰውም፡ ምድርን፡ የሚገዛበት፡ ምክንያት፡ በዕውቀት፡ ነው፡ እንጂ፡ በጒልበት፡ ኣይደለም ። እንደ፡ ፈረስ ፡ ልሩጥ፡ እንደ፡ ግመል፡ ልሸከም፡ እንደ፡ ዓሣ፡ በውሃ፡ ውስጥ ፡ ልሂድ፡ ቢል፡ የተሰጠው፡ አካሉ፡ በጅ፡ አይለውም ። ዕውቀት፡ ባይኖረው፡ ከነዚህ፡ እንስሶች፡ አይበልጥም፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን፡

በዕውቀቱ፡ በልጦ፡ እንስሳን፡ ሁሉ፡ ይገዛል ። ሀብት ፡ ሲባል፡ የምድር፡ ጌትነት፡ ነው፤ማለት፡ በዕውቀት፡ ሀብት ፡ ሁሉ፡ ከምድር፡ ይገኛል ። ዕውቀት፡ የሌለው፡ ሕዝብ፡ ግን ፡ ሀብታም፡ ሊሆን፡ አይችልም ። ሀብትም፡ የሚሰፋ፡ ዕውቀት ፡ ሲሰፋ፡ ነው ። ባንድ፡ ነገር፡ ዕውቀት፡ ሲጠፋ፡ ሀብቱም ፡ አብሮ፡ ይጠፋል ። በዚሁ፡ በሦስተኛው፡ ክፍል፡ የሰው፡ ጥረቱ፡ ምድርን፡ ለመግዛት፡ እንደ፡ ሆነ፡ ተረድተነዋል ። ሀብት ፡ ማለትም፡ የምድርን፡ ግዛት፡ መለኪያ፡ ነው፤ድኻ፡ የሆነ ፡ ሕዝብ፡ የምድር፡ ሎሌ፡ ነው ። በረኃብና፡ በበሽታ፡ በሞት ፡ ስታንገላታው፡ ትኖራለች ። ሀብታም፡ ሕዝብ፡ ግን፡ የምድር ፡ ጌታ፡ ነውና፡ ምድር፡ ሎሌ፡ ሆና፡ ታገለግለዋለች ። እንግዲህ ፡ ይህነን፡ ካወቅን፡ ዘንድ፡ የሕዝብን፡ ሀብት፡ የሚያለማና፡ የሚያጠፋ፡ ምክንያቱ፡ ምን፡ እንደ፡ ሆነ፡ እንመርምር ።

# ፭ኛ፡ ምዕራፍ።

## የለውጥና፡ የንግድ፡ ማስረጃ።

ከዚህ፡ ቀደም፡ እንዳየነው፤ሰው፡ በመዠመሪያ፡ መጥፎውን፡ መሬት፡ ያርሳል። እየበዛ፡ ሲሄድ፡ ደኅናውን፡ መሬት፡ ለማቅናት፡ ኀይል፡ ያገኛል። ይህን፡ ኀይል፡ ግን፡ የሚያገኘው፡ እንዴት፡ ነው፤ብዛት፡ ብቻውን፡ ምን፡ ያደርጋል፤ሰው፡ በጕልበቱ፡ ምንም፡ ቢበዛ፡ ዕውቀት፡ ባይጨምርበት፡ ላመት፡ ምግቡና፡ ልብሱ፡ የሚበቃውን፡ ያኽል፡ ሊያፈራ፡ አይችልም፡ ነበር። በዕውቀቱ፡ ግን፡ ትልቅ፡ ኃይል፡ አግኝቶ፡ ከምግቡና፡ ከልብሱ፡ በላይ፡ ብዙ፡ ያተርፋል። እንግዲህ፡ ሰው፡ ሲበዛ፡ የሰው፡ ሀብት፡ እያደገ፡ የሚሄድበት፡ ዋናው፡ ምክንያት፡ ተባብረው፡ በዕውቀት፡ ስለ፡ ተጋገዙ፡ ነው። የሰው፡ ጥረቱ፡ ምድርን፡ ለመግዛት፡ ስለ፡ ሆነ፤ይህ፡ ጥረቱ፡ እንዲፈጸምለት፡ የሚያስፈልገው፡ ሰፊ፡ ዕውቀት፡ ነው። አንድ፡ ሰው፡ ለብቻው፡ ሁኖ፡ ለኑሮው፡ የሚያሳስበውን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ለመሥራት፡ አይችልም። አሁን፡ እስቲ፡ ጥጡን፡ ዘርቶ፡ ለቅሞ፡ ነድፎ፡ ፈትሎ፡ መኑን፡ አበጅቶ፡ ልብሱን፡ ሠርቶ፡ እስኪለብስ፡ ድረስ፡ ደግሞም፡ የብረቱን፡ ዐፈር፡ አቅልጦ፡ ማረሻ፡ ሥርቶ፡ የበሬውን፡ ዕቃ፡ ሁሉ፡ ራሱ፡ ኣበጅቶ፡ አርሶ፡ ጕልጕሎ፡ አርሞ፡ ዐጭዶ፡ ወቅቶ፡ እኽሉን፡ አበጥሮ፡ ፈጭቶ፡ አቡክቶ፡

ጋግሮ፡ እንጀራውን፡ እስኪበላ፡ ድረስ፡ አንድ፡ ሰው፡ ብቻውን፡ ቢሆን፡ ስንት፡ ጊዜ፡ ይፈጅበት፡ ይሆን፤ሌላው፡ ለኑሮው፡ የሚያስፈልገው፡ ነገር፡ ሁሉ፡ በቀር፡ እንኳ ፥ ላንድ፡ ነጠላ፡ ልብስና፡ ዕለት፡ እንጀራ፡ ሲል፡ ዕድሜውን፡ ሙሉ፡ ሲደክም፡ አልነበረምን። ብዙ፡ ሰዎች፡ ቢሆኑ፡ ሥራቸው፡ ፩፡ ዐይነት፡ ከሆነ፡ ዘንድ፡ ብዙ፡ ሊረዳዱ፡ ይችላሉን፤አራት፡ ሰዎች፡ ባንድ፡ ጥንድ፡ በሬ፡ ቢያርሱ፡ ወይም፡ ባንድ፡ መስፍ፡ ብቻ፡ መጥረቢያ፡ ቢያበጁ ፥ ሥራቸው፡ በጣም፡ እንዳይፋጠን፡ የታወቀ፡ ነገር፡ ነው። እንዲሁም፡ ሁለቱ፡ ሲያርሱ፡ ደግሞ፡ ሁለቱ፡ መጥረቢያ፡ የሡሩ፡ እንደ፡ ሆነ፡ በየያዙት፡ ሥራ፡ በቶሎ፡ ለማገባደድ፡ ይችላሉ። ሁለት፡ ሰዎችም፡ ባንድ፡ ሞፈር፡ ከሚያርሱ፡ አንደኛው፡ ሲያርስ፡ አንደኛው፡ ቢጐለጕል፡ የሚበልጥ፡ ሥራ፡ ይፈጽማሉ። እንዲሁም፡ መጥረቢያውንም፡ የሚሡሩ፡ ሰዎች፡ አንዱ፡ የብረት፡ ዐፈር፡ ሲያቀልጥ፡ አንዱ፡ ከሰል፡ ሰብሳቢ፡ ሲሆን፡ ሥራቸው፡ እየተፋጠነ፡ ይሄዳል። ባጭሩ፡ ብንናገር፡ ማናቸውም፡ ሥራ፡ እንዲፋጠን፡ ሥራውን፡ ማከፋፈል፡ ያስፈልጋል። ይህም፡ የሥራ፡ ማከፋፈል፡ ባሕሪ፡ የሰው፡ የተፈጥሮ፡ ባሕሪ፡ ነው። ስለዚህም ሥራውን፡ ለማከፋፈል፡ ሲል፡ ዘወትር፡ ርስ፡ በርሱ፡ ሲተባበር፡ እናያለን።

አሁን፡ ሰው፡ ሚስት፡ ቢያገባ፡ ሥራውን፡ ለመከፋፈል፡ እንደ፡ መተባበር፡ ያኽል፡ ነው። ርሱ፡ ሲያርስ፡ እሷ፡ ትጐለጕላለች፤በሮቹን፡ ሲያበላ፡ በውጭ፡ ቢያመሽ፡ ርሷ፡ የጋራ፡ እራታቸውን፡ ሠርታ፡ ትቈየዋለች። ባሏም፡ ደኑን፡ ሊመነጥር፡ መጥረቢያውን፡ ይዞ፡ ሲወጣ፡ ሚስቱ፡ እንዝርቷን፡ ይዛ፡ ልብሳቸውን፡ ትፈትላለች፤ልጆችም፡ ቢወልዱ፡ የቤታቸው፡ ሥራ፡ እንደ፡ ገና፡ ይከፋፈላል። እናቲቱ፡ ስትጋግር፡ ልጅቱ፡ ውሃ፡ ትቀዳለች፤ወይም፡ ትፈጫለች፤አባትዮውም፡ ዕንጨት፡ ሲቈርጥ፡ ልጅዮው፡ የተቈረጠውን፡ ዕንጨት፡ ተሸክሞ፡ ወደ፡ ቤት፡ ያመላልሳል። በዚሁም፡ ሥራቸው፡ እየተቃለለና፡ እየተፋጠነ፡ ይሄዳል።

ስለዚህም፡ ምክንያት፡ ሰው፡ እየበዛ፡ ሲሄድ፡ የሰውም፡ ሥራ፡ እየተለያየና፡ እየተከፋፈለ፡ ይሄዳል። ሰዎችም፡ የብረት፡ ሠሪዎች፡ ሰፊዎች፡ አናጢዎች፡ እየተባሉ፡ ሞያ፡ ሞያቸውን፡ ይይዛሉ፤ይሠለጥኑበታልም። የሡሩትንም፡ ዕቃ፡ እንደየሥራቸው፡ መጠን፡ ይለዋወጣሉ። በመለዋወጥም፡ ሥራቸው፡ እየተፋጠነ፡ ይሄዳል። በያዙትም፡ ሥራ፡ ስለ፡

ሥለጠኑ፡ የበለጠ፡ ሌላ፡ ዐይነት፡ ሥራ፡ ይሠራሉ። ስለዚህም፡ ለሰው፡ ኑሮ፡ የሚያስፈልግ፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ዋጋው፡ ያንሳል፤በምድርም፡ ገዢነት፡ ስላገኘ፡ የሰው፡ ሀብት፡ ያድጋል። እንግዲህ፡ ለሰው፡ የሚያስፈልገው፡ ዋናው፡ ነገር፡ ሥራውን፡ ተከፋፍሎ፡ የሥራውን፡ ፍሬ፡ መለዋወጥ፡ ነው። ሥራውን፡ ተከፋፍሎ፡ ካልተለዋወጠ፡ ግን፡ ብቻውን፡ ሲሆን፡ ማናቸውም፡ ሥራ፡ በምሉ፡ አይሳካለትም። ስለዚህም፡ መሰናከልን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ኣሸንፎ፡ የምድር፡ ጌታ፡ ለመሆንና፡ ከፍ፡ ወዳለው፡ የዕውቀት፡ ደረጃ፡ ለመድረስ፡ ያዳግተዋልና፡ አይችልም።

መለዋወጥም፡ የሰው፡ የተፈጥሮ፡ ባሕሪ፡ መሆኑ፡ ከሰው፡ ኑሮ፡ ውስጥ፡ ማናቸውንም፡ ኣንዳች፡ ነገር፡ አስተውለን፡ ብንመለከት፡ እንረዳለን። ባልና፡ ሚስት፡ ከደጅና፡ ከቤት፡ ሁነው፡ ሠርተው፡ የሠሩትን፡ ሥራ፡ ይለዋወጣሉ። አባትና፡ እናትም፡ ልጆቻቸውን፡ መግበው፡ ስላሳደጉ፡ ልጆቹ፡ ሲያድጉ፡ በሥራ፡ ይረዳሉ። ወላጆቻቸውንም፡ ሲያረጁ፡ ይጦሯቸዋል። ብረት፡ ሠሪውም፡ ማረሻ፡ አበጅቶ፡ ጤፍ፡ ይቀበላል። አራሹም፡ ጤፍ፡ ሰጥቶ፡ የተሻለ፡ ማረሻ፡ ያገኛል። በሌላም፡ ነገር፡ ሁሉ፡ እንደዚሁ፡ ነው። ዕውቀት፡ ባለው፡ ሕዝብ፡ መካከል፡ ግን፡ በከንቱ፡ የሚሰጥ፡ ሰው፡ የለም። በከንቱም፡ የሚበላ፡ ሰው፡ የለም። የሁሉም፡ ትዳሩ፡ ተለዋውጦ፡ ነውና፡ እንካ፡ ሥራ፡ አምጣ፡ ሥራ፡ ይባባላል፤ይህ፡ ሳይሆን፡ ቀርቶ፡ በላተኛው፡ ከሠራተኛው፡ ሲበዛ፡ በማናቸውም፡ ቤት፡ ሀብት፡ ሊገባ፡ አይችልም። ዕውቀትም፡ ከሌለው፡ ሕዝብ፡ ውስጥ፡ ከሠራተኛው፡ በላተኛው ፥ ሹም፡ ወታደር፡ ነጋዴ፡ እየሆነ፡ ይበዛልና፡ ባገሩ፡ ሀብት፡ ሊከማች፡ አይችልም። የሥራው፡ ፍሬ፡ እንደ፡ ገባ፡ ወዲያው፡ ያልቃል።

ውሃን፡ ለማፍላት፡ የፈለገ ሰው፡ ድስቱን፡ ጥዶ፡ ዕንጨት፡ ያነድበታል። ውሃው፡ ፈልቶ፡ ድስቱ፡ ለጊዜው፡ የማያስፈልገው፡ ከሆነ፡ በኋላ፡ ግን፡ ዕንጨቱ፡ የተሰበሰበው፡ በድካም፡ ነውና፡ በከንቱ፡ እንዳይባክንበት፡ ቢፈልግ፡ እሳቱን፡ አጥፍቶ፡ ዕንጨቱን፡ ለሌላ፡ ጊዜ፡ እንዲሆነው፡ ሊያቈየው፡ ይችላል። ድስቱንም፡ እንዲያፈላ፡ ዕንጨት፡ እንደሚያስፈልገው ፥ ሰውም፡ እንዲሁ፡ እንዲሠራ፡ ምግብ፡ ያስፈልገዋል። ያልሠራ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ግን፡ ለድስቱ፡ እሳትና፡ ዕንጨት፡ ይቅርበት፡ እንደሚባል፡ ሁሉ፡ እንዲሁ፡ ለሰውም፡ ምግቡ፡ ይቅርበት፡ እንደ፡ ማለት፡

ያለ፡ ነው። ሰው፡ ቢሠራም፡ ባይሠራም፡ በብዙ፡ ድካም፡ የተከማቸውን፡ ምግብ፡ መፍጀቱ፡ አይቀርም። ስለዚህም፡ የሠራተኛውን፡ ድካም፡ በከንቱ፡ ይፈጃል። ማናቸውም፡ ሥራ፡ እየቀለለ፡ የሚሄድ፡ ግን፡ ከተገርመረ፡ ወዲያ፡ ነው። ትልቅም፡ ሀብት፡ የሚሰበሰብ፡ በጥቂት፡ ሀብት፡ ሲዠመር፡ ነው፤ከዚህ፡ ምክንያት፡ የተነሣ፡ ባንድ፡ አገር፡ ውስጥ፡ ከሠራተኛው፡ በላተኛው፡ ሲበዛ፡ የተዠመረ፡ ሥራ፡ ሁሉ፡ እንደ፡ ገና፡ ይጠፋልና፡ ከዱሮው፡ የበለጠ፡ ሥራ፡ ወደ፡ ፊት፡ መሥራት፡ አይችልም። በእንደዚህም፡ ያለ፡ አገር፡ ውስጥ፡ ሕዝቡ፡ እየበዛ፡ ሲሄድ፡ ምግቡ፡ የማይበቃ፡ እየሆነ፡ ድሕነትና፡ ችጋርም፡ በሽታም፡ እየሰፋ፡ ይሄዳል። ስለዚህም፡ ያንድ፡ አገር፡ ሀብት፡ የሚያድገው፡ ከሁሉ፡ ነገር፡ በፊት፡ ሠራተኛው፡ ከበላተኛው፡ ያላነሰ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ማናቸውም፡ ሕዝብ፡ ለኑሮው፡ ከሚያስፈልገው፡ አብልጦ፡ ሲሠራ፡ የበለጠ፡ ሀብት፡ ያገኛል። ስለዚህም፡ ሥራው፡ ይፋጠንለታል። ሥራ፡ የሚፋጠነው፡ በምን፡ ምክንያት፡ እንደ፡ ሆነ፡ እንደ፡ ገና፡ መጠየቅ፡ አያስፈልገንም፤ከዚህ፡ ቀደም፡ ተረድተነዋል። ሥራ፡ የሚፋጠነው፡ እየተባበሩ፡ ተከፋፍለው፡ ሲሠሩት፡ ነው፤በመላውም፡ ሥራ፡ ከመሠልጠን፡ ባንዱ፡ የሥራ፡ ክፍል፡ መሠልጠን፡ ይቀናል። በየሠለጠኑበትም፡ ሥራ፡ ብዙ፡ ለመሥራት፡ ይቻላል። ስለዚህም፡ ሴት፡ ባቅሟ፡ አርሳ፡ ከምታገባው፡ እኽል፡ የፈተለችው፡ ጥጥ፡ ለርሷ፡ ለባሏም፡ የበለጠ፡ ጥቅም፡ ይሆናል።

እንዲሁም፡ አራሹ፡ የሠለጠነበትን፡ ሥራ፡ ትቶ፡ ማረሻን፡ ከሚያበጅ፡ አርሶ፡ ካገባው፡ እኽል፡ ትርፉን፡ ሰጥቶ፡ ከብረት፡ ሠሪው፡ ማረሻውን፡ ቢገዛ፡ ይሻላል። ሰው፡ የሠለጠነበትን፡ ሥራ፡ ሲሠራ፡ ጊዜው፡ አይባክንም። ለኑሮውም፡ ከሚያስፈልገው፡ ይልቅ፡ ሊሠራ፡ ይችላል። በትርፉም፡ ለወደ፡ ፊት፡ የበለጠ፡ ጥቅም፡ ያገኝበታል። ስለዚህም፡ ባንድ፡ አገር፡ ውስጥ፡ ሥራ፡ እየተከፋፈለ፡ ሲሄድ፡ ሰውም፡ በየያዘው፡ ሥራ፡ ሲሠለጥን፡ ያገሩ፡ ሀብት፡ እያደገ፡ ይሄዳል። ሕዝቡ፡ አንድ፡ ዓመት፡ ሠርቶ፡ ካገባው፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ለኑሮው፡ ከሚያስፈልገው፡ ሲተርፈው፡ በዚያው፡ በትርፉ፡ በሚመጣው፡ ዓመት፡ የበለጠ፡ ትርፍ፡ ያገኝበታል። ሥራ፡ ሳይዠመር፡ አይፈጸምም፤ሀብትም፡ መዠመሪያ፡ ሳይመሠረት፡ እያደገ፡ አይሄድም፡ ስለዚህም፡ ያንድ፡ ነገር፡ ሀብት፡ እንዲያድግ፡ መመሪያ፡ ሠራተኛው፡ ከበላተኛው፡ እንዳያንስ ፥ ሁለተኛም፡ ሕዝቡ፡

ተከፋፍሎ፡ እንዲለዋወጥ፡ ያስፈልጋል። እንደ፡ ሥራውም፡ አከፋፈል፡ ብዛትና፡ እንደ፡ ለውጡ፡ አፈጣጠን፡ መጠን፡ የሕዝቡ፡ ሀብት፡ ከፍ፡ ወይም፡ ዝቅ፡ ይላል።

እንሆም፡ የብረት፡ ሠሪው፡ ካራሹ ፥ አራሹም፡ ከሸማኔው፡ ከተራራቀ፡ ግን፡ የሠሩትን፡ ዕቃ፡ በፍጥነት፡ ለመለዋወጥ፡ እንደ፡ ምን፡ ይችላሉ። የጋሪ፡ መንገድ፡ ወይም፡ የምድር፡ ባቡር፡ ሠርቶ፡ መንግሥት፡ ካላቀራረባቸው፡ ለመገናኘት፡ ሲፈልጉ፡ አንዱ፡ ወዳንዱ፡ መንደር፡ ሄዶ፡ እስኪመለስ፡ ድረስ፡ ብዙ፡ ቀን፡ ሥራ፡ ይፈታል። ወይም፡ እሱ፡ ራሱ፡ ባይሄድ፡ ደክሞ፡ ካገባው፡ ሥራ፡ ከፍሎ፡ ዕቃውን፡ ለሚያመላልስ፡ ነጋዴ፡ ይሰጣል። ለሰው፡ የሚያስፈልገውን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ምድር፡ በሆዷ፡ ይዛለች፤ ማናቸውም፡ ነገር፡ ከምድር፡ ወጥቶ፡ እስኪበጅ፡ ድረስ፡ የሚደከመው፡ ድካም፡ ይጠቅማል። ነገሩ፡ ከተበጀ፡ በኋላ፡ ካንዱ፡ ስፍራ፡ ወደ፡ ሌላው፡ ስፍራ፡ ለመውሰድ፡ የሚደከመው፡ ድካም፡ ግን፡ በነገሩ፡ ላይ፡ አንዳች፡ ትርፍ፡ አይጨምርምና፡ ከንቱ፡ ነው። ስለዚህም፡ ምክንያት፡ ባንድ፡ አገር፡ ውስጥ፡ ነጋዴ፡ ሲበዛ፡ ለሕዝቡ፡ ትልቅ፡ ጉዳት፡ ነው።

ባንድ፡ አገርም፡ ውስጥ፡ ነጋይ፡ ያለመጠን፡ ሲበዛ፡ ባገሩ፡ ውስጥ፡ ደኅና፡ መንገድ፡ የሌለ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ሠራተኞቹ፡ ቶሎ፡ ለመገናኘት፡ ባይችሉ፡ ነውና፡ ከድካማቸው፡ ራሱ፡ ሳይሠራ፡ ቀምቶ፡ የሚበላ፡ ቢኖር፡ ተባብረው፡ ሊመክቱ፡ አይቻላቸውም። ስለዚህም፡ ባንድ፡ አገር፡ ውስጥ፡ ነጋዴ፡ ሲበዛ፡ ሹምም፡ ወታደርም፡ ቀማኛም፡ ይበዛል። የፊት፡ የፊቱም፡ ሥራ፡ በከንቱ፡ እያለቀ፡ በእንደዚህ፡ ያለ፡ አገር፡ ውስጥ፡ ሀብት፡ አይከማችም። ድኽነትና፡ ችጋር፡ በሽታም፡ ሞትም፡ እጅ፡ ለጅ፡ ተያይዘው፡ ይገቡበታል።

ነገር፡ ግን፡ ለኑሮው፡ የሚያስፈልገውን፡ ዕቃ፡ ሁሉ፡ በያይነቱ፡ የሚሠሩ፡ ሠራተኞች፡ አጠገብ፡ ላጠገብ፡ ካልሰፈሩ፡ ምንም፡ የሚያገናኛቸው፡ የጋሪ፡ መንገድ፡ የምድር፡ ባቡርም፡ መርከብም፡ ቢበጅላቸው፡ ጉዳታቸው፡ ይቀላል፡ እንጂ፡ መቸገራቸው፡ ፈጽሞ፡ አይቀርም። ባለጋሪው፡ ሳለምድር፡ ባቡሩም፡ በከንቱ፡ ዕቃ፡ አያመላልሱም፤ሠራትኞቹ፡ ደክመው፡ ከሚያገኙት፡ ትርፍ፡ ተካፍለው፡ ነው፡ እንጂ። ስለዚህም፡ የሠራተኞቹ፡ ቦታ፡ እየተራራቀ፡ ሲሄድ፡

ትርፋቸው፡ እያነሰ፡ ይሄዳል። ሰፈራቸውም፡ ሲቀራረብ፡ ትርፋቸውም፡ ያድጋል። ጎረቤቶችም፡ ከሆኑ፡ ዘንድ፡ ሌላ፡ ሰው፡ በመካከላቸው፡ ሳይገባባቸው፡ ሥራ፡ በሥራ፡ እየተለዋወጡ፡ የድካማቸውንም፡ ዋጋ፡ ያገኛሉ። የድካማቸውንም፡ ሙሉ፡ ዋጋ፡ ሲያገኙ፡ ለወደፊት፡ የበለጠ፡ ሀብት፡ ለማግኘት፡ ይሆንላቸዋል። ኣመላላሾችም፡ ሆነው፡ ሲያገለግሉ፡ የነበሩ፡ ሰዎች፡ ሌላ፡ የሚጠቅም፡ ሥራ፡ ይይዛሉ። በዚሁም፡ የሠራተኞቹ፡ ቍጥር፡ እየበዛ፡ ይሄዳል። ይህም፡ ብቻ፡ አይደለም፤ሠራተኞቹ፡ ኣጠገብ፡ ላጠገብ፡ ከሆኑ፡ ወይም፡ በፍጥነት፡ ስመገናኘት፡ ከተቻላቸው፡ ዘንድ፡ ደከመው፡ ካገቡት፡ ፍሬ፡ ቀምቶ፡ ሊበላ፡ ማንም፡ ቢፈልግ፡ ተባብረው፡ ለመመከት፡ ይሆንላቸዋል፤በዚህም፡ ምክንያት፡ ቀማኛ፡ ይጠፋል። የሹምና፡ የወታደርም፡ ቍጥር፡ በልክ፡ ይሆናል። በዚሁም፡ የሠራተኞቹ፡ ቍጥር፡ እንደ፡ ገና፡ ያድጋል፤አገሩም፡ ከዱሮው፡ ይልቅ፡ እየሰፋ፡ ይሄዳል።

ሕዝብ፡ የሚጠቀምበት፡ ሥራው፡ ሲከፋፈልና፡ የሠሩትን፡ ሥራ፡ የሚለዋወጡ፡ ሠራተኞች፡ ሲቃረቡ፡ ነው። መንግሥትም፡ የሚበረታውና፡ ሀብት፡ የሚያገኝ፡ ሕዝቡ፡ ሲጠቀም፡ ነው። ስለዚህም፡ መንግሥት፡ ሊበረታ፡ ከፈለገ፡ ዘንድ፡ በሥራ፡ የሚያሠለጥኑ፡ የትምርት፡ ቤቶችና፡ ሕዝቡን፡ በፍጥነት፡ የሚያገናኝ፡ መንገድ፡ መሥራት፡ ያስፈልገዋል።

ከዚህ፡ ቀደምም፡ አንድ፡ ነገር፡ ተረድተናል። የሠሩትን፡ ሥራ፡ የሚለዋወጡ፡ ሠራተኞች፡ እንደየድካማቸው፡ መጠን፡ የሚለዋወጡ፡ ለየሥራቸው፡ የሚያስፈልጋቸው፡ ዕውቀት፡ ሚዛኑ፡ ትክክል፡ ሲሆን፡ ነው፡ የውቀታቸው፡ ሚዛን፡ ትክክል፡ ካልሆነ፡ የሚለዋወጡበት፡ ዋጋ፡ ትክክል፡ አይሆንም።

ስለዚህም፡ ዕውቀት፡ የሌላቸው፡ ሕዝቦች፡ ዕውቀታቸው፡ ከፍ፡ ካለ፡ ሕዝቦች፡ ጋራ፡ የሠሩትን፡ ነገር፡ ሲለዋወጡ፡ ዕውቀት፡ የሌላቸው፡ ሕዝቦች፡ የሚያገኙት፡ ጉዳት፡ ትልቅ፡ ነው። የዚህንም፡ ጉዳት፡ ልክ፡ ፈጽመን፡ እንድንረዳው፡ ቀጥሎ፡ የተጻፈውን፡ ምሳሌ፡ እንመልከት።

ከኢትዮጵያ፡ ወደ፡ ኤሮፓ፡ አገር፡ ከጥር፡ ፲፱፻፸፡ ዓመተ፡ ምሕረት፡ እስከ፡ ጥር፡ ፲፱፻፸፫፡ ዓመት፡ ድረስ፡ የሄደው፡ ቆዳ፡ ፪፻፵፩ሺ፡ ፸፻፶፱፡ ፈረሱላ፡ ነው። ያንዱም፡ ፈረሱላ፡ ቆዳ፡ ዋጋ፡ ባዲስ፡ አበባ፡ ገበያ፡ ዐሥራ፡

ሦስት፡ ብር፡ ነበረ። የዚያ፡ የሄደው፡ ቆዳ፡ የዋጋው፡ ድምር፡ ብናስበው፡ ፫፡ ሚሊዮን፡ ፻፴፱ሺ፡ ፬፻፹፯፡ ብር፡ ይሆናል። በፈረንጅ፡ አገር፡ ተበጅቶ፡ የሚመጣው፡ ቆዳ፡ ግን፡ ባዲስ፡ አበባ፡ በፈረሱላ፡ ብናስበው፡ እስከ፡ ፪፻፡ ብር፡ አወጣ። እንግዲህ፡ አንዱ፡ ፈረሱላ፡ ቆዳ፡ ከፈረንጅ፡ አገር፡ ተሠርቶ፡ እስኪመለስ፡ ድረስ፡ በፈረሱላው፡ ፹፱፡ ብር፡ ፈጀ፡ ማለት፡ ነው። የኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡ ፪፻፵፩ሺ፡ ፬፻፺፱፡ ፈረሱላ፡ ቆዳ፡ ከዚሁ፡ ካገሩ፡ ማበጀቱን፡ ትቶ፡ ወደ፡ ኤሮፓ፡ ቢሰድ፡ ከሳራው፡ ፷፩፡ ሚሊዮን፡ ፬፻፺፫ሺ፡ ፬፻፲፩፡ ብር፡ ይሆናል። ቆዳው፡ ባገሩ፡ ውስጥ፡ ቢበጅ፡ አመላላሽና፡ ሠሪዎች፡ የሆኑት፡ የውጭ፡ ሰዎች፡ የሚበሉት፡ ይህ፡ ገንዘብ፡ በኢትዮጵያ፡ ይቀር፡ ነበረ። በሌላም፡ የንግድ፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ሲሆን፡ ከዚህ፡ ይከፋል፡ እንጂ ፥ አይሻልም፤እንደዚሁ፡ እንደ፡ ሆነ፡ አዙሮ፡ ማየት፡ ነው። የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ስምንት፡ ቀን፡ ሲሠራ፡ ቢያንስ፡ ቢያንስ፡ ሰባት፡ ቀን፡ ለኤሮፓ፡ ሰዎች፡ ሠርቶ፡ አንድ፡ ቀን፡ ለራሱ፡ ነው። አሁን፡ ለወሬው፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ፲፡ ሚሊዮን፡ ሕዝብ፡ ተብሎ፡ ይገመታል። ሠራተኛውም፡ ቢበዛ፡ የሕዝቡ፡ ሢሶ፡ ቢሆን፡ ነው። ያሥሩም፡ ሚሊዮን፡ ሰው፡ ሢሶ፡ ፫ ሚሊዮን፡ ፫፻፴፫ሺ፡ ፫፻፴፫፡ ይሆናል። ከነዚህም፡ ሠራተኞች፡ ለኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ የሚሠሩ፡ ፬፻፲፮ሺ፡ ፮፻፷፮፡ ሰዎች፡ ብቻ፡ ናቸው። የ፪፡ ሚሊዮን፡ ፱፻፲፮ሺ፡ ፮፻፷፮፡ ሠራተኞች፡ ድካም፡ ለኤሮፓ፡ ሰዎች፡ ጥቅም፡ መሄዱ፡ ነው። ስለዚህም፡ ሕዝቡ፡ የድካሙን፡ ፍሬ፡ እንደ፡ ተቀማ፡ ያኽል፡ ነውና፤ከሠራተኛው፡ በላተኛው፡ በዝቶበት፡ ዕውቀት፡ አግኝቶ፡ ካልሠለጠነ፡ ወደ፡ ፊት፡ እየበዛ፡ ሲሄድ፡ ድኽነትም፡ እያደር፡ እየተጫነው፡ ይሄዳል።

አንባቢው፡ ግን፡ እንደዚህ፡ ብሎ፡ ይጠይቅ፡ ይሆናል። የቆዳው፡ ምሳሌ፡ ደኅና፡ አድርጎ፡ አያስረዳም፤የኢትዮጵያ፡ ሰው፡ ቆዳውን፡ ሸጦ፡ ብሩን፡ መቀበል፡ እንጂ፡ ከፈረንጅ፡ ኣገር፡ ተበጅቶ፡ የሚመጣውን፡ ቈርበት፡ መግዛት፡ አያስፈልገውም። ያንን፡ ቈርበት፡ የሚገዙ፡ ባገራችን፡ ውስጥ፡ ያሉት፡ ፈረንጆች፡ ናቸው፡ እንጂ፤የኢትዮጵያ፡ ሰውስ፡ ለኮርቻውም፡ ለመጫኛውም፡ ለሌላም፡ ጕዳይ፡ ለሚያስፈልገው፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ባገሩ፡ የለፋ፡ ቈርበት፡ ይበቃዋል፤ስለዚህም፡ የከብት፡ በሽታ፡ ገብቶ፡ በሬው፡ ሙቶ፡ በከንቱ፡ ሊበሰብስ፡ የነበረው፡ ቆዳ፡ ዋጋ፡ ሲያወጣ፡ ትርፍ፡ ይሆናል፡ እንጂ፤ለኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ከሳራ፡ ይሆናል፡ የተባለው፡ ስለ፡

ምንድር፡ ነው፡ የተባለ፡ እንደሆነ፤አስተውለን፡ ከመረመርን፡ ዘንድ፡ የዚህን፡ ጥያቄ፡ መልሱን፡ በቶሎ፡ ልንረዳው፡ እንችላለን።

ተሠርቶ፡ የሚመጣውን፡ ቆዳ፡ ባንገዛ፡ አቡጀዲድ፡ ቈጫ፡ የብረት፡ ድስት፡ ሳሕንም፡ ምንጣፍም፡ ሌላም፡ ደግሞ፡ ልዩ፡ ልዩ፡ የሆነ፡ ዕቃ፡ ከኤሮፓ፡ አገር፡ የሚመጣውን፡ በያይነቱ፡ ብዙ፡ ዕቃ፡ መግዛታችን፡ አይቀርም፡ ነገር፡ ግን፡ የሠራተኞቹ፡ ዕውቀት፡ ሚዛኑ፡ ትክክል፡ በሆነ፡ አገር፡ ውስጥ፡ ሠራተኞቹ፡ ዕቃቸውን፡ ሲለዋወጡ፡ እንደየሥራቸው፡ መጠን፡ መሆኑን፡ ከዚህ፡ ቀደም፡ ዐውቀናል። ስለዚህም፡ ያቡጀዲዱ፡ ሠራተኛና፡ የቈርበት፡ ሠራተኛው፡ ሁለቱ፡ በኤሮፓ፡ አገር፡ ሲለዋወጡ፡ እንደየሥራቸው፡ መጠን፡ ነው። ስለዚህም፡ በቈርበቱ፡ ፈንታ፡ አቡጀዲዱ፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ አገር፡ ቢመጣ፡ ለተበጀው፡ ቈርበት፡ ሊሰጥ፡ የነበረውን፡ ዋጋ፡ እንደ፡ ሥራው፡ መጠን፡ ይወስዳል፤ማለት፡ ቈርበቱ፡ ተበጅቶ፡ ባይመለስ፡ ወኪሎቹን፡ እነአቡጀዲድንና፡ እነቈጫን፡ ልኮ፡ የኢትዮጵያን፡ ሕዝብ፡ ድካም፡ ይወስዳል።

የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ጕዳቱ፡ ግን፡ ይህ፡ ብቻ፡ አይደለም፤መሬት፡ ማናቸውንም፡ ነገር፡ ብትሰጥ፡ በብድር፡ ነው። ብድሯን፡ ካልመለሱላት፡ እንደ፡ ባንኮች፡ ሁሉ፡ ታስቸግራለች። በአይሁድና፡ በክርስቲያን፡ የሃይማኖት፡ መጽሐፍ፡ እንደምናየው፡ እንሆ፡ እግዚአብሔር፡ አዳምን፡ አለው፤አንተ፡ መሬት፡ ነኽና፡ ወደ፡ መሬት፡ ትመለሳለኽ፡ የሚፈጠር፡ ሁሉ፡ ከመሬት፡ ነውና፡ ወደ፡ መሬት፡ ይመለሳል፡ (ዘፍጥረት፡ ፫፡ ፲፱)።

ምድር፡ ያበደረችውን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ካልመለሱላት፡ ለወደ፡ ፊት፡ ስጭኝ፡ ቢሏት፡ ትለግማለች። ሄዶ፡ ሳይመለስ፡ የቀረባትም፡ ነገር፡ ሲበዛ፡ ከነከታቴው፡ በጭራሽ፡ እንቢ፡ ትላለች። ተበድሯት፡ ብድሩንም፡ ሳይመልስላት፡ እንቢ፡ ያለውን፡ ሕዝብ፡ በረኃብና፡ በበሽታ፡ ትፈጀዋለች። ይህ፡ ቃል፡ ሐሰት፡ እንዳይደለ፡ ማንም፡ ባላገር፡ ይመሰክራል።

አንድ፡ ጊዜ፡ ታርሶ፡ እኽሉ፡ የተበላ፡ መሬት፡ ፍግ፡ ካልወደቀበት፡ የሚያፈራው፡ እኽል፡ በያመቱ፡ እያነሰ፡ ይሄዳል። አዘውትረውም፡ ካረሱት፡ ዘንድ፡ ፍግም፡ ሳይወድቅበት፡ ቢቀር፡ የእርሻ፡ መሬት፡ ሁሉ፡ እኽል፡ መስጠቱን፡ ፈጽሞ፡ ያቋርጣል።

ስለዚህም፡ ያገራችን፡ መሬት፡ የዝኖን፡ ጥርስ፡ ዝባድ፡ ቆዳ፡ ቡና፡ እኸል፡ በሬ፡ ላም፡ ፈረስ፡ አህያ፡ በቅሎ፡ እየሆነ፡ በያመቱ፡ ወደ፡ ውጭ፡ አገር፡ ቢሄድ፡ አሁን፡ ለጊዜው፡ ለኛ፡ ሳይሰማን፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ በዝቶ፡ መሬት፡ እየጠበበ፡ ሲሄድ፡ ጉዳቱን፡ ያገኘዋል። ሕዝቡ፡ በሥራ፡ ሠልጥኖ፡ ሥራውንም፡ ሁሉ፡ እንደ፡ መጠኑ፡ ተከፋፍሎ፡ የሚያስፈልገውን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ባገሩ፡ ለማበጀት፡ ቢችል፡ ግን፡ ፍጉ፡ ባገሩ፡ ይቀርለት፡ ነበር። ስለዚህም፡ ዕውቀት፡ ያነሰው፡ ሕዝብ፡ ዕውቀታቸው፡ ከፍ፡ ካለ፡ ሕዝቦች፡ ጋራ፡ ሲገበያይ፡ መዥመሪያ፡ ትርፍ፡ ድካም፡ ይሰጣቸዋል። ሁለተኛም፡ መሬቱ፡ ወደነሱ፡ እየተጓዘ፡ ይሄዳል። እንደዚህ፡ ያለውም፡ ዕውቀት፡ ያነሰው፡ ልብ፡ ሲበዛ፡ መሬቱ፡ የሚሰጠው፡ ፍሬ፡ አይበቃውም። ስለዚህም፡ በጊዜ፡ ብዛት፡ ሠርቼ፡ እበላለሁ፡ ሲል፡ መሬቱ፡ ወደ፡ ሄደበት፡ አገር፡ ተከትሎ፡ ዕውቀት፡ ወዳላቸው፡ ሕዝቦች፡ አገር፡ ይሰደዳል። ባገሩም፡ የቀሩ፡ ሕዝቦች፡ ወንድሞቹ፡ ከረኃብና፡ ከበሽታ፡ ጋራ፡ እየታገሉ፡ ዕርፊት፡ ሳያገኙ፡ ጊዜ፡ ሞታቸው፡ ይደርስና፡ ይሄዳሉ።

አንባቢም፡ ደግሞ፡ እንደዚህ፡ ብሎ፡ እንደ፡ ገና፡ ይጠይቅ፡ ይሆናል። እኛ፡ ቆዳና፡ በና፡ ብንሰድ፡ ከኤሮፓ፡ አገር፡ አቡጀዲድና፡ ሱካር፡ ይመጣልናል፤ስለዚህም፡ ኣንድ፡ ክፍል፡ ቢሄድ፡ አንድ፡ ክፍል፡ ከመሬታቸው፡ ወደኛ፡ ይመጣል። እንግዲህ፡ በዚህ፡ የሚያገኘንን፡ ጉዳት፡ እንናገር፤ከመሬታቸውማ፡ አንድ፡ ክፍል፡ እንደሚመጣልን፡ ርግጥ፡ ነው። ነገር፡ ግን፡ እንደ፡ ሰጠነው፡ መሬት፡ ልክ፡ አልመጣልንም። አሁን፡ እስቲ፡ ባንድ፡ ክንድ፡ አቡጀዲድና፡ ባንድ፡ ክንድ፡ የበሬ፡ ቈዳ፡ ያለውን፡ ፍግ፡ አስተውለን፡ እንመልከት። ባንዱ፡ ክንድ፡ ቆዳ፡ ውስጥ፡ ያለው፡ ፍግ፡ ባይነቱም፡ በብዛቱም፡ ይበልጣል። አንዱ፡ ኰረጃ፡ አቡጀዲድ፡ እስከመቶ፡ ኻያ፡ ብር፡ ያወጣል። ያንድ፡ ጮማ፡ በሬ፡ ዋጋ፡ ግን፡ ቢበዛ፡ ዛሬ፡ ፵፡ ብር፡ ነው። እንግዲህ፡ ላንዱ፡ ኰረጃ፡ አቡጀዲድ፡ እስከ፡ ሦስት፡ በሬ፡ ይሰጥበታል። ስለ፡ ምን፡ በሬው፡ በሽታ፡ እንዳይገድለው፡ አውሬም፡ እንዳይበላው፡ ከመጠበቅና፡ ወደ፡ ገበያ፡ ከመውሰድ፡ በቀር፡ ሌላ፡ የሰው፡ ድካምና፡ ዕውቀት፡ አላለፈበትም። ያቡጀዲዱ፡ ጥጥ፡ ግን፡ አቡጀዲድ፡ እስኪሆን፡ ድረስ፡ በብዙ፡ ሰዎች፡ እጅና፡ በብዙ፡ መኪናዎች፡ ውስጥ፡ ገብቶ፡ ተደክሞበታል። በፈረንጅ፡ አገር፡ በሬውም፡ ቢሆን፡ ብዙ፡ ዋጋ፡ ያወጣል። ስለ፡ ምን፡ ሕዝቡ፡ በዝቶ፡ አገሩ፡ ጠባብ፡ ስለ፡ ሆነ፡ በሬው፡

በልቶት፡ የሚያድገው፡ ሣር፡ ተዘርቶ፡ ታጭዶ፡ ተከምሮ፡ ነው። ሜዳ፡ ለሜዳም፡ አይሰማራም፤የሚኖረውም፡ በቤት፡ ውስጥ፡ ነው። ቤቱም፡ የሚሠራ፡ በብዙ፡ ድካም፡ ነው። ስለዚህም፡ የኤሮፓ፡ አገር፡ በሬ፡ የሚያወጣው፡ ዋጋ፡ ብዙ፡ ነው። ያልተደከመበት፡ ነገር፡ ዋጋ፡ አያወጣም። ወደየደኑ፡ ሄዶ፡ ኢጋምን፡ ለቅሞ፡ የሚበላ፡ ሰው፡ ሄዶ፡ እስኪመጣ፡ ድረስ፡ ከሚደክመው፡ መንገድ፡ በቀር፡ ሌላ፡ ዋጋ፡ ኣይፈጅበትም። ተለቅሞ፡ ወደ፡ ገበያ፡ የመጣውን፡ ኢጋም፡ ሊበላ፡ ቢፈልግ፡ ግን፡ ዋጋ፡ ሰጥቶ፡ ነው።

ስለዚህም፡ ከኤሮፓ፡ አገር፡ ለሚመጣልን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ዋጋ፡ የምንሰጠው፡ ስለ፡ ሥራው፡ ነው፡ እንጂ፡ ስለ፡ ብዛቱ፡ አይደለም። ያቡጀዲዱ፡ ጥጥ፡ እንጂ፡ ሥራው፡ ወዳገራችን፡ መጥቶ፡ ፍግ፡ እንዳይሆነን፡ የታወቀ፡ ነው።

እንግዲህ፡ ዕውቀት፡ አንሶት፡ የሚያስፈልገውን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ በገዛ፡ እጁ፡ ለመሥራት፡ የማይችል፡ ሕዝብ፡ የሚያገኘው፡ ጒዳት፡ ምን፡ እንደ፡ ሆነ፡ ከተረዳነው፡ ዘንድ፤ይህነን፡ ጒዳትና፡ ባርነት፡ አጥፍቶ፡ ወደ፡ ሀብትና፡ ወደ፡ አርነት፡ የሚወስደውን፡ መንገድ፡ እናመልከት።

ሀብት፡ ማለት፡ የተከማቸ፡ ሥራ፡ ማለት፡ ነው። ሰውም፡ ነጻነት፡ ያለው፡ ነውና፡ የድካሙን፡ ፍሬ፡ ሁሉ፡ ለራሱ፡ ቢከማች፡ ነው። ዕውቀት፡ የሌለው፡ ሕዝብ፡ ግን፡ ሥራው፡ አይስማችለትም። የፊት፡ የፊቱ፡ ወዲያው፡ ያልቃል። ከድካሙም፡ ፍሬ፡ የሚያገኘው፡ ጥቅም፡ ጥቂት፡ ነው። ስለዚህም፡ ዕውቀት፡ የሌለው፡ ሕዝብ፡ ድኻና፡ የሰው፡ ሎሌ፡ ነው። ዕውቀትም፡ ሳይጨምር፡ እየበዛ፡ ቢሄድ፡ ድኽነቱና፡ ሎሌነቱ፡ እያደገ፡ እየጠነከረበት፡ ይሄዳል። ባንድ፡ ሕገብ፡ ላይ፡ እንደዚሁ፡ ያለው፡ መዓት፡ እንዳይወርድበት፡ እንግዲህ፡ ምን፡ ይበጀዋል።

## መልሱ፡ አጭር፡ ነው።

መዠመሪያ፤ርስ፡ በርሱ፡ በፍጥነት፡ እንዲገናኝ፡ ብልኀት፡ ይበጅለት። ሁለተኛ፤በየሥራውም፡ እንዲሠለጥን፡ የትምርት፡ ቤት፡ ይቍምለት። ሦስተኛ፤ሕዝቡ፡ የሚያስፈልገውን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ባገሩ፡ ውስጥ፡ እንዲሠራ፡ ለቀረጡ፡ የመንግሥት፡ ሹማምቶች፡ ይጠብቍት፡ እነዚህን፡ ሦስት፡ ቃላት፡ ግን፡ ለይተን፡ ለየብቻቸው፡ እንመርምራቸው።

# መግመሪያ።

ዕውቀት፡ በሌለው፡ አገር፡ ውስጥ፡ መንገድም፡ የምድር፡ ባቡርም፡ ቢሠራ፡ ለጊዜው፡ ይንቀዋል። ለጊዜውም፡ ብዙ፡ ብር፡ ይገባለትና፡ ሀብቱም፡ ያደገ፡ ይመስላል። ካንድ፡ ባንክ፡ ፲ሺ፡ ብር፡ የተበደረ፡ ሰው፡ ዐሥሩን፡ ሺ፡ ብር፡ አሸክሞ፡ በመንገድ፡ ሲሄድ፡ መበደሩን፡ ላላወቀ፡ ሰው፡ ሀብታም፡ ይመስለዋል። መበደሩን፡ የሚያውቅ፡ ሰው፡ ግን፡ ወዳጁ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ያዝንለታል። ጠላቱም፡ እንደ፡ ሆነ፡ ይንቀዋል። እውነትም፡ በዚሁ፡ ባ፲ሺ፡ ብር፡ ነግዶ፡ ለራሱ፡ የሚቈይ፡ ትርፍ፡ አግብቶ፡ የተበደረውን፡ ፲ሺ፡ ብር፡ ከነወለዱ፡ በቶሎ፡ ለባንኩ፡ ካልመለሰ፡ ተይዞ፡ በወህኒ፡ ቤት፡ ታስሮ፡ ይሞታል። በሕዝብም፡ ትዳር፡ እንደዚሁ፡ ነው። ዕውቀት፡ ያነሳቸው፡ ሕዝቦች፡ ዕውቀታቸው፡ ከፍ፡ ካለ፡ ሕዝቦች፡ ላይ፡ ዕቃ፡ ሲጓዙ፡ እየተበደሩ፡ ነው። የሚበደሩትም፡ ብድር፡ እኩሌታው፡ ከጕልበታቸው ፥ እኩሌታው፡ ከምድራቸው፡ ነው። ከጥር፡ ፲፱፻፫፡ ዓ፡ ም፡ እስከ፡ ፲፱፻፴፡ ዓ፡ ም፡ ድረስ፡ ማለት፡ በፈረንጆች፡ ቊጥር፡ ባ፲፱፻፲፪፡ ዓመት፡ ከኤሮፓ፡ በጅቡቲ፡ መንገድ፡ ለኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ የመጣለት፡ ዕቃ፡ ዋጋው፡ ቢታሰብ፡ ፯፡ ሚሊዮን፡ ፳፻፸፳ሺ፡ ፫፻፵፴፡ ብር፡ ሆነ። የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ካገሩ፡ ወደ፡ ኤሮፓ፡ ኣገር፡ በዚያ፡ ጊዜ፡ የሰደደው፡ ዕቃ፡ ዋጋው፡ ቢታሰብ፡ ፯፡ ሚሊዮን፡ ፰፻፹፰ሺ፡ ፴፻፵፱፡ ብር፡ ሆነ። ብናሰላው፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ከሸጠው፡ ዕቃ፡ የገዛው፡ ዕቃ፡ ፻፲፩ሺ፡ ፱፻፱፡ ብር፡ በለጠ። ብር፡ የሚመጣ፡ ግን፡ ከባሕር፡ ማዶ፡ ነው። የኢትዮጵያ፡ ሕዝብም፡ ብርን፡ የሚያገኝ፡ ምድሩ፡ የሚሰጠውን፡ ነገር፡ እየሸጠ፡ ነው። ስለዚህ፡ ዕቃ፡ ውን፡ ሸጦ፡ ካገባው፡ ብር፡ በላይ፡ ትርፍ፡ ብር፡ ሰጥቶ፡ የውጭን፡ አገር፡ ዕቃ፡ ለመግዛት፡ እንዴት፡ ተቻለው፤ትርፉንስ፡ ብር፡ ከየት፡ አመጣው። ሰው፡ የሌለውን፡ ነገር፡ ሊሰጥ፡ ይችላልን፤ርግጥ፡ ተበድሮ፡ ለመስጠት፡ ይችላል። የተበደረውን፡ ገንዘብ፡ ግን፡ ቈይቶ፡ ከነወለዱ፡ ይመልሳል።

የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ እንደዚሁ፡ ተበድሯል። ማንኛውም፡ የኤሮፓ፡ ሰው፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ ሲመጣ፡ አስቦበት፡ እንደ፡ መጣበት፡ ሥራ፡ መጠን፡ ጥቂት፡ ወይም፡ ብዙ፡ ገንዘብ፡ ይዞ፡ ይመጣል። ከዚሁም፡ ገንዘቡ፡ ቤት፡ ይሠራበታል፤ወይም፡ ይከራይብታል። ወይም፡ ምግቡን፡ ይገዛበታል፤ወይም፡ አሽከር፡ ይቀጥርበታል። ወደ፡ ኤሮፓም፡ አገር፡ ዕቃ፡

ሳይሰድ፡ ከዚያም፡ ዕቃ፡ አስመጥቶ፡ ሳይሸጥ፡ ዝም፡ ብሎ፡ ያለውን፡ ብር፡ የፈጀ፡ እንደ፡ ሆነ፡ የሚመጣው፡ ገንዘብ፡ ለኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ጥቅም፡ ይሆናል፤ብድርም፡ አይባል።

ነገር፡ ግን፡ ከዚህ፡ ቀደም፡ ገንዘቡን፡ ብቻ፡ ለመፍጀት፡ አንድም፡ የውጭ፡ አገር፡ ሰው፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ አገር፡ አልመጣ፤ሁሉም፡ የመጡት፡ ትርፍ፡ ሲፈልጉ፡ ነው። እንደዚህ፡ ያለውም፡ ሰው፡ በኢትዮጵያ፡ መጥቶ፡ ለቤት፡ ኪራይም፡ ለምግቡም፡ ላሽከሩም፡ ደመወዝ፡ ቢሰጥ፡ ለኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ እንደ፡ ማበደር፡ ያኽል፡ ነው።

ይህም፡ ያበደረው፡ ገንዘብ፡ በቶሎ፡ ከብዘ፡ ወለድ፡ ጋራ፡ እንዲመለስለት፡ ይጥራል። እንሆም፡ ካገሩም፡ አቡጀዲድ፡ አስመጥቶ፡ የቤት፡ ኪራይ፡ ለሰጠው፡ ሰውና፡ ለሚያገለግለው፡ አሽከሩ፡ ይሸጥላቸዋል። አቡጀዲዱንም፡ ሲሸጥ፡ ትንሽ፡ ትርፍ፡ ያገኛል። ያም፡ ቤቱን፡ ያከራየ፡ ሰውና፡ የፈረንጁ፡ አሽከር፡ አቡጀዲዱንና፡ ሌላውንም፡ የሚያስፈልጋቸውን፡ ዕቃ፡ ሁሉ፡ ዘወትር፡ ገንዘቡን፡ ከሚሰጣቸው፡ ፈረንጅ፡ ከገዙ ፥የፈረንጁ፡ ትርፍ፡ በጊዜ፡ ብዛት፡ ተጠራቅሞ፡ ፈረንጁ፡ ያመጣውን፡ ገንዘብ፡ ከነወለዱ፡ ያገኛል። አሁን፡ ለምሳሌ፡ አንድ፡ ሰው፡ ቤት፡ ሠርቶ፡ እሱው፡ ራሱ፡ የተቀመጠበት፡ እንደ፡ ሆነ፡ ቤቱ፡ የተሠራበት፡ ዋጋ፡ አይመለስለትም። ያከራየው፡ እንደ፡ ሆነ፡ ግን፡ በጊዜ፡ ብዛት፡ በኪራዩ፡ ዋጋውን፡ ከነወለዱ፡ ያገኛል። የፈረንጆችም፡ አካሄድ፡ በኢትዮጵያ፡ እንደዚሁ፡ ነው። ብር፡ ኣይቈረጠምም፤አይበላም፤ አይጠጣም፤የለውጥ፡ መሣሪያ፡ ነው። ስለዚህም፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ የሚመጡ፡ የውጭ፡ አገር፡ ሰዎች፡ በቃላቸው፡ ባይናገሩት፡ እንኳ፡ የኢትዮጵያን፡ ሕዝብ፡ እንደዚህ፡ የሚሉት፡ ይመስላል። እኛ፡ የመጣነው፡ ያገራችሁን፡ ሀብት፡ ለመውሰድ፡ ነው፤ነገር፡ ግን፡ መሬቱ፡ የናንተ፡ ነውና፡ እኛ፡ ሠርተን፡ በመሬታችሁ፡ ውስጥ፡ ያለውን፡ ሀብት፡ እንድንወስድ፡ እሺ፡ ኣትሉንምን፤እሺ፡ የምትሉን፡ እንደ፡ ሆነ፡ ያገራችንን፡ ሠራተኛ፡ አናመጣም ፥ ዋጋው፡ ይበዛብናልና፤ስለዚህ፡ የጉልበታችሁ፡ ዋጋ፡ እጅግ፡ ትንሽ፡ ነውና፡ እናንተው፡ ራሳችሁ፡ ሠርታችሁ፡ ስጡን፤ለድካማችሁ፡ ዋጋ፡ ጥቂት፡ ብር፡ እንሰጣችኋለን። በዚሁ፡ በምንሰጣችሁ፡ በጥቂቱ፡ ብር፡ ግን፡ የሚያስፈልገውን፡ መሣሪያና፡ መኪና፡ ገዝታችሁ፡ ልብሳችሁንና፡ ለኑሯችሁ፡ የሚያስፈልጋችሁን፡ ሁል፡ ጊዜ፡ ሌላ፡ ዕቃ፡ አትሥሩ።

ከዚህም፡ ቀደም፡ ባገራችሁ፡ ውስጥ፡ ሸማና፡ ጐራዴ፡ ሌላም፡ የሚሠራ፡ ነገር፡ እንዳለ፡ ለእንግዴህ፡ ወዲህ፡ አትሥሩ። ሁሉንም፡ ነገር፡ ከኛው፡ ግዙ፤የሰጠናችሁንም፡ ገንዘብ፡ ከብዙ፡ ወለድ፡ ጋራ፡ በቶሎ፡ መልሱልን።

የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ይህን፡ ነገር፡ ሰምቶ፡ ሸማውን፡ ትቶ፡ ቊጫና፡ አቡጀዲድ፤ሸማውንና፡ ማለፊያውንም፡ በርኖስ፡ ትቶ፡ የማይረባውን፡ የብርድ፡ ልብስ፤ሌላው፡ ይቅርና፡ ጋሻና፡ ጐራዴንም፡ እንኳ፡ ከእነሱ፡ እጅ፡ ይገዛል። ይህነንም፡ ሁሉ፡ ገዝቶ፡ አንዲት፡ ብር፡ የተረፈችው፡ እንደ፡ ሆነ፡ ሄዶ፡ መሸታ፡ ይጠጣባታል። ባለመሸታይቱም፡ ሻሽ፡ እገዛባታለሁ፡ ስትል፡ ያችን፡ ኣንዲት፡ ብር፡ ይዛ፡ ሄዳ፡ ላመጣት፡ ፈረንጅ፡ ትመልስለታለች። ለፍቶ፡ ለፍቶም፡ ለኢትዮጵያ፡ ሰው፡ ትርፉ፡ የጒልበት፡ መባከን፤ሑካርና፡ ፍሬ፡ የሚሰጠውም፡ የደኅና፡ መሬቱ፡ መሄድ፡ ነው። ካገሩም፡ ውስጥ፡ ግራና፡ ቀኝ፡ መንገድ፡ ቢሠራ፡ የምድር፡ ባቡርም፡ ቢዘረጋ፡ የሕዝቡ፡ ዕውቀት፡ ካልሰፋ፡ ከዛሬ፡ ሁኔታውም፡ ካልበለጠ፡ መበደሩን፡ ያበዛና፡ የተበደረውንም፡ ከነወለዱ፡ እመልሳለሁ፡ ሲል፡ ለውጭ፡ አገር፡ ሰዎች፡ ጥቅም፡ ከዛሬው፡ ይልቅ፡ ይደክማል። ብድሩንም፡ ለመመለስ፡ የሚበቃ፡ ጉልበት፡ ስለሌለው፡ ከምድሩ፡ ተበድሮ፡ ይሰጣል። የኢትዮጵያም፡ ምድር፡ ለጊዜው፡ ብድሬን፡ መልስ፡ ብላ፡ ባታስጨንቀው፤የሚመጡት፡ ትውልዶች፡ ያባቶቻችሁን፡ ዕዳ፡ መልሱ፡ ተብለው፡ ሳይያዙሰት፡ አይቀሩም። ዕውቀትም፡ አግኝተው፡ ያባቶቻቸውን፡ ዕዳ፡ ያልከፈሉ፡ እንደ፡ ሆነ፡ በድኽነትም፡ በችጋርም፡ በበሽታም፡ በሞትም፡ ያልቃሉ። ከሞትም፡ እናመልጣለን፡ ሲሉ፡ አባቶቻቸው፡ መሬቱን፡ ወደ፡ ሸጡበት፡ ወይም፡ ወደ፡ ሌላ፡ ነገር፡ ይሰደዳሉ። ዕዳውኝ፡ በጊዜ፡ የማይመልስ፡ ሕዝብ፡ ጒዳቱ፡ ይህ፡ ነው። ስለዚህ፡ ዕውቀት፡ በሌለው፡ ሕዝብ፡ አገር፡ መንገድና፡ የምድር፡ ባቡር፡ ቢሠራ፡ ሕዝቡ፡ እንዲደኸይ፡ ያፋጥናል፡ እንጂ፤አይጠቅመውም። ጥቅሙ፡ ከርሱ፡ ጋራ፡ ለሚገበያዩ፡ ዐዋቂዎች፡ ሕዝቦች፡ ነው።

## ሁለተኛ።

መንገድኛ፡ የምድር፡ ባቡር፡ ግን፡ በቶሎ፡ ካወቊበት፡ ትልቅ፡ ጥቅም፡ ይሆናል። ለየሥራውም፡ ማሠልጠኛ፡ የሚሆኑ፡ የትምርት፡ ቤቶች፡ ወዲያው፡ በቶሎ፡ ማቆም፡ ያስፈልጋል። ሕዝቡም፡ ሲሠለጥን፡ ለኑሮው፡

የሚያስፈልገውን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ በገዛ፡ እጁ፡ ይሠራል። ሥራውም፡ በጣም፡ ተከፋፍሎ፡ ሠራተኞቹም፡ አጠገብ፡ ላጠገብ፡ ይሆናሉ። የሠሩትንም፡ ሥራ፡ ካንዱ፡ ቦታ፡ ወዳንዱ፡ ቦታ፡ ለማንቀሳቀስ፡ ደካም፡ የለባቸውም። ስለዚህም፡ ሠራተኞችም፡ በየያዙት፡ ሥራ፡ ብዙ፡ ለመሥራት፡ ጊዜ፡ ያገኛሉ። በዚህም፡ ምክንያት፡ በያመቱ፡ አዲስ፡ አዲስ፡ ብልኀትና፡ አዲስ፡ ሥራ፡ ራሳቸው፡ መርምረው፡ ያገኙና፡ ያወጣሉ። በትርፉም፡ የበለጠ፡ ትርፍ፡ ይገኝበታል። እያደረም፡ የሕዝቡ፡ ሀብትና፡ የመንግሥቱ፡ ኃይል፡ እያደገ፡ ይሄዳል። ሀብትም፡ ማለት፡ አንዱም፡ ኃይል፡ ነው። መንገድና፡ የምድር፡ ባቡር፡ ግን፡ ያለዕውቀት፡ አገሩን፡ ያደኸያሉ፤አይጠቅሙም። ስለዚህም፡ የሕዝቡን፡ ጥቅም፡ የፈለገ፡ መንግሥት፡ እነዚህን፡ ሁለት፡ ነገሮች፡ አይለያይም፤ባንድነት፡ ለማቆም፡ ይጥራል፡ እንጂ።

# ሦስተኛ።

መንግሥት፡ ቀረጥ፡ ሲወስድ፡ ሕዝቡን፡ ሊጠቅም፡ ወይም፡ ሊጐዳ፡ ይችላል። ካገሩ፡ ውስጥ፡ የተበጀው፡ ዕቃ፡ ሲሸጥና፡ ሲለወጥ፡ በየገበያው፡ የቀረጠ፡ እንደ፡ ሆነ፥ዕቃውን፡ ሠርተው፡ የሚለዋወጡትን፡ ሠራተኞች፡ እንደ፡ መራራት፡ ያኸል፡ ነው። እስኪገናኙ፡ ድረስ፡ ከሚደክሙት፡ ድካም፡ በላይ፡ ሌላ፡ ትርፍ፡ ድካም፡ ይሄድባቸዋል። ስለዚህም፡ ትርፍ፡ ሥራ፡ ለመሥራት፡ ጊዜ፡ ያጥርባቸዋል። ይህም፡ ብቻ፡ አይደለም፤ደግሞ፡ የሚፈልጉትን፡ ዕቃ፡ ከሚሸጠው፡ ሠራተኛ፡ ጋራ፡ እስኪገናኙ፡ ድረስ፡ የሚፈጅባቸው፡ ድካም፡ ሲበዛ፡ የግድ፡ ካልሆነባቸው፡ በቀር፡ አይፈላለጉም። ኣራሹ፡ ላንድ፡ ዓመት፡ የሚበቃውን፡ ልብስ፡ ካገኘ፡ ትርፍ፡ እገዛለሁ፡ ብሎ፡ ሸማኔውን፡ አይፈልግም። ሸማኔውም፡ ላንድ፡ ዓመት፡ የሚበቃውን፡ እኸል፡ ካገኘ፡ ትርፍ፡ አገኛለሁ፡ ሲል፡ አራሹን፡ ለመፈለግ፡ አይሄድም።

አራሹና፡ ሸማኔው፡ ሊገዙ፡ የሚፈልጉት፡ ነገር፡ ጥቂት፡ ስለ፡ ሆነ፡ የሚሠሩትም፡ ሥራ፡ ያንሳል። አራሹ፡ እኸል፡ ሰብስቤ፡ ከሆዴ፡ የተረፈውን፡ ለሌላ፡ ነገር፡ ልለውጠው፡ ብል፡ ድካሜ፡ ከበዛ፡ እኸሉ፡ ቢቈለል፡ ለኔ፡ ምን፡ ይሆናል፡ ይላል። ለምግብ፡ የሚበቃውን፡ ያኸል፡ አርሶ፡ ከዘራ፡ በኋላ፡ ሥራ፡ ፈቶ፡ ዝም፡ ብሎ፡ ይቀመጣል። ሸማኔውም፡ እንዲህ፡ ያስባል፤የሠራሁትን፡ ሥራ፡ የሚገዛኝ፡ ካላገኘሁ፡ ለምን፡ በከንቱ፡

እደከማለሁ። እሱም፡ የሚሸጥለትን፡ ያኽል፡ ሸማ፡ ከሠራ፡ በኋላ፡ ሥራ፡ ፈቶ፡ ይቀመጣል። ሠራተኞቹም፡ ሥራ፡ ሲፈቱ፡ ባገሩ፡ ውስጥ፡ የሚሠራው፡ ሥራ፡ ያንሳል፤መንግሥትም፡ ብዙ፡ ግብር፡ ሊያገኝ፡ አይችልም።

ሠራተኞቹም፡ ድካሙን፡ ፈርተው፡ ብዙ፡ ጊዜ፡ የማይገናኙ፡ ስለ፡ ሆነ፡ መንግሥት፡ የሚያገኘው፡ ቀረጥ፡ ጥቂት፡ ይሆናል። ሠራትኞቹ፡ ሥራ፡ ከመፍታታቸው፡ የተነሣ፡ የሚቀረው፡ ግብር፡ ይበልጣል። ስለዚህ፡ የሕዝቡን፡ ልማትና፡ የራሱን፡ ጥቅም፡ የፈለገ፡ መንግሥት፡ ባገሩ፡ ውስጥ፡ ካንዱ፡ ወረዳ፡ ወዳንዱ፡ ወረዳ፡ በሚሄደው፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ምንም፡ ቢሆን፡ የቀረጥ፡ በር፡ ማበጀት፡ አይገባውም። ባዲስ፡ አበባ፡ ከተማ፡ ፩፡ ዳውላ፡ ገብስ፡ ፬፡ ብር፡ ሲያወጣ፡ አዲስ፡ ዓለም፡ ባ፩፡ ብር፡ ከሦስት፡ ሩብ፡ ይገኛል። በሜጫ፡ ግን፡ ያንድ፡ ዳውላ፡ ገብስ፡ ዋጋው፡ አንድ፡ ብር፡ ነው፡ ደግሞ፡ ጥቂት፡ መንገድ፡ እስከ፡ ጨቦ፡ ድረስ፡ እልፍ፡ ብንል፡ ዋጋው፡ አላድ፡ ይሆናል። እንግዲህ፡ ገብሱ፡ ከጨቦ፡ ተነሥቶ፡ አዲስ፡ አበባ፡ እስኪገባ፡ ድረስ፡ ታርሶ፡ ከገባበት፡ ድካም፡ ይልቅ፡ መሰናከሉ፡ ስምንት፡ ጊዜ፡ ይበልጣል። ስለዚህም፡ የጨቦ፡ ባላገር፡ ዕራቆቱን፡ ሁኖ፡ የግድ፡ ካልሆነበት፡ በቀር፡ ሸማን፡ ለመግዛት፤አዲስ፡ አበባ፡ ድረስ፡ አይመጣም። ትርፍ፡ ልብስና፡ ብርጭቆ፡ ምንጣፍም፡ የብረት፡ ድስትም፡ ሱካርም፡ መቼም፡ የግድ፡ አያስፈልጉትምና፤እነሱን፡ እገዛለሁ፡ ሲል፡ አይጣጣርም።

ስለዚህም፡ ምግቡና፡ ለልብሱ፡ መግዣ፡ የሚበቃውን፡ ያኽል፡ አርሶ፡ ገብስ፡ ካገባ፡ በኋላ፡ ሥራ፡ ፈቶ፡ ይቀመጣል። ለመንግሥትም፡ የሚያገባው፡ ዐሥራት፡ ጥቂት፡ ይሆናል። እንዲሁም፡ ባዲስ፡ አበባ፡ የሚኖሩ፡ ሸማኔዎች፡ የሠሩትን፡ ሸማ፡ የሚገዟቸው፡ ባዲስ፡ አበባ፡ ዙሪያ፡ ያሉት፡ ባላገሮች፡ ብቻ፡ ይሆናሉ። ስለዚህም፡ የሸማኔዎች፡ ቍጥር፡ ያንሳል። ለመንግሥትም፡ ከሸማኔዎች፡ የሚገባለት፡ ግብር፡ እያደር፡ እያነሰ፡ ይሄዳል።

እንሆ፡ ከዚህ፡ ቀደም፡ ያልነውን፡ አሁንም፡ ኣስረግጠን፡ እንናገረው። ዕቃ፡ የሚረክሰው፡ ገዢውና፡ ሠሪው፡ ሽያጩ፡ አጠገብ፡ ላጠገብ፡ ቀርቦ፡ ሲሰፍር፡ ነው። ማለት፡ የተላላኪው፡ ነጋዴ፡ ደመወዝ ይቀራል። ስለዚህ፡ በተላላኪው፡ ነጋዴ፡ ደመወዝ፡ ላይ፡ ቀረጥ፡ ቢጨመር፡ ሠራተኞቹ፡ ከሚያገኙት፡ ዕቃ፡ ይልቅ፡ በከንቱ፡ የሚደክሙት፡ ድካም፡ ይበልጣልና፤

ብዙ፡ ሥራ፡ ለመሥራት፡ ጊዜ፡ አያገኙም። ይልቁንም፡ የግድ፡ ከሚያስፈልጋቸው፡ በቀር፡ ትርፍ፡ ነገር፡ ለመግዛት፡ አይከጅሉም። ብዙ፡ ሥራ፡ ሊሠሩበት፡ የነበረውንም፡ ጊዜያቸውን፡ ግማሹን፡ በከንቱ፡ ድካም፡ ግማሹንም፡ በስንፍና፡ ያሳልፉታል። የሕዝቡም፡ ኑሮ፡ እንደዚህ፡ የሆነው፡ መንግሥት፡ ሀብቱና፡ ኃይሉ፡ እያነሰ፡ እንጂ፡ እያደገ፡ እንዳይሄድ፡ በግልጽ፡ የታወቀ፡ ነገር፡ ነው።

እንግዲህ፡ ከውጭ፡ አገር፡ የሚመጣውስ፡ ዕቃ፡ እንደ፡ ምን፡ ይሁን፡ ይቀረጥን፤ወይስ፡ አለቀረጥ፡ ይግባ። ለዚሁ፡ ጥያቄ፡ ርግጠኛ፡ መልስ፡ ለመስጠት፡ ከመቶ፡ ዓመታት፡ በፊት፡ ዠምሮ፡ እስከ፡ ዛሬ፡ ድረስ፡ ብዙ፡ የዓለም፡ ሊቃውንት፡ ይከራከሩ፡ ነበርና፡ ከተከራካሪዎችም፡ ሊቃውንት፡ ከዚህ፡ ቀደም፡ ያሸነፈና፡ የተሸነፈ፡ የለም። መንግሥታት፡ ሁሉ፡ ለጊዜው፡ እንደሚጠቅማቸው፡ እያዩ፡ አንድ፡ ጊዜ፡ ያንዱን፡ ወገን፡ አሳብ፡ ሌላ፡ ጊዜ፡ ደግሞ፡ የሁለተኛውን፡ ወገን፡ አሳብ፡ እየተከተሉ፡ የቀረጣቸውን፡ ደንብ፡ በየጊዜው፡ ይለዋውጡታል። ይልቁንም፡ ጊዜው፡ የሚጠቅም፡ መሆኑን፡ ሲረዱት፡ የሁለቱን፡ አሳብ፡ ተቀብለው፡ ከውጭ፡ አገር፡ የሚመጣውን፡ ነገር፡ ግማሹ፡ እንዲቀረጥ፡ ግማሹ፡ ያለቀረጥ፡ እንዲገባ፡ የደነቡ፡ መንግሥታት፡ ኣሉ። ይህም፡ ሦስተኛው፡ ያቀራረጥ፡ መንገድ፡ እንደ፡ ጸሓፊው፡ አሳብ፡ እንደ፡ ኢትዮጵያ፡ ላለው፡ አገር፡ የሚበጅ፡ ነውና፤ የሚበጀው፡ ምክንያቱ፡ ምን፡ እንደ፡ ሆነ፡ ለይተን፡ እንመርምር።

ከዚህ፡ ቀደም፡ እንዳየነው፡ ሕዝብ፡ ሁሉ፡ መሰናከል፡ ነገር፡ ካላገኘው፡ ከፍ፡ ወዳለው፡ የዕውቀት፡ ደረጃ፡ ለመድረስ፡ ይችል፡ ነበር። መሰናከል፡ ነገር፡ ያላገኘው፡ ሕዝብ፡ ግን፡ በዓለም፡ ላይ፡ አይገኝም። እንዳገኛቸውም፡ መሰናከል፡ ነገር፡ ማነስና፡ ማደግ፡ እንደዚሁ፡ መጠን፡ ዕውቀታቸውና፡ ሀብታቸው፡ ከፍ፡ ወይም፡ ዝቅ፡ ይላል። በዛሬውም፡ ዘመናችን፡ የዕውቀትን፡ መዠመሪያ፡ ደረጃ፡ የያዙ፡ የኤሮፓና፡ ያሜሪካ፡ ሕዝቦች፡ ናቸው። ስለዚህም፡ ያገራቸው፡ ሀብት፡ በብዙ፡ ዘመናት፡ የተሠራና፡ የተከማቸ፡ መሣሪያ፡ መኪና፡ ፋብሪካ፡ እየሆነ፡ ሀብታቸው፡ ከሌሎች፡ ሕዝቦች፡ ሀብት፡ ይበልጣል።

ሕዝቦቹም፡ በዘመናት፡ ብዛት፡ ዕውቀትና፡ ጥበብ፡ ትጋትም፡ ከሰውነታቸው፡ ጋራ፡ ስለ፡ ተዋሐደ፤ከነሱ፡ ጋራ፡ ለመተካከል፡ ቢፈልጉ፡ ለቀሩት፡ የዓለም፡ ሕዝቦች፡ የሚያስቸግር፡ ነገር፡ ነው። በመላው፡ ዓለም፡

ሁሉ፡ ለነሱ፡ ሰግዷል። ከጃፓንና፡ ከቱርክ፡ ከሺናም፡ ከሲያምም፡ ከኢትዮጵያ፡ ነገሥታት፡ በቀር፡ ዛሬ፡ ዓለም፡ ሁሉ፡ በመላው፡ ቅኛቸው፡ ሁኗል። ከነዚህም፡ እስከ፡ ዛሬ፡ አርነታቸው፡ ከቈየላቸው፡ ነገሥታት፡ አለጃፓን፡ የቀሩት፡ ነገሥታት፡ አርነት፡ አላቸው፡ ቢባል፡ ለስም፡ ብቻ፡ ነው።

እስቲ፡ አሁን፡ እኛ፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ኣርነት፡ አለን፡ ሊባል፡ ነውን፤አርነት፡ ያለው፡ ሕዝብ፡ ማለት፡ እውነተኛ፡ ትርጕሙ፡ ለብቻው፡ መንግሥት፡ ያለው፡ ሕዝብ፡ ማለት፡ ብቻ፡ አይደለም፤ራሱንም፡ የቻለ፡ ሕዝብ፡ ማለት፡ ነው፡ እንጂ። የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ እስከ፡ ዛሬ፡ ድረስ፡ ገና፡ ራሱን፡ አልቻለም። እስቲ፡ የለበስነውን፡ እንይ፤ከወዴት፡ የተሠራና፡ ማን፡ ያመጣው፡ ነው፤የቤታችንስ፡ ዕቃ፡ ሁሉ፡ ከወዴት፡ የመጣ፡ ነው፤ የምንለብሰውስ፡ ልብስ፡ የምንጠጣበትና፡ የምንበላበት፡ ምግባችንንም፡ የምናበስልበት፡ ዕቃና፡ መሣሪያ፡ ሁሉ፡ ፈጽሞ፡ ከውጭ፡ አገር፡ መጣ፡ አይደለምን። ከዚህም፡ ቀደም፡ በሀገራችን፡ ራሳችን፡ ለመሥራት፡ ስንችለው፡ የነበረው፡ ሥራ፡ ሁሉ፡ ዛሬ፡ ተረሳ፤ቈጫና፡ በፈረንጅ፡ አገር፡ የተሠራ፡ ሸማ፡ ፈትልም፡ ያገራችንን፡ ቡልኮና፡ ጋቢ፡ ያማረውንም፡ ሸማችንን፡ የሴቶቻችንንም፡ ቀጭን፡ ፈትል፡ ከገበያው፡ አባረው፡ ዋጋውንም፡ ወሰዱት። የዶማውንና፡ የመጥረቢያውን፡ ነገርማ፡ ዛሬ፡ ምን፡ ብለን፡ እናውጋው። ባዲስ፡ አበባና፡ በድሬ፡ ዳዋ፡ በሐረርጌም፡ ገበያ፡ በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ የተሠራ፡ ከእነዚህ፡ መሣሪያዎች፡ አንድም፡ አይታይም። ይልቊንም፡ በትግሬማ፡ በጭራሽ፡ ዛሬ፡ ባላገሩ፡ ማረሻው፡ እንኳ፡ ሳይቀር፡ ከውጭ፡ አገር፡ ኣስመጥቶ፡ ነው። ማለት፡ የኤሮፓ፡ ሰዎች፡ ባገራችን፡ ከመውና፡ ከገቡ፡ ወዲህ፡ እንኳን፡ ዕውቀት፡ ልንጨምር፡ አባቶቻችንም፡ ያቈዩልንን፡ ሥራ፡ ሁሉ፡ ግማሹን፡ ዛሬውኑ፡ ረስተነዋል። ግማሹንም፡ አሁን፡ ከጅቡቲ፡ ወደ፡ አዲስ፡ አበባ፡ በተሠራው፡ የምድር፡ ባቡር፡ ምክንያት፡ እስከ፡ ቅርብ፡ ጊዜ፡ ድረስ፡ ፈጽመን፡ ሳንረሳው፡ አንቀርም። በኢትዮጵያም፡ ሕዝብ፡ ውስጥ፡ ያለው፡ የያንዳንዱ፡ ሰው፡ የዛሬው፡ ጥረቱ፡ በደኅና፡ ለመኖር፡ ሰውነቱንና፡ ቤቱን፡ ለማስጌጥ፡ ነው፤ በማናቸውም፡ ሕዝብ፡ ልብ፡ ውስጥ፡ እንደዚሁ፡ ያለ፡ ጥረት፡ ቢኖር፡ ሕዝቡ፡ ዕውቀት፡ ፈላጊ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ይመሰክራልና፡ እጅግ፡ ያስመሰግነዋል። ይህንንም፡ ጥረት፡ አይቶ፡ መንግሥት፡ በደኅና፡ መንገድ፡

ከመራው፡ እንደዚህ፡ ያለ፡ ተጣጣሪ፡ ሕዝብ፡ ከፍ፡ ወዳለው፡ የዕውቀት፡ ደረጃ፡ ለመድረስና፡ ትልቅ፡ ሀብት፡ ለማግኘት፡ ይችላል።

ደኅናውን፡ መንገድ፡ መንግሥት፡ ለክቶ፡ ካልሰጠውና፡ ካላሳየው፡ ግን፡ እንደዚህ፡ ያለ፡ ጌጥና፡ ምቹ፡ ኑሮ፡ የሚወድ፡ ሕዝብ፡ መጨረሻው፡ ክፉ ነው። ብዙ፡ ነገር፡ ይለምዳል፤ነገር፡ ግን፡ የለመደውን፡ ነገር፡ ለማድረግ፡ ዐቅም፡ ያጣል። ይህም፡ ብቻ፡ አይደለም፤የሚያስፈልገው፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ዕውቀት፡ ባላቸው፡ አገሮች፡ በመኪናና፡ በተሻለ፡ መሣሪያ፡ ተሠርቶ፡ ሲመጣ፡ ዋጋው፡ ባገሩ፡ ከተሠራው፡ ይረክሳልና፡ ለዋጋው፡ ሲል፡ ባገሩ፡ የተሠራውን፡ ትቶ፡ ከውጭ፡ አገር፡ የመጣውን፡ ዕቃ፡ ይገዛል። በዚሁም፡ ባገሩ፡ ውስጥ፡ የነበሩት፡ ሥራተኞች፡ የሩትን፡ ሥራ፡ የሚገዛቸው፡ አጥተው፡ የለመዱትን፡ ሥራ፡ ትተው፡ የዕለት፡ እንጀራ፡ የሚገኝበትን፡ ሌላ፡ ሥራ፡ ይይዛሉ። ከዚህም፡ የተነሣ፡ ሕዝቡ፡ ዕውቀት፡ ፈጽሞ፡ ይለየዋልና፤የውጭ፡ አገር፡ ሕዝቦች፡ ታዛዥ፡ ይሆናል። አሁን፡ ከውጭ፡ አገር፡ ንግድ፡ ባይመጣ፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ለጊዜው፡ የሚለብሰው፡ አጥቶ፡ ይቸገር፡ ነበር። የኢትዮጵያ፡ የሰሜን፡ ሕዝቦችማ፡ የብረት፡ ማረሻን፡ አጥተው፡ በዕንጨት፡ መሬቱን፡ መቈፈር፡ የግድ፡ ይሆንባቸው፡ ነበር። የሐረርጌም፡ ጋላ፡ አካፋ፡ ኣጥቶ፡ እርሻው፡ ሁሉ፡ ይበላሽበት፡ ነበር። ሠራተኛና፡ ጒልበትም፡ መኪናም፡ ከመታጣት፡ የተነሣ፡ ዛሬ፡ ስምቶ፡ የምናየው፡ የኢትዮጵያ፡ እርሻ፡ የሚበዛው፡ ዱርና፡ ደን፡ ይሆናል።

የኢትዮጵያም፡ ሕዝብ፡ ከውጭ፡ አገር፡ ዕቃ፡ እንዲያስፈልገው፡ የዛሬ፡ ፫፡ ዓመት፡ ተገለጠ። በትግሬ፡ የእኽል፡ ሽመታ፡ ተወዶ፡ ሰራዊታቸው፡ ቢቸገር፡ ራስ፡ ስብሐትና፡ ደጃዝማች፡ ሥዩም፡ ተማከረው፡ እኽል፡ ወደ፡ ሐማሴን፡ እንዳይወርድ፡ ከለከሉ። ከዚሁም፡ የተነሣ፡ የሐማሴን፡ ገዢ፡ አንዳች፡ የባሕር፡ ማዶ፡ ዕቃ፡ ከሐማሴን፡ ወደ፡ ትግሬ፡ እንዳይሄድ፡ ከለከለ። ከጥቂት፡ ጊዜ፡ በኋላ፡ ራስ፡ ስብሐትና፡ ደጃዝማች፡ ሥዩም፡ ሰራዊታቸው፡ በዚህ፡ ነገር፡ እንደ፡ ተቸግረ፡ አይተው፡ ክልክሉን፡ አፈረሱት። ስለዚህም፡ የኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡ መንግሥትነቱና፡ የሕዝቡ፡ ኣርነት፡ በዋዛ፡ እንዳይጠፋበት፡ የፈለገ፡ እንደ፡ ሆነ፡ መመከቻውን፡ ማሰናዳት፡ ነው። ዋናውም፡ መመከቻ፡ የሚሆነው፡ የተደላደለ፡ የጉምሩክ፡ ደንብና፡ ሥራ፡ ማሠልጠን፡ ነው።

# ፺ኛ፡ ምዕራፍ።

ዛሬ፡ ያገራችን፡ ጉምሩኮች፡ ከውጭ፡ ነገር፡ የመጣውን፡ ልብስ፡ ሲቀርጡ፡ እንደ፡ ሌላው፡ ሁሉ፡ ካሥር፡ አንድ፡ ነው። የልብሱም፡ መሥሪያ፡ መሣሪያና፡ መኪና፡ ቢመጣ፡ እንዲሁ፡ ካሥር፡ አንድ፡ ይቀረጣል። የልብስም፡ መሣሪያ፡ መኪና፡ ፋብሪካ፡ አቆማለሁ፡ የሚል፡ ሰው፡ ቢመጣ፡ እንደ፡ ዛሬው፡ ያገራችን፡ ሹማምት፡ አያያዝ፡ ቢሆን፡ ይከለከላል። ያለዚያ፡ ግን፡ ሊሥራው፡ ያሰበው፡ ልብስ፡ እንደማይሸጥለት፡ አድርገው፡ ለኋላ፡ የሚሰጠውን፡ ግብር፡ ያበዙበታል። እንዲሁም፡ ደግሞ፡ በረሓውን፡ መሬት፡ አቅንቼ፡ ጥጥ፡ ዘርቼ፡ አበቅላለሁ፡ የሚል፡ ሰው፡ ቢመጣ፤ማስቸገር፡ እንጂ፡ አንድም፡ ርዳታ፡ ከኢትዮጵያ፡ ሹማምት፡ አያገኝም። ከዚህም፡ ምክንያት፡ የተነሣ፡ በኢትዮጵያ፡ ፋብሪካ፡ አቁሜ፡ ልብስ፡ እሠራለሁ፡ የሚልና፡ የሚያስብ፡ አንድም፡ አስተዋይ፡ ሰው፡ በኤሮፓና፡ ባሜሪካ፡ አይገኝም። ያገራችንም፡ የዛሬ፡ ዋኖች፡ ሹማምት፡ መንግሥታቸውን፡ እንዳገለገሉ፡ ሊታወቅላቸው፡ ሲፈልጉ፡ ደኅና፡ ውል፡ እንደ፡ መዋዋል፡ ዛሬ፡ ውል፡ አስቀረሁ፡ እያሉ፡ በየቤታቸው፡ ያወራሉ። በዚሁም፡ ድንቊርናቸው፡ ዕውቀት፡ የሌላቸውና፡ ያለፈው፡ ኑሯቸው፡ የማይታወቅ፡ ባሕሪም፡ የሌላቸው፡ አንዳንድ፡ የውጭ፡ አገር፡ ስደተኞችም፡ በልተን፡ እንደር፡ ሲሉ፡ ያገራችን፡ ሹማምት፡ ዛሬ፡ የያዙትን፡ የስሕተት፡ መንገድ፡ እንዳይለቁ፡ ያጠነክሩታል። አይዟችሁ፡ እያሉ፡ ከየመጻሕፍቱ፡ የለቀሙትን፡ ትርጉሙ፡ ግን፡ ለራሳቸውም፡ ቢሆን፡ ያልተገለጠላቸውን፡ አንዳንድ፡ የተሰበረ፡ ቃል፡ ያስጠኗቸዋል።

ያገራችንም፡ ሹማምት፡ ሩቅ፡ እንዳያዩ፡ እነዚህ፡ የተሰባበሩ፡ ቃላት፡ እንደ፡ ጉም፡ ነው፡ ዐይናቸውን፡ ሸፍነው፡ ይከለክሏቸዋል። ዕውቀት፡ አለንም፡ ብለው፡ ራሳቸው፡ ይዞራል። ውሏቸውም፡ ሥራን፡ ትተው፡ በከርከርና፡ በመግት፡ ብቻ፡ ነው። አገልጋዮች፡ ተብለው፡ በእንደዚህ፡ ያሉት፡ መኳንንት፡ ላይ፡ የሆነ፡ መንግሥት፡ እንደዚህ፡ ባሉ፡ ሩቅ፡ በማያዩ፡ ሰዎች፡ የተመራም፡ ሕዝብ፡ ተያይዞ፡ ያውም፡ በፍጥነት፡ ወደ፡ ገደል፡ መግባት፡ እንደ፡ ሆነ፡ ግን፡ የማይጠረጠር፡ ነገር፡ ነው።

የዛሬው፡ የኢትዮጵያ፡ ሁኔታ፡ ገልጾ፡ ያሳየናል። በዚህ፡ አገር፡ ውስጥ፡ ወዳሉት፡ ከተሞች፡ ወይም፡ ትልልቅ፡ መንደሮች፡ ብንዞር፡ ሕዝቡ፡

የተመቸ፡ ኑሮ፡ እንደ፡ ለመደ፡ ጌትነቱም፡ እየበዛ፡ እንደ፡ ሄደ፡ እናያለን፤ ግን፡ አይሠራም። ወደ፡ ኣገር፡ ቤትም፡ ብንሄድ፡ ባላገሩ፡ ከድኽነት፡ ጋራ፡ ሲታገል፡ እናገኘዋለን። ባንድ፡ ፊት፡ በየከተማው፡ ሥራ፡ ፈተው፡ የሚኖሩትን፡ ሰዎች፡ እመግባለሁ፡ ሲል፡ ይደከማል። ባንድ፡ ፊትም፡ የሚመጣበት፡ ገበያ፡ ሩቅ፡ ስለ፡ ሆነ፡ ባገሩ፡ ቢሠራ፡ ባንድ፡ ጊዜ፡ ያለብዙ፡ ድካም፡ ያገኘው፡ የነበረውን፡ ልብስና፡ የቤት፡ መሣሪያ፡ እገዛለሁ፡ ሲል፡ ስምንት፡ ጊዜ፡ ይደከምበታል፤በዚሁም፡ ጉልበቱ፡ ይባክናል። በመጨረሻም፡ መሬቱ፡ በዕዳ፡ ተይዞ፡ ወደ፡ ሌላ፡ እጅ፡ ያልፋል። ወይም፡ ደግሞ፡ ላንድ፡ ትንሽ፡ ርዳታ፡ ሲል፡ መሬቱን፡ ላንድ፡ ሹም፡ አውርሶ፡ ይሞታል። ልጆቹም፡ የሚቀመጡበት፡ ቦታ፡ አጥተው፡ ቦታም፡ ቢያገኙ፡ የባላገሩን፡ መከራ፡ ጠልተው፡ ወደ፡ ከተማው፡ ይሄዳሉ። ሳይሠሩ፡ የሚበሉትንም፡ ሰዎች፡ ቍጥር፡ ማሳደጊያ፡ ይሆናሉ። ወይም፡ ያንዱ፡ ፈረንጅ፡ አሽከር፡ ሁነው፡ ለራሳቸውም፡ ላገራቸውም፡ ጥቅም፡ ሳይሆኑ፡ ዕድሜያቸውን፡ ሙሉ፡ በከንቱ፡ ያሳልፉታል። እንግዲህም፡ ኣራሹ፡ እያነሰ፡ ባራሹ፡ ድካም፡ የሚመገቡ፡ እየበዙ፡ ይሄዳሉ። በሥርዐት፡ ተከፋፍሎ፡ የነበረውም፡ መሬት፡ በዕዳም፡ በውርስም፡ ሄዶ፡ በጥቂቶች፡ ሰዎች፡ እጅ፡ ይገባል። የመንግሥትንም፡ ሥራ፡ በእጃቸው፡ የጨበጡ፡ እነዚህ፡ ጥቂቶች፡ ሰዎች፡ ስለ፡ ሆኑ፡ በግብር፡ የሚጫናቸው፡ ሰው፡ የለም። መከራው፡ ሁሉ፡ ገና፡ በመሬቱን፡ ባልሸጠ፡ ባላገር፡ ላይ፡ ይወድቃል። ስለዚህም፡ መከራውን፡ ጠልቶ፡ ባላገሩ፡ ሁሉ፡ መሬቱን፡ እየሸጠ፡ ወይም፡ እያወረሰ፡ የነዚህ፡ ጥቂቶች፡ ሰዎች፡ አራሽ፡ መሆን፡ ዝምሯል። መሬቱም፡ ገንዘቡ፡ እንዳልሆነ፡ ያውቃልና፡ ሊያሳምረውና፡ አጥብቆ፡ ሊያርሰው፡ አይተጋም። ጥቂቶች፡ ባለመሬቶችም፡ የያዙት፡ መሬት፡ ብዙና፡ ሰፊ፡ ስለ፡ ሆነ፡ ከየመሬቱ፡ የሚመጣላቸው፡ ጥቂት፡ ትርፍ፡ ተጠራቅሞ፡ በከተማው፡ ተቀምጠው፡ በስንፍና፡ ለሚያሳልፉት፡ ኑሯቸው፡ ይበቃቸዋል። ባይበቃቸውም፡ መሬቱን፡ ገና፡ ያልሸጠውን፡ ወይም፡ ያላወረሰውን፡ ባላገር፡ አስጨንቀው፡ ይዘው፡ ያለደንቡ፡ በጉቦና፡ በማስፈራራት፡ ብዙ፡ ገንዘብ፡ ይበሉበታል። በዚሁም፡ ምክንያት፡ ሌሎቹ፡ ባላገሮች፡ መሬታቸውን፡ ለመልቀቅ፡ የግድ፡ ይሆንባቸዋል።

እንሆ፡ ነገሩን፡ አስተውለን፡ ከተመለከትነው፡ ባገራችን፡ እያንዳንዱ፡ ሰው፡ ብዙ፡ መሬት፡ የያዘ፡ እየጨመረም፡ የሚሄድ፡ ባላገሩም፡ የእርሻን፡

ሥራ፡ ትቶ፡ ሹሞቹን፡ እንደ፡ ውሻ፡ እየተከተለ፡ ሥራ፡ ፈቶ፡ የሚኖር፡ የመንግሥትም፡ ጥቅም፡ እያነሰ፡ የሚሄድ፡ ዋናው፡ ምክንያቱ፡ አራሹ፡ የሚያስፈልገውን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ የሚገዛበት፡ ገበያ፡ ሩቅና፡ በውጭ፡ አገር፡ ስለ፡ ሆነ፡ ነው።

ይህ፡ በሽታ፡ ግን፡ መንግሥት፡ ከተነሣበት፡ ዘንድ፡ መጥፊያውን፡ መድሃኒት፡ በቶሎ፡ ለማግኘት፡ ይሆንለታል።

እስቲ፡ አሁን፡ ድንገት፡ ከውጭ፡ አገር፡ የሚመጣው፡ ልብስ፡ ና፡ ፈትል፡ ቀረጡ፡ ለእንግዲህ፡ ወዲሁ፡ በመቶው፡ ዐሥር፡ ፈንታ፡ ከመቶው፡ አምሳ፡ ይሁን፡ ቢባል፡ ልብሱና፡ ፈትሉ፡ የሚሠራበት፡ መሣሪያና፡ መኪና፡ ግን፡ ያለቀረጥ፡ እንዲገባ፡ ቢፈቀድ፡ የልብስም፡ ፋብሪካ፡ አቆማለሁ፡ የሚሉ፡ የታመኑ፡ ሰዎች፡ ወደዚህ፡ አገር፡ እንዲመጡለት፡ መንግሥት፡ ቢጥር፡ ከመጡለትም፡ በኋላ፡ እንደሚገባ፡ አድርጎ፡ ቢረዳቸው ፥ የጥጥን፡ መሬት፡ ማረሻና፡ መቈፈሪያ፡ መሣሪያ፡ ሁሉ፡ የጥጥም፡ ዘር፡ ያለቀረጥ፡ ገብቶለት፡ ጥጥን፡ ዘርቶ፡ የሚያበቅል፡ ሰው፡ ያበቀለውንም፡ ጥጥ፡ ወደ፡ ውጭ፡ አገር፡ ሊሰድ፡ ካልፈለገ፡ በቀር፡ በግብር፡ እንዳይጐዳ፡ የተደላደለ፡ ደንብ፡ ሲያወጣ። ከዚህ፡ በኋላ፡ የልብስንም፡ ሥራና፡ የጥጥን፡ እርሻ፡ እየሠሩ፡ ሕዝቡን፡ የሚያሠለጥኑ፡ ጥቂት፡ ገንዘብ፡ ባመት፡ ባመቱ፡ ሊሰጥ፡ ሠራተኞች፡ ከናለቆቻቸው፡ መንግሥት፡ ቀጥሮ፡ ከውጭ፡ ነገር፡ ቢያስመጣ፤ከነዚህም፡ ተምረው፡ የሠለጠኑትን፡ የኢትዮጵያን፡ ልጆች፡ ረድቶ፡ ቢያበረታታቸው ፥ ከዚህ፡ በኋላ፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ኑሮ፡ እንዴት፡ እያማረ፡ በሄደ፡ ነበር፤አሁንም፡ ለወደ፡ ፊት፡ እንዲሆን፡ ተስፋ፡ እናደርጋለን።

በመዠመሪያ፡ የልብስ፡ ዋጋ፡ ብዙ፡ ይሆናል። ምንም፡ ቀረጡ፡ ቢያድግ፡ የውጭ፡ አገር፡ ልብስ፡ መምጣቱ፡ አይቀርምና፡ ብዙ፡ ሰው፡ ይጐዳበታል። ከጥቂት፡ ጊዜ፡ በኋላ፡ ግን፡ ልብስን፡ ከውጭ፡ ነገር፡ የሚያመጡ፡ ሰዎች፡ የበለጠ፡ ጥቅም፡ እንዲያገኙ፡ ያውቃሉና፡ በረሓን፡ አቅንተው፡ ጥጥን፡ ለመዝራት ፥ የልብስንም፡ መሥሪያ፡ ፋብሪካ፡ ለማቆም፡ ከኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡ ፈቃድ፡ ይለምናሉ። ቀረጥም፡ የሌለበት፡ ስለ፡ ሆነ፡ በየባላገሩ፡ ቤትም፡ የሚሠራበት፡ የተሻለ፡ የጥጥ፡ መፍተያና፡ የልብስ፡ መሥሪያ፡ መሣሪያ፡ አምጥተው፡ ለባላገሩ፡ ሁሉ፡ ይሸጣሉ።

ቀረጥም፡ ስለሌለው፡ ዋጋው፡ ያንሳልና፡ እንደዚህ፡ ያለውን፡ መሣሪያ፡ ብዙ፡ ሰው፡ ይገዛል። በጊዜም፡ ብዛት፡ የጥጡ፡ እርሻ፡ ይሰፋል። በየባላገሩም፡ ቤት፡ ያሉት፡ ሴቶችም፡ ዱሮ፡ በስንፍና፡ የተዉትን፡ ሥራ፡ ዛሬ፡ ባዲሱ፡ መሣሪያ፡ ተግተው፡ ይሠራሉ። አዲሱም፡ መሣሪያ፡ ከዱሮው፡ እንዝርት፡ እጅግ፡ የበለጠ፡ ስለ፡ ሆነ፡ ሴቶቹም፡ ከዱሮው፡ በጣም፡ አብልጠው፡ ይፈትላሉ። ሸማኔውም፡ ከጥንቱ፡ የተሻለ፡ መን፡ ከኤሮፓ፡ መጥቶለት፡ ከዱሮው፡ አብልጦ፡ በትጋት፡ ይሠራል።

በከተማውም፡ የሚቆመው፡ የልብስ፡ ፋብሪካ፡ በየቀኑ፡ ልዩ፡ ልዩ፡ የሆነ፡ ብዙ፡ ልብስ፡ ይሠራል። በዚሁም፡ ለባላገሩ፡ የሚያስፈልገው፡ ልብስ፡ ካጠገቡ፡ ይሠራለታልና፡ የተሳላኪው፡ ነጋዴ፡ ደመወዝ፡ ስለ፡ ቀረ፡ ባላገሩ፡ ልብሱን፡ እንደ፡ ድካሙ፡ መጠን፡ በቅርቡ፡ ያገኛል። ስለዚህም፡ ለርሱና፡ ስልጆቹ፡ ትርፍ፡ ልብስ፡ እገዛለሁ፡ ሲል፡ በብዙ፡ ያርሳል። ሸማኔውም፡ ብዙ፡ እኽል፡ ሲፈልግ፡ እንደ፡ ድካሙ፡ መጠን፡ በቅርብ፡ ያገኛል። ገዢም፡ ኣጠገቡ፡ ስላገኘ፡ በመፍጠን፡ ብዙ፡ ሸማ፡ ይሠራል። ከዚህም፡ አጠገብ፡ ሳጠገብ፡ ሆኖ፡ መተባበር፡ የተነሣ፡ ሸማኔው፡ ለሸማው፡ ብዙ፡ እኽል አራሹም፡ ለእኽሉ፡ ብዙ፡ ሸማ፡ ያገኛል። አራሹም፡ ዱሮ፡ የሚያስፈልገው፡ ሸማ፡ የሚመጣለት፡ ከሩቅ፡ ስለ፡ ነበረ፡ ባንድ፡ ጊዜ፡ ድካም፡ የሚገኘውን፡ ሸማ፡ ለመግዛት፡ ስምንት፡ ጊዜ፡ ሲደክም፡ ነበረ። ሸማኔው፡ አጠገቡ፡ ከሆነ፡ ወዲያ፡ ግን፡ ዱሮ፡ በከንቱ፡ ለተላላኪው፡ ነጋዴ፡ ደመወዝ፡ ሲባክን፡ የነበረው፡ ድካም፡ ትርፉ፡ ነው። ስለዚህም፡ ምንም፡ እንኳ፡ የሚከፍለው፡ ግብር፡ ከዱሮ፡ ባይቀልለት፡ የሸማው፡ ዋጋ፡ ከዱሮው፡ ይልቅ፡ ያንስለታልና፤ሚዛን፡ ይሆናል። መሬቱንም፡ ለዕዳ፡ አሳልፎ፡ ለመስጠት፡ ወይም፡ ስለ፡ ጥቂት፡ ርዳታ፡ ሲል፡ ለማውረስ፡ እንደ፡ ዱሮ፡ አይቸኩልበትም። ሥራው፡ ሁሉ፡ ተቃሎለታል፤ዕዳውንም፡ ዱሮ፡ ለሸማ፡ ሊሰጠው፡ በነበረ፡ ትርፍ፡ ይከፍለዋል። ነገርም፡ ሲያገኘው፡ በዚሁ፡ በትርፉ፡ ጠበቃ፡ ይገዛል። ይልቁንም፡ ባገሩ፡ ውስጥ፡ ሥራ፡ ሲበዛ፡ ሕዝቡም፡ ጭቅጭቅንና፡ ነገርን፡ ይጠላል። ማለት፡ ጭቅጭቅና፡ ጦር፡ ቅሚያ፡ የሚበዛው፡ በሥራ፡ ባልሠለጠኑ፡ ሕዝቦች፡ ውስጥ፡ ነውና፤ሕዝቡም፡ ሲሠለጥን፡ የሹሞቹን፡ ርዳታና፡ ቸርነት፡ የሚፈልግበት፡ ምክንያት፡ ሁሉ፡ ያንሳል። ስለዚህም፡ ባላገሩ፡ እርሻውን፡ ለቆ፡ ወደ፡ ከተማው፡ ለመሄድ፡ እንደ፡ ዱሮው፡

የማያስፈልገው፡ ይሆናል። ከታኅሣሥ፡ ፳፫፡ ቀን፡ ፲፱፻፫፡ ዓመተ፡ ምሕረት፡ ዝምሮ፡ እስከ፡ ታኅሣሥ፡ ፳፬፡ ቀን፡ ፲፱፻፬፡ ዓመተ፡ ምሕረት፡ ድረስ፡ ከውጭ፡ አገር፡ የገዛነው፡ ልብስ፡ ዋጋው፡ ቢታሰብ፡ ፬፡ ሚሊዎን፡ ፬፻፲፪ሺ፡ ፻፫፡ ብር፡ ሆነ።

ልብስ፡ ባገራችን፡ ውስጥ፡ የሚሠራ፡ ቢሆን፡ ይህ፡ ገንዘብ፡ ወደ፡ ውጭ፡ አገር፡ አይሄድብንም፡ ነበር። ወዲያውም፡ ልብስ፡ ሁሉ፡ ባገራችን፡ ውስጥ፡ ሥራ፡ ገበያው፡ ይቀርብ፡ ነበርና፤ሕዝቡ፡ ይህን፡ ያኸል፡ ዋጋ፡ ባልፈጀበት፡ ነበር። ሌላም፡ ነገር፡ ሁሉ፡ እንደ፡ ልብሱ፡ ባገራችን፡ ውስጥ፡ እንዲሠራ ፥ የሚሠራበት፡ መሣሪያ፡ ሁሉ፡ ያለቀረጥ፡ እንዲገባ፡ ዕቃው፡ በውጭ፡ ነገር፡ ተሠርቶ፡ ሲመጣ፡ ግን፡ ከፍ፡ ያለ፡ ቀረጥ፡ ቢያደርጉበት፡ ከውጭ፡ ነገር፡ የሚመጣ፡ የተሠራ፡ ዕቃ፡ ሁሉ፡ ተወዶ፡ ባገራችን፡ ውስጥ፡ ሥራ፡ ይዠመር፡ ነበር። ሥራውም፡ እየተለመደ፡ ይሄዳል፤ዕቃውም፡ ለጊዜው፡ ቢወደድ፡ ሕዝቡ፡ በሥራው፡ ሲሠለጥንበት፡ እያደረ፡ ይረክሳል። የሠሩትንም፡ ዕቃ፡ የሚለዋወጡ፡ ሠራተኞች፡ አጠገብ፡ ላጠገብ፡ ስለ፡ ሆኑ፡ በከንቱ፡ ትርፍ፡ ድካም፡ አይሄድባቸውምና፡ እንደየሥራቸው፡ መጠን፡ ይለዋወጣሉ። የሚፈልጉትንም፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ያለብዙ፡ ድካም፡ ለማግኘት፡ ሲሆንላቸው፡ በየሥራቸው፡ እየተጉ፡ በመካከላቸውም፡ ጠብ፡ እያነሰ፡ ይሄዳል። በጠቡም፡ ፈንታ፡ ስምምና፡ ዕውቀት፡ ደስታም፡ ይገባል። ከስምምነቱም፡ የተነሣ፡ ሕዝቡ፡ ተባብሮ፡ ይመከታልና፡ ሹሞችና፡ ወታደሮች፡ የሕዝቡ፡ አለቆች፡ መሆናቸው፡ ቀርቶ፡ የሕዝቡ፡ ሎሌዎች፡ ይሆናሉ። ባላገሩም፡ እንዳይጠቃ፡ ታውቆት፡ ሹምና፡ ወታደር፡ ሁኜ፡ ልብላ፡ አይልም። መሬቱንም፡ ሸጦ፡ ወይም፡ ለሹም፡ አውርሶ፡ ወደ፡ ከተማ፡ ለመሄድ፡ አያስብም። የሚሸጥበትና፡ የሚገዛበት፡ ገበያ፡ አጠገቡ፡ ስለ፡ ሆነ፡ ዱሮ፡ ለነጋዴው፡ ሊሰጠው፡ በነበረው፡ ትርፍ፡ ድካም፡ ዕዳ፡ እንካ፡ ቢኖርበት፡ ይከፍላል። ከዱሮውም፡ ይልቅ፡ በሥራው፡ ሁሉ፡ ትርፍ፡ ስላገኘ፡ የመንግሥትም፡ ግብር፡ ቢበዛበት፡ እንደ፡ ዱሮው፡ አይጫነውም፤የሚከፍለውን፡ አያጣምና። እንደዚህም፡ ዕቃ፡ ሁሉ፡ ባገሩ፡ ሲሠራ፡ መንግሥትም፡ የሚያስፈልገውን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ከውጭ፡ ነገር፡ ማስመጣቱን፡ ጥሎ፡ ከገዛ፡ ገባሮቹ፡ ይገዛቸዋል። የመንግሥትም፡ ሹማምትና፡ ሠራተኞች፡ ለኑሯቸው፡ የሚያስፈልጋቸውን፡ ነገር፡ ሁሉ፡

ከገዛ፡ አገራቸው፡ ውስጥ፡ ይገዛሉ። ከሕዝብ፡ የሚሰበሰበው፡ የግብር፡ ገንዘብ፡ ተመልሶ፡ የሕዝቡ፡ መትጊያ፡ ይሆናል።

እስቲ፡ ኣሁን፡ ማንኛውንም፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ራሱ፡ መሥራት፡ በሚችል፡ አገር፡ ውስጥ፡ አንድ፡ መንገድ፡ ቢሠራ፡ ስንት፡ ሰዎች፡ በሥራቸው፡ በተጉ። ብረት፡ ሠሪዎች፡ ዶማንና፡ ድጅኖን፡ እንሸጣለን፡ ሲሉ ፥ አናጢዎችም፡ ያፈር፡ ማመላለሻውን፡ ጋሪ፡ እንሠራለን፡ ሲሉ፡ ሸማኔውም፡ የሠራተኞቹን፡ ልብስ፡ ሲሠራና፡ ሲሸጥ፤እረኛውም፡ ለሠራተኞች፡ የብርድና፡ የዝናብ፡ ልብስ፡ የሚሆነውን፡ የበግ፡ ጠጕር፡ ሲቈርጥ፤ማለት፡ ሕዝቡ፡ በሠለጠነ፡ አገር፡ ውስጥ፡ መንገድ፡ ቢሠራ፡ ብዙ፡ አእላፋት፡ ሰዎች፡ በየሥራቸው፡ ይተጋሉ። ሠራተኞችንም፡ ሁሉ፡ የሚመግብ፡ አራሹ፡ ነውና፤ትርፉን፡ ሲፈልግ፡ ይተጋል። ባለርስትም፡ በመሬቱ፡ ይኮራል፤ከርስቱም፡ የበለጠ፡ እኽል፡ እንዲገባለት፡ በጣም፡ ይጥራል።

እንሆም፡ በዚሁ፡ ጥረቱ፡ ባጠገቡ፡ ያሉት፡ በያይነቱ፡ ሥራ፡ የሚሠሩ፡ ሠራተኞች፡ በጥቂት፡ ዋጋ፡ ይረዱታል። ፍሬያማውም፡ መሬት፡ ከጐርፍ፡ ጋራ፡ እየተነዳ፡ እንዳይሄድ፡ ረግረግም፡ እንዳይሆን፡ ብልኀት፡ ይበጅበታል። እኽሉንና፡ በሬውን፡ ቆዳውንም፡ የሚሸጥበት፡ ገበያ፡ ቅርብ፡ ስለ፡ ሆነ፡ ፍጉ፡ በዐረብያና፡ በምድር፡ ባቡር፡ በጥቂት፡ ድካም፡ ይመላለስለታል። መሬቱም፡ ያበደረው፡ እኽልና፡ ሣር፡ በቶሎ፡ ስለ፡ ተመለሰለት፡ ሁለተኛ፡ ለመስጠት፡ ይቸኩላል፡ እንጂ፤አይለግምም። ይልቍንም፡ በዕውቀት፡ ከያዙትና፡ ብዙ፡ ፍግም፡ ከሰጡት፡ ከዱሮው፡ ይልቅ፡ ብዙ፡ እኽል፡ ያበቅላል። በዚህም፡ ምክንያት፡ የመሬቱ፡ ጌታ፡ በያመቱ፡ እየከበረ፡ ይሄዳል። ዱሮ፡ አባቶቹ፡ በዕዳ፡ ተይዘው፡ ወይም፡ ለሹም፡ አውርሰው፡ እንደ፡ ሆነ፡ የተነቀለውም፡ ሰው፡ ሁሉ፡ የእጅ፡ ሥራ፡ ተምሮ፡ ሠርቶ፡ ባገኘው፡ ትርፍ፡ እንደ፡ ገና፡ መሬት፡ ለመግዛት፡ ይጣጣራል። እነዚያም፡ ያላቅማቸው፡ ብዙ፡ መሬት፡ የያዙት፡ ሰዎች፡ ከመሬታቸው፡ ከፍለው፡ ይሸጡለታል። በዚሁም፡ ባገር፡ ውስጥ፡ ያለው፡ ቦታና፡ መሬት፡ ከጥቂት፡ ሰዎች፡ ወጥቶ፡ እንደ፡ ገና፡ ይከፋፈላል። እያንዳንዱም፡ አራሽ፡ የሚያርሰው፡ መሬት፡ ገንዘቡና፡ ርስቱ። እንደ፡ ሆነ፡ በጣም፡ ይታወቃል። እንዲሻሻልለትና፡ እንዲያምርለት፡ ባለው፡ ጕልበቱ፡ ይተጋበታል። በዚሁም፡ ትጋቱ፡ ለራሱና፡ ላገሩ፡ ትርፍ፡ ያገባል።

እንሆ፡ መሬት፡ በጥቂቶች፡ ሰዎች፡ እጅ፡ ሲገባ፡ ላገሩ፡ ክፉ፡ ምልክት፡ ነው። ሕዝቡ፡ እንደ፡ ደኸየና፡ የመንግሥቱ፡ ኀይል፡ እያነሰ፡ እንደ፡ ሄደ፡ ይመሰክራል። መሬቱ፡ ተከፋፍሎ፡ በብዙ፡ ሰዎች፡ እጅ፡ የሆነ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ግን፡ የሕዝቡን፡ ሀብትና፡ የመንግሥቱን፡ ኃይል፡ ያመለክታል። ይህ፡ ስለ፡ ተባለ፡ ግን፡ መሬት፡ አይሸጥ፡ አይለወጥ፡ ተብሎ፡ ቢታወጅ፡ ለሕዝቡ፡ የበለጠ፡ ጉዳት፡ ይሆንበታል። ባላገሩ፡ ያለው፡ ገንዘቡ፡ መሬቱ፡ ብቻ፡ ነውና፤ይህነንም፡ ያለውን፡ ገንዘቡን፡ እንደ፡ ልቡ፡ ካልሸጠ፡ ካለወጠ፡ ገንዘቤ፡ ነው፡ የሚለውን፡ ነገር፡ ፈጽሞ፡ ያጣል። በዕዳም፡ ቢያዝ፡ እጁን፡ የሚያወጣበት፡ ነገር፡ አያገኝም።

ግብርም፡ ሲበዛበት፡ እንዳይሸጥ፡ ስለ፡ ተከለከለ፡ ለሌላ፡ ለሚያርስ፡ ሰውም፡ ሳያስረክብ፡ መሬቱን፡ ባዶውን፡ ትቶት፡ ይሰደዳል። መሬቱም፡ የሚያርሰውና፡ የሚጠብቀው፡ ሰው፡ አጥቶ፡ ቈይቶ፡ ከተበላሸ፡ በኋላ፡ መንግሥት፡ ለሌላው፡ ሰው፡ ቢፈቅድለት፡ እንኳ፡ እንደ፡ ፈቃዴ፡ ልሸጠውና፡ ልለውጠው፡ የማልችለው፡ መሬት፡ ምን፡ ይጠቅመኛል፡ ሲል፡ ደስ፡ ብሎት፡ አያቀናውም። ምናልባት፡ እንኳ፡ ለእርሻ፡ ማትጊያና፡ ርዳታ፡ ተብለው፡ ባንኮች፡ ቢቆሙ፡ ወይም፡ ማናቸውም፡ ሌላ፡ ዐይነት፡ አበዳሪዎች፡ ቢተባበሩ፡ ባላገሩ፡ ከርስቱ፡ እንዲነቀል፡ ለማፋጠን፡ ነው፡ እንጂ፤ዛሬ፡ ኣይጠቅሙትም። እስቲ፡ አሁን፡ ባገራችን፡ ከባንክ፡ የተበደረ፡ ባለርስት፡ ሁሉ፡ ከመሬቱ፡ ሳይነቀል፡ ወይም፡ መሬቱን፡ ለዋሱ፡ ወይም፡ ለሌላ፡ ሰው፡ ሳይሸጥ፡ ብድሩን፡ የመለሰ፡ ከመቶ፡ ስንት፡ ይገኛል። ለዚሁም፡ ቃል፡ አንዳንዱ፡ ሰው፡ እንዲህ፡ ብሎ፡ ይመልስ፡ ይሆናል። ዛሬ፡ በኢትዮጵያ፡ አገር፡ ያለው፡ ባንክ፡ ለባለርስቱ፡ ሲያበድር፡ ገንዘቡን፡ የሚመልስበት፡ ጊዜ፡ ያጥርበታልና፡ ባላገሩ፡ መሬቱን፡ ሳይሸጥ፡ ብድሩን፡ ለመመለስ፡ አይሆንለትም። ለዚህ፡ መልስ፡ ግን፡ መሠረት፡ የለውም። ለብድሩ፡ መመለሻ፡ ብዙ፡ ጊዜ፡ ቢሰጡት፡ ግን፡ በጥቂት፡ በጥቂቱ፡ ሲል፡ ስመመለስ፡ ኣያቅተውም፡ ነበር። ባንኮቹም፡ ለባለርስቱ፡ ዐሥር፡ ወይም፡ ኻያ፡ ዓመትም፡ ጊዜ፡ ቢሰጡት፡ ያው፡ ነውና፤ለባላገሩ፡ አንዳች፡ ጥቅም፡ አይሆነውም። ባላገር፡ የሚበደር፡ ከመሬቱ፡ በሚያገኘው፡ ትርፍ፡ ለምግቡ፡ ያኸል፡ አስቀርቶ፡ ነው። ነገር፡ ግን፡ የሚያስፈልገው፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ባጠገቡ፡ ተሠርቶ፡ ቢሆን፡ ድካሙ፡ ጥቂት፡ ይሆን፡ የነበረው፡ የሚመጣው፡ ከሩቅ፡ አገር፡ ስለ፡ ሆነ፡ የስምንት፡ ጊዜ፡ ድካም፡ ሲፈጅበት፡

ጊዜ፡ ደክሞ፡ ለራሱ፡ የሚቀርለት፡ ትርፍ፡ ምንድነው። ከዚህ፡ በኋላ፡ ደግሞ፡ መከራ፡ ይጫነዋል። መንግሥትም፡ በባላገር፡ ውስጥ፡ ካሉት፡ ሠራተኞች፡ የሚያስፈልገውን፡ ዕቃ፡ ሁሉ፡ የሚገዛ፡ ቢሆን፡ ዕቃውን፡ የሚሸጡለት፡ ሠራተኞች፡ የሚያስፈልጋቸውን፡ ምግባቸውን፡ የሚገዙት፡ ከባላገሩ፡ ነበርና፡ ያ፡ ግብር፡ ሆኖ፡ ከባላገሩ፡ እጅ፡ የወጣው፡ ገንዘብ፡ እንደ፡ ገና፡ ይመለስለት፡ ነበር፤ዳሩ፡ ግን፡ ነገሩ፡ ገና፡ እንደዚህ፡ አልሆነም።

ባላገሩ፡ ዛሬ፡ ሲገብር፡ ዕንጨት፡ ሰብሮ፡ እኽል፡ ጭኖ፡ ወይም፡ ቤት፡ ሠርቶ፡ ወይም፡ ደግሞ፡ ዐሥራት፡ አፍሶ፡ ነው። በጕልበቱ፡ የሚገብረው፡ ግብር፡ መቼም፡ ሲገበር፡ ወዲያው፡ ያልቃል። በእኽሉም፡ የገበረውን፡ ግብር፡ ሥራ፡ የማይሠሩ፡ ሰዎች፡ በከንቱ፡ ይመገቡታል። ማለት፡ እንደ፡ መዠመሪያው፡ ዐይነት፡ ግብር፡ በከንቱ፡ ይባክናል። ሦስተኛውም፡ ዐይነት፡ ግብሩ፡ ብር፡ ነው። ይህ፡ ብር፡ የሆነ፡ ግብር፡ ግን፡ ለሱ፡ አይመስስለትም። መርፌ፡ ምስማር፡ ቢላዎ፡ መጥረቢያ፡ ዶማ፡ ጕራዴ፡ ጠመንዣ፡ ሱሪ፡ ቀሚስ፡ ካባ፡ ባርሜጣ፡ ምንጣፍ፡ መጋረጃ፡ ወንበር፡ አልጋ፡ ሌላውንም፡ ምናምንቴ፡ ዐይነት፡ ዕቃ፡ ሁሉ፡ ለሚያመጡ፡ ነጋዴዎች፡ ከባሕር፡ ማዶ፡ ሆነው፡ ለሚሠሩት፡ ይራተኞች፡ ይሄዳል። እነዚህ፡ ሠራተኞችና፡ ነጋዴዎች፡ ግን፡ ከጥቂቶቹ፡ በቀር፡ የሚበዙቱ፡ ምግባቸውን፡ የሚገዙት፡ ካገራችን፡ ባላገር፡ አይደለም፤ካገራቸው፡ የሚመጣውን፡ ነው፡ እንጂ።

እንሆ፡ የኢትዮጵያ፡ ባላገር፡ የተጐዳው፡ በሁለት፡ ፊት፡ ነው። መዠመሪያ፡ የሚያስፈልገውን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ እገዛለሁ፡ ሲል፡ ትርፍ፡ ድካም፡ በከንቱ፡ ይሄድበታል። ለመንግሥትም፡ የሚከፍለው፡ ግብር፡ ግማሹ፡ በከንቱ፡ ይባክናል ፥ ግማሽም፡ ለውጭ፡ አገር፡ ሰዎች፡ ጥቅም፡ ነውና፤መትጊያ፡ አይሆነውም። እንግዲህ፡ የኢትዮጵያ፡ ገበሬ፡ ትርፉ፡ ምን፡ ይሆን፤ከወዴትስ፡ ይምጣ። ለዚሁ፡ መሞገቻ፡ ግን፡ ኣንዱ፡ እንዲህ፡ ይል፡ ይሆናል፤እኽል፡ ከዱሮ፡ ይልቅ፡ አሁን፡ ተወደደ፤እኽሉን፡ እየሸመተ፡ ብድሩን፡ መመለስ፡ ምን፡ ያቅተዋል። እንግዲህ፡ የሚመልስ፡ ሰው፡ ግን፡ የሚያስተውል፡ ሰው፡ ነው።

ዛሬ፡ እኽል፡ የተወደደበት፡ ሁለት፡ ምነ፡ አለው፤መዠመሪያ፡ የባላገሩ፡ ቤተ፡ ሰብ፡ እየበዛ፡ ሄደ።

ሁለተኛ፡ ገበሬዎቹ፡ ደኅና፡ መሣሪያና፡ የሚበቃ፡ ዕውቀት፡ የሌላቸው፡ ስለ፡ ሆኑ፤መሬታቸው፡ እያረጀ፡ የሚሰጣቸው፡ ፍሬ፡ የዱሮውን፡ አያኽልምና፡ ከምግባቸው፡ ተርፎ፡ ሊሸጥ፡ ወደ፡ ገበያ፡ የሚሄድ፡ እኽል፡ ጥቂት፡ ነውና፤ለሸማቾቹ፡ ስላልበቃቸው፡ የእኽል፡ ዋጋ፡ እየተወደደ፡ ሄደ። እንግዲህ፡ ባላገሩ፡ ዱሮ፡ ከምግቡ፡ የሚተርፈው፡ ሁለት፡ ዳውላ፡ ስለ፡ ነበረ፡ በሁለቱ፡ ዳውላ፡ ያገኘው፡ ትርፍ፡ ፳፡ ብር፡ ሲሆን፡ በኋላ፡ ደግሞ፡ ከምግቡ፡ የሚተርፈው፡ ፬፡ ቀና፡ ስለ፡ ሆነ፡ ባራቱ፡ ቊና፡ አንድ፡ ብር፡ ቢያገኝበት፡ ከዱሮው፡ ይልቅ፡ ያገኘው፡ ትርፍ፡ ምን፡ ይሆን፡ እውነት፡ ነው፤እንደ፡ ዱሮው፡ ከምግቡ፡ ሁለት፡ ዳውላ፡ ቀርቶት፡ ቢሆን፡ ሁለቱ፡ ዳውላ፡ አምስት፡ ብር፡ ቢያወጣለት፡ ኑሮ፡ ከዱሮው፡ ይልቅ፡ ኣራት፡ ብር፡ ትርፍ፡ አገኘ፡ ለመባል፡ ይቻል፡ ነበረ። ዛሬ፡ ከምግቡ፡ የሚቀረው፡ አራት፡ ቀና፡ ብቻ፡ ስለ፡ ሆነ፡ ግን፡ የሚያገኘው፡ ትርፍ፡ እንደ፡ ዱሮው፡ አንድ፡ ብር፡ ብቻ፡ ነው። ስለዚህም፡ እኽሉ፡ በገበያ፡ ስለ፡ ተወደደ፡ ባላገር፡ አንድም፡ ትርፍ፡ አያቱኝበትምና፡ የተበደረውን፡ ብድር፡ ለመክፈል፡ ጒልበት፡ ኣያገኝም።

ተከራካሪው፡ አንባቢ፡ ግን፡ ደግሞም፡ እንደዚህ፡ ይል፡ ይሆናል። ዛሬ፡ ብር፡ የሚገኘው፡ በባላገር፡ ቤት፡ ነው። ትርፍ፡ ካላገኘ፡ በምን፡ ምክንያት፡ ብር፡ አገኘ። አንዳንድ፡ ሰዎች፡ መሬታቸው፡ ሰፊ፡ ሆኖ፡ ቤተ፡ ሰቦቹ፡ ጥቂቶች፡ ስለ፡ ሆኑ፡ ብዙ፡ ብር፡ ቢያገኙ፡ ባሁኑ፡ ሒሳባችን፡ አይገባም። አሁን፡ እኛ፡ የምንመራመረው፡ የያንዳንዱን፡ ሰው፡ ጥቅም፡ አይደለም፤የመላውን፡ ሕዝብ፡ ጥቅም፡ ነው፡ እንጂ። ኻያ፡ ቀላድ፡ ያለው፡ ሰው፡ ከኻያው፡ ቀሳዱ፡ ፫፻፡ ብር፡ ባመት፡ ቢያገኝ፡ ካምስቱ፡ መቶ፡ ደግሞ፡ ሦስቱን፡ መቶ፡ ብር፡ ላመት፡ ምግቡ፡ አስቀርቶ፡ ሁለቱን፡ መቶ፡ ብር፡ ወደ፡ ባንክ፡ ቢያገባ፡ ትርፍ፡ አግኝቷል፡ ብለን፡ በዚህ፡ ባሁኑ፡ ሒሳባችን፡ አናገባውም። እኛ፡ የምናገባው፡ ሒሳብ፡ ከያንዳንዱ፡ ቀላድ፡ ባመት፡ ፳፭፡ ብር፡ ማግኘቱን፡ ነው።

እንሆም፡ የሚበዛው፡ ባላገር፡ አንድ፡ ሙሉ፡ ቀላድ፡ ወይም፡ እኩሌታ፡ ቀላድ፡ ብቻ፡ ነው፡ እንጂ፡ ብዙ፡ ቀላድ፡ የለውም። በዛሬውም፡ መሣሪያው፡ አንድ፡ ቀላድ፡ አርሶ፡ ከምግቡና፡ ከልብሱ፡ የሚቀረው፡ ትርፍ፡ ጥቂት፡ ነው። ማለት፡ ቀላዱን፡ ብቻውን፡ ሁኖ፡ ቢያርሰው፡ ጨርሶ፡ በመላው፡ ሊያርሰው፡ አይችልም። ሌላ፡ ገበሬም፡ ቢጨምር፡

ገበሬውም፡ ምግብና፡ ልብስ፡ ይፈልጋል። ስለዚህም፡ ባለመሬቱ፡ የሚያገኘው፡ ትርፍ፡ ጥቂት፡ ነው።

አንባቢው፡ ግን፡ ይህንን፡ ነገር፡ አሁንም፡ ቢሆን፡ በጣም፡ ያልተረዳው፡ እንደ፡ ሆነ፡ እንዲህ፡ ይላል። ካንዱ፡ ቀላድ፡ ከዱሮው፡ ይልቅ፡ እኽል፡ አለማግኘቱ፡ ባላገሩ፡ ደኅና፡ መሣሪያ፡ በማጣቱ፡ ነውና፤ ባንክ፡ የሚያበድረው፡ ባላገሩ፡ የተሻለ፡ መሣሪያ፡ ገዝቶ፡ ብዙ፡ እኽል፡ ከመሬቱ፡ አግብቶ፡ የሚበቃቸውን፡ ያኽል፡ በኢትዮጵያ፡ ለሚኖሩ፡ ሸማቾች፡ ሸምቶ፡ ከነዚህም፡ ሸማቾች፡ የተረፈውን፡ ወደ፡ ውጭ፡ አገር፡ በባቡር፡ ሰዶ፡ እንዲሸምተው፡ ነው፤ይህ፡ ቃል፡ ግን፡ ሲናገሩት፡ ያምራል፤ ነገር፡ ግን፡ አጥብቀን፡ ከመረመርነው፡ ዘንድ፡ መሠረት፡ አልባ፡ ሆኖ፡ እናገኘዋለን። ከሁሉ፡ ነገር፡ በፊት፡ አንድ፡ የማይጠረጠር፡ ቃል፡ እናጥና፤ ቃሉም፡ ይህ፡ ነው። በየሥራው፡ ባልሠለጠነ፡ ሕዝብ፡ ውስጥ፡ አራሹ፡ ለብቻው፡ ተለይቶ፡ ሊሠለጥን፡ አይችልም። ነገር፡ ግን፡ ደግሞ፡ ቢሻው፡ እስቲ፡ የሚችል፡ ይሁን። ግን፡ አራሹ፡ ለብቻው፡ ተለይቶ፡ በሥራው፡ ቢሠለጥንም፡ አንዳች፡ ጥቅም፡ አያገኝበትም። ምክንያቱ፡ ምን፡ ይሆን፤ዛሬ፡ እኽሉ፡ የተወደደው፡ ስለ፡ ታጣ፡ ነው፤የገበሬው፡ ቍጥር፡ እየበዛ፡ ሄዶ፡ አይደለም። ስለዚህም፡ አርሶ፡ ካገባው፡ እኽል፡ ለምግቡ፡ የሚተርፈው፡ ጥቂት፡ ነው። አሁን፡ ግን፡ ድንገት፡ ደኅና፡ የእርሻ፡ መሣሪያ፡ ወጥቶ፡ ባላገሩም፡ ባዲሱ፡ መሣሪያ፡ ቢያርስ፡ ከያንዳንዱ፡ ቀላድ፡ ብዙ፡ እኽል፡ ሊያገኝ፡ ይችላል። ባላገሩም፡ ከምግቡ፡ የሚተርፈው፡ ብዙ፡ ይሆናል፤ የተረፈውንም፡ በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ሸማቾች፡ የማይጨርሱት፡ ይሆናል። ከዚያም፡ በኋላ፡ ለገበሬው፡ ቀጥለው፡ ከተጻፉት፡ ሁለት፡ መንገዶች፡ አንዳቸውን፡ መምረጥ፡ የግድ፡ ይሆንበታል።

አንደኛ፤ከምግቡና፡ ከሸማቾች፡ ምግብ፡ የሚተርፈው፡ እኽል፡ በከንቱ፡ እንዳይነቅዝበት፡ ፈርቶ፡ እኽሉን፡ ሁሉ፡ ወደ፡ ገበያ፡ ሊያወጣው፡ ነውና፤እኽሉ፡ ይረክሳል። ማለት፡ ዱሮ፡ ባራት፡ ቍና፡ ፩፡ ብር፡ ሲያገኝ፡ ኑሮ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ያገባውም፡ እኽል፡ ከዱሮው፡ ሦስት፡ እጅ፡ በልጦ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ፩፡ ብር፡ የሚያገኘው፡ ፲፪፡ ቀና፡ ሰጥቶ፡ ነው።

ሁለተኛ፤ከምግቡና፡ ከሸማቾቹ። ምግብ፡ የሚተርፈውን፡ እኽል፡ ወደ፡ ውጭ፡ አገር፡ የሰደደ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ግን፡ እኽሉ፡ የሚሄድበት፡ ገበያ፡ ሩቅ፡ ነውና፡ ይዘውት፡ የሚሄዱት፡ ተላላኪዎች፡ ነጋዴዎች፡ ሊያተርፉበት፡

ከፈለጉ፡ እኽሉን፡ የሚሸምቱት፡ በጥቂት፡ ዋጋ፡ ይሆናል። ማናቸውም፡ ዕቃውን፡ ወደ፡ ውጭ፡ ኣገር፡ የሚሰድ፡ ሰው፡ የመልከተኛውንና፡ የጫኙን፡ ደመወዝ፡ መክፈሉ፡ የታወቀ፡ ነገር፡ ነው።

ስለዚህም፡ የኢትዮጵያ፡ ባላገር፡ እኽሉን፡ ወደ፡ ኤሮፓ፡ አገር፡ ቢሰድ፡ ከድካሙ፡ ከፍሎ፡ ያውም፡ የሚበልጠውን፡ ክፍል፡ ለተላላኪዎችና፡ ለነጋዴዎች፡ መስጠት፡ የግድ፡ አለበት። የድካሙን፡ ሙሉ፡ ዋጋ፡ ካላገኘ፡ ዕዳውን፡ ለመክፈል፡ አይቻለውም። ስለዚህም፡ ባላገሩ፡ በተበደረው፡ ገንዘብ፡ የተሻለ፡ መሣሪያ፡ ቢገዛ፡ ትርፉ፡ ለሱ፡ አይደለም፤ለውጭ፡ ኣገር፡ ነው፡ እንጂ። የዕዳውም፡ መክፈያ፡ ቀን፡ ሲደርስ፡ መሬቱን፡ ለመሸጥ፡ ይሰናዳል። ወይም፡ መሬቱን፡ አሳልፎ፡ ለባለዕዳው፡ ይሰጣል። ከዚህም፡ ምክንያት፡ የተነሣ፡ ያ፡ ለመንግሥት፡ ትልቅ፡ ጉዳት፡ ይሆንበታል፡ ያልነው፡ ነገር፡ ይደርሳል። ማለት፡ ባገሩ፡ ውስጥ፡ ያለው፡ የእርሻ፡ መሬት፡ በጥቂቶች፡ ሰዎች፡ እጅ፡ ይጠቀለላል።

ነገር፡ ግን፡ ለዚህም፡ ቃል፡ ቢሆን፡ መከራከሪያ፡ መልስ፡ አይታጣበትም፤ይባልም፡ ይሆናል። ስለ፡ ምንድነው፡ እንግዲያው፡ በየነገሥታቱ፡ አገር፡ ብንሄድ፡ ከመሬታቸው፡ ያገቡትን፡ እኽል፡ ወደ፡ ውጭ፡ አገር፡ ሰደው፡ እያቀኑ፡ ትልልቅ፡ ሀብት፡ የሰበሰቡ፤ይኸው፡ በዚህ፡ የከበሩ፡ ሰዎች፡ በአሜሪካ፡ በመስኮብ፡ በሩማንያ፡ ብዙ፡ አይደሉምን፤ ደግሞም፡ ወደ፡ ውጭ፡ አገር፡ እየሰደዱ፡ የበለጸጉበት፡ ከነሱ፡ አገር፡ የተገኘውን፡ እኽል፡ ብቻ፡ አይደለም። የሕዝብን፡ አስተዳደር፡ የማያውቁ፡ ሰዎች፡ ካልሆኑ፡ በቀር፡ እናውቃለን፡ የሚሉ፡ ሰዎች፡ በዚህ፡ ነገር፡ አይረቱም። የማይረቱበትንም፡ ምክንያት፡ ቀጥሎ፡ የተጻፈው፡ ምሳሌ፡ ያሳየናል።

እንሆ፡ አንድ፡ ሰው፡ ፫፻፡ ጋሻ፡ መሬት፡ ቢኖረው፡ ከያንዳንዱ፡ ጋሻ፡ መሬቱም፡ ፪፻፡ ዳውላ፡ እኽል፡ ቢያገኝ። እንግዲህ፡ ካምስቱ፡ መቶ፡ ጋሻ፡ መሬት፡ ላይ፡ የሚያገኘው፡ እኽል፡ በድምር፡ መቶ፡ ሺሕ፡ ውላ፡ እኽል፡ መሆኑ፡ ነው። አንዳንዱም፡ ዳውላ፡ እኽል፡ ፩፡ ብር፡ ቢያወጣለት፡ የመቶው፡ ሺ፡ ዳውላ፡ እኽል፡ ዋጋ፡ ፪ሺ፡ ብር፡ መሆኑ፡ ነው። ከዚህም፡ እኩሌታውን፡ ለገበሬዎቹ፡ ልብስና፡ ቀለብ፡ ቢያወጣለት፡ ለርሱ፡ ፴ሺ፡ ብር፡ ይተርፈዋል። ፴ሺ፡ ብር፡ ላንዱ፡ ሰው፡ በያመቱ፡ ሲገባለት፡ የሚከፍለው፡ የሰው፡ ዕዳ፡ ከሌለበት፡ ሀብታም፡ ነው፡ ለመባል፡ ይቻላል።

ነገር፡ ግን፡ ከያንዳንዱ፡ ጋሻ፡ መሬት፡ ባመት፡ የሚገባለት፡ ትርፍ፡ ስንት፡ እንደ፡ ሆነ፡ እንመርምር። ብናስበው፡ እንሆ፡ ፫፡ ብር፡ ብቻ፡ ሆነ። እንግዲህ፡ የያንዳንዱ፡ ጋሻ፡ መሬት፡ የተገዛበት፡ ዋጋ፡ ሺ፡ ብር፡ ይሆናል። ሺ፡ ብር፡ ባመት፡ ያገባው፡ ወለድ፡ ፫፡ ብር፡ ብቻ፡ መሆኑ፡ ነው፤ዛሬ፡ ግን፡ በኢትዮጵያ፡ ያለው፡ ባንክ፡ ሲያበድር፡ የሚፈልገው፡ ወለድ፡ ቢያንስ፡ ቢያንስ፡ በመቶው፡ ፲፪፡ ብር፡ ነውና፤እንሆ፡ የሺው፡ ብር፡ ወለድ፡ ባመት፡ ፻፳፡ ብር፡ ሆነ። ስለዚህ፡ ባላምስቱ። መቶ፡ ጋሻ፡ መሬት፡ ርስቱን፡ ሁሉ፡ የገዛው፡ ባምስት፡ መቶ፡ ሺ፡ ብር፡ ሊሆን፡ ነው። መሬቱንም፡ ሁሉ፡ የገዛው፡ ተበድሮ፡ እንደ፡ ሆነ፡ እንሆ፡ ወለዱ፡ ከመቶው፡ ባ፲፪፡ ሒሳብ፡ ፰፡ ሺሕ፡ ብር፡ ሆነ። የሚያገኘው፡ ያመት፡ ትርፉ፡ ግን፡ ፲፡ ሺሕ፡ ብር፡ ብቻ፡ ስለ፡ ሆነ፡ ሌላውስ፡ ይቅርና፡ ወለዱንም፡ ብቻ፡ ለመክፈል፡ አይችልም። ስለዚህም፡ ምክንያት፡ እንኳን፡ ዋናውን፡ ሊከፍልና፡ ለወለዱም፡ ዕዳ፡ ብቻ፡ ሲል፡ ከመሬቱ፡ ከፍሎ፡ በየመቱ፡ መሸጥ፡ ኣይቀርለትም። ለዚሁም፡ ነገር፡ ደግሞ፡ አንድ፡ መከራከሪያ፡ መልስ፡ አለው። ባላገር፡ የሚበደር፡ መሬትን፡ ለመግዛት፡ አይደለም። መሬቱን፡ አሳምሮ፡ የበለጠ፡ ትርፍ፡ እንዲያገኝ፡ ነው፡ እንጂ። ይህም፡ ቢሆን፡ ያው፡ ነው። ባላገሮች፡ እርሻቸውን፡ አሳምረው፡ የሚያበቅለውን፡ እኽል፡ በዘ፡ ቍጥር፡ መላው፡ እኽል፡ ተሸጦ፡ የሚበላበት፡ ገበያው፡ ከቅርብ፡ ካልሆነ፡ በቀር፡ ትርፋቸው፡ እያነሰ፡ ይሄዳል። ማለት፡ ለያንዳንዱ፡ ቀላድ፡ መሬት፡ የሺሕ፡ የሺሕ፡ ብር፡ መሣሪያ፡ ገዝተው፡ አምጥተው፡ ብዙ፡ እኽል፡ ቢያገቡ፡ ያ፡ ያገቡት፡ እኽል፡ ሲቀና፡ የሚቀናበት፡ ገበያ፡ ሩቅ፡ ሲሆን፡ ከዱሮው፡ ሺሕ፡ ብር፡ ያነሰ፡ ዋጋ፡ ያመጣል። እንደዚህ፡ ያለውም፡ ገበያው፡ ሩቅ፡ የሆነበት፡ ባላገር፡ ምናልባት፡ ትርፍ፡ የሚያገኘው፡ እኽሉን፡ በሚሰድበት፡ አገር፡ ከሰማይ፡ መዓት፡ ወርዶ፡ መከሩ፡ ተበላሽቶ፡ ወይም፡ በሌላ፡ ምክንያት፡ ረኃብ፡ የገባ፡ እንደሆነ፡ ነው። ስለዚህም፡ በውጭ፡ ኣገር፡ መከሩ፡ በጠፋ፡ ቍጥር፡ ትርፍ፡ ሲያገኝ። የውጭ፡ አገርም፡ መከር፡ ባማረ፡ ቍጥር፡ ደግሞ፡ ሲከስር፡ ይኖራል። ማለት፡ የዕድል፡ ሎሌ፡ ሁኖ፡ ይኖራል፡ እንጂ፤በጭራሽ፡ የተደላደለ፡ ትዳር፡ የለውም። ባሜሪካና፡ በመስኮብ፡ በሩማንያም፡ የሚታየው፡ ነገር፡ ይኸው፡ ነው። በእነዚያ፡ አገሮች፡ ኣንዳንዳቸው፡ ሰዎች፡ ካባቶቻቸው፡ የወረሱትን፡ ወይም፡ ሰው፡ ሳይገባበት፡ ራሳቸው፡ ያቀኑትን፡ ብዙ፡ መሬት፡ ይዘው፡ ከየመሬታቸው፡ ተጠራቅሞ፡ ባመት፡ የሚገባላቸው፡ ትርፍ፡ ብዙ፡ ነው። እንደዚህ፡

ባለውም፡ ሕዝቡ፡ ከመሬቱ፡ ያገኘውን፡ ፍሬ፡ ወደ፡ ውጭ፡ አገር፡ መስደድ፡ የግድ፡ የሆነበት፡ አገር፡ ውስጥ፡ የመሬት፡ ዋጋ፡ ጥቂት፡ ነው። በየከተማው፡ ዙሪያ፡ ያለው፡ መሬት፡ መወደዱ፡ ለጊዜው፡ ነው። የተወደደበትም፡ ምክንያት፡ ሁለት፡ ነው። አንደኛው፡ ከጅቡቲ፡ ወደ፡ አዲስ፡ አበባ፡ የምድር፡ ባቡር፡ ስለ፡ ተዘረጋ፡ ባለመሬት፡ የሆኑ፡ ሰዎች፡ ለወደ፡ ፊት፡ ብዙ፡ ትርፍ፡ የሚያገኙ፡ ይመስላቸዋልና፡ አይሸጡም።

ሁለተኛው፡ ደግሞ፡ በየከተማው፡ ያሉ፡ ሰዎች፡ በዝተው፡ በከተማቸው፡ ዙሪያ፡ ታርሶ፡ የሚገባው፡ እኽል፡ ለባላገሩና፡ ለነርሱ፡ ምግብ፡ እንደ፡ ዱሮ፡ የማይበቃ፡ ሆነ። ከዱሮውም፡ የበዛ፡ እኽል፡ እንዳይገባ፡ ባላገሩ፡ ደኅና፡ መሣሪያና፡ የሚበቃ፡ ዕውቀት፡ የለውም። ከከተማዎቹም፡ ራቅ፡ ያሉት፡ አገሮች፡ ታርሰው፡ እኽላቸው፡ ወደ፡ ከተማ፡ ይመጣል፡ እንዳይባል፡ ደኅና፡ የጋሪ፡ መንገድና፡ የምድር፡ ባቡር፡ ስለሌለ፡ ድካሙ፡ ብዙ፡ ነውና፡ አይቻልም። ከዚህ፡ ምክንያት፡ የተነሣ፡ ባዲስ፡ አበባ፡ ዙሪያ፡ ካለው፡ አንዱ፡ ቀላድ፡ ሁለት፡ ወይም፡ ሦስት፡ ሺሕ፡ ብር፡ ሲያወጣ፡ በባሌ፡ ወይም፡ በወለጋ፡ ያለው፡ መሬት፡ ፲፡ ብር፡ እንካ፡ ሊያወጣ፡ አይችልም።

አሁን፡ እንግዲህ፡ ለወደ፡ ፊት፡ ባዲስ፡ አበባ፡ ዙሪያ፡ ያለው፡ ባላገር፡ የሚበቃ፡ ዕውቀትና፡ ደኅና፡ መሣሪያ፡ አግኝቶ፡ ካጠገቡ፡ መሬት፡ ብዙ፡ እኽል፡ አርሶ፡ ለማግባት፡ የተቻለው፡ እንደ፡ ሆነ፡ እኽሉ፡ በከተማ፡ ውስጥ፡ ካሉት፡ ሸማቾች፡ ምግብ፡ ተርፎ፡ ሊረክስ፡ ነውና፡ በየከተማው፡ ዙሪያ፡ ያለው፡ መሬት፡ ወዲያው፡ ይረክሳል፤ይህም፡ ቀርቶ፡ ወደ፡ ባሌ፡ ወደ፡ ሲዳሞ፡ ወደ፡ ወለጋ፡ የጋሪ፡ መንገድ፡ ወይም፡ የምድር፡ ባቡር፡ ቢዘረጋ፡ ከነዚያ፡ ወረዳዎች፡ ብዙ፡ እኽል፡ ወደ፡ አዲስ፡ ኣበባ፡ ሊመጣ፡ ነውና፤ስለዚህ፡ ባዲስ፡ አበባ፡ ዙሪያ፡ ያለው፡ መሬት፡ ሁሉ፡ ይረክሳል። የባሌውና፡ የወለጋው፡ መሬት፡ ግን፡ እኽሉ፡ ወደ፡ አዲስ፡ አበባ፡ ሊመጣ፡ ነውና፤ባዲስ፡ አበባ፡ ዙሪያ፡ ያለው፡ መሬት፡ የረከሰውን፡ ያኽል፡ ጨምሮ፡ ዋጋው፡ ከፍ፡ ይላል።

ስለዚህ፡ ባላገሩ፡ እንዲጠቀም፡ ተብሎ፡ ገንዘብ፡ ቢያበድሩት፡ ለዛሬው፡ የኢትዮጵያ፡ ባላገር፡ አንዳችም፡ ጥቅም፡ አይሆነውም። ይልቍንም፡ መሬቱ፡ እየተሸጠ፡ በጥቂቶች፡ ሰዎች፡ እጅ፡ ይገባል። እነዚህም፡ ጥቂቶች፡ ሰዎች፡ የሚያገኙት፡ ጥቅም፡ ብዙ፡ መሆኑ፡

ተጠራቅሞ፡ ነው፡ እንጂ፤ከያንዳንዱ፡ መሬት፡ የሚያገኙት፡ ትርፍ፡ ቢታሰብ፡ ጥቂት፡ ነው። ይህ፡ ስለ፡ ተባለ፡ መቼም፡ አልፎ፡ አልፎ፡ አንዳንዱ፡ ደኅና፡ መሬት፡ ተገኝቶ፡ ብዙ፡ ትርፍ፡ አይገኝም፡ ማለት፡ አይደለም። ጭራሹን፡ አንዳች፡ ነገር፡ የማይገኝበት፡ መሬት፡ መልቶ፡ የለምን። ስለዚህ፡ እንደዚህ፡ ያለ፡ ድንገተኛ፡ ነገር፡ በሒሳባችን፡ አይገባም።

በሒሳባችን፡ የሚገባ፡ ከሥርዐት፡ ጋራ፡ የሚስማማ፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ነው። ይህም፡ ሥርዐት፡ እንዲህ፡ ይለናል፤ባንድ፡ አገር፡ ውስጥ፡ ባለመሬት፡ የሚጠቀም፡ መዠመሪያ፡ ከጠባቡ፡ መሬት፡ ብዙ፡ እኽል፡ ለማግባት፡ የሚበቃ፡ መሣሪያና፡ ዕውቀት፡ ሲያገኝ፡ ነው።

በሁለተኛም፡ አርሶ፡ ያገባውን፡ እኽል፡ የሚሸጥበትና፡ የሚበላበት፡ ገበያው፡ ቅርብ፡ ሲሆን፡ ነው።

የማንኛውም፡ መንግሥት፡ መሠረት፡ ግን፡ እርሻ፡ እንደ፡ ሆነ፡ በጣም፡ እንረዳለን። ባለእርሻው፡ ሲጠቀም፡ መንግሥትም፡ ኀይል፡ ያገኛል። ባለእርሻውም፡ ሲጐዳ፡ የመንግሥትም፡ ኀይል፡ እያነሰ፡ ይሄዳል። ስለዚህም፡ ሕዝቡ፡ እንዲረዳና፡ እንዲበረታ፡ የፈለገ፡ መንግሥት፡ ከሁሉ፡ ነገር፡ በፊት፡ የሳላገሩ፡ ትዳር፡ እየተሻለ፡ እንዲሄድ፡ መጣር፡ አለበት። የባሳገሩ፡ ትዳር፡ ግን፡ እየተሻለ፡ የሚሄድ፡ ምናልባት፡ ለያንዳንዱ፡ ነገር፡ አልፎ፡ አልፎ፡ የውጭ፡ አገር፡ ደንብ፡ ሲያወጡለት፡ ይደለም። የነፍሰ፡ ገዳዩ፡ አቀጣጥ፡ ደንብ፡ በመስቀል፡ ወይም፡ በጐራዴ፡ እንዲሆን ዳኛው፡ የሚፈርደው፡ ባንድ፡ ደንጊያ፡ ላይ፡ ተቀምጦ፡ እንደ፡ ሆነ፤ወይም፡ ባማረ፡ ወንበር፡ ላይ፡ እንዲሆን ፥ እስረኛውንም፡ የሚይዝና፡ የሚጠብቅ፡ ዘበኛ፡ ጥሩ፡ ልብስ፡ ወይም፡ ቅዳጅ፡ ጨርቅ፡ ሲለብስ። ከቀረጥም፡ የሚገኘው፡ ገንዘብ፡ ቢያንስ፡ ወይም፡ ቢበዛ፡ መንገድና፡ የምድር፡ ባቡር፡ ሲሠራ፡ ወይም፡ ባይሠራ፡ ለባለእርሻው፡ አንዳች፡ ጥቅም፡ አይሆነውም። እንደዚህም፡ ባለው፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ባለመሬቱ፡ ካልተጠቀመበት፡ መንግሥትም፡ አይጠቀምም። የማንኛውም፡ ቤት፡ መስኮት፡ ወይም፡ መዝጊያ፡ የሚጠቅም፡ የቤቱ፡ መሠረት፡ ሲጠና፡ ነው። የቤቱም፡ መሠረት፡ ካልጠና፡ ለመስኮቱና፡ ለመዝጊያው፡ የወጣው፡ ገንዘብ፡ ከሳራ፡ ይሆናል። በሕዝብም፡ ትዳር፡ እንደዚሁ፡ ነው። ቤቱም፡ ሊጠነክርና፡ ሊያምር፡ የፈለገ፡ መንግሥት፡ መስኮትና፡ መዝጊያ፡ ጣራም፡ በረንዳም፡ ሳያበጅ፡

ከሁሉ፡ ነገር፡ በፊት፡ የቤቱን፡ መሠረት፡ ማጠንከር፡ ያስፈልገዋል። የቤቱ፡ መሠረት፡ ግን፡ የሚጠነክርለት፡ በምንድር፡ ነው፤እስኪ፡ እንመርምር።

የዚህ፡ ጥያቄ፡ መልሱ፡ በጣም፡ አጭር፡ ነው። ማንኛውም፡ ለሕዝቡ፡ ኑሮ፡ የሚያስፈልግ፡ ዕቃ፡ ሁሉ፡ ባገሩ፡ ውስጥ፡ እንዲሠራ ፥ ካገሩም፡ ወደ፡ ውጭ፡ አገር፡ የሚሄድ፡ ዕቃ፡ ሁሉ፡ የተሠራ፡ እንዲሆን፡ መንግሥት፡ አጥብቆ፡ እንዲጥርበት፡ ተስፋ፡ እናደርጋለን። መንግሥት፡ እንደዚህ፡ አድርጎ፡ ሲጥር፡ ግን፡ ከሁሉ፡ በፊት፡ ዋና፡ አጋዥ፡ የሚሆነው፡ የተደላደለ፡ መሠረት፡ ያለው፡ የጉምሩክ፡ ደንብ፡ ነው። መሠረትም፡ ያለው፡ የጉምሩክ፡ ደንብ፡ ለሕዝቡ፡ ጥቅምና፡ መሠልጠኛ፡ የሚሆነውንና፡ ባገሩ፡ ውስጥ፡ ሊበጅ፡ የማይቻለውን፡ መሣሪያና፡ መኪና፡ ሁሉ፡ ያለቀረጥ፡ እንዲገባ፡ ይፈቅዳል። ያለቀረጥ፡ እንዲገቡ፡ በተፈቀዱ፡ መኪናዎችና፡ መሣሪያዎችም፡ ሊሠራ፡ የሚቻል፡ ነገር፡ ሁሉ፡ በብዙ፡ እንዲቀረጥ፡ ይደነገጋል።

ዳሩ፡ ግን፡ ዋናው፡ የመንግሥት፡ ኣጋኝዥ፡ ደኅና፡ የጉምሩክ፡ ደንብ፡ ነው፡ ስለ፡ ተባለ፡ ብቻውን፡ ይበቃል፡ ማለት፡ ኣይደለም። ደግሞ፡ የጉምሩኩን፡ ደንብ፡ የማይለዩት፡ ሦስት፡ ባልንጀሮች፡ አሉት፤እነዚህም፡ ባልንጀሮች ፥

**አንደኛው**፤የሕዝብ፡ ማሠልጠኛ፡ ትምርት፡ ቤት፡ በያይነቱ፡ ማቆም፡ ነው።

**ሁለተኛው**፤ሕዝቡን፡ ርስ፡ በርሱ፡ የሚያቃርብ፡ መንገድና፡ የምድር፡ ባቡር፡ ማሠራት፡ ያስፈልጋል።

**ሦስተኛው**፤ባገራችሁ፡ ውስጥ፡ ሁኜ፡ እሠራለሁ፡ የሚለውን፡ ሰው፡ ሁሉ፡ የማንኛውም፡ መንግሥት፡ ዜጋ፡ ቢሆን፡ በደስታ፡ ተቀብሎ፡ በቸገረው፡ ነገር፡ መርዳት፡ ነው። ሦስቱ፡ ዋና፡ ባልንጀሮቹ፡ የተባሉ፡ እነዚህ፡ ናቸው።

መቼም፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ የሚያስፈልገውን፡ ዕቃ፡ ሁሉ፡ የሚገዛው፡ ከውጭ፡ አገር፡ ሰዎች፡ ነው። ሠራተኞቹ፡ ያሉበት፡ ቦታ፡ ሩቅ፡ ስለ፡ ሆነ፡ ግን፡ ዕቃውን፡ አገኛለሁ፡ ሲል፡ ብዙ፡ ትርፍ፡ ድካም፡ ይሄድበታል። ጥቅሙን፡ የሚያገኙ፡ ግን፡ ነጋዴዎች፡ ናቸው። ስለዚህ፡

የውጭ፡ አገር፡ ሰዎች፡ ድካማችንን፡ መውሰዳቸው፡ ላይቀር፡ አጠገባችን፡ እየሠሩ፡ ቢወስዱት፡ ይሻላል። ባገራችን፡ ውስጥ፡ ሆነው፡ የሠሩ፡ እንደሆን፡ ግን፡ የመልከተኞቹ፡ ነጋዴዎች፡ ትርፍ፡ ይቀራልና፡ ያገራችን፡ ሰው፡ የሚያስፈልገውን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ እንደ፡ ድካሙ፡ መጠን፡ ያገኛል። የመሥሪያውም፡ ፋብሪካ፡ ባገሩ፡ ውስጥ፡ ስለ፡ ቆመለት፡ እያየ፡ ሕዝቡም፡ ይሠለጥንበታል። በጊዜም፡ ብዛት፡ ለኑሮው፡ የሚያስፈልገውን፡ ዕቃ፡ ሁሉ፡ ራሱ፡ ለመሥራት፡ ዕውቀት፡ ያገኛል። ስለዚህም፡ ባገራችን፡ ውስጥ፡ ሆኖ፡ ሊሠራ፡ የሚፈልግ፡ ሰው፡ ቢመጣ፡ የማንኛውም፡ መንግሥት፡ ዜጋ፡ ቢሆን፡ በመልካም፡ ቢቀበሉት፡ ይጠቅማል፡ እንጂ፡ አይጐዳም። መንግሥትም፡ እንዲህ፡ ያሉ፡ ሰዎች፡ እንዲመጡለትና፡ ባገሩ፡ ውስጥ፡ አስቀምጦ፡ ሕዝብን፡ ለማሠልጠን፡ ሥራዬ፡ ብሎ፡ መጣር፡ ይገባዋል። መንግሥት፡ እነዚህን፡ የተጻፉትን፡ መንገዶች፡ አጥብቆ፡ ቢከተል፡ ኃይሉና፡ ሀብቱ፡ እያደገ፡ እንዲሄድ፡ የታወቀ፡ ነው።

እንሆም፡ በብዙ፡ ድካም፡ ተለቅሞ፡ አንዳች፡ ነገር፡ ሳያበስል፡ ወይም፡ ሳያሞቅ፡ ነዶ፡ ያለቀ፡ ዕንጨት፡ በከንቱ፡ መጥፋቱ፡ ነው። እንዲሁም፡ የማይሠራ፡ ሰው፡ የበላው፡ እኽል፡ በከንቱ፡ ይጠፋል። በዚህ፡ ምክንያት፡ ያ፡ ከጥር፡ ፲፱፻፱፡ ዓ፡ ም፡ እስከ፡ ጥር፡ ፲፱፻፳፡ ዓመት፡ ምሕረት፡ ድረስ፡ ከኢትዮጵያ፡ ወደ፡ ውጭ፡ አገር፡ የሄደ፡ ቆዳ፡ ሳይሠራ፡ ስለ፡ ሄደ፡ ያሳዝናል። ሳይሠራም፡ ስለ፡ ሄደ፡ ያወጣው፡ ዋጋ፡ በፈረሱላ፡ ፲፫፡ ብር፡ ስለ፡ ሆነ፡ ብናስበው፡ የዋጋው፡ ድምር፡ ፻፴፱ሺ፡ ፬፻፷፯፡ ብር፡ ብቻ፡ ሆነ። በኢትዮጵያ፡ ደኅና፡ ሆኖ፡ ተሠርቶ፡ ቢሆን፡ ግን፡ እጅግ፡ ቢያንስ፡ ቢያንስ፡ ፈረሱላው፡ ፱፡ ብር፡ ያወጣ፡ ነበር፡ ማለት፡ ነው። በዚያ፡ ጊዜ፡ የሄደው፡ ቆዳ፡ በዚህ፡ ሒሳብ፡ የዋጋው፡ ድምር፡ ፲፡ ሚሊዮን፡ ፷፬ ሺ፡ ፱፻፱፡ ብር፡ ይሆን፡ ነበር። ይህም፡ ሆኖ፡ ቢሆን፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ በዚያ፡ ዓመት፡ የበላው፡ እኽል፡ እንኳን፡ ሊጠፋ፡ ሥራ፡ ሁኖ፡ ተሸጦ፡ ትርፍ፡ ጨምሮ፡ ይመለስ፡ ነበር። ካገር፡ የሚገኝ፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ተሠርቶ፡ ወደ፡ ገበያ፡ ሲወጣ፡ ሕዝቡ፡ የበሳውን፡ ምግብ፡ ጨምሮ፡ ይሄዳል። ሁለቱም፡ ወደ፡ ኀበያ፡ ተያይዘው፡ ሄደው፡ ዋጋ፡ ያወጣሉ። የተበላውም፡ እኽል፡ ፍጉ፡ ባገሩ፡ ውስጥ፡ ይቀራል። በተሠራውም፡ ዕቃ፡ ውስጥ፡ የሄደው፡ ፍግ፡ ዋጋ፡ ያወጣል። ስለዚህም፡ በሥራ፡ በሠለጠነ፡ መንግሥት፡ ውስጥ፡ ማናቸውም፡ አንድ፡ ጊዜ፡ የተደከመበት፡ ነገር፡ ቢበላም፡

ባይበላም፡ ጠፍቶ፡ አይቀርም። ወደ፡ ፊት፡ መንግሥቱ፡ የበለጠ፡ ሀብትና፡ ኃይል፡ እንዲያገኝ፡ ይረዳል፡ እንጂ፤ደግሞም፡ እንደዚሁ፡ ባገሩ፡ ውስጥ፡ የተደከመበት፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ዋጋ፡ .ሳያወጣ ፥ የፊት፡ የፊቱ፡ ወዲያው፡ የሚባክንበት፡ መንግሥት፡ ኀይልና፡ ሀብት፡ አይጨምርም።

እንሆ፡ ባጭሩ፡ ባንድ፡ ሕዝብ፡ ውስጥ፡ ሀብት፡ ምን፡ እንደ፡ ሆነ፡ የሚያድግበትንና፡ የሚያንስበትንም፡ ምክንያት፡ ባጭሩ፡ ተረዳን። የሕዝብ፡ ሀብት፡ የሚያንሰው፡ በላተኛው፡ ከሠራተኛው፡ ሲበዛ፡ ነው። ሕዝቡም፡ ዕውቀት፡ በሌለው፡ መንግሥት፡ ውስጥ፡ የሕዝቡም፡ ትዳር፡ ቀጥሎ፡ እንደ፡ ተጻፈውና፡ እንደ፡ ተሣለው፡ ነው።

የመዠመሪያው፡ ሥዕል፡ ምሳሌ፡ ዕውቀት፡ በሌለው፡ መንግሥት፡ ውስጥ፡ ንግድና፡ ጦርነት፡ እየሰፋና፡ እየታደሰ፥ የእጅ፡ ሥራ፡ እየተናቀና፡ እያነሰ፡ ይሄዳል። መሬትም፡ ከዚህ፡ ምክንያት፡ የተነሣ፡ ምድረ፡ በዳነት፡ እየበዛባት፡ የተመሠረተው፡ እርሻ፡ አንሶ፡ ከሁሉ፡ በታች፡ ሆኖ፡ ይቀራል። የሚያርሱትም፡ ጥቂቶች፡ ሰዎች፡ ስለ፡ ሆኑ፡ ከሠራተኛው፡ በላተኛው፡ በዝቷልና፡ ስሕዝቡ፡ ምግብ፡ ስላልበቃው፡ ያ፡ ዕውቀት፡ የሌለው፡ መንግሥት፡ ለሥራ፡ ፈቶቹ፡ ከውጭ፡ ነገር፡ ምግብ፡ ለማስመጣት፡ ይሰናዳል። ሀብቱና፡ ኀይሉም፡ እያነሰ፡ ይሄዳል።

## ኣንደኛ፡ ሥዕል።

ንግድና፡ ጦር

የእጅ፡ ሥራ።

እርሻ።

እንሆ፡ የሁለተኛውም፡ ምሳሌ፡የሀብትንና፡ የዕውቀትን፡ አቀለጣጠፍ፡ ያሳየናል።

ዕውቀት፡ ባለው፡ መንግሥት፡ ውስጥ፡ ግን፡ መሠረቱ፡ እርሻ፡ ስለ፡ ሆነ፡ መሠረቱን፡ እርሻን፡ ያሰፋና፡ የእጅን፡ ሥራ፡ አስከትሎ፡ ንግድንና፡ ጦርን፡ እያሳነሰና፡ እያጠበበ፡ ይሄዳል። ስለዚህም፡ ዕውቀት፡ ባለው፡ መንግሥት፡ ውስጥ፡ ያለ፡ ሕዝብ፡ ዕውቀትና፡ ሀብት፡ እየጨመረ፡ ስለ፡ ሄደ፡ መንግሥቱም፡ የበለጠ፡ ሀብትና፡ ኃይል፡ ያገኛል። ሕዝቡ፡ ሀብታምና፡ ዕውቀተኛም፡ በሆነ፡ መንግሥት፡ ውስጥ፡ ግን፡ የሕዝቡ፡ ትዳር፡ መሠረቱ፡ እንደ፡ ሰፋና፡ እንዳማረ፡ ሁለተኛው፡ ሥዕል፡ ያስረዳናል።

## ሁለተኛ፡ ሥዕል።

| |
|---|
| ንግድና፡ ጦር። |
| የእጅ፡ ሥራ። |
| እርሻ። |

እነዚህም፡ ሁለት፡ ሥዕሎች፡ ያሜሪካው፡ ሊቅ፡ ካሪ፡ ከጻፈው፡ መጽሐፍ፡ የተቀዱ፡ ናቸውና፤ሕዝቡ፡ ዕውቀት፡ የሌለው፡ መንግሥት፡ እንደ፡ ምን፡ ትንሽ፡ እንደ፡ ሆነ ፥ ከዚህም፡ ምክንያት፡ የተነሣ፡ ጥንካሬ፡ እንደሌለው፡ ደግሞ፡ ሕዝቡ፡ ዕውቀት፡ አግኝቶ፡ በየሥራው፡ ሲሠለጥን፡ መሠረቱ፡ ሰፍቶ፡ እንዲበረታ፡ ይገልጹልናል። እንግዲህም፡ ወደ፡ ሌላ፡ ክፍል፡ ሳንሻገር፡ ከዚህ፡ ቀደም፡ ያጠናናቸውን፡ ሁሉ፡ ባጭር፡ ቃል፡ በታናናሽ፡ ሥር፡ ክፍሎች፡ እንድገማቸው።

***መዠመሪያ***፤ሰው፡ የተፈጠረ፡ የምድር፡ ጌታ፡ ለመሆን፡ ነበረ። ነገር፡ ግን፡ በመዠመሪያ፡ ጥቂት፡ ራሱን፡ ስለ፡ ሆነ፡ የሚበቃ፡ መሣሪያ፡ የለውምና፤የምድር፡ ተገዥ፡ ሆነ።

***ሁለተኛ***፤በኋላ፡ ግን፡ ዕውቀት፡ ስላገኘ፡ ተባዛ፤ተባበረም።

**ሦስተኛ**፤በዝቶ፡ ከተባበረም፡ ዘንድ፡ ሥራውን፡ ተከፋፍሎ፡ የሠራውን፡ ሥራ፡ እንደየሥራው፡ መጠን፡ መለዋወጥ፡ ዠመረ፤ዋጋ፡ ማለት፡ የሥራ፡ መለኪያ፡ ነው፡ እንዳልነው፡ **አራተኛ**፤ሀብት፡ ማለት፡ የዓለም፡ ጌትነት፡ መለኪያ፡ ነው።

ሰው፡ ግን፡ ምንም፡ የሚያስፈልገውን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ለማግኘት፡ ቢችል፡ አንቀሳቅሶ፡ ከማጋጠም፡ በቀር፡ ሌላ፡ ዐቅም፡ እንደሌለው፡ የታወቀ፡ ነገር፡ ነው። ሁሉንም፡ የምትሰጥ፡ መሬት፡ ናት። ማንቀሳቀስና፡ ማጋጠም፡ ግን፡ የሚሆነው፡ በሥራ፡ ብቻ፡ ነውና፤ሀብት፡ ማለት፡ የተከማቸ፡ ሥራማለት፡ ነው።

**አምስተኛ**፤ማንኛውም፡ የተሠራ፡ ሥራ፡ ከኋላ፡ የሚከተለውን፡ ሥራ፡ ያቀላል። ማንኛውንም፡ ሀብት፡ የበለጠ፡ ሀብት፡ ይከተለዋል። በመዠመሪያ፡ ግን፡ ሥራ፡ ሁሉ፡ እጅግ፡ ያስቸግራል። ዥምርም፡ የሌለው፡ ሥራ፡ ፍጻሜ፡ አያገኝም። ሀብትም፡ ሳይዠመር፡ አያድግም። ስለዚህም፡ ዥምሩ፡ ወዲያው፡ ወዲያው፡ ሲጠፋ፡ አንዳች፡ ሥራ፡ አይጠራቀምም። ከዚህም፡ ምክንያት፡ የተነሣ፡ ዕውቀት፡ በሌለው፡ ሕዝብ፡ ውስጥ፡ በላተኛው፡ ከሠራተኛው፡ ይበዛልና፤አንዳችም፡ የተሠራ፡ ነገር፡ አይከማችም። እንደዚህም፡ ያለው፡ ሕዝብ፡ ከድኽነት፡ አይወጣም።

**ስድስተኛ**፤የሕዝብ፡ ሀብት፡ የሚሰፋው፡ ሕዝቡ፡ የሚያስፈልገውን፡ ሁሉ፡ ለመሥራት፡ ሥራውን፡ በብዙ፡ ተካፍሎ፡ የተለዋወጠ፡ እንደሆን፡ ነው። የሠሩትን፡ ሥራ፡ የሚለዋወጡ፡ ሠራተኞች፡ የተራራቁ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ግን፡ እስኪገናኙ፡ ድረስ፡ ብዙ፡ ድካም፡ በከንቱ፡ ይባክንባቸዋል። የሚያገናኛቸውም፡ ነጋዴ፡ ከሆነ፡ ከየድካማቸው፡ ከፍለው፡ ይሰጡታል። ስለዚህም፡ የድካማቸውን፡ ሙሉ፡ ዋጋ፡ አያገኙም። ከንቱ፡ ድካም፡ ሲበዛባቸው፡ ልባቸው፡ ይሰንፋል። በዚህም፡ ምክንያት፡ ባገሩ፡ ውስጥ፡ የሚሠራ፡ ሥራ፡ ጥቂት፡ ነውና፤ያገሩ፡ ሀብት፡ አያድግም። ይልቁንም፡ ድኽነት፡ እየሰፋና፡ እየተጫነ፡ ይሄዳል።

**ሰባተኛ**፤ስለዚህም፡ የድካማቸውን፡ ፍሬ፡ የሚለዋወጡ፡ ሠራተኞች፡ እንዲቃረቡ፡ መንግሥት፡ መጣር፡ ይገባዋል። ይህም፡ ማቃረብ፡ የሚሆነው፡ በመንገድና፡ በምድር፡ ባቡር፡ ነው። ባንድ፡ መንግሥትም፡ ውስጥ፡ ካንዱ፡ አውራጃ፡ ወዳንዱ፡ አውራጃ፡ የሚመላለስ፡ ዕቃ፡ ሲቀረጥ፡

ሠራተኞቹን፡ እንደ፡ ማራራቅ፡ ያኽል፡ ነውና፤ሕዝብንም፡ መንግሥትንም፡ ይጐዳል።

**ስምንተኛ**፤መንገድና፡ የምድር፡ ባቡርም፡ ጥቅም፡ የሚሆነው የሥራ፡ ማሠልጠኛ፡ የትምርት፡ ቤቶች፡ በያይነቱ፡ ሲሠሩና፡ ማንኛውም፡ ዕቃ፡ ሁሉ፡ እንደሚቻል፡ መጠን፡ ባገሩ፡ ውስጥ፡ እንዲበጅ፡ መንግሥትም፡ ሲጥርበት፡ ነው። በዚሁም፡ ጥረቱ፡ ዋና፡ አጋዥ፡ የሚሆነው፡ የተደላደለ፡ የጉምሩክ፡ ደንብ፡ ነው። በቀረጥ፡ የሚገባ፡ ገንዘብ፡ ቢበዛ፡ ለመንግሥት፡ ትልቅ፡ ጥቅም፡ አይሆነውም፤ዋና፡ ጥቅሙ፡ ያገሩ፡ ገባር፡ ሀብት፡ ጥቅም፡ ነው። የሚያስፈልገውን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ከውጭ፡ አገር፡ የሚያመጣ፡ ሕዝብ፡ ግን፡ ፍጹም፡ ድኻ፡ ነው። ገበያው፡ ርቆበት፡ ዕቃውን፡ ለሚያመጣለት፡ ነጋዴ፡ ዕቃው፡ በውነት፡ ከሚያወጣው፡ ዋጋ፡ ብዙ፡ አብልጦ፡ ይሰጣል።

**ዘጠነኛ**፤በእንደዚህ፡ ያለውም፡ አገር፡ ውስጥ፡ የባላገሩ፡ ጥቅም፡ እያነሰ፡ ይሄዳል፤መሬቱም፡ ይረከሳል። በጥቂቶችም፡ ሰዎች፡ እጅ፡ ይገባል። መሬቱም፡ በጥቂቶች፡ ሰዎች፡ እጅ፡ ከገባ፡ ሕዝብ፡ በጣም፡ ይደኸያል። ሕዝቡ፡ በያይነቱ፡ ሥራ፡ ባልሠለጠነም፡ አገር፡ ለባላገሩ፡ ቢያበድሩት፡ ይጐዳዋል፡ እንጂ፡ አይጠቅመውም።

**ዐሥር**፤የመንግሥት፡ መሠረት፡ እርሻ፡ ነው። ባለእርሻ፡ የሚያገኘው፡ ጥቅም፡ ሲያንስ፡ የመንግሥት፡ መሠረት፡ አይጠናም። ባለእርሻ፡ ሲጠቀም፡ ግን፡ መንግሥትም፡ ይጠነክራልና፡ ይበረታል።

# ፳ኛ፡ ምዕራፍ።

እስኪ፡ የለውጥን፡ አገባብ፡ ምን፡ እንደ፡ ሆነ፡ እንመለስና፡ እንመርምር። እንሆ፡ ሰው፡ ሁሉ፡ ትልቁም፡ ትንሹም፡ ቢሆን፡ ብርን፡ ሲያገኛት፡ ደስ፡ ይለዋል። ማንኛቸውም፡ ሰው፡ ጌታ፡ መሆኑን፡ ሊያስታውቅ፡ ብርን፡ ያከማቻል። እኛም፡ ጌትነቱን፡ ስናደንቅለት፡ እገሌ፡ እኮ፡ ብር፡ መልቶታል፡ እያልን፡ እናወራለን። ድኻ፡ የሆነ፡ ሰው፡ ደግሞ፡ ያየን፡ እንደ፡ ሆነ፡ እገሌ፡ አንድም፡ ብር፡ የለው፡ ወይም፡ ደግሞ፡ አንድም፡ ተሙን፡ የለውም፡ እንላለን። ደግሞ፡ ሰው፡ ሁሉ፡ ባለው፡ ድካሙ፡ ብርን፡ ለማግኘት፡ ይጥራል። አንዱም፡ በእውነተኛ፡ መንገድ፡ አንዱም፡ በጉቦ። ማለት፡ እያንዳንዱ፡ ሰው፡ ብርን፡ የሚፈልግበት፡ መንገድ፡ ምንም፡ ቢለያይ፡ ሰው፡ ሁሉ፡ በዚያው፡ በሚፈልግበት፡ መንገድ፡ ብዙም፡ ብር፡ ቢያገኝ፡ በቃኝ፡ አይልም። የገንዘብ፡ ፍቅር፡ አድሮበታልና ፥ ብርን፡ የሚጠላ፡ ሰው፡ የለም። ሰውም፡ ሁሉ፡ ብር፡ እንዳይበላ፡ እንዳይቈረጠም፡ ተበጥብጦም፡ እንዳይጠጣ፡ ተለብሶም፡ እንዳይሞቅ፡ እያወቀ፡ ብዙ፡ ድካም፡ ደክሞ፡ ያለውንም፡ ዕቃ፡ ሰጥቶ፡ ብር፡ ቢያገኝ፤እጅግ፡ ደስ፡ ይለዋል፤ሌላ፡ ዋጋም፡ አይፈልግም። ከብር፡ ግን፡ ደግሞ፡ ወርቅ፡ ይወደዳል። ዳሩ፡ ግን፡ ምክንያት፡ የሌለው፡ ነገር፡ የለም። ስለዚህም፡ ደግሞ፡ ብርና፡ ወርቅን፡ የዓለም፡ ሕዝቦች፡ ሁሉ፡ ይህን፡ ያኸል፡ የሚወዷቸው፡ ምክንያት፡ ይኖረዋልና፡ ይህ፡ ምክንያት፡ ምን፡ እንደ፡ ሆነ፡ እንመርምር።

ሰው፡ የተፈጠረ፡ የምድር፡ ጌታ፡ ሆኖ፡ በዓለም፡ ሊኖር፡ ነበረ። በመዠመሪያ፡ ጥቂት፡ ራሱን፡ ስለ፡ ነበረ፡ ይህነን፡ ጌትነት፡ ለማግኘት፡ የሚበቃ፡ ዐቅም፡ አላገኘም። በኋላ፡ ግን፡ እየተባዛ፡ መሬትንም፡ አሸንፋለሁ፡ ሲል፡ ተባብሮ፡ ሥራውንም፡ ተከፋፍሎ፡ በየባሕሪው፡ ሞያ፡ ሞያውን፡ ያዘ። ሥራውን፡ መከፋፈሉ፡ ግን፡ ከየሠራው፡ ሥራ፡ ከራሱ፡ የተረፈውን፡ እንዲለዋወጥ፡ ነው። ነገር፡ ግን፡ መሬትን፡ ለመቈፈር፡ ዶማ፡ ዛፍንም፡ ለመቀረጥ፡ መጥረቢያ ፥ ወጥንም፡ ለማብሰል፡ ማንኛውንም፡ አንድ፡ ዐይነት፡ ድስት ፥ እንዲሁም፡ ለወጥ፡ አንድ፡ ዐይነት፡ መሣሪያ፡ እንዲያስፈልግ፡ የግድ፡ የታወቀ፡ ነገር፡ ነው። የለውጥም፡ መሣሪያ፡ ባይኖር፡ እያንዳንዱ፡ ሰው፡ የሠራውን፡ ሥራ፡ እስኪለዋወጥ፡ ድረስ፡ ብዙ፡

ጊዜ፡ ማንኛውም፡ የሰው፡ ሥራ፡ ሁሉ፡ አይፋጠንም፡ ነበር። ሰውም፡ ከፍ፡ ያለ፡ የዕውቀት፡ ደረጃ፡ ኣግኝቶ፡ የምድር፡ ጌታ፡ ለመሆን፡ አይችልም፡ ነበር።

እንሆ፡ በያንዳንዱ፡ ቦታ፡ ሁሉ፡ ላይ፡ ለያንዳንዱ፡ ሰው፡ የሚያስፈልግ፡ ዕቃ፡ ሁሉ፡ አይገኝም። እስቲ፡ አሁን፡ ለምሳሌ፤ ባለበርበሬና፡ ባለጤፍ፡ ባንድ፡ መንደር፡ ውስጥ፡ አጠገብ፡ ላጠገብ፡ ከኖሩ፡ ዘንድ፡ ባለበርበሬው፡ ጤፍን፡ ሲፈልግ ፥ ባለጤፍ፡ በርበሬ፡ የፈለገ፡ እንደ፡ ሆነ፡ የለውጥ፡ መሣሪያ፡ ባይኖር፡ ያለችግር፡ መለዋወጥ፡ ይሆንላቸዋል። ነገር፡ ግን፡ ባለበርበሬው፡ ጤፍን፡ ሲፈልግ፡ ባለጤፉ፡ የሚፈልገው፡ ኣቡጀዲድ፡ እንደ፡ ሆነ፡ እነዚህ፡ ሁለት፡ ጎረ፡ ቤቶች፡ አንድ፡ የሚያስማማቸው፡ የለውጥ፡ መሣሪያ፡ ባይኖር፡ ሊስማሙ፡ አይሆንላቸውም። እንግዲህ፡ የለውጥ፡ መሣሪያ፡ ባይኖር፡ ባለበርበሬው፡ አጠገቡ፡ ያለውን፡ ጤፍ፡ እሽምታለሁ፡ ሲል፡ በርበሬውን፡ ይዞ፡ አቡጀዲድ፡ የሚሸጠውን፡ ሊፈልግ፡ ይሄዳል። ባለአቡጀዲዱንም፡ ነጋዴ፡ ካገኘ፡ በኋላ፡ ምናልባት ነጋዴው፡ ደግሞ፡ እንዲህ፡ ይሰው፡ ይሆናል፤ ወንድሜ፡ ሆይ፡ በከንቱ፡ መድከምኽ፡ እጅግ፡ ያሳዝነኛል። የኔን፡ ኣቡጀዲድ፡ ከፈለግኽ፡ ዘንድ፡ ለጨው፡ ነውና፡ እምሸጠው፡ ጨው፡ እንዳለኽ፡ አምጣና፡ ውሰድ፡ ይለው፡ ይሆናል።

እንሆ፡ ያ፡ ባለበርበሬውም፡ ሰው፡ ጨው፡ የሚሸጠውን፡ ነጋዴ፡ ፈልጎ፡ አግኝቶ፡ ለውጠኝ፡ ቢለው፡ እንዲህ፡ ብሎ፡ ይመልስለት፡ ይሆናል፤ እኔ፡ በርበሬ፡ መልቶኛል፡ ኣሁንስ፡ የጐደለኝ፡ ብረት፡ ድስት፡ ብቻ፡ ነው፤ ብረት፡ ድስት፡ እንዳለህ፡ አምጣልኝና፡ ጨው፡ ልስጥኽ፡ ይለዋል። ነገሩም፡ ሁሉ፡ እንደዚህ፡ ባለበርበሬው፡ ከጎረ፡ ቤቱ፡ ያለውን፡ ጤፍ፡ ለመሸመት፡ ሲል፡ መከራው፡ ሊበዛበት፡ ነበርና ፥ በመካከል፡ ሲዞር፡ የፈለገውንም፡ ሳያገኝ፡ አለጊዜው፡ ወይ፡ ሞቶ፡ ይቅር፡ ነበረ። ደግሞ፡ የግድ፡ ካልሆነበትም፡ በቀር፡ ሁለተኛ፡ ማንኛውንም፡ አንድ፡ ዐይነት፡ ሊለዋወጥ፡ አይከጅልም፡ ነበር። ከመለዋወጡም፡ የተነሣ፡ እያንዳንዱ፡ ሰው፡ ለየብቻው፡ እየሆነ፡ ለኑሮው፡ የሚያስፈልገውን፡ ዕቃ፡ ሁሉ፡ ሊሠራ፡ ነበርና፡ ሰው፡ ሁሉ፡ ዐቅም፡ አንሶት፡ እስከ፡ ዛሬ፡ ድረስ፡ የምድር፡ ሎሌ፡ ሁኖ፡ ሊኖር፡ ነበር።

እንሆ፡ የዓለም፡ ሕዝቦች፡ ሁሉ፡ ይህን፡ ነገር፡ ከጥንት፡ ገዥምረው፡ ተረድተውት፡ የሚስማሙበትን፡ አንድ፡ ዐይነት፡ የለውጥ፡ መሣሪያ፡ ኣውጥተው፡ ሲገበያዩበት፡ እንደ፡ ነበሩ፡ የዓለም፡ ታሪክ፡ ያስረዳናል።

የዱሮ፡ ዘመን፡ ግሪኮች፡ የለውጥ፡ መሣሪያቸው፡ ከብት፡ ነበረ። ከብትንም፡ የለውጥ፡ መሣሪያ፡ ያደረጉት፡ ካንድ፡ ቦታ፡ ወዳንዱ፡ ቦታ፡ ለማንቀሳቀስ፡ የሚመችና፡ ሰው፡ ሁሉ፡ የሚቀበለው፡ ዕቃ፡ ስለ፡ ሆነ፡ ነው። እንግሊዞችም፡ የዱሮ፡ የለውጥ፡ መሣሪያቸው፡ ከብትና፡ ባሪያ፡ ነበረ። የቀሩትም፡ አንዳንዶቹ፡ ሕዝቦች፡ በዓሣና፡ በትንባኾ፡ የሚያስፈልጋቸውን፡ ዕቃ፡ ሲገዛዙ፡ ነበር። በሀገራችንስ፡ ቢሆን፡ እስከ፡ ቅርብ፡ ጊዜ፡ ድረስ፡ ዋናው፡ የለውጥ፡ መሣሪያችን፡ ጨው፡ አልነበረምን፧ ይህ፡ የተጠራው፡ የለውጥ፡ መሣሪያ፡ ሁሉ፡ ግን፡ የማይመች፡ ሆኖ፡ ነበር። ከብትና፡ በሬው፡ ሲከሳ፡ ወይም፡ በበሽታ፡ ሲሞት ፥ ትንባኾውና፡ ዓሣውም፡ ሲበላሽ፡ ጨዉም፡ ጥቂት፡ ውሃ፡ የነካው፡ እንደሆነ፡ ሲና፡ ሲወረዛ፡ ለመለወጥ፡ ለየሰዉ፡ ሁሉ፡ እጅግ፡ ጒዳት፡ ነበረበት። ይህንንም፡ የኋላ፡ ጒዳቱን፡ እየፈራ፡ ሰው፡ ሁሉ፡ በጣም፡ ካልቸገረው፡ በቀር፡ ለለውጥ፡ ይሆነኛል፡ ብሎ፡ ደክሞ፡ ያገኘውን፡ ዕቃ፡ ሰጥቶ፡ ለገዛቸው፡ ፈቃድ፡ አልነበረውም። ብረትና፡ መዳብም፡ ከታወቁ፡ በኋላ፡ መሣሪያዎች፡ እንደ፡ ሆኑ፡ ታይተው፡ ከላይ፡ በተጠሩት፡ የለውጥ፡ መሣሪያዎች፡ ፈንታ፡ ገቡ። ዳሩ፡ ግን፡ ብረትና፡ መዳብም፡ ቢሆኑ፡ እየዛጉና፡ እየተበላሹ፡ እንቢ፡ አሉ። ወዲያውም፡ ከመሬት፡ ውስጥ፡ የሚወጡበት፡ ብልኀት፡ ከታወቀ፡ በኋላ፡ እጅግ፡ በረከቱ። ያለብዙ፡ ድካም፡ ይገኙ፡ ዠመሩ፤በጣምም፡ ረከሱ። ከመርከሳቸውም፡ የተነሣ፡ ለያንዳንዱ፡ ነገር፡ መግዣ፡ የሚያስፈልገው፡ ብረት፡ ወይም፡ መዳብ፡ ሸክሙ፡ እየበዛና፡ እየከበደ፡ ካንዱ፡ ቦታ፡ ወዳንዱ፡ ቦታ፡ ለማንቀሳቀስ፡ የማይመች፡ የማይቻል፡ ሆነ። ስለዚህም፡ ለሸክም፡ የማይከብዱ፡ ካንዱም፡ ቦታ፡ ወዳንዱ፡ ቦታ፡ ያለብዙ፡ ድካም፡ የሚላኩ የማይዝጉና፡ የማይበላሹ፡ ሌሎች፡ የለውጥ፡ መሣሪያዎች፡ ተገኙ። በመላውም፡ ዓለም፡ ታውቀው፡ ተለመዱ። እነሱም፡ ብርና፡ ወርቅ፡ ናቸው፤የመላውም፡ ዓለም፡ ሕዝቦች፡ ምንም፡ ተሰብስበው፡ ተማክረው፡ ባይዋዋሉ፡ በዘመናት፡ ብዛት፡ ለምደዋቸው፡ ብርና፡ ወርቅ፡ የለውጥ፡ መሣሪያዎቻቸው፡ እንዲሆኑ፡ ተስማምተውባቸዋል። ስለዚህም፡ ብርና፡ ወርቅ፡ የተወደዱበት፡ ዋናው፡

ምክንያት፡ የለውጥ፡ መሣሪያዎች፡ ስለ፡ ሆኑ፡ ነው፡ ሰው፡ ሁሉ፡ ብርን፡ ሲፈልግ፡ ብርን፡ ራሱን፡ አይደለም፤ያንን፡ በብር፡ የሚለወጠውን፡ ለኑሮው፡ የሚያስፈልገውን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ሲፈልግ፡ ነው፡ እንጂ። ብርና፡ ወርቅ፡ ሰው፡ ሁሉ፡ በዘመናት፡ ብዛት፡ የተስማማባቸው፡ ምልክቶች፡ ናቸው።

እንሆ፡ አንድ፡ የበርኖስ፡ ሰፊ፡ ጤፍን፡ ከተቀበለ፡ በኋላ፡ ሳንዱ፡ አራሽ፡ አንድ፡ ዐይነት፡ ምልክት፡ ሰጥቶ፡ ይህንን፡ ምልክት፡ ይዘኽ፡ ሄደኽ፡ ከሚስቴ፡ በርኖስ፡ ተቀበል፡ ብሎ፡ እንደሚፈቅድለት፤እንዲሁም፡ አንዳች፡ ነገር፡ ተቀብሎ፡ ብር፡ የሚሰጥ፡ ሰው፡ ሁሉ፡ ከፈቀድኸው፡ ቦታ፡ ሄደሽ፡ የፈለግኸውን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ በዚህ፡ ምልክት፡ ተቀበል፡ ብሎ፡ ብርን፡ ለተቀበለ፡ ሰው፡ እንደ፡ ፈቀደለት፡ ያኽል፡ ነው። ብርና፡ ወርቅን፡ እንደ፡ ምልክት፡ የያዘ፡ ሰው፡ የትም፡ አገር፡ ቢሄድ፡ የፈለገውን፡ ዕቃ፡ ሁሉ፡ ይለውጥበታል። ብርና፡ ወርቅን፡ ስለ፡ ምልክት፡ ተቀብሎ፡ ስንት፡ እንደሚሰጥ፡ የተወሰነ፡ ነውና፤ማንም፡ ሰው፡ ብርና፡ ወርቅን፡ ሲቀበል፡ ደክሞ፡ ካገኘው፡ ዕቃ ፥ ስንት፡ እንደሚሰጥ፡ አይጠፋውም። ብርና፡ ወርቅ፡ ምንም፡ የለውጥ፡ መሣሪያ፡ ቢሆኑ፡ እንደ፡ ሌላው፡ ለኑሮ፡ የሚያስፈልገው፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ከመሬት፡ የሚወጡት፡ በድካም፡ ነው። ይልቍንም፡ ብርና፡ ወርቅን፡ ስመቀበል፡ የሚደከመው፡ ድካም፡ ከሌላው፡ ድካም፡ ሁሉ፡ ይበልጣል። ከዚህ፡ ምክንያት፡ የተነሣ፡ ምልክት፡ እንዲሆኑት፡ ብርንና፡ ወርቅን፡ የፈለገ፡ ሰው፡ እንደ፡ ተደከመባቸው፡ መጠን፡ የሠራውን፡ ወይም፡ ያለውን፡ ዕቃ፡ ይሰጥባቸዋል። ዋጋ፡ ማለት፡ የሥራ፡ መለኪያ፡ ነውና፤ብርና፡ ወርቅም፡ ካንዱ፡ እጅ፡ ወዳንዱ፡ እጅ፡ ሲያልፉ፡ እንደ፡ ተደከመባቸው፡ መጠን፡ ዋጋ፡ እየተሰጠ፡ ነው። ስለዚህም፡ ብርና፡ ወርቅ፡ እንደ፡ ሌላው፡ ምልክት፡ ሁሉ፡ የሚሳቱ፡ ምልክቶች፡ አይደሉም። እነዚህም፡ ሁለቱ፡ የለውጥ፡ መሣሪያዎች፡ ባይኖሩ፡ ሰው፡ ምድሮን፡ ሎሸንፎ፡ ጌታዋ፡ መሆን፡ አይችልም፡ ነበር። መርከብ ፥ የምድር፡ ባቡር ፥ጋሪ፡ ምንም፡ የተመሰገኑ፡ የሕዝብ፡ ማቃረቢያ፡ መሣሪያዎች፡ ቢሆኑ፡ ምንም፡ ፍጥነት፡ ቢያበዙ፡ እንደ፡ ብርና፡ እንደ፡ ወርቅ፡ ኣያቃርቡም። ብርና፡ ወርቅም፡ አውራው፡ የሚመሰገኑበት፡ ምክንያት፡ በብዙ፡ ትንንሽ፡ ክፍሎች፡ እየተከፋፈሉ፡ ሰው፡ ከየሥራው፡ ትንንሽ፡ ክፍል፡ በነሱ፡ አማካይነት፡ እንዲለዋወጥ፡ ስለ፡ አደረጉ፡ ነው።

እስቲ፡ አሁን፡ ከገበያ፡ ሄደን፡ ባንድ፡ ተሙን፡ ዳቦ፡ ስንገዛ፡ የስንት፡ ሰዎች፡ የድካማቸውን፡ ትንንሽ፡ ክፍል፡ መግዛታችን፡ ነው። ያንድ፡ ተሙን፡ ዳቦ፡ የሚጋገረው፡ ካራሹ፡ ከጐልጓዩ። ካጫጁ ፥ ከወቂው ፥ ከጫኙ፡ ከፈጫይቱ ፥ ምጣዱን፡ ከሠራችው፡ የሸክላ፡ ሠሪ፡ ከዕንጨት፥ለቃሚው፡ ከብዙዎችም፡ ሌሎች፡ ሠራተኞች፡ ብዙ፡ ትንንሽ፡ ድካም፡ እየተከፈለ፡ ተጠራቅሞ፡ አይደለምን፤ባገራችን፡ ብር፡ ከታወቀ፡ ብዙ፡ ጊዜው፡ ነው። ነገር፡ ግን፡ እንደ፡ ዛሬው፡ አልተለመደም፡ ነበር። ዱሮ፡ ከትልልቅ፡ ለውጥ፡ በቀር፡ ትንንሽ፡ ለውጥ፡ እንዲለዋወጥ፡ ሕዝቡን፡ የሚያስችል፡ የለውጥ፡ መሣሪያ፡ ኣልነበረምና፤የሚያስፈልገው፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ባገሩ፡ መልቶ፡ ሳለ፡ የኢትዮጵያ፡ ሰው፡ ሲቸግር፡ ነበር። ዱሮ፡ ተሙን፡ ሩብ፡ አላድ፡ ሳይለመዱ ፥ ጐመን፡ እገዛለሁ፡ የሚል፡ ሰው፡ አልነበረም። ባንድ፡ ሙሉ፡ ብር፡ ገዝቶ፡ እንዳያስቀምጠው፡ አንድ፡ ቀን፡ ሳያድር፡ እንዲበሰበስ፡ ዐወቀው፤ከብርም፡ ባነሰ፡ ነገር፡ እንዳይገዛው፡ ከብር፡ ያነሰ፡ የለውጥ፡ መሣሪያ፡ አልነበረም። ስለዚህ፡ የዚያን፡ ጊዜ፡ ጐመን፡ ሊበላ፡ የፈለገ፡ ሰው፡ ወይም፡ ለምኖ፡ ወይም፡ ዘርቶ፡ አብቅሎ፡ ነው። ያለመነና፡ ያልዘራ፡ ሰው፡ ግን፡ ጐመንን፡ አግኝቶ፡ ለመብሳት፡ አይሆንለትም፡ ነበር። እንዲሁም፡ የዚያ፡ ጊዜ፡ ሰው ወደ፡ መንገድ፡ ሲሄድ፡ ሥንቁን፡ ተሸክሞ፡ ከቤቱ፡ ካልተነሣ፡ ሰቀር፡ መከራውና፡ ችጋሩ፡ ይበዛበት፡ ነበር። ለብዙ፡ ቀን፡ የሚያስፈልገውን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ባንድ፡ ጊዜ፡ ካልሸመት፡ በቀር፡ የዕለት፡ ምግቡን፡ የሚያገኝበት፡ የለውጥ፡ መሣሪያ፡ አልነበረም። ዛሬ፡ ግን፡ ለጊዜው፡ የሚበቃውን፡ በተሙን፡ እየገዛ፡ ማንም፡ ሰው፡ ቢሆን፡ መንገድ፡ ሲወጣ፡ አይቸገርም። ባላገሩም፡ ዱሮ፡ ለማኙ፡ መንገደኛ፡ ሲበዛበት፡ ሲመረር፡ የነበረው፡ ዛሬ፡ ባጠገቡ፡ የሚሄደው፡ መንገደኛ፡ ሲያንስ፡ ያዝናል። ተሙን፡ ሩብ፡ አላድ ፣ ከታወቀ፡ በኋላ፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ርስ፡ በርሱ፡ ይጠቃቀም፡ ዠመር፤ነቃም። ስለዚህም፡ የለውጥ፡ መሣሪያውን፡ በትንንሽ፡ ክፍሎች፡ ከፍለው፡ ትንንሾቹን፡ ክፍሎች፡ በገራቸው፡ ሕዝብ፡ ውስጥ፡ እንዲለመዱ፡ ስላደረጉ፡ ለዐፄ፡ ምኒልክ፡ ትልቅ፡ ምስጋና፡ ይገባቸዋል። እውነት፡ ነው፤የዛሬው፡ የለውጥ፡ መሣሪያችን፡ የተደላደለ፡ መሠረት፡ የለውምና፡ ሕዝቡ፡ ብዙ፡ ይጐዳበታል። የሚጐዳበትንም፡ ምክኝያት፡ ቀኋይተን፡ እናስረዳለን። ስለ፡ ሆነ፡ ግን፡ ዠርማሪው፡ ዐፄ፡ ምኒልክ፡ ናቸውና፤ለዚሁም፡ ምክንያት፡ ተብሎ፡ ምንም፡ ቢሆን፡ ለርሳቸው፡ የሚገባው፡ ምስጋና፡ አይቀርም።

እንሆ፡ ማንኛውም፡ ሕዝብ፡ ከፍ፡ ወዳለው፡ የዕውቀት፡ ደረጃ፡ የሚደርስና፡ ሀብት፡ የሚያገኝ፡ በውስጡ፡ ያሉት፡ የያይነቱ፡ ዕቃ፡ ሠራተኞች፡ በቶሎ፡ እየተገናኙ፡ የተለዋወጡ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ነው። ባገሩ፡ ውስጥ፡ ያለው፡ የለውጥ፡ መሣሪያ፡ ካነሰ፡ ዘንድ፡ ግን፡ የምድር፡ ባቡርና፡ መንገድ፡ ምንም፡ ቢበዙ፡ ትልቅ፡ ጥቅም፡ አይሆኑም። የዚህ፡ ዓለም፡ ሕዝቦች፡ የለውጥ፡ መሣሪያዎቻቸው፡ ብርና፡ ወርቅ፡ ብቻ፡ ስለ፡ ሆኑ፡ ብርና፡ ወርቅ፡ ያነሰበት፡ ሕዝብ፡ ከፍ፡ ወዳለው፡ የዕውቀት፡ ደረጃ፡ ደርሶ፡ ሀብታም፡ ሊሆን፡ አይችልም። እንሆ፡ ነገሩ፡ እንደተገለጠልን ፥ ብርና፡ ወርቅ፡ ላንድ፡ ሕዝብ፡ ሀብትም፡ የሚሆኑት፡ የሚበሉና፡ የሚቈረጠሙ፡ ሆነው፡ አይደለም። ሕዝሱ፡ የሥራውን፡ ሥራ፡ ሲለዋወጥ፡ መሣሪያዎች፡ ስለ፡ ሆኑት፡ ነው፡ እንጂ፤ይህነንም፡ ካወቅን፡ ዘንድ፡ ባንድ፡ አገር፡ ውስጥ፡ እነዚህ፡ የለውጥ፡ መሣሪያዎች፡ በእንዴት፡ ያለ፡ ምክንያት፡ እንዲበዙ ፥ በእንዴትስ፡ ያለ፡ ምክንያት፡ እንዲያንሱ፡ እንመርምር።

# ፱ኛ፡ ምዕራፍ።

ወዳንዱ፡ አገር፡ ብርና፡ ወርቅ፡ ከገባ፡ በኋላ፡ ከሕዝቡ፡ ውስጥ፡ ያለው፡ እያንዳንዱ፡ ሰው፡ ከብሩና፡ ከወርቁ፡ የሚያገኝበትና፡ የሚያጣበት፡ መንገድ፡ ልዩ፡ ልዩ፡ ነውና፡ ተቈጥሮ፡ አይጨረስልንም፤ ደግሞ፡ በሒሳባችን፡ አይገባም። ወዳንድ፡ መንግሥት፡ አገር፡ የሚመጣው፡ ብርና፡ ወርቅ፡ የሚበዛበትና፡ የሚያንስበት፡ ምክንያት፡ ግን፡ ታውቆ፡ የተለየ፡ ነው። ይህም፡ ምክንያት፡ በቶሎ፡ እንዲገለጽልንና፡ መሪ፡ እንዲሆነን ፡ ቀጥሎ፡ የተጻፈውን፡ ቃል፡ አጥብቀን፡ እናስተውል ።

እንሆ፡ ያለፋ፡ ቆዳ፡ የሚረክስ፡ በከብት፡ አራጁ፡ ቤት ፡ ነው ። የሚከበረውም፡ ከፋቂው፡ ቤት፡ ነው ። የለፋ፡ ቈርበት፡ ግን፡ የሚረክሰው፡ ከፋቂው፡ ቤት፡ ነው ። አራጁም፡ ከፈለገው፡ ዘንድ፡ ብዙ፡ ዋጋ፡ ይፈጅበታል ። እንዲሁም፡ ጥጥ ፡ ታርሶ፡ በበቀለበት፡ አገር፡ ርካሽ፡ ነው ። ወደ፡ ሸማኔው ፡ ሲደርስ፡ ግን፡ ይከበራል ። ሸማ፡ ግን፡ በርካሽ፡ ዋጋ፡ የሚገኝ ፡ ከሸማኔው፡ ቤት፡ ነው ። ጥጠን፡ ዘርቶ፡ ላበቀለው፡ ሰው፡ ግን ፡ ሸማው፡ ውድ፡ ይሆንበታል ። እንግዲህ፡ ማናቸውንም፡ ሌላ ፡ ዐይነት፡ ዕቃ፡ ብንመለከት፡ ዕቃው፡ ሁሉ፡ አጠቃቀሙ፡ ወደ ፡ ታወቀበት፡ ቦታ፡

ይሄዳል ። አጠቃቀሙ፡ ግን፡ በዚያው ፡ በታወቀበት፡ ቦታ፡ ይረከሳል ። አጠቃቀሙ፡ ወዳልታወቀበትም፡ ቦታ፡ ሲደርስ፡ እንደ፡ ገና፡ ይከብራል። እንግዲህ፡ በምሳሌ ፡ ብንነጋገር ፥ ጥጥ፡ እንዴት፡ እንደሚጠቅም፡ የሚያውቅበት ፡ ሸማኔ፡ ነውና ፤ጥጥ፡ ሁሉ፡ ዞሮ፡ ዞሮ፡ ወደ፡ ሸማኔ፡ ይሄዳል ። የጥጥም፡ አጠቃቀም፡ በሸማ፡ ነው ። ሸማም፡ የሚረከስ፡ በሸማኔ፡ ቤት፡ ነው ። አጠቃቀሙን፡ ሳያውቅበት፡ ቀርቶ፡ ጥጡን ፡ ወደ፡ ዐዋቂው፡ ሸማኔ፡ በወሰደው፡ ጊዜ፡ እጥጥ፡ ተካይ፡ ቤት ፡ ተመልሶ፡ ሲደርስ፡ ሸማ፡ እንደ፡ ገና፡ ይከብራል ።

እንሆ፡ የብርና፡ የወርቅም፡ ነገር፡ እንደዚሁ፡ ነው። የዕውቀታቸው፡ ደረጃ፡ ከፍ፡ ያለ፡ ሥራቸውም፡ ልዩ፡ ልዩ፡ ሁኖ ፡ የሠሩትን፡ ዕቃ፡ የሚለዋወጡ፡ ሕዝቦች፡ ሥራ፡ ከማያውቁ ፡ ሕዝቦች፡ ይልቅ፡ የለውጥን፡ መሣሪያ፡ አጠቃቀም፡ ያውቁበታልና፤የሠሩትን፡ ሥራ፡ እየሰጡበት፡ የለውጥ፡ መሣሪያ፡ የሆነው፡ ብርና፡ ወርቅ፡ ሁሉ፡ ወደነሱ፡ ይሄዳል ። ሲበደሩትም ፡ አጠቃቀሙን፡ ስላወቁበት፡ የብርና፡ የወርቅ፡ ወለድ፡ በነሱ ፡ አገር፡ ያንሳል ። ሸማ፡ በሸማኔ፡ ቤት፡ እንደሚረከሰው ፥ እንግዲህ፡ ለኑሮው፡ የሚያስፈልገውን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ራሱ፡ ሊሠራ፡ የሚችል፡ ሕዝብ፡ ባገሩ፡ ውስጥ፡ ያለውን፡ ብርና፡ ወርቅ ፡ ርስ፡ በራሱ፡ ይለዋወጥበታል፡ እንጂ፤ልለውጥበት፡ ሲል ፡ ወደ፡ ውጭ፡ አገር፡ አይሰደውም ። ለጊዜውም፡ ቢሰደው፡ እንደ፡ ቆዳ ፥ ሠም፡ የዝኆን፡ ጥርስ፡ የመሰለውን፡ ያልተሠራ፡ ነገር፡ ለመግዛት፡ ነውና፡ ይህ፡ ሁሉ፡ ዕቃ፡ ከተሠራ፡ በኋላ ፡ ለኑሮው፡ የሚበቃውን፡ ያኸል፡ አስቀርቶለት፡ ሕዝቡ፡ በሥራ ፡ ወዳልሠለጠነበት፡ አገር፡ ትርፉን፡ እንደ፡ ገና፡ ሰዶ፡ ዕቃው፡ ሳይሠራ፡ የፈጀበትን፡ ብርና፡ ወርቅ፡ ይመልስበታል ።

ይኸውም፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ በያመቱ፡ ያልተሠራ ፡ ቆዳ፡ ወደ፡ ውጭ፡ አገር፡ ይሰዳል ። ያንዱም፡ ፈረሱላ፡ ቆዳ ፡ ዋጋ፡ ባገራችን፡ እስከ፡ ፲፫፡ ብር፡ ነው ። ይህን፡ ዐሥራ፡ ሦስት፡ ብር፡ ግን፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ርስ፡ በርሱ፡ እንዳይለዋወጥበት፡ በየሥራው፡ ስላልሠለጠነ፡ በሥራ፡ የሠለጡኑ፡ ሕዝቦች ፡ የሠሩትን፡ ዕቃ፡ ሲገዛ ፡ ስለ፡ ቆዳው፡ ዋጋ፡ የተቀበለውን፡ ብር፡ እንደ፡ ገና፡ ይመልሰዋል። አንድ፡ ፈረሱላ፡ ቆዳ፡ ባዲስ፡ አበባ፡ ዋጋው፡ ፲፫፡ ብር፡ ብቻ፡ ነው ። እፈረንጅ፡ አገር፡ ሄዶ፡ ተሠርቶ ፡ የተመለሰው፡ ቆዳ፡ ግን፡ አንዱ፡ ፈረሱላ፡ እስከ፡ ፲፱፡ ብር ፡ ድረስ፡

ይሰጥበታል ። ስለዚህም፡ የኤሮፓ፡ ሰዎች፡ ለቆዳ፡ ሲሉ፡ ለኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ብርና፡ ወርቅ፡ ሲሰጡት፡ ቆዳው ፡ ከተሠራ፡ በኋላ፡ ለኑሯቸው፡ የሚበቃቸውን፡ እህርተው ፡ የተረፈውን፡ ቆርበት፡ እንደ፡ ገና፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ ሰደው ፡ ያን፡ በመዠመሪያ፡ ያወጡትን፡ ፲፫፡ ብር፡ ይመልሱበታል ። ቆዳውም፡ ራሱ፡ ተሠርቶ፡ በምትኩ፡ እነቈጫ ፥ እነአቡጀዲድ፡ ሌሎችም፡ ዕቃዎች፡ መጥተው፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ የመጣውን፡ ብር፡ ወደ፡ ኤሮፓና፡ ወደ፡ አሜሪካ፡ ይመልሱለታል ። እንሆ፡ ሸማኔ፡ ብር፡ ሰጥቶ፡ ካንድ፡ ባላገር፡ ጥጦ፡ ቢገዛ፡ ሸማውን፡ ከሠራ፡ በኋላ፡ ለራሱ፡ ትርፍ፡ አስቀርቶ፡ የቀረውን ፡ ሸማ፡ ለባላገሩ፡ ይሸጠዋል ። በዚሁም፡ ያ፡ በመዠመሪያ ፡ ለጥጡ፡ ዋጋ፡ ያወጣው፡ ብር፡ ይመለስለታል ። በሕዝቦችም ፡ ትዳር፡ እንዲሁ፡ ነው ። በሥራ፡ የሠለጠኑ፡ ሕዝቦች፡ ብርና ፡ ወርቅ፡ ቢያወጡ፡ ትርፍ፡ ካገኙበት፡ በኋላ፡ ይመለስላቸዋል ። ስለ፡ ሆነ፡ ግን፡ ሸማኔው፡ ብዙ፡ ብር፡ ትርፍ፡ የሚገባለት ፡ ሸማውን፡ የሠራበት፡ ጥጥ፡ ሳይገዛው፡ የራሱ፡ የሆነ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ነው፡ እንጂ፤ጥጡን፡ ከውጭ፡ ከገዛው፡ ሸማውን፡ ሠርቶ ፡ ሲሸጥ፡ የሚያገኘው፡ ትርፍ፡ የድካመን፡ ዋጋ፡ ብቻ፡ ነው ። እንዲሁም፡ ያልተሠራውን፡ ዕቃ፡ ከውጭ፡ አገር፡ እያስመጣ፡ ይቶ፡ እንደ፡ ገና፡ የሚሸጥ፡ ሕዝብ፡ የድካሙን፡ ዋጋ፡ ያገኛል፡ እንጂ፤ሌላ፡ ትርፍ፡ ኣይገባለትም። ትጉ፡ ሕዝብ፡ ከሆነ፡ ዘንድ፡ ግን፡ በድካሙ፡ የሚያገኘው፡ ትርፍ፡ ትልቅ፡ ሊሆን፡ ይችላል። ብርና፡ ወርቅም፡ በዝተው፡ የሚሄዱ፡ ከውጭ፡ አገር፡ ሳይገዛ፡ ከመሬቱ፡ ውስጥ፡ ያወጣውን፡ ነገር፡ ብቻ፡ ሠርቶ ፥ከሠራው፡ ዕቃ፡ ለኑሮው፡ የሚበቃውን፡ ያኸል፡ አስቀርቶ፡ የተረፈውን፡ ዕቃ፡ ለውጭ፡ ሕዝቦች፡ ወደሚሸጥ፡ ኣገር፡ ነው። ይህነን፡ የሚያደርግ፡ ግን፡ አንድም፡ ሕዝብ፡ በኤሮፓ፡ የለም። እንደያገሩ፡ ሁኔታ፡ ይነስ፡ ይደግ፡ እንጂ፡ የኤሮፓ፡ ሕዝቦች፡ ኑሯቸው፡ ሁሉ፡ ከውጭ፡ አገር፡ ያልተሠራውን፡ ዕቃ፡ እያስመጡ፡ ነው። ሕዝቡ፡ በሥራ፡ ሠልጥኖ፡ ቢሆን፡ ግን፡ እንደ፡ ኢትዮጵያ፡ ብርና፡ ወርቅ፡ የሚበዛበት፡ አገር፡ አልነበረም። ባገራችን፡ ሁሉ፡ ነገር፡ ሊበቅል፡ ይችላል፤ ሁሉ፡ ነገር፡ ሊሠራ፡ ይችላል። የበቀለውና፡ የተሠራውም፡ ከሕዝብ፡ ተርፎ፡ ብዙ፡ ብርና፡ ወርቅ፡ ወደ፡ ሀገራችን፡ ያመጣ፡ ነበር። ብርና፡ ወርቅም፡ እየበዛ፡ ቢሄድ፡ መለዋወጡ፡ እየፈጠነለት፡ የኢትዮጵያ፡ ሰው፡ በያዘው፡ ሥራ፡ ጠንክሮ፡ እየሠራ፡ እየተለዋወጠ፡ እየተደጋገፈ፡ ከፍ፡

ያለውን፡ የዕውቀት፡ ደረጃ፡ ለማግኘትና፡ ብዙ፡ ሀብት፡ ለማከማቸት፡ ይሆንለት፡ ነበር።

መንግሥቱም፡ በርትቶ፡ በዓለም፡ ነገሥታት፡ ፊት፡ ያድግ፡ ነበር። ብርና፡ ወርቅ፡ መፈለጉ፡ እኮ፡ ስለ፡ መሣሪያነቱ፡ ነው። የለውጥ፡ መሣሪያም፡ ባልበዛበት፡ አገር፡ ከሕዝቡ፡ አንዳንድ፡ ሰው፡ ከየሥራው፡ የተረፈውን፡ ለመለዋወጥ፡ ይቸግረዋልና፤በየሥራው፡ ሊሠለጥን፡ አይችልም። እንዲሁም፡ ደግሞ፡ በሥራ፡ ያልሠለጠነ፡ ሕዝብ፡ የለውጥ፡ መሣሪያ፡ ሲያገኝ፡ ሊለዋወጥበት፡ አይችልምና፤የለውጡን፡ መሣሪያ፡ ለሚፈልጉት፡ ሕዝቦች፡ መልሶ፡ ይሸጠዋል። ስለዚህም፡ ሕዝቡ፡ እንዲበለጽግና፡ እንዲበረታ፡ የሚፈልግ፡ መንግሥት፡ ከሁሉ፡ ነገር፡ በፊት፡ ለሕዝቡ፡ ኑሮ፡ የሚያስፈልግ፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ባገሩ፡ ውስጥ፡ እንዲሠራ፡ መጣጣር፡ ይገባዋል። ይህንንም፡ ካደረገ፡ ዘንድ፡ ብርና፡ ወርቅ፡ በዝተው፡ ወዳገሩ፡ እንዲገቡለት፡ የታወቀ፡ ነው። ብርና፡ ወርቅም፡ በብዙ፡ ቍጥር፡ ከመርከብ፡ ከምድር፡ ባቡር ፥ ከጋሪ፡ ከሌላም፡ ነገር፡ የበለጠ፡ የለውጥ፡ አፋጣኞች፡ መሣሪያዎች፡ ናቸውና፤የሠሩትን፡ ሥራ፡ የሚለዋወጡ፡ ሠራተኞች፡ እስኪለዋወጡ፡ ድረስ፡ በከንቱ፡ የሚባክንባቸው፡ ድካም፡ እያነሰ፡ ሠራተኞቹም፡ በየያዙት፡ ሥራ፡ ለመሥራት፡ የሚተርፉቸው፡ ጊዜ፡ እየበዛ፡ ይሄዳል። የሚሠሩትም፡ ትርፍ፡ ሥራ፡ ላገሩ፡ ሀብት፡ ጭማሪም፡ ይሆናል። ዕንጨት፡ በሌለበት፡ ቦታ፡ መጥረቢያ፡ አያስፈልግምና፤ መጥረቢያው፡ ወደ፡ ተፈለገበት፡ ቦታ፡ ይሸጣል። ዕንጨት፡ ባለበት፡ ቦታ፡ ግን፡ መጥረቢያ፡ ይፈለጋል። መጥረቢያውም፡ ሲበዛ፡ የሚቈረጠው፡ ዕንጨት፡ ይበዛል። የብርና፡ የወርቅም፡ ነገር፡ እንደዚሁ፡ ነው። እነዚህ፡ ሁለት፡ የለውጥ፡ መሣሪያዎች፡ በያይነታቸው፡ በሥራ፡ ሠልጥነው፡ ርስ፡ በርሳቸው፡ በማይለዋወጡ፡ ሕዝቦች፡ እጅ፡ አይቀመጡም። ወደሚፈለጉበት፡ ቦታ፡ ይሸጣሉ፡ እንጂ፤በየሥራው፡ በሠለጠነ፡ ሕዝብ፡ እጅ፡ ሲገቡ፡ ግን ርስ፡ በርሳቸው፡ መለዋወጡን፡ እያፋጠኑለት፡ እያንዳንዱ፡ ሰው፡ በየሥራው፡ እንዲሠለጥንና፡ የበለጠ፡ ሀብት፡ እንዲያገኝ፡ ይረዱታል።

እንሆ፡ ብርና፡ ወርቅ፡ ምን፡ እንደ፡ ሆኑ፡ በምንስ፡ ምክንያት፡ እንዲያንሱና፡ እንዲበዙ፡ ተረዳነው። እንግዲህም፡ ሥራቸውን፡ እንመርምር።

# ፲ኛ፡ ምዕራፍ።

የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ በያመቱ፡ ከሚሸጠው፡ ዕቃ፡ የሚገዛው፡ ዕቃ፡ እንደ፡ በዛ፡ ከዚህ፡ ቀደም፡ አስረድተናል። ትርፉንም፡ ዕቃ፡ የገዛው፡ በምን፡ እንደ፡ ሆነ፡ ብንመረምር፡ ከውጭ፡ ሕዝቦች፡ ብዙ፡ ገንዘብ፡ መበደሩን፡ ተረዳነው። እንግዲህ፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ እንዳሁኑ፡ መበደሩን፡ ትቶ፡ ለወደ፡ ፊቱ፡ የሚገዛውና፡ የሚሸጠው፡ ዋጋ፡ ትክክል፡ የሆነለት፡ እንደሆን፡ ይጠቀማልን፤ለዚህ፡ ጥያቄ፡ መልሱ፡ ግን፡ ይህ፡ ነው። እንደ፡ ዛሬው፡ ሁኔታ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ሕዝቡ፡ አይጠቀምም። ካደረገ፡ ዘንድ፡ ብርና፡ ወርቅ፡ በዝተው፡ ወዳገሩ፡ እንዲገቡለት፡ የታወቀ፡ ነው። ብርና፡ ወርቅም፡ በብዙ፡ ቍጥር፡ ከመርከብ ፥ ከምድር፡ ባቡር ፥ ከጋሪ፡ ከሌላም፡ ነገር፡ የበለጡ፡ የለውጥ፡ አፋጣኞች፡ መሣሪያዎች፡ ናቸውና፤የሠሩትን፡ ሥራ፡ የሚለዋወጡ፡ ሠራተኞች፡ እስኪለዋወጡ፡ ድረስ፡ በከንቱ፡ የሚባክንባቸው፡ ድካም፡ እያነሰ፡ ሠራተኞቹም፡ በየያዙት፡ ሥራ፡ ለመሥራት፡ የሚተርፋቸው፡ ጊዜ፡ እየበዛ፡ ይሄዳል። የሚሠሩትም፡ ትርፍ፡ ሥራ፡ ላገሩ፡ ሀብት፡ ጭማሪም፡ ይሆናል። ዕንጨት፡ በሌለበት፡ ቦታ፡ መጥረቢያ፡ አያስፈልግምና፤መጥረቢያው፡ ወደ፡ ተፈለገበት፡ ቦታ፡ ይሸጣል። ዕንጨት፡ ባለበት፡ ቦታ፡ ግን፡ መጥረቢያ፡ ይፈለጋል። መጥረቢያውም፡ ሲበዛ፡ የሚቈረጠው፡ ዕንጨት፡ ይበዛል። የብርና፡ የወርቅም፡ ነገር፡ እንደዚሁ፡ ነው። እነዚህ፡ ሁለት፡ የለውጥ፡ መሣሪያዎች፡ በያይነታቸው፡ በሥራ፡ ሠልጥነው፡ ርስ፡ በርሳቸው፡ በማይለዋወጡ፡ ሕዝቦች፡ እጅ፡ አይቀመጡም። ወደሚፈለጉበት፡ ቦታ፡ ይሸጣሉ፡ እንጂ፤ በየሥራው፡ በሠለጠነ፡ ሕዝብ፡ እጅ፡ ሲገቡ፡ ግን፡ ርስ፡ በርሳቸው፡ መለዋወጡን፡ እያፋጠኑለት፡ እያንዳንዱ፡ ሰው፡ በየሥራው፡ እንዲሠለጥንና፡ የበለጠ፡ ሀብት፡ እንዲያገኝ፡ ይረዱታል።

እንሆ፡ ብርና፡ ወርቅ፡ ምን፡ እንደ፡ ሆኑ፡ በምንስ፡ ምክንያት፡ እንዲያንሱና፡ እንዲበዙ፡ ተረዳነው። እንግዲህም፡ ሥራቸውን፡ እንመርምር።

ከውጭ፡ አገር፡ የሚመጣለት፡ ዕቃ፡ ያልተሠራ ፥ ካገሩ፡ ወደ፡ ውጭ፡ አገር፡ የሚሰደው፡ ዕቃ፡ ግን፡ የተሠራ፡ ቢሆን፡ ማን፡ ትርፍ፡ ድካም፡ አይሄድበትም፡ ነበርና፤ሕዝቡ፡ ይጠቀም፡ ነበር። እንደ፡ ዛሬው፡ ሁኔታ፡

ግን፡ ሕዝቡ፡ የሚገዛውና፡ የሚሸጠው፡ ዕቃ፡ ዋጋው፡ እዚህ፡ ምንም፡ ትክክል፡ ቢሆን፡ ተሠርቶ፡ የሚመጣው፡ ዕቃ፡ ስለ፡ መጣበት፡ መንገድ፡ ርቀት፡ ዋጋ፡ እየጨመረ፡ ከዚህ፡ የሚሄደው፡ ዕቃ፡ ግን፡ ሄዶ፡ የሚሠራበት፡ ቦታ፡ ስለ፡ ራቀ፡ ዋጋ፡ እያጐደለ፡ ነው፡ እንጂ፤የገቢውና፡ የወጨው፡ ዕቃ፡ በእውነት፡ ትክክል፡ ሆኖ፡ ኣይደለም። ስለዚህ፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ሲገዛ፡ ብዙ፡ ዋጋ፡ እየሰጠ፡ ሲሸጥ፡ ግን፡ ጥቂት፡ ዋጋ፡ እየተቀበለ፡ ነውና፤ጒዳት፡ አይቀርለትም። ደግሞም፡ ሌላ፡ ጥያቄ፡ እንጠይቅ። የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ በያመቱ፡ ከሚገዛው፡ ዕቃ፡ ዋጋ፡ የሚሸጠው፡ ዕቃ፡ ዋጋ፡ ቢበዛ፡ ሕዝቡ፡ ይጠቀምበታልን፤የዚሁም፡ ጥያቄ፡ መልስ፡ እንደ፡ ፊተኛው፡ ነው። ሕዝቡ፡ የሚሸጠው፡ ዕቃ፡ ያልተሠራ፡ ከሆነ፡ ዘንድ፡ ሕዝቡም፡ ባተረፈው፡ ብርና፡ ወርቅ፡ ከውጭ፡ አገር፡ መሣሪያ፡ አስመጥቶ፡ ካልሠለጠነበት፡ ብር፡ ቢሰበሰብ፡ ለሕዝቡ፡ አንዳች፡ ጥቅም፡ አይሆነውም። ብርና፡ ወርቅ፡ ለሕዝቡ፡ እውነተኛ፡ ጥቅም፡ የሚሆነው፡ በሕዝቡ፡ ውስጥ፡ አንዳንዱ፡ ሰው፡ ርስ፡ በርሱ፡ ሲለዋወጥ፡ ረጅ፡ መሣሪያ፡ ሲሆኑ፡ ነው፡ እንጂ፡ በያንዳንድ፡ ባላገር፡ እንቅብ፡ ውስጥ፡ ተቈልለው፡ ቢቀመጡ፡ አይደለም። አንድ፡ ባላገር፡ ካሉት፡ ከብቶች፡ በያመቱ፡ አንዳንዱን፡ በ፩፡ በ፻፡ ብር፡ እየሸጠ፡ ባ፲፡ ብር፡ ልብሱን፡ እየገዛ፡ ፳፡ ፳፡ ብር፡ ከምድር፡ በታች፡ ቢቀብር፡ ለባላገሩ፡ ትርፍ፡ መሆኑ፡ ነውን፤ ብር፡ ኣይበላ ፥ አይቈረጠም፤ላሚቱ፡ ከተሸጠችበት፡ ፩፡ ብር፡ ኻያ፡ ብር፡ ቢቀበር፡ ላሚቱ፡ ታርዳ፡ የሥጋዋ፡ ሢሶ፡ ትበልቶ፡ ሁለቱ፡ እጅ፡ በከንቱ፡ እንደ፡ ተጣለ፡ ያኽል፡ ነውና፤እንደዚህ፡ ያለው፡ ባላገር፡ አይረባም። ላሚቱን፡ በ፩፡ ብር፡ ሸጦ፡ ባ፲፡ ብር፡ ልብሱን፡ ገዝቶ፡ በ፳፡ ብር፡ የተሻለ፡ የእርሻ፡ መሣሪያ፡ ገዝቶ፡ ለርሱና፡ ለቤተ፡ ሰቦቹ፡ የሚሆን፡ እኽል፡ አብዝቶ፡ ቢያገባ፡ ግን፡ ብልኅ፡ ይባል፡ ነበር።

በሕዝቦቹም፡ ትዳር፡ ልክ፡ እንደዚሁ፡ ነው። ራሱ፡ ሳይሠራ፡ ከመሬቱ፡ እየተበደረ፡ እየሸጠ፡ ብዙ፡ ብር፡ ሰብስቦ፡ የሚያስቀምጥ፡ ሕዝብ፡ የማይረባ፡ ሕዝብ፡ ነው። ይህንንም፡ ሲያደርግ፡ መሬቱ፡ ፍጉ፡ እየሄደበት፡ በቶሎ፡ አርጅቶ፡ እኽል፡ ማብቀሉን፡ እንዲያቋርጥ፡ ማፋጠኑ፡ ነው። በኋላ፡ ልጆቹና፡ የልጅ፡ ልጆቹ፡ በረኃብ፡ እንዲያልቁ፡ የታወቀ፡ ነው። በሥራ፡ ያልሠለጠነውም፡ ሕዝብ፡ የሰበሰበው፡ ብርና፡ ወርቅ፡ በያንዳንዱ፡ ሰው፡ ቤት፡ ሥራ፡ ፈቶ፡ መቀመጡ፡ ቀርቶ፡ ተሰብስቦ፡ ወደ፡

ባንክ፡ ገብቶ፡ ወለድ፡ ቢያተርፍ፡ ለእንደዚህ፡ ያለው፡ ሕዝብ፡ ጥቅም፡ አይሆነውም። ለጊዜውም፡ ወለድ፡ ቢያመጣ፡ ጥቂት፡ ብር፡ ይጨመራል፡ እንጂ፤ሌላ፡ ትርፍ፡ አያገባም። ወለዱስ፡ የሚገባው፡ ከምን፡ ዘንድ፡ ነው። ከገዛ፡ አገሩ፡ መሬት፡ ኣሠራሩ፡ የሚበደረው፡ ብድር፡ ካለፈው፡ ዓመት፡ ይልቅ፡ ሊበዛ፡ አይደለምን።

እንሆም፡ ስድስት፡ ላም፡ ያለው፡ ባላገር፡ አንዲት፡ ላም፡ በ፴፡ ብር፡ ሸጦ፡ ወለድ፡ እንዲያመጣለት፡ ሲል፡ ሰውን፡ ብር፡ ላንድ፡ ነጋይ፡ ቢያበድር፡ ነጋዴውም፡ ሠላሳውን፡ ብር፡ ተቀብሎ፡ ካበደረው፡ ሌላ፡ ላም፡ ገዝቶ፡ ላሚቱን፡ ወደ፡ ሩቅ፡ አገር፡ ወስዶ፡ ባ፡ ብር፡ ሸጦ፡ በሽያጩ፡ ወዲያው፡ አቡጀዲድ፡ ገዝቶ፡ አምጥቶ፡ ላበዳሪው፡ ባርባ፡ አምስት፡ ብር፡ ሸጦ፤ከዚያ፡ በኋላ፡ እንደዚህ፡ ቢለው፤ወንድሜ፡ አንተ፡ ያበደርከኝ፡ ፴፡ ብር፡ ነው። እንሆ፡ ከነወለዱ፡ ፴፫፡ ብር፡ መሆኑ፡ ነውና፡ ተቀበለኝ፡ ቢለው፤እንግዲህ፡ ካበዳሪውና፡ ከተበዳሪው፡ ማንኛቸው፡ ተጠቀሙ፤ ያበዳሪው፡ ትርፍ፡ ፫፡ ብር፡ ሲሆን፡ የተበዳሪው፡ ትርፍ፡ ፲፪፡ ብር፡ ሆነ፤ ነገሩ፡ ይህ፡ ብቻ፡ ቢሆን፡ አበዳሪው፡ ተጐዳ፡ ባላልነ፡ ነበር። ነገር፡ ግን፡ ተበዳሪው፡ ሲገዛም፡ ሲሸጥም፡ ያገኘው፡ ትርፍ፡ ካበዳሪው፡ ብቻ፡ ነውና፤ አበዳሪው፡ ያገኘው፡ ጉዳት፡ ሁለት፡ ነው። አንዱ፡ ወለዱ፡ ጥቂት፡ ስለ፡ ሆነ። ሁለተኛው፡ በፊት፡ ስድስት፡ ላሞች፡ ነበሩት፤አሁን፡ ግን፡ አራት፡ ላሞች፡ ብቻ፡ ቀሩት። ላሞቹም፡ ባይሸጡ፡ ረብተው፡ ሀብቱን፡ ያበዙት፡ ነበር። ሁለቱንም፡ ላሞች፡ ከሸጣቸው፡ በኋላ፡ ያገኘው፡ ትርፍ፡ ፲፰፡ ብርና፡ የማይረባ፡ በቶሎ፡ የሚቀደድ፡ አቡጀዲድ፡ ብቻ፡ ነው። እንግዲህ፡ ባላገሩ፡ ዐሥራ፡ ስምንቱን፡ ብር፡ በፊተኛው፡ ወለድ፡ ሒሳብ፡ እንደ፡ ገና፡ ያበድር፤ይህ፡ ከሆነለት፡ ዘንድ፡ ተበዳሪው፡ ነጋዴ፡ ያገኘውን፡ ፲፪፡ ብር፡ ትርፍ፡ ጨምሮ፡ ካበዳሪው፡ በ፴፡ ብር፡ ላም፡ ይገዛል። ያችንም፡ ላም፡ ሩቅ፡ ነገር፡ ወስዶ፡ ሸጦ፡ በሽያጪም፡ እንደ፡ ገና፡ አቡጀዲድ፡ ገዝቶ፡ ላበዳሪው፡ ባ፵፫፡ ብር፡ ሸጦ፡ ብሩንም፡ በ፳፡ ተሙን፡ ሸርፍ፡ ምንዛሪ፡ አስቦ፡ ላበዳሪው፡ ፲፰፡ ብር፡ ከነወለዱ፡ ሲመልስ፡ ለራሱ፡ ፳፭፡ ብር፡ ከ፮፡ ተሙን፡ ይተርፈዋል። እንደዚህም፡ ካበዳሪው፡ ላም፡ እየገዛ፡ በያመቱ፡ ላበዳሪው፡ ባ፵፫፡ ብር፡ ኣቡጀዲድ፡ እየሸጠ፡ ይህንን፡ ንግድ፡ በያመቱ፡ ቢደጋግም፡ ያበዳሪው፡ ባላገር፡ ላሞች፡ ፈጽመው፡ ተሸጠው፡ አልቀው፡ ባላገሩ፡ የሚበላውና፡ የሚለብሰው፡ አጥቶ፡ ለነጋዴው፡ ሎሌ፡ ሊሆን፡

የግድ፡ ይሆንበታልና፤ከጥንት፡ ኑሮው፡ ተስፋ፡ ቈርጦ፡ ነጋዴውን፡ ይከታተላል። ይህንንም፡ እንድንረዳ፡ ቀጥሎ፡ የተጻፈውን፡ ሰንጠረዥ፡ ሒሳቡን፡ አስተውለን፡ እንይ። ይህም፡ ሰንጠረዥ፡ ነጋዴው፡ ትርፍ፡ እያገኘ፡ መሄዱንና፡ አበዳሪ፡ እየከሰረ፡ መሄዱን፡ ያስረዳናል።

| | የባላገሩ፡ የላም፡ ቍጥር፡ | | የባላገሩ፡ የገንዘብ፡ ቍጥር፡ | | ነጋዴው፡ ከባላገሩ፡ ያገኘው፡ ትርፍ፡ የገንዘብ፡ ቍ | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቀሪ፡ | የተሸጡት | ብር፡ | መሐ፡ | ብር፡ | መሐ፡ |
| መዠመሪያ፡ | ፮ | | | | | |
| ሁለተኛ፡ ጊዜ፥ | ፯ | ፩ | ፶ | | | |
| ሦስተኛ፡ | ፬ | ፩ | ፲፰ | | ፲፪ | |
| አራተኛ፡ | ፫ | ፩ | ፲፱ | ፲፬ | ፳፯ | ፮ |
| አምስተኛ፡ | ፪ | ፩ | ፬ | ፲፬ | ፵፬ | ፲፮ |
| ስድስተኛ፡ | ፩ | ፩ | ፲፱ | ፲፬ | ፶፬ | ፲፮ |
| ሰባተኛ፡ | | | | | ፸፬ | ፲ |

ሳይሸጥ፡ የነበሩት፡ ነጋዴው፡ ግን፡ የለውም፡ ነበር።

፯ ፸፬፡ ብር፡ ካ፲፡ ሆነ፤ነጋዴው፡ ከባላገሩ፡ ያገኘው፡ ትርፍ፡ በለጠ።

ተጠራጣሪ፡ አንባቢ፡ ግን፡ የሰንጠረዡን፡ ማመልከቻ፡ በመልካም፡ ተመራምሮ፡ ስላልተረዳ፡ እንሆ፡ ደግሞ፡ እንደ፡ ገና፡ በግልጽ፡ ተርጕመንለት፡ እንዲረዳ፡ እንጥራለን።

የመዠመሪያው፡ ሰንጠረዥ፡ ምሳሌ፡ ባላገሩ፡ ስድስት፡ ላሞች፡ እንደ፡ ነበሩት፡ ስላስረዳን፡ በኋላ፡ ግን፡ ትርፍ፡ አገኛለሁ፡ ሲል፡ አንዲቷን፡ ላም፡ ራሱ፡ ለ፶፡ ብር፡ ሸጠ፡ በወለድ፡ ለነጋዴው፡ አበደረው። ሁለተኛ፡ ነጋዴውም፡ ከባላገሩ፡ ላይ፡ በተበደረው፡ ብር፡ እንደ፡ ገና፡ ደግሞ፡ ከርሱው፡ ላይ፡ አንዲት፡ ላም፡ በ፬፡ ብር፡ ገዝቶ፡ ሩቅ፡ አገር፡ ወስዶ፡ ባ፡ ብር፡ አቡጀዲድ፡ ገዝቶ፡ ወደ፡ ባላገሩ፡ ቢያመጣው፡ እንሆ፡ ባላገሩ፡

ባጬ፰፡ ብር፡ ገዛው። ከዚሁ፡ ካርባ፡ አምስቱ፡ ብር፡ ሠላሳ፡ ሦስቱን፡ ብር፡ ከነወለዱ፡ ለባላገሩ፡ ከፈለና፡ ለራሱ፡ ፲፪፡ ብር፡ ትርፍ፡ አገኘ። ያን፡ ጊዜ፡ ባላገሩ፡ ፬፡ ላሞች፡ ቀርተውት፡ ነበር። ባላገሩ፡ ግን፡ ያገኘው፡ ከዋና፡ ገንዘቡ፡ ፲፫፡ ብርና፡ የማይረባ፡ አቡጀዲድ፡ ብቻ፡ ነው።

ሦስተኛ፤ያ፡ ነጋይ፡ ፈጽሞ፡ ራሱን፡ ስላልቻለ፡ ያንን፡ የባላገሩን፡ ፲፫፡ ብር፡ በወለድ፡ ይበደርና፡ ራሱ፡ ያገኘውን፡ ትርፍ፡ ፲፪፡ ብር፡ ጨምሮ፡ ከባላገሩ፡ አንዲት፡ ሳም፡ በ፬፡ ብር፡ ገዝቶ፡ ይዞ፡ ሄዶ። በውድ፡ ይሸጥና፡ በሸጠው፡ ብር፡ አበጀዲድ፡ ገዝቶ፡ አምጥቶ፡ ለባላገሩ፡ እንደ፡ ልማዱ፡ ሸጦ፡ ፲፱፡ ብር፡ ካ፲፬፡ መሐለቅ፡ ከነወለዱ፡ ዕዳውን፡ ለዚያ፡ ባላገር፡ ይከፍልና፡ ለራሱ፡ ፳፫፡ ብር፡ ከ፮፡ መሐለቅ፡ አተረፈ። ባላገሩ፡ ግን፡ ያን፡ ጊዜ፡ ፫፡ ላሞች፡ ቀርተውት፡ ነበር።

ባራተኛው፡ ጊዜ፡ እንግዲህ፡ ያ፡ ነጋዴ፡ ራሱን፡ ሊችል፡ ፰፡ ብር፡ ብቻ፡ ስለ፡ ጐደለው። አምስቱን፡ ብር፡ ከባላገር፡ ተበድሮ፡ በ፬፡ ብር፡ ደግሞ፡ ከቀሩት፡ ከሦስቱ፡ ላሞች፡ አንዲቷን፡ ገዝቶ፡ ወስዶ፡ ወደ፡ ተወደደበት፡ ሸጠና፡ እንደ፡ ቀድሞ፡ ልማዱ፡ እግረ፡ መንገዱን፡ አቡጀዲድ፡ አምጥቶ፡ ለዚያው፡ ለባላገር፡ ሸጠለትና፡ ከዚያው፡ ላይ፡ ፲፡ ብር፡ ካ፲፬፡ መሐለቅና፡ አንድ፡ መጥፎ፡ አቡጀዲድ፡ ለዕዳው፡ ከፍሎ፡ ለራሱ፡ ፴፬፡ ብር፡ ካ፲፮፡ መሐለቅ፡ አተረፈ። ነጋዴውም፡ እንግዲህ፡ ራሱን፡ ችሏል፤ ብድሩን፡ ጨርሶ፡ ከፍሏልና፡ ከዚያ፡ ከባላገሩ፡ ሁለተኛ፡ ብድር፡ ለወደ፡ ፊቱ፡ አልፈለገም። ያን፡ ጊዜ፡ ባላገሩ፡ ፪፡ ላሞች፡ ናቸው፡ የነበሩት።

ባምስተኛው፡ ጊዜ፡ ደግሞ፡ ከቀሩት፡ ከሁለቱ፡ ላሞች፡ እንዲቷን፡ በ፵፡ ብር፡ ገዝቶ፡ እንደ፡ ፊተኛው፡ አድርጎ፡ መልሶ፡ ለባላገሩ፡ ሸጠና፡ ፳፬፡ ብር፡ ካሥራ፡ ስድስት፡ መሐለቅ፡ ኣተረፈ። በስድስተኛው፡ ጊዜ፡ ያቺን፡ ለባላገሩ፡ የተረፈቺዋን፡ አንዲቷን፡ ላም፡ ገዝቶ፡ ሄዶ፡ ሸጠና፡ ሲመለስ፡ እንደ፡ ወትሮ፡ ልማዱ፡ አቡጀዲድ፡ ገዝቶበት፡ ቢመጣ፡ ፳፬፡ ብር፡ ካ፲፡ መሐለቅ፡ ተሸጠለት። ስለዚህም፡ የነጋዴው፡ እያደገ፡ የባላገሩ፡ ሀብት፡ እያነሰ፡ ሄደና፤የሚበላውና፡ የሚለብሰው፡ ስላጣ፡ ለነጋዴው፡ ሎሌ፡ ሊሆን፡ ይዘጋጃል።

እንሆ፡ ነጋዴው፡ ባራተኛው፡ ጊዜ፡ ትርፉ፡ ከ፳፫፡ ብር፡ ስለ፡ በለጠ፡ ከባላገሩ፡ የተበደረው፡ ፰፡ ብር፡ ብቻ፡ ነው። ከዚያ፡ በኋላ፡ ግን፡

አልተበደረውም። ያገኘው፡ ትርፍ፡ ራሱን፡ አስችሎት፡ በገንዘቡ፡ ገዝቶ፡ አቡጀዲድ፡ ማምጣት፡ ዠመረ። ሳላገሩም፡ በያመቱ፡ የሚገዛው፡ ልብስ፡ በ፴፫፡ ብር፡ ስለ፡ ሆነ፡ በእጁ፡ የቀረው፡ ብር፡ ላቡጀዲዱ፡ መግዣ፡ ባይመላለት፡ በስድስተኛው፡ ጊዜ፡ የቀሩትን፡ ላሞች፡ ሁሉ፡ ሸጠ። በሰባተኛው፡ ጊዜ፡ ግን፡ የቀረው፡ ብር፡ ለልብሱ፡ መግዣ፡ የማይበቃው፡ ሆነ። ላምም፡ እንዳይሸጥ፡ ስም፡ ስላጣ፡ በረኃብና፡ በብርድ፡ እንዳልሞት፡ ሲል፡ ለነጋዴው፡ ሎሌ፡ ሆኖ፡ ያድራል። በሕዝቦችም፡ ትዳር፡ እንደዚሁ፡ ነው። በሥራ፡ ያልሠለጠኑ፡ ሕዝቦች ፥ ያልተሠራ፡ ዕቃ፡ ካገራቸው፡ አውጥተው፡ ሸጠው፡ ትርፍ፡ ብር፡ ቢያገኙ፡ ለጊዜው፡ ነው፡ እንጂ፡ አያዛልቃቸውም። መሬታቸው፡ በጊዜ፡ ብዛት፡ አርጅቶ፡ እኽል፡ መስጠቱን፡ ሲያቋርጥ፡ የሚሸጡት፡ ነገር፡ ሲጠፋ፡ የልብስ፡ መግዣና፡ ምግብ፡ አጥተው፡ እናገኛለን፡ ሲሉ፡ ወደ፡ ሴላ፡ አገር፡ ይሰደዳሉ።

እንደዚህ፡ ያለውም፡ ሕዝብ፡ በመዠመሪያ፡ ያገኘው፡ ትርፍ፡ ብር፡ ከባንክ፡ ገብቶ፡ ቢወልድለት፡ ወለዱ፡ ከገዛ፡ ጒዳቱ፡ የተገኘ፡ ነው፡ እንጂ፡ ከውጭ፡ አገር፡ የመጣ፡ ትርፍ፡ አይደለም። እንደዚህ፡ ያለውም፡ ሕዝብ፡ ራሱ፡ ዕውቀትና፡ ኃይል፡ የለውምና፡ በባንክ፡ የገባውን፡ ብር፡ ተበድረው፡ የሚነግዱበትና፡ የሚያተርፉበት፡ የውጭ፡ አገር፡ ሰዎች፡ ናቸው። ተበድረው፡ የሚነግዱበትም፡ ነጋዴዎች፡ ያገሩ፡ ሰዎች፡ ቢሆኑ፡ ያው፡ ነው። ባለመሬቱ፡ እየደኸየ፡ ነጋዴው፡ ግን፡ እየትጠቀመ፡ ይሄዳል። ማለት፡ ያገሩ፡ ሀብት፡ በጊዜ፡ ብዛት፡ በጥቂቶች፡ ሰዎች፡ እጅ፡ ይጠቀለላል። እነዚህም፡ ጥቂቶች፡ ሰዎች፡ የተወለዱበት፡ አገር፡ ብዙ፡ ፍሬ፡ እንደማይሰጥ፡ ሲያዩ፡ የሰበሰቡትን፡ ብርና፡ ወርቅ፡ ይዘው፡ በደኅና፡ ወደሚኖሩበት፡ አገር፡ ይሄዳሉ። ብዙ፡ ሀብት፡ ያከማቸ፡ ሰው፡ በሄደበት፡ አገር፡ ሁሉ፡ ይመቸዋልና፡ ያገር፡ መውደድን፡ ነገር፡ ከጒዳይ፡ አይቈጥረውም።

የሚበላውንና፡ የሚለብሰውንም፡ ያጣ፡ ድኻ፡ የተወለደበትን፡ አገር፡ የሚወድበትን፡ ምክንያት፡ ያጣልና፡ ያገሩ፡ መንግሥት፡ ቢበረታ፡ ወይም፡ ቢጠፋ፡ ግድ፡ የለውም፤ስለዚሁም፡ መንግሥት፡ የሚጠቀምበት፡ ያገሩ፡ ሀብት፡ በጥቂቶች፡ ሰዎች፡ እጅ፡ ሲሰበሰብ፡ አይደለም። ያገሩን፡ ሀብት፡ በመላው፡ ሕዝበ፡ ሲከፋፈለው፡ ነው፡ እንጂ። የሀብታሞች፡ አኗኗርና፡ የሠራተኛው፡ ድኻ፡ አኗኗር፡ ዐይነቱ፡ እንበለ፡ መጠን፡ የሚራራቅበት፡

አገር፡ መንግሥቱ፡ ከጥፋት፡ አፋፍ፡ እንደ፡ ደረሰ፡ ያስረዳል። የኢትዮጵያንም፡ ሕዝብ፡ ሁኔታ፡ ብንመለከት፡ እንደዚሁ፡ ያለ፡ ጥፋት፡ እንዳይደርስ፡ ያስፈራል። ባንድ፡ ፊት፡ ነግደው፡ የሚያድሩት፡ የውጭ፡ ኣገር፡ ሰዎችና፡ ለሕዝቡ፡ አንዳች፡ ጥቅም፡ ሳይሠሩ፡ ድካሙን፡ እየቀሙ፡ ኣንዳንድ፡ ሹማምት፡ ደኅና፡ ደኅና፡ ቤት፡ እየሠሩ፡ እያጌጡ፡ የተመቸ፡ ኑሮ፡ ሲኖሩ፡ እናያለን። ባንድ፡ ፊትም፡ የዕለት፡ ምግብና፡ ያንድ፡ ዓመት፡ ልብስ፡ እናገኛለን፡ ሲሉ፡ ብዙ፡ ሺሕ፡ ድኾች፡ ወባና፡ ችጋር፡ ፈጅቷቸው፡ ከድሬ፡ ዳዋ፡ አንሥቶ፡ እስከ፡ አዲስ፡ አበባ፡ ድረስ፡ ከምድር፡ ባቡር፡ ጐን፡ ለጐን፡ አልፈው፡ አልፈው፡ ተቀብረዋል። ግማሾቹም፡ የተቀበሩበት፡ መቃብር፡ ጠሊቅ፡ ስላልሆነ፡ ዱሮ፡ ዐጥንታቸው፡ ወጥቶ፡ ከምድር፡ ባቡር፡ መንገድ፡ ግራና፡ ቀኝ፡ ተበታትኗል።

ደግሞም፡ ይኸንን፡ ያኸል፡ ሩቅ፡ መንገድ፡ መሄድ፡ አያስፈልገንም፤ ነገሩ፡ በየከተማው፡ ውስጥ፡ ይገለጽልናል። ያማረ፡ ግንብ፡ ቤትና፡ ትንንሽ፡ ጐጆ፡ አጠገብ፡ ላጠገብ፡ ተሠርተው፡ እናያለን። ባንዱ፡ ቤት፡ ውስጥ፡ ትልቍ፡ ጌታ፡ ሕዝቡ፡ ደክሞ፡ ያፈራውን፡ ገንዘብ፡ በከንቱ፡ ሲያባክን፡ በጐጆው፡ ውስጥ፡ የሚኖረው፡ ድኻ፡ የሚበላውና፡ የሚለብሰው፡ የሚያበራውም፡ አጥቶ፡ በረኃብና፡ በብርድ፡ ተጨብጦ፡ በኵበት፡ ጠስና፡ በእድፍ፡ ውስጥ፡ ይጨማለቃል። ሳንዱ፡ ቤት፡ ጌትነቱ። እየበዛ፡ ሲሄድ፡ ባንዱ፡ ቤት፡ ድኽነቱ፡ እየሰፋ፡ ይሄዳል። የጐውንና፡ ያዲሱን፡ ግንብ፡ ቍመት፡ ብናስተያይ፡ ባገራችን፡ ድኻ፡ ጌታ፡ እንዴት፡ እየተራራቍ፡ እንዲሄዱ፡ ይገልጹልናል። ይህ፡ ግን፡ ለመንግሥት፡ ክፉ፡ ምልክት፡ ነው። ይህም፡ ክፉ፡ ነገር፡ እየሰፋ፡ እንዳይሄድ፡ መንግሥት፡ ሕዝቡን፡ በሥራ፡ እንዲያሠለጥን፡ ያስፈልገዋል። ሕዝቡ፡ በሥራ፡ ከሠለጠነ፡ ዘንድ፡ ጌታና፡ ድኻ፡ እንደ፡ ገና፡ ይቃረባሉ። በምክርና፡ በኀይልም፡ ተደጋግፈው፡ የመንግሥታቸውን፡ መሠረት፡ ያጠነክራሉ። ብርና፡ ወርቅም፡ ረዳቶች፡ የለውጥ፡ መሣሪያዎች፡ የሚሆኑት፡ በዚያ፡ ጊዜ፡ ነው።

# ፲፩ኛ፡ ምዕራፍ።

እንሆም፡ በላይኛው፡ ክፍል፡ ሁለት፡ ሦስት፡ ጊዜ፡ ያኸል፡ እየመላለስን፡ የባንክን፡ ስም፡ አነሣን፤ባንክ፡ ማለት፡ ምን፡ ይሆን፤ የሚገባበትስ፡ ምክንያት፡ ምን፡ ይሆን፤እስቲ፡ እንመልከትና፡ እንመርምር።

በዱሮ፡ ዘመን፡ በኤሮፓ፡ አንዳንድ፡ ሰውና፡ ነጋዴም፡ ያገኘውን፡ ብርና፡ ወርቅ፡ በየቤቱ፡ ሲያስቀምጥ፡ ነበር። ብርና፡ ወርቍም፡ እንዳይጠፋበት፡ ሰው፡ ሁሉ፡ ርሱው፡ ራሱ፡ ሲጠብቅ፡ ነበረ። በኋላ፡ ግን፡ ደኅና፡ ቤት፡ ሠርተው፡ ጥቂት፡ ዋጋ፡ እየተቀበሉ፡ ያመናቸውን፡ ሰው፡ ሁሉ፡ ብርና፡ ወርቅ፡ የሚያስቀምጡ፡ ሰዎች፡ ተገኙ። እነዚህም፡ የገንዘብ፡ አስቀማጮች፡ የሚበዙት፡ የብርና፡ የወርቅ፡ ሠራተኞች፡ ነበሩ። ብርና፡ ወርቍንም፡ በተቀበሉ፡ ቍጥር፡ ፊርማቸው፡ ያለበትን፡ የደረሰኝ፡ ወረቀት፡ ሲሰጡ፡ ነበሩ። በኋላ፡ ግን፡ በጣሊያን፡ አገር፡ ገንዘብ፡ እየተቀበሉ፡ የሚያስጠብቍና፡ ገንዘቡን፡ ካንዱ፡ ቦታ፡ ወዳንዱ፡ በሐዋላ፡ የሚሰዱ፡ ባንክ፡ የሚባሉ፡ ማኅበሮች፡ ቆሙ። ለዚሁም፡ ሥራቸው፡ ከገንዘብ፡ አስቀማጩ፡ ወይም፡ ወሳጁ፡ ዋጋ፡ ሲቀበሉ፡ ነበሩ። ይህም፡ የባንክ፡ ሥራ፡ በቀሩት፡ የኤሮፓ፡ ነገሥታት፡ አገር፡ በጊዜ፡ ብዛት፡ ተለመደ። እንሆም፡ ወደ፡ ሺ፻፬፡ ዓመት፡ ምሕረት፡ ግድም፡ በሆላንድ፡ ነገር፡ በአምስተርዳም፡ ከተማ፡ የብርና፡ የወርቅ፡ አደራ፡ አስቀማጭ፡ ማኅበር፡ ቆመ። የአምስተርዳም፡ ባንክ፡ ተብሎም፡ ተሰየመ። ይህም፡ የአምስተርዳም፡ ባንክ፡ ሰመገርመሪያ፡ ዋና፡ ሥራው፡ አደራ፡ የሰጡትን፡ ገንዘብ፡ ማስቀመጥ፡ ነበረ። አደራ፡ የሚያስቀምጡም፡ ሲያወጡም፡ የጠባቂነትን፡ ዋጋ፡ ለማኅበሩ፡ ሲከፍሉ፡ ነበሩ። አደራ፡ አስቀማጮች፡ እንዳይከስሩ፡ ግን፡ የሆላንድ፡ መንግሥት፡ ራሱ፡ ዋስ፡ ሆነ። ባንክም፡ በመቆሙ፡ ለሆላንድ፡ ሕዝብ፡ ትልቅ፡ ጥቅም፡ ሆነ። ዱሮ፡ እያንዳንዱ፡ ሰው፡ ያለውን፡ ብርና፡ ወርቅ፡ ራሱ፡ ሲያስቀምጥ፤ወይም፡ ደግሞ፡ ራሱ፡ ላመነው፡ ሰው፡ አደራ፡ ሲሰጥ፡ አሳብ፡ ይበዛበት፡ ነበረ። መንግሥት፡ የተዋሰው፡ የታመነ፡ የገንዘብ፡ ማስቀመጫ፡ ቦታ፡ ከቆመ፡ በኋላ፡ ግን፡ ለያንዳንዱ፡ ሰው፡ አሳብና፡ መጨነቅ፡ ቀረለት። ይህም፡ የባንክ፡ ሥራ፡ እያደረ፡ ለሕዝቡ፡ የበለጠ፡ ጥቅም፡ ሆነ። በመዠመሪያ፡ በባንክ፡ ያስቀመጠውን፡ ገንዘብ፡ ለሌላ፡ ሰው፡ አሳልፎ፡ ሊሰጥ፡ የፈለገ፡ ሰው፡ ሁሉ፡ ባለቤቱ፡ እየሄደ፡

ሲያሰጥ፡ ነበረ። በኋላ፡ ግን፡ ለእገሌ፡ ይህነን፡ ያኽል፡ ስጡልኝ፡ ብሎ፡ በፊርማው፡ ካስታወቀ፡ ዘንድ፡ ይበቃል፡ ተብሎ፡ ተደነባ። ይህም፡ ደንብ፡ ትልቅ፡ ጥቅም፡ ሆነ። የገንዘቡ፡ ከፋይና፡ የገንዘቡ፡ ተቀባይ፡ ብርን፡ ሲቈጥሩ፡ ብዙ፡ ጊዜ፡ በከንቱ፡ ሲሄድባቸው፡ ኑሮ፡ ዐረፉ። እንደ፡ አምስተርዳም፡ ባንክም፡ ዐይነት፡ በጊዜ፡ ብዛት፡ በኤሮፓ፡ ትልልቅ፡ ከተሞች፡ ሌሎች፡ ባንኮች፡ ቆሙ። ከነዚህም፡ ባንኮች፡ ቀጥለው፡ የዲስኮንቶ፡ የሚባሉ፡ ባንኮች፡ ወጡ። ዲሲኮንቶ፡ ማለት፡ የሒሳብ፡ ትርፍ፡ እንደ፡ ማለት፡ ያኽል፡ ነው። እነዚህም፡ የዲስኮንቶ፡ ባንኮች፡ የቆሙት፡ በማኅበር፡ ገንዘብ፡ ነበርና፤ሥራቸው፡ ሁለት፡ ዐይነት፡ ነበረ። አንዱ፡ የማኅበሩን፡ ገንዘብ፡ እያበደሩ፡ የዲስኮንቶ፡ ወይም፡ የሒሳብ፡ ትርፍ፡ ማግኘት፤የዲስኮንቶ፡ ወይም፡ የሒሳብ፡ ትርፍ፡ ማለት፡ ወለድም፡ እንደ፡ ማለት፡ ያኽል፡ ነው። ሁለተኛው፤ያደራ፡ ገንዘብ፡ እየተቀበሉ፡ እየጠበቁ፡ ካደራ፡ ሰጭዎቹ፡ ሲቀበሉ፡ ነበሩ።

በነዚህም፡ አዲስ፡ ዐይነት፡ ባንኮች፡ የሕዝቡ፡ ጥቅም፡ አደገ። በፊት፡ እያንዳንዱ፡ ሰው፡ ያለውን፡ ገንዘብ፡ ሁሉ፡ በየቤቱ፡ ሲያስቀምጥ፡ ገንዘቡ፡ ለርሱም፡ ሳገሩም፡ ጥቅም፡ አልሆነውም። ወለድ፡ እንዲያመጣለትም፡ ሲል፡ ገንዘቡን፡ ቢያድር፡ ከትርፉ፡ ጭቅጭቁ፡ እየበዛበት፡ እያንዳንዱ፡ ሰው፡ ያለውን፡ ብርና፡ ወርቅም፡ ዝም፡ ብሎ፡ ቀብሮት፡ ሲቀመጥ፡ ነበረ። በኋላ፡ ግን፡ እነዚህ፡ ባለገንዘቦች፡ ተባበሩ። ከመካከላቸውም፡ አለቆች፡ መረጡ። ገንዘባቸውንም፡ ባንድነት፡ ሰብስበው፡ እነዚህም፡ የተሾሙት፡ አለቆች፡ ስለ፡ ማኅበሩ፡ ጥቅም፡ እያደሩ፡ ወለድ፡ እንዲያተርፉበት፡ ፈቀዱ።

ማኅበረተኞቹም፡ ያገቡትን፡ ገንዘብ፡ ልክ፡ የሚያሳዩበት፡ የምስክር፡ ወረቀት፡ ተቀበሉ። ይህ፡ እንደዚህ፡ ሆኖ፡ የተሰበሰበውም፡ ገንዘብ፡ ለባለገንዘቦቹም፡ ለሕዝቡም፡ ትልቅ፡ ጥቅም፡ ሆነ። ዱሮ፡ በያንዳንዱ፡ ባለገንዘብ፡ እጅ፡ ሳለ፡ ሥራ፡ ፈቶ፡ ኑሮ፡ አሁን፡ ባለመሬት፡ ወይም፡ ነጋዴ፡ እየተበደረው፡ ይሠራበት፡ ዠመረ። በዚሁም፡ ለባለገንዘቦቹ፡ ወለድ፡ አመጣላቸው። ተበድረው፡ የሠሩበትም፡ ሰዎች፡ ትርፍ፡ አገኙበት። ጥቅሙም፡ በዚሁ፡ ብቻ፡ አላለቀም። ባንኩንም፡ ያቆሙት፡ ማኅበረተኞች፡ ገንዘብ፡ ባስፈለጋቸው፡ ቊጥር፡ በእጃቸው፡ የያዙትን፡ የማኅበር፡ የምስክር፡ ወረቀት፡ ለመሸጥና፡ ለመለወጥ፡ ተፈቅዶላቸው፡ ነበርና፤

በባንኩ፡ የተሰበሰበው፡ ገንዘብ፡ አንድ፡ ሳለ፡ በሁለት፡ ፊት፡ ተሠራበት። ተበዳሪዎቹ፡ በተበደሩት፡ ገንዘብ፡ ሲሸጡ፡ ሲለውጡ ፥ አበዳሪዎቹ፡ ከማኅበሩ፡ የተቀበሉትን፡ የምስክር፡ ወረቀት፡ ሸጠው፡ የፈለጋቸውን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ለመግዛት፡ ተቻላቸው።

እንሆም፡ በዚሁ፡ አዲስ፡ ጥበብ፡ አንዱ፡ የለውጥ፡ መሣሪያ፡ ስለ፡ ሁለት፡ እየሆነ፡ ስለ፡ ሥራ፡ ባገራቸው፡ ባንክ፡ ያቆሙ፡ ሕዝቦች፡ መለዋወጣቸው፡ እየፈጠነላቸው፡ በውስጣቸው፡ ያለው፡ እያንዳንዱ፡ ሠራተኛ፡ በያዘው፡ ሥራ፡ ተጋ፤ሠለጠነበትም። የሕዝቦቹም፡ ሀብት፡ እያደገ፡ ሄደ። ጥቂት፡ ጊዜም፡ ይህነን፡ ሀብት፡ የሚያሰፋ፡ ሌላ፡ መንገድ፡ ተገኘ። በመገጽመሪያ፡ እያንዳንዱ፡ ሰው፡ በባንክ፡ ገንዘቡን፡ አደራ፡ ያስቀመጠ፡ ሰው፡ ሁሉ፡ ባንኮቹ፡ ገንዘቡን፡ ስለ፡ ጠበቊለት፡ ከገንዘቡ፡ ከፍሎ፡ ዋጋ፡ ሲሰጣቸው፡ ነበረ። በኋላ፡ ግን፡ ገንዘባቸውን፡ በባንክ፡ የሚያስቀምጡ፡ ሰዎች፡ ሁሉ፡ ባንድነት፡ ተሰብስበው፡ ያስቀመጡትን፡ ገንዘብ፡ ባንድ፡ ጊዜ፡ ከባንክ፡ እንዳያወጡ፡ ታየ፤ብልኀትም፡ ወጣበት። ባንኮቹ፡ ሰው፡ አደራ፡ ከሰጣቸው፡ ገንዘብ፡ ከፍለው፡ ለታመኑ፡ ሰዎች፡ እያበደሩ፡ ወለድ፡ ያተርፉበት፡ ዠመሩ። በዚሁም፡ የሚበቃ፡ ትርፍ፡ አግኝተው፡ ከባለገንዘቦቹ፡ እንደ፡ ዱሮ፡ የጠባቂነት፡ ዋጋ፡ መፈለጋቸውን፡ ተዉት። ይህም፡ አዲስ፡ የባንክ፡ ደንብ፡ ሕዝቡን፡ በሁለት፡ ፊት፡ ጠቀመ። መዠመሪያ፡ አደራ፡ አስቀምጠልኝ፡ ብሎ፡ ገንዘቡን፡ ለባንክ፡ የሰጠ፡ ሰው፡ ገንዘቡ፡ እንዳይሰረቅ፡ ወይም፡ እንዳይቀማ፡ ዐውቆት፡ አሳብና፡ ጭንቅ፡ ቀረለት። ወዲያውም፡ ገንዘቡን፡ ለጠባቂዎች፡ ሲሰጥ፡ ዋጋ፡ የማይወስድበት፡ ሆነ። ገንዘቡንም፡ ከባንክ፡ በፈለገ፡ ጊዜ፡ ሲያወጣ፡ ከቤቱ፡ ሳይነቃነቅና፡ ሥራ፡ ሳይፈታ፡ ወረቀት፡ አሲዞ፡ አንዱን፡ አሽከሩን፡ እየላከ፡ ገንዘቡ፡ እስከ፡ ቤቱ፡ ድረስ፡ ይመጣላት፡ ዠመር። ዕቃም፡ ገዝቶ፡ ገንዘብ፡ ሲከፍል፡ የሚከፍለውን፡ ገንዘብ፡ ሊቈጥር፡ ጊዜው፡ ሰከንቱ፡ ሳይባክንበት፡ ቼክ፡ የሚባለውን፡ ይህን፡ ያኽል፡ ገንዘብ፡ ለእገሌ፡ ስጡ፡ የሚለውን፡ ትንሽ፡ ወረቀት፡ ጽፎ፡ ዕቃውን፡ ለሸጠለት፡ ሰው፡ ሰጥቶ፡ ወደ፡ ሳንክ፡ ሲልክ፡ የሚበቃ፡ ሆነ። በየባንኩም፡ ባይራ፡ የተቀመጠ፡ ገንዘብ፡ ሁሉ፡ ጌታው፡ መልሶ፡ እስኪወስደው፡ ድረስ፡ በሠራተኞች፡ ሰዎች፡ እጅ፡ ገብቶ፡ ሲሠራ፡ ለመላው፡ ሕዝብ፡ ጥቅም፡ ሆነ። ብርና፡ ወርቅ፡ እኮ፡ የለውጥ፡ መሣሪያዎች፡ ናቸው፡ እንጂ፤ሌላ፡ ብልኀት፡

የላቸውም። ሕዝቡም፡ ርስ፡ በርሱ፡ ሲለዋወጥ፡ ካልረዱ፡ በያንዳንዱም፡ ሰው፡ ሴት፡ ውስጥ፡ ከመሬት፡ በታች፡ ቢቀበሩ፡ ለባለገንዘበም፡ ለመላውም፡ ሕዝብ፡ አንዳች፡ ጥቅም፡ ሊሆኑ፡ አይችሉም። ሥርዐት፡ በሌለበት፡ አገር፡ የሰው፡ ርስትና፡ ገንዘብ፡ በማይታፈርበት፡ በማናቸውም፡ ትንሽ፡ ምክንያት፡ ሰው፡ በብዙ፡ ድካም፡ ያከማቸውን፡ ገንዘብ፡ በሚወረስበት፡ አገር፡ ውስጥ፡ ብርና፡ ወርቅ፡ ምንም፡ ቢበዙ፡ በያንዳንዱ፡ ሰው፡ ቤት፡ እየተሸሸጉ፡ ይኖራሉ፡ እንጂ፤በሚኀባ፡ ኣይረዱም። የተደላደለ፡ ሥርዐት፡ በሌለበት፡ አገር፡ ሁሉ፡ ሕዝቡ፡ ርስ፡ በርሱ፡ ካለመተማመኑ፡ የተነሣ፡ ያለውን፡ ወርቅና፡ ብር፡ ሲሆን፡ ይቀብረዋል። ያለዚያ፡ ግን፡ እንደ፡ ጌጥ፡ ኣድርጎ፡ በሚመክትበት፡ ጋሻ፡ ላይ፡ ይለጥፈዋል። ወይም፡ በሚዋጋበት፡ ፈረስ፡ ላይ፡ መጣምር፡ ያደርገዋል። ወይም፡ ጐራዴውን፡ ያስጌጥበታል። ዕውቀት፡ የሌለውም፡ ሕዝብ፡ ይህነን፡ የመሰለውን፡ ጌጥ፡ ሁሉ፡ መውደዱ፡ ዋና፡ ምክንያቱ ፥ ባለው፡ ብርና፡ ወርቅ፡ ሌላ፡ ሥራ፡ ሲይዝበት፡ መሰናክል፡ ነገር፡ እንዲበዛበት፡ ሰውነቱ፡ እያወቀበት፡ ነው። ከዚህም፡ ምክንያት፡ የተነሣ፡ ዕውቀት፡ የሌለው፡ ሕዝብ፡ ሁሉ፡ ተመችቶት፡ እንዲኖር፡ ቢፈልግ፡ እንደማይሆንለት፡ ያውቃልና፡ ምቹ፡ ኑሮ፡ እንዲያገኝ፡ መጣሩን፡ ትቶ፡ ለጌጥ፡ ያስባል። በእንደዚህ፡ ያሉ፡ ዕውቀት፡ ያነሳቸውም፡ ሕዝቦች፡ ውስጥ፡ ብዙ፡ ሰው፡ አምስት፡ ብር፡ የሚያወጣውን፡ ልብስ፡ ለብሶ፡ የጋሻውና፡ የፈረሱ፡ ጌጥ፡ ወደ፡ ሁለቱ፡ መቶ፡ ብር፡ የሚያወጣ፡ ሆኖ፡ ቢገኝ፡ የሚገርም፡ ነገር፡ አይደለምን፤ሰው፡ ከውጭ፡ ይልቅ፡ የቤት፡ ምቹነት፡ የሚያስብ፡ የተደላደለ፡ ሥርዐት፡ ሲያገኝ፡ ነው። ያንዱ፡ አገር፡ ሥርዐት፡ ግን፡ ምንም፡ የተደላደለ፡ ቢሆን፡ ለሌላው፡ አገር፡ ሕዝብ፡ የተመቸ፡ ሥርዐት፡ አይሆንም። ሕዝብ፡ የሚወድ፡ ለባሕሪው፡ የሚመች፡ ሥርዐት፡ ሲያወጡለት፡ ነው። ስለዚህም፡ አንዳንዶቹ፡ የሀገራችን፡ መኳንንት፡ ወይም፡ ሹማምት፡ አስቀድመው፡ የትምርት፡ ቤት፡ ሳያቆሙ፡ የኤሮፓን፡ ሥርዐት፡ እናግባ፡ ብለው፡ ቢጥሩ፡ ከንቱ፡ ድካም፡ ነው።

እንሆም፡ ሥርዐት፡ የሚመች፡ ይሆናል፡ ተብሎ፡ በብልኖች፡ ሰዎች፡ ልብ፡ ውስጥ፡ ተፈጥሮ፡ አይጻፍም፤ከሕገቡ፡ ልብ፡ ይቀዳል፡ እንጂ፤ንጉሥ፡ ወይም፡ ሹም፡ በኋለኞች፡ ትውልዶች፡ የሚመሰገን፡ ልቡ፡ ፈልስፎ፡ ደንብ፡ ሲያወጣ፡ አይደለም። የሕዝቡን፡ አሳብ፡ ተርጕሞ፡ በትርጕሙ፡ ሲሄድ፡

ነው፡ እንጂ። የኤሮፓ፡ ሕዝቦች፡ የዛሬ፡ ሥርዐታቸው፡ ባንድ፡ ቀን፡ አልተደነባም። በዘመናት፡ ብዛት፡ የተጣራ፡ ነው፡ እንጂ፤ስለዚህም፡ የሕዝቡ፡ ዕውቀት፡ እየሰፋ፡ ሲሄድ፡ ወደ፡ ፊት፡ ደግሞ፡ እንደ፡ ገና፡ እየተጣራ፡ ይሄዳል። ስለዚህም፡ ባገሩ፡ የኤሮፓን፡ ሥርዐት፡ ሊያገባ፡ የሚፈልግ፡ መንግሥት፡ አስቀድሞ፡ የትምርት፡ ቤት፡ አቊሞ፡ ለሕዝቡ፡ የኤሮፓን፡ ባህል፡ ማስተማር፡ ያስፈልገዋል። እንደዚሁም፡ ኣድርጎ፡ ሕዝቡን፡ ካሠለጠነ፡ በኋላ፡ የኤሮፓን፡ ሥርዐት፡ ባገሩ፡ ቢያገባ፡ ሕዝቡ፡ ይጠቀማል፤ርሱም፡ ይበረታል። ትምርት፡ በሌለበት፡ አገር፡ ለሥርዐት፡ የሚሆን፡ መሠረት፡ ኣይገኝም። ሥርዐት፡ የሚፈለግ፡ በትምርት፡ ነውና፡ ትምርት፡ የሌለው፡ ሕዝብ፡ ሥርዐት፡ አይወድም፤አይጠቅመውም። ስለዚህም፡ ዛሬ፡ የኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡ አዲስ፡ ደንብ፡ ያወጡልኛል፡ ሲል፡ ለውጭ፡ አገር፡ ሰዎች፡ ደመወዝ፡ በያመቱ፡ ቢከስር፡ መሠረት፡ ያለው፡ ጥቅም፡ አያገኝም። የትምርት፡ ቤት፡ አቊሞ፡ ሕዝቡን፡ ቢያስተምር፡ ግን፡ የሚያስፈልገው፡ ደንብ፡ ምን፡ እንደ፡ ሆነ፡ በኋላ፡ ሕዝቡ፡ ራሱ፡ ያውቀውና፡ ይረዳዋል።

የመንግሥት፡ መሠረት፡ የትምርት፡ ቤት፡ ነው። ትምርት፡ በሌለበት፡ አገር፡ አዲስ፡ ደንብ፡ ቢወጣ፡ ከሚጠቅመው፡ የሚጐዳው፡ ይበልጣል። አሁን፡ ከላይ፡ እንደ፡ ተናገርነው፡ ሕዝቡ፡ በሥራ፡ በሠለጠነ፡ አገር፡ ውስጥ፡ ባንክ፡ ሲቆም፡ ትልቅ፡ ጥቅም፡ ነው። በሥራ፡ ያልሠለጠነውን፡ ሕዝብ፡ ግን፡ ባንክ፡ ይጐዳዋል፡ እንጂ፡ አይጠቅመውም። ባንክ፡ የሚቆም፡ ባገር፡ ያለው፡ ብርና፡ ወርቅ፡ ሥራ፡ እንዳይፈታ፡ ባንድነት፡ ሰብስቦ፡ ሥራ፡ ለሚያውቅ፡ ሰው፡ እያበደረ፡ እንዲሠራበት፡ ነው። ዕውቀት፡ የሌለውና፡ በሥራ፡ ያልሠለጠነ፡ ሕዝብ፡ ግን፡ ራሱ፡ ሊሠራ፡ ኣይችልምና፤ገንዘቡን፡ በባንክ፡ ቢያስቀምጥ፡ ጥቅሙ፡ ለውጭ፡ አገር፡ ሰዎች፡ ነው። በኢትዮጵያ፡ የቆመው፡ የእንግሊዝ፡ ባንክ፡ ከታኅሣሥ፡ ፳፪፡ ቀን፡ ፲፱፻፱፡ ዓመተ፡ ምሕረት፡ እስከ፡ ታኅሣሥ፡ ፳፪፡ ቀን፡ ፲፱፻፫፡ ዓመተ፡ ምሕረት፡ ድረስ፡ ያበደረው፡ ገንዘብ፡ ብናስበው፡ ወደ፡ ፩፡ ሚሊዮን፡ ፪፻፳ሺ፡ ፳፻፵፡ ብር፡ ይሆናል። ከዚሁም፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ የተበደረው፡ ከ፸ሺ፡ ብር፡ በላይ፡ አይሆንም፡ ይሆናል። የቀረው፡ ግን፡ ፩፡ ሚሊዮን፡ ፲፪ሺ፡ ፳፻፶፡ ብር፡ የውጭ፡ አገር፡ ሰዎች፡ ተበድረው፡ ሥሩበት። ፬ውን፡ ሺሕ፡ ብር፡ የኢትዮጵያ፡ ሰዎች፡ ተበድረውት፡ ይሆናል፡ ስለ፡ ተባለ ፥ደግሞ፡ ብድሩ፡

ያለጥርጥር፡ ሞያ፡ አልተሠራበትም። የኢትዮጵያ፡ ሰው፡ ገንዘብ፡ ሲበደር፡ እጅግ፡ ቢበረታ፡ ከፈረንጅ፡ አገር፡ የመጣውን፡ ዕቃ፡ ገዝቶ፡ ለገዛ፡ አገሩ፡ ሰዎች፡ በትርፍ፡ ሸጦ፡ ዕዳውን፡ ሰመመለስ፡ ነው። ይህነን፡ ሲያደርግ፡ ግን፡ ዕቃውን፡ ለሸጠለት፡ ፈረንጅ፡ ወኪል፡ ሆኖ፡ ያገሩን፡ ሰዎች፡ ድካም፡ በከንቱ፡ መውሰዱ፡ ነውና፤የኢትዮጵያን፡ ሕዝብ፡ አይጠቅምም። ብዙ፡ ሰው፡ የነጋዴን፡ ሥራ፡ ያመሰግናል። ለመንግሥትም፡ ዋና፡ ጠቃሚ፡ ነጋዴ፡ ነው፡ ይላል። ይህ፡ ቃል፡ ግን፡ መሠረት፡ የለውም። ባንድ፡ መንግሥት፡ ውስጥ፡ ካንዱ፡ ወረዳ፡ ወዳንዱ፡ እየተመላለሰ፡ የያንዳንዱ፡ ወረዳ፡ ሠራተኞች፡ የሠሩትን፡ ዕቃ፡ የሚለዋውጥ፡ ነጋዴ፡ በእውነት፡ ላገሩ፡ ይጠቅማል። እንደዚህ፡ ያለውንም፡ ነጋዴ፡ መንግሥት፡ በማናቸውም፡ ረገድ፡ ቢረዳና፡ ቢያበረታታ፡ የተገባ፡ ነው። ከውጭ፡ አገር፡ ዕቃ፡ አስመጥቶ፡ የሚነግድ፡ ነጋይ፡ ግን፡ ያገሩን፡ ድካምና፡ ሀብት፡ የውጭ፡ አገር፡ ሰዎች፡ በከንቱ፡ እንዲወስዱት፡ ሊረዳ፡ እንደ፡ ተነሣ፡ ያኸል፡ ነውና፤ከመንግሥት፡ አንዳች፡ ርዳታ፡ አያስፈልገውም። ነጋዴውም፡ የውጭ፡ አገር፡ ሰው፡ ከሆነ፡ ዘንድ፡ ኣንዳች፡ ርዳታ፡ አይገባውም። ስለዚህ፡ የውጭ፡ አገር፡ ነጋዴዎች፡ በተቈጡ፡ ቍጥር፡ ብዙ፡ ያገራችን፡ ሹማምት፡ ቢሸበሩ፡ ምክንያት፡ የሌለው፡ ሽብር፡ ነው። ባገር፡ ውስጥ፡ ነጋዴና፡ ወታደር፡ ሲበዛ፡ ለሕዝብም፡ ለመንግሥትም፡ ኣይረባም። የመንግሥት፡ ዋና፡ መሠረቱ፡ እርሻ፡ ነው። ስለዚህ፡ ያገራችን፡ ሰው፡ ከባንክ፡ እየተበደረ፡ ቢነግድ፡ ለኢትዮጵያ፡ ሕዝብና፡ መንግሥት፡ ደስ፡ የሚያሰኝ፡ ነገር፡ አይደለም። ስለ፡ ሆነ፡ ግን፡ ገንዘብ፡ ከባንክ፡ እየተበደረ፡ በከንቱ፡ ከሚያባክን፡ ሰው፡ የሚነግድበት፡ ይሻላል። ከባንክ፡ የሚበደሩ፡ የኢትዮጵያ፡ ሰዎች፡ ግን፡ ሹማምቶች፡ ናቸው። እነሱም፡ የሚበደሩ፡ ከየገባራቸው፡ የሚመጣላቸው፡ ግብር፡ እስኪደርስላቸው፡ ድረስ፡ በከንቱ፡ የሚያባክኑትን፡ ገንዘብ፡ ሲያጡ፡ ነው፡ እንጂ፤በተበደሩት፡ ገንዘብ፡ የረባ፡ ነገር፡ ለመሥራት፡ እንኳን፡ በውናቸው፡ በሕልማቸውም፡ ቢሆን፡ አያስቡትም።

ከጥቂት፡ ዓመት፡ በፊት፡ ኣያሌ፡ ያገራችን፡ ባለገንዘቦች፡ ተሰብስበው፡ ለእርሻ፡ ማስፊያ፡ ሲሉ፡ አንድ፡ የባንክ፡ ዐይነት፡ ማኅበር፡ አቍመው፡ ነበር። ነገር፡ ግን፡ ከዚህ፡ ቀደም፡ አንድም፡ ጥቅም፡ ለባላገሩ፡ አላመጣም። ለወደ፡ ፊትም፡ ኢያመጣስትም። ይልቍንም፡ ብዙ፡ ሰው፡ ከዚሁ፡ ማኅበር፡

ገንዘብ፡ እየተበደሩ፡ የብድሩ፡ መክፈያ፡ ጊዜ፡ ሲደርስ፡ ስዕዳው፡ የሚከፍለው፡ ገንዘብ፡ እያጣ፡ ከርስቱ፡ ተነቀለ። ከዚህ፡ ቀደም፡ በምርም፡ እንደ፡ ተረዳነው፡ ሕዝቡ፡ በሥራ፡ ባልሠለጠነ፡ ኣገር፡ ባላገር፡ ከባንክ፡ ገንዘብ፡ ቢበደር፡ የተበደረውን፡ ገንዘብ፡ ሊመልስ፡ አይችልም። የተበደረውም፡ ገንዘብ፡ የሚጠቅመው፡ ለኑሮው፡ የሚያስፈልገው፡ ዕቃ፡ ሁሉ፡ ባገሩ፡ የተሠራስት፡ እንደ፡ ሆነ፡ ነው። ይህንንም፡ በዚህ፡ መጽሐፍ፡ ውስጥ፡ በውል፡ አይተነዋል፤ተረድተነዋል።

እንግዲህ፡ እንደ፡ ምድር፡ ባብርና፡ የጋሪ፡ መንገድ፡ ባንክም፡ የሚጠቅም፡ በሥራ፡ የሠለጠነውን፡ ሕዝብ፡ ነው። የኢትዮጵያም፡ ሕዝብ፡ መንግሥት፡ ባገሩ፡ የምደር፡ ባቡር፡ እንዲሠራና፡ ባገሩም፡ ባንክ፡ እንዲቆም፡ ፈቅዷል። ሕዝቡን፡ ከጥፋት፡ ሊያድን፡ ፈቃዱ፡ ከሆነ፡ ዘንድ፡ በፍጥነት፡ ሕዝቡን፡ በሥራ፡ ማሠልጠን፡ አለበት። የምድር፡ ባቡር፡ አዲስ፡ አበባ፡ ደርሷል። ባንኩም፡ ይኸው፡ ቍሞ፡ ይሠራል። የኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡ ሕዝቡን፡ ሊጠቅም፡ ፈቃዱ፡ ሆኖ፡ ለወደ፡ ፊት፡ የሚሠራበትን፡ ደኅና፡ መንገድ፡ አስቀድሞ፡ ለይቶ፡ ነድፎ፡ የነደፈውን፡ ንድፍ፡ ለመፈጸም፡ ታጥቆ፡ ቢነሣ፡ የምድር፡ ባበርና፡ ባንኩ፡ በብዙ፡ ሳይረዱት፡ አይቀሩም። ለሕዝቡ፡ ማሠልጠኛ፡ የሚሆነውን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ የምድር፡ ባቡር፡ በፍጥነት፡ ሲያመላልስ፤የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ርስ፡ በርሱ፡ ሲለዋወጥና፡ ባንኩም፡ በሰበሰበው፡ ገንዘብ፡ ሲረዳ፤የኢትዮጵያ፡ መንግሥትም፡ ሕዝቡን፡ ለማሠልጠን፡ ቢነሣ፡ ማለፊያ፡ አጋዥ፡ ይሆኑት፡ ነበር። የኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡ ይህ፡ ሐሳብ፡ ከሌለው፡ ግን፡ የምድር፡ ባቡርና፡ ባንኩ፡ ወዳገራችን፡ አመጣጣቸው፡ የኢትዮጵያን፡ ሕዝብ፡ መቃብር፡ ለመማስ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ጥርጥር፡ የለውም።

# ፲፪ኛ፡ ምዕራፍ።

ብርና፡ ወርቅ፡ በሥራ፡ በሠለጠኑ፡ ሕዝቦች፡ እጅ፡ ሲደርሱ፡ አንዱ፡ ብር፡ ስለ፡ ሁለት፡ ስለ፡ ሦስት፡ ብር፡ እየሆነ፡ እንዲሠራ፡ አይተናል። የብርንና፡ የወርቅንም፡ ጥቅም፡ እንደዚህ፡ አድርጎ፡ የሚያስፋፋ፡ ባንክ፡ ነውና፤በሥራ፡ የሠለጠነ፡ ሕዝብ፡ ሁሉ፡ ያለባንክ፡ አይሳካለትም። ብርና፡ ወርቅ፡ ባገር፡ ስለ፡ በዛ ጥቅም፡ አይሆነውም። ብርና፡ ወርቅ፡ የሚጠቅም፡

ካንዱ፡ እጅ፡ ወዳንዱ፡ እጅ፡ በፍጥነት፡ እየተላለፈ፡ ሲለዋወጥ፡ ነው፡ እንጂ፡ ቤት፡ ያለው፡ ሰው፡ ቤቱን፡ ቢሸጥ፡ ምናልባት፡ ቀላድ፡ ለመግዛት፡ ይሆናል።

ባለቀላዱም፡ መሬቱን፡ የሚሸጥ፡ ምናልባት፡ በሬና፡ ላም፡ ለመግዛት፡ ይሆናል። በሬውንና፡ ላሙንም፡ የሸጠ፡ ሰው፡ ምናልባት፡ ቤት፡ ሊሠራበት፡ ይሆናል። ቤቱንም፡ የገነቡ፡ ሠራተኞች፡ በደመወዛቸው፡ ምግባቸውንና፡ ልብሳቸውን፡ ሊገዙበት፡ ይሆናል። ማለት፡ የብር፡ ሥራው፡ ካንዱ፡ እጅ፡ ወዳንዱ፡ እጅ፡ እየተላለፈ፡ ማለዋወጥ፡ ብቻ፡ ነው። በያንዳንዱም፡ እጅ፡ ገብቶ፡ ወዳንዱ፡ እጅ፡ እስኪያልፍ፡ ድረስ፡ ቢዘገይ፡ ለሕዝብም፡ ለመንግሥትም፡ ጒዳት፡ ነው። ሕዝቡ፡ በሥራ፡ ባልሠለጠነ፡ አገር፡ ግን፡ ብር፡ ካንዱ፡ እጅ፡ ወዳንዱ፡ እጅ፡ እስኪያልፍ፡ ድረስ፡ ይዘገያል። በእንደዚህ፡ ያለው፡ አገር፡ ደኅና፡ መንገድና፡ የምድር፡ ባቡር፡ ስለሌለ፡ ሕዝቡ፡ በቶሎ፡ እየተገናኘ፡ ለመለዋወጥ፡ አይችልም። ቢገናኝም፡ አይለዋወጥም። ሥራው፡ አንድ፡ ዐይነት፡ የሆነ፡ ሕዝብ፡ ርስ፡ በርሱ፡ ምን፡ ሊለዋወጥ፡ ይችላል። ሕዝብ፡ ርስ፡ በርሱ፡ መለዋወጥ፡ የሚችል፡ በያይነቱ፡ ሥራ፡ ሠልጥኖ፡ ሥራው፡ የተከፋፈለ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ነው። በሕዝቡ፡ ውስጥ፡ ያለውም፡ እያንዳንዱ፡ ሰው፡ የሠለጠነበት፡ ሥራ፡ ልዩነት፡ ሲበዛ፡ ሕዝቡ፡ የሚለዋወጠው፡ ለውጥ፡ ይበዛል። በሕዝቡ፡ ውስጥ፡ ያለውም፡ ብርና፡ ወርቅ፡ ካንዱ፡ ወዳንዱ፡ እጅ፡ በፍጥነት፡ ይተላለፋል። ሕዝቡ፡ በሥራ፡ ባልሠለጠነ፡ አገር፡ ግን፡ እያንዳንዱ፡ ሰው፡ የፈለገውን፡ ነገር፡ በፍጥነት፡ ኢያገኝምና፡ አንዳች፡ ነገር፡ ሸጦ፡ የተቀበለው፡ ብር፡ ወደ፡ ሌላ፡ እጅ፡ እስኪያልፍ፡ ድረስ፡ ብዙ፡ ጊዜ፡ ይሄድበታል። እስቲ፡ አሁን፡ አንድ፡ የመንዝ፡ ባሻገር፡ አንዲት፡ ላም፡ ሸጦ፡ ብር፡ ካገኘ፡ በኋላ፡ ለራሱና፡ ለልጆቹ፡ ልብስ፡ የሚሆነውን፡ አቡጀዲድ፡ እስኪገዛበት፡ ድረስ፡ ብሩ፡ በርሱ፡ እጅ፡ ሥራ፡ ፈቶ፡ የሚቀመጥበት፡ ጊዜ፡ ጥቂት፡ ነውን፤ሕዝቡ፡ ሥራ፡ ባልሠለጠነበት፡ አገር፡ ብር፡ ቢበዛ፡ እንደ፡ ብዛቱ፡ አይጠቅምም። ብሩ፡ ከሚሠራበት፡ ቀን፡ ይልቅ፡ ሥራ፡ ፈቶ፡ በየቤቱ፡ የሚቀበርበት፡ ጊዜ፡ ይበልጣል።

በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ያለው፡ ብር፡ ጥቂት፡ አይደለም። እስከ፡ ፩፡ መቶ፡ ሚሊዮን፡ ይሆናል፡ ተብሎ፡ ይገመታል። የሚሠራበት፡ ብር፡ ግን፡ ከኻያ፡ ሚሊዮን፡ ኣይበልጥም። ስለዚህም፡ በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ሥራ፡

ፈቶ፡ የተቀመጠው፡ ብር፡ ፫፡ ሚሊዮን፡ ይሆናል። ይህም፡ ፫፡ ሚሊዮን፡ ብር፡ ግማሹ፡ ጌጥ፡ ሁኖ፡ ይሆናል። ግማሹም፡ ከመሬት፡ በታች፡ ተቀብሮ፡ መልኩን፡ እያበላሸ፡ ሥራ፡ ፈቶ፡ ተቀምጦ፡ ይሆናል። ከዚህም፡ ምክንያት፡ የተነሣ፡ የኢትዮጵያ፡ ብር፡ ያለ፡ አይመስልም። የሚበዛው፡ ብር፡ ተቀብሮ፡ ስለ፡ ተቀመጠ፡ ወደ፡ ገበያ፡ የሚወጣው፡ ብር፡ ጥቂት፡ ነው። በኢትዮጵያ፡ ብር፡ የሚበደር፡ ሰው፡ ወለድ፡ ይበዛበታል። ሌላው፡ ባለገንዘብስ፡ ይቅርና፡ በኢትዮጵያ፡ ያለው፡ ባንክ፡ አፍ፡ አቢሲኒያ፡ ሲያበድር፡ የሚቀበለው፡ ወለድ፡ በመቶው፡ ዐሥራ፡ ሁለት፡ ይሆናል። የኤሮፓ፡ ነገሥታት፡ ግን፡ ባገራቸው፡ እያንዳንዱ፡ ሰው፡ ሲበደር፡ ሥርዐቱ፡ የሚያስከፍለው፡ ወለድ፡ ስንት፡ እንደ፡ ሆነ፡ ለይተው፡ ወስነውታል። ይህም፡ በደንብ፡ የተወሰነው፡ ወለድ፡ እንደያገሩ፡ ሁኔታ፡ ከፍና፡ ዝቅ፡ ይላል። ስለ፡ ሆነ፡ ግን፡ በማናቸውም፡ መንግሥት፡ በመቶው፡ ከስድስት፡ ብር፡ አያልፍም።

ይህነን፡ መናገራችን፡ ግን፡ ምናልባት፡ የኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡ እንደዚሁ፡ ወለድ፡ ከመቶው፡ ስድስት፡ እንዳይበልጥ፡ ደንብ፡ ያድርግ፡ ማለታችን፡ አይደለም። ስለ፡ ሆነ፡ ወሰኑ፡ እንኳ፡ ይህን፡ ያኽል፡ ዝቅ፡ ባይል፡ ሕዝቡ፡ እንበለ፡ መጠን፡ እንዳይጐዳ፡ አንድ፡ ወሰን፡ መደንገግ፡ ነው። መንግሥት፡ ባገሩ፡ ወለድ፡ ዝቅ፡ እንዲል፡ ከፈለገ፡ ግን፡ ሕዝቡን፡ በየሥራው፡ ያሠልጥን። መንገድና፡ የምድር፡ ባቡርም፡ ያዞራ። በየወረዳውም፡ የባንክ፡ ቤት፡ እንዲቆም፡ ይጣር፤ባገሩም፡ የውጭ፡ አገር፡ ገንዘብ፡ እንዳይገባ፡ ሥርዐት፡ ይደረግ። ይህም፡ ሁሉ፡ ከሆነ፡ በኋላ፡ እያንዳንዱ፡ ሰው፡ የሚፈልገውን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ በፍጥነት፡ ሲያገኝ፡ የተቀበለውን፡ ብር፡ ቀብሮ፡ አያስቀምጥም፤ወዲያው፡ ወደ፡ ገበያ፡ ያወጣዋል፡ እንጂ። የፈለገውንም፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ገዝቶ፡ ብር፡ ቢያተርፈው፡ ብሩ፡ ሥራ፡ ሲፈታበት፡ አይወድም። ወይም፡ ራሱ፡ አንዳች፡ ነገር፡ ይሠራበታል። ወይም፡ ደግሞ፡ ወለድ፡ የምትሰጠውን፡ ባንክ፡ ባጠገቡ፡ ሲያገኝ፡ ብሩን፡ በዚያው፡ ያስቀምጣል። ባንኩም፡ ለሚሠሩ፡ ሰዎች፡ ብሩን፡ አበድሮ፡ ያሠራበታል። ከዚህም፡ ምክንያት፡ የተነሣ፡ ወደ፡ ገበያው፡ የሚወጣው፡ ብር፡ ይበዛል። ተበዳሪው፡ የሚከፍለው፡ ወስድ፡ ምንም፡ ቢሆን፡ ማነሱ፡ አይቀርም።

የማናቸውም፡ መንግሥት፡ ሀብትና፡ ኀይል፡ የሚያድግ፡ ሕዝቡ፡ በሥራ፡ የሠለጠነ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ነው። ማናቸውም፡ ሕዝብ፡ በሥራ፡ መሠልጠኑንና፡ ያለመሠልጠኑን፡ ለማወቅ፡ ስንፈልግ፡ ባገሩ፡ የሚከፍለውን፡ ወለድ፡ ማየት፡ ነው። ባንድ፡ አገር፡ ወለድ፡ ከፍ፡ ሲል፡ የዚያ፡ አገር፡ መንግሥት፡ ህብትና፡ ኀይል፡ እንዳነሰ፤ሕዝቡም፡ በሥራ፡ እንዳልሠለጠነ፡ ይመሰክርልናል። ባገሩ፡ ልማድ፡ የሆነውም፡ ወለድ፡ ዝቅ፡ ሲል፡ መንግሥቱ። እንደ፡ ሰረታና፡ ሀብቱ፡ እንዳደገ፡ ሕዝቡ፡ በሥራ፡ እንደ፡ ሠለጠነለት፡ ያስታውቃል። ከዚህ፡ ቀደም፡ እንደ፡ ተረዳነው፡ ሕዝቡ፡ በሥራ፡ ካልሠለጠነ፡ ዘንድ፡ በባንክ፡ ኣማካይነት፡ አንዱ፡ ብር፡ ስለ፡ ሁለት፡ ሆኖ፡ ሊያለዋውጠን፡ ይችላል። ይህም፡ የሚሆነው፡ እንዴት፡ ባለ፡ መንገድ፡ እንደሆነ፡ መልሰን፡ እናሳይ።

ባንድ፡ አገር፡ ባንክ፡ የቆመ፡ እንደ፡ ሆነ፡ የባንኩ፡ ማኅበረተኞች፡ የያዙትን፡ ሥራ፡ ማኅበረተኛ፡ መሆናቸውን፡ የሚያስታውቅ፡ የምስክር፡ ወረቀት፡ ሸጠው፡ የፈለጉትን፡ ነገር፡ ለማግኘት፡ ይችላሉ። በባንኩ፡ የገባው፡ ገንዘብ፡ ግን፡ ሌሎች፡ ሰዎች፡ ተበድረውት፡ ይሠራበታል። የባንክ፡ ሥራ፡ የሠለጠነውን፡ ሕዝብ፡ የሚጠቅምበት፡ መንገድ፡ ግን፡ ይህ፡ ብቻ፡ አይደለም። ገንዘብ፡ ያለው፡ ሰው፡ ገንዘቡን፡ በባንክ፡ ቢያስቀምጥ፡ በፈለገው፡ ጊዜ፡ እንደ፡ ፈለገው፡ መጠን፡ ባንድ፡ ጊዜ፡ ወይም፡ በየጥቂቱ። ያስቀመጠውን፡ ገንዘብ፡ መልሶ፡ ሊወስድ ይችላል። ወዲያውም፡ ጥቂት፡ የጠባቂ፡ ዋጋ፡ መክፈል፡ አያስፈልገውም። ባለገንዘቡ፡ በባንክ፡ ያስቀመጠውን፡ ገንዘብ፡ መልሶ፡ እስኪወስድ፡ ድረስ፡ ግን፡ ገንዘቡ፡ ሥራ፡ ፈቶ፡ አይቀመጥም፤ባንክ፡ እያበደረ፡ ይሠራበታል፡ እንጂ። በዚሁም፡ አንዱ፡ ብር፡ ስለ፡ ሁለት፡ እየሆነ፡ ይሠራል። ባንክም፡ የሠለጠነውን፡ ሕዝብ፡ የሚጠቅምበት፡ ደግሞ፡ ሌላ፡ መንገድ፡ አለ። ገንዘቡን፡ በባንክ፡ ያስቀመጠ፡ ሰው፡ ከገንዘቡ፡ ከፍሎ፡ ለሌላ፡ ሰው፡ እሰጣለሁ፡ በል፡ ከቤቱ፡ መነቃነቅ፡ አያስፈልገውም። ቼክ፡ በሚባለው፡ ወረቀት፡ ላይ፡ ይህነን፡ ያኸል፡ ገንዘብ፡ ከኔ፡ ሒሳብ፡ ስእገሌ፡ ስጡ፡ ብሎ፡ ሲያዝ፡ የሚበቃ፡ ይሆናል።

ስለዚህም፡ ገንዘብ፡ በመቀጠር፡ ሰከንቱ፡ የሚደክመው፡ ድካም፡ ለባለገንዘቡ፡ ይቀርለታል። ባንድ፡ ከተማ፡ ውስጥ፡ ባንክ፡ ከመ፡ በኋላ፡ ገንዘብ፡ ያለው፡ ሰው፡ ሁሉ፡ የገንዘብ፡ ጠባቂ፡ እንዲሆነው፡ ሲል፡

ሠራተኛ፡ መቅጠር፡ አያስፈልገውም። የገንዘብ፡ ጠባቆችም፡ ሆነው፡ በየቤቱ፡ ሲቀጠሩ፡ የነበሩ፡ ሰዎች፡ ሌላ፡ ሥራ፡ ይዘው፡ አገራቸውን፡ ይጠቅማሉሙቶ፡ የገንዘብ፡ ጠባቂዎችም፡ ሆነው፡ በየቤቱ፡ ሲሠሩት፡ የነበረ፡ ሥራ፡ ገንዘቡ፡ ሁሉ፡ በባንክ፡ ሲገባ፡ ባንድ፡ ሰው፡ እጅ፡ ይሠራል። ባንክም፡ በሥራ፡ የሠለጠነውን፡ ሕዝብ፡ የሚጠቅምበት፡ መንገድ፡ ይህ፡ ብቻ፡ አይደለም፤እያንዳንዱ፡ ሰው፡ በባንክ፡ ያስቀመጠውን፡ ብር፡ ለእገሌ፡ ስጡልኝ፡ ብሎ፡ ከጻፈ፡ በኋላ፡ ያ፡ ገንዘቡን፡ ሊቀበል፡ ቼክ፡ የተጻፈለት፡ ሰው፡ ለሌላ፡ ሰው፡ አሳልፎ፡ መስጠት፡ ሲፈልግ፡ በወረቀቱ፡ ዠርባ፡ ሳይ፡ ስሙን፡ ከመጻፍ፡ በቀር፡ ሌላ፡ ድካም፡ የለበትም። ቼኩ፡ በሁለት፡ እጅ፡ ከደረሰ፡ በኋላ፡ ግን፡ ያስቸግራልና፤ቼኩ፡ ካልተለወጠ፡ አይሆንም። ከዚህም፡ ምክንያት፡ የተነሣ፡ ሌላ፡ ብልኀት፡ ተበጀ። ባንኩ፡ ራሱ፡ ባንክ፡ ኖት፡ የሚባል፡ የታተመ፡ ወረቀት፡ አወጣ። ይህም፡ ባንክ፡ ኖት፡ የሚባለው፡ ወረቀት፡ ምን፡ እንደ፡ ሆነ፡ እንዲገለጸልን፡ ቀጥሎ፡ የተጻፈውን፡ ቃል፡ እንመልከት። የሰው፡ ኑሮ፡ መሠረት፡ እምነት፡ ነው። ሰው፡ እጸድቃለሁ፡ ብሎ፡ ከማመኑ፡ የተነሣ፡ በጎ፡ ሥራ፡ ይሠራል። ዳኛም፡ የምስክርን፡ ቃል፡ አምኖ፡ ይፈርዳል። ሴትም፡ ባሏን፡ አምና፡ ወላጅቷን፡ ትታ፡ ትሄዳለች። ተማሪውም፡ መምህሩ፡ የነገረውን፡ ቃል፡ አምኖ፡ የተማረውን፡ ትምርት፡ መሠረት፡ ያደርጋል። አስተማሪው፡ የነገረውን፡ ቃል፡ ተጠራጥሮ፡ የተማረው፡ ነገር፡ እውነት፡ መሆኑንና፡ አለመሆኑን፡ የሚመራመር፡ ተማሪ፡ ከሺሕ፡ አንድ፡ አይገኝም። በዚህ፡ ዓለም፡ የሚሠራው፡ ሥራ፡ የሚበዛው፡ በእምነት፡ ነው። ከሰው፡ ልብ፡ እምነት፡ ቢጠፋ፡ አንዳችም፡ ሥራ፡ አይሠራም፡ ነበር። ዕውቀት፡ የሌለው፡ ሕዝብ፡ ርስ፡ በርሱ፡ ኣይተማመንም። ስለዚህም፡ የሚሠራው፡ ሥራ፡ ጥቂት፡ ነው። ሕዝቡ፡ ዕውቀት፡ ሲጨምር፡ ግን፡ ርስ፡ በርሱ፡ መተማመኑ፡ ይበዛል። ዕውቀት፡ የሌለው፡ ሰው፡ ቼክ፡ ሰጥተው፡ ከባንክ፡ ብር፡ ተቀበል፡ ቢሉት፡ አያምንም፤አታለው፡ ከቤት፡ ሊያስወጡት፡ ያሰቡ፡ ይመስለዋል። ብሬን፡ ቈጥራችሁ፡ በእጄ፡ ካልሰጣችሁኝ፡ ኣለቃችሁም፡ ይላል። በዚሁም፡ ራሱ፡ ሥራ፡ ፈቶ፡ ገንዘብ፡ የሚሰጠውንም፡ ሰው፡ ሥራ፡ ያስፈታል። የተማረ፡ ሰው፡ ግን፡ ብሩን፡ ቈጥረው፡ በእጁ፡ ከሚሰጡት፡ ቼክ፡ ጽፈው፡ ወደ፡ ባንክ፡ ቢዳርጉት፡ ይወዳል። በቼኩም፡ ዠርባ፡ ፊርማውን፡ አድርጎ፡ ገንዘቡን፡ ወደ፡ ሒሳቤ፡ ጨምራችሁ፡ የደረሰኝ፡ ወረቀት፡ ላኩልኝ፡ ብሎ፡ ለባንኩ፡ ይጽፋል። ባንኩም፡ ቼኩን፡ ተቀብሎ፡

ብሩን፡ ሲቈጥር፡ ጊዜ፡ በከንቱ፡ ሳይባክንበት፡ በቼኩ፡ ላይ፡ የተመለከተውን፡ ገንዘብ፡ ከከፋዩ፡ ሐሳብ፡ ወደ፡ ተቀባዩ፡ ሒሳብ፡ ያሸጋግራል። ከዚህም፡ መተማመን፡ ምክንያት፡ የተነሣ፡ ዕውቀት፡ ባላቸው፡ ሕዝቦች፡ መካከል፡ ማንም፡ ሰው፡ ገንዘብ፡ ሲሰጥም፡ ሲረከብም፡ ጊዜውን፡ በከንቱ፡ ኣያባክንም፤ሌላ፡ የሚጠቅም፡ ሥራ፡ ይሠራበታል። በመንግሥትም፡ ታምኖ፡ የቆመ፡ ባንክ፡ መታመኑንም፡ መንግሥት፡ ከመሰከረለት፡ ዘንድ፡ ወይም፡ መንግሥት፡ ከተዋሰው፡ ሕዝቡም፡ እንዲያምነው፡ የተገባ፡ ነው። ስለዚህም፡ ነገሥታት፡ የተዋሷቸው፡ ባንኮች፡ ይህነን፡ ወረቀት፡ ይዞ፡ ወደኛ፡ የመጣ፡ ሰው፡ ይህነን፡ ያኽል፡ ገንዘብ፡ እንሰጠዋለን፡ እያሉ፡ ወረቀቶች፡ እያተሙ፡ ያወጣሉ። እነዚህንም፡ ወረቀቶች፡ ሕዝቡ፡ እየተቀበላቸው፡ እንደ፡ ብርና፡ እንደ፡ ወርቅ፡ ይገበያይባቸዋል። ወረቀቶቹንም፡ የሚቀበል፡ ሰው፡ ምናልባት፡ ወረቀቱ፡ ራሱ፡ ብር፡ ነው፡ ብሎ፡ አይደለም። ነገር፡ ግን፡ ብር፡ በፈለገ፡ ጊዜ፡ ወረቀቱን፡ ሲያሳይ፡ ባንኩ፡ በወረቀቱ፡ ላይ፡ የተጻፈውን፡ ገንዘብ፡ ወዲያው፡ እንዲሰጠው፡ እያመነ፡ ነው፡ እንጂ። ባንክ፡ ኖትም፡ የሚባል፡ እንደዚሁ፡ ያለው፡ ወረቀት፡ ነው። በኢትዮጵያም፡ የቆመው፡ ባንክ፡ አፍ፡ አቢሲኒያ፡ እንደዚሁ፡ እንደ፡ ተናገርነው፡ ያለ፡ የብር፡ ባንክ፡ ኖት፡ አውጥቷል። አንባቢው፡ ግን፡ እንዲህ፡ ብሎ፡ ይጠይቅ፡ ይሆናል። ባንክ፡ ይህንን፡ ያኽል፡ ገንዘብ፡ እሰጣችኋለሁ፡ እያለ፡ ብዙ፡ ባንክ፡ ኖት፡ በመላው፡ አገር፡ ዘርቶ፡ ሕዝቡን፡ ኣታሎ፡ በኋላ፡ የሚከፍለው፡ ያጣ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ሕዝብ፡ አይጐዳምን፤እንደዚህ፡ ያለ፡ ወረቀት፡ ባገር፡ ቢለመድ፡ ምን፡ ይረባል።

ለዚህ፡ ጥያቄ፡ ግን፡ እኛ፡ ብንመልስ፡ ኣንባቢው፡ አይጠቀምም። ባንክ፡ ኖት፡ የሚታተም፡ እንዴት፡ እንደ፡ ሆነ፡ ከዚህ፡ ቀጥሎ፡ የተጻፈውን፡ አንብቦ፡ ይረዳ፤ከዚያም፡ በኋላ፡ እሱው፡ ራሱ፡ ይፍረድ። ባንክ፡ ሲቆም፡ ባንኩን፡ ያቆሙ፡ ማኅበረተኞች፡ ያገቡትን፡ ገንዘብ፡ ልክ፡ የሚያሳዩ፡ የምስክር፡ ወረቀቶች፡ ይቀበላሉ። እነዚህም፡ የምስክር፡ ወረቀቶች፡ አክሲዮን፡ ይባላሉ።

እንሆም፡ ባንክ፡ ኦፍ፡ አቢሲኒያ፡ ሲቆም፡ ፪፡ ሺሕ፡ አክሲዮን፡ ታተመ። ስባንኩ፡ ማቆሚያ፡ የሚሆነውንም፡ ገንዘብ፡ እናገባለን፡ ያሉትም፡ ማኅበረተኞች፡ ሊያገቡት፡ እንደ፡ ፈለጉ፡ ገንዘብ፡ መጠን፡ ለ፵፡ ብር፡

አንድ፡ አክሲዮን ለ፻፡ ብር፡ አንድ፡ አክሲዮን፡ ተቀበሉ። ማለት፡ መቶ፡ ብር፡ አገባለሁ፡ ያለ፡ ማኅበረተኛ፡ ሁለት፡ አክሲዮን፡ አምስት፡ መቶ፡ ብር፡ አገባለሁ፡ ያለ፡ ዐሥር፡ አክሲዮን፡ ሺሕ፡ ብር፡ አገባለሁ፡ ያለ፡ ፲፡ አክሲዮን፡ ተቀበለ። ስለዚህም፡ በ፫፡ ሺሕ። አክሲዮን፡ ይገባል፡ የተባለው፡ ገንዘብ፡ ፭፡ ሚሊዮን፡ ብር፡ ሆነ። ነገር፡ ግን፡ በኢትዮጵያ፡ ገና፡ ሥራ፡ አልሰፋምና፡ ይህ፡ ኣምስት፡ ሚሊዮን፡ በሙሉ፡ ገና፡ አልተሰበሰበም። አምስቱ፡ ሚሊዮን፡ በሙሉው፡ ጨርሶ፡ ከማኅበረተኞቹ፡ ቢሰበሰብ፡ ሥራ፡ ይፈታል፡ ተብሎ፡ እንዳንዱ፡ ማኅበረተኛ፡ በመዠመሪያ፡ የሚከፍለው፡ አገባለሁ፡ ካለው፡ ገንዘብ፡ ሩብ፡ ይሁን፡ ተባለ። የቀረውንም፡ ፫፡ ሩብ፡ ያግባ፡ በተባለ፡ ጊዜ፡ እንዲመስ፡ እያንዳንዱ፡ ማኅበረተኛ፡ የሚበቃ፡ ዋስ፡ ሰጠ።

ስለዚህም፡ ዛሬ፡ ባንክ፡ አፍ፡ አቢሲኒያ፡ የሚሠራበት፡ ገንዘብ፡ ልኩ፡ ፩፡ ሚሊዮን፡ ፪፻፶፡ ሺሕ፡ ብር፡ ብቻ፡ ነው። የቀረው፡ ፫፡ ሚሊዮን፡ ፯፻፶፡ ሺሕ፡ ብር፡ ግን፡ እንደሚያስፈልግ፡ እየታየ፡ ለወደ፡ ፊት፡ ይሰበሰብ፡ ይሆናል። እንግዲህ፡ ባንኩ፡ ዛሬ፡ የሚሠራበት፡ ገንዘብ፡ ፩፡ ሚሊዮን፡ ከ፪፻፶፡ ሺሕ፡ ብር፡ ከሆነ፡ ዘንድ፡ ባንክ፡ ኖት፡ ሲያወጣ፡ ቢያንስ፡ ቢያንስ፡ በዚሁ፡ ገንዘብ፡ ልክ፡ ያትማል። ባንክ፡ ኖቱንም፡ ሁሉ፡ ሕዝብ፡ የተቀበለለት፡ እንደ፡ ሆነ፡ ፩፡ ሚሊዮን፡ ፪፻፶፡ ሺሕ፡ ብር፡ እንደ፡ ውስትና፡ በባንክ፡ ውስጥ፡ ተቀምጦ፡ ያኔ፡ ሚሊዮን፡ ፪፻፶፡ ሺሕ፡ ብር፡ ባንክ፡ ኖት፡ ሕዝቡ፡ ይገበያይበታል። ነገር፡ ግን፡ ባንክ፡ ኖቱን፡ የያዙ፡ ሰዎች፡ ሁሉ፡ ተሰብስበው፡ ባንድነት፡ ወደ፡ ባንክ፡ መጥተው፡ በባንክ፡ ኖቱ፡ ፈንታ፡ ብር፡ ስጡን፡ እንዳይሉ፡ የታወቀ፡ ነውና፤በባንኩ፡ ቤት፡ ውስጥ፡ ስለ፡ ውስትና፡ ከተቀመጠው፡ ፩፡ ሚሊዮን፡ ፪፻፶፡ ሺሕ፡ ብር፡ እጅግ፡ ቢበዛ፡ እኩሌታው፡ ያኽል፡ ለመጠባበቂያ፡ ቀርቶ፡ እኩሌታውን፡ ሰው፡ ተበድሮት፡ ይሥራበታል። ይህም፡ የሆነ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ማኅበረተኞቹ፡ ያገቡት፡ ፩፡ ሚሊዮን፡ ፪፻፶፡ ሺሕ፡ ብር፡ ስለ፡ ፫፡ ሚሊዮን፡ ፯፻፶፡ ሺሕ፡ ብር፡ ሆኖ፡ መሥራቱ፡ ነው። ይህንንም፡ ያኽል፡ የሚሆንበትን፡ ምክንያት፡ ቀጥሎ፡ የተጻፈው፡ ያሳየናል። በእጃቸው፡ አክሲዮን፡ የያዙ፡ ሰዎች፡ ኣክሲዮኑን፡ በከፈሉት፡ ገንዘብ፡ ልክ፡ ለሌላ፡ ሰው፡ አሳልፈው፡ ሸጠው፡ በዋጋው፡ የሚያስፈልጋቸውን፡ ነገር፡ ሊገዙበት፡ ይችላሉ። መቶው፡ ሺሕ፡ ኣክሲዮንም፡ የተከፈለበት፡ ዋጋው፡ ፩፡ ሚሊዮን፡ ፪፻፶፡ ሺሕ፡ ብር፤

የታተመው፡ ባንክ፡ ኖትም፡ ስለ፡ ፩፡ ሚሊዮን፡ ፪፻፶፡ ሺሕ፡ ብር፤ባንኩም፡ የሚያበድረው፡ ጥሬ፡ ብር፡ ፮፻፹፯፡ ሺሕ፡ ብር፤አንድ፡ ላይ፡ ድምሩ፡ ፫፡ ሚሊዮን፡ ፻፹፭፡ ሺሕ፡ ብር፡ ነው።

እንሆ፡ ባንክ፡ ኖት፡ የሚታተም፡ በእንደዚህ፡ ያለ፡ ሒሳብ፡ ነው። ከታኅሣሥ፡ ፳፪፡ ቀን፡ ፲፱፻፬፡ ዓ፡ ም፡ እስከ፡ ፲፱፻፭፡ ዓመተ፡ ምሕረት፡ ድረስ፡ ባንኩ፡ አደራ፡ ለማስቀመጥ፡ የተቀበለው፡ ገንዘብ፡ ወደ፡ ፰፻፲፯፡ ሺሕ፡ ብር፡ ይሆናል። ዛሬም፡ ቢሆን፡ ይበዛል፡ እንጂ፡ አያንስም። የታመነ፡ ተበዳሪም፡ ከተገኘ፡ ከዚህ፡ ገንዘብ፡ ቢያንስ፡ ቢያንስ፡ እኩሌታውን፡ ያኽል፡ ከፍሎ፡ ባንኩ፡ ያተርፍበት፡ ይሆናል። ስለዚህም፡ እላይ፡ ከደመርነው፡ ፫፡ ሚሊዮን፡ ፻፹፭፡ ሺሕ፡ ብር፡ ፬፻፮፡ ሺሕ፡ ፫፻፡ መጨመሩ፡ ነውና፤ባንኩ፡ የራሱ፡ ገንዘብ፡ ፩፡ ሚሊዮን፡ ፪፻፶ ሺሕ፡ ብር፡ ብቻ፡ ሆኖ፡ ባንኩ፡ የሚሠራበት፡ ገንዘብ፡ ፫፡ ሚሊዮን፡ ፫፻፴፱፡ ሺሕ፡ ፫፻፡ ብር፡ ሊሆን፡ ነው። ይኸንንም፡ ያኽል፡ እንዲሆን፡ ቀጥሎ፡ የተጻፈው፡ ሒሳብ፡ ያስረዳናል።

የአክሲዮን፡ ፩፡ ሚሊዮን፡ ፪፻፶፡ ሺሕ፡ ብር።

የባንክ፡ ኖት፡ ፩፡ ሚሊዮን፡ ፪፻፶፡ ሺሕ፡ ብር።

ባንክ፡ የሚያበድረው፡ ጥሬ፡ ብር፡ ከራሱ፡ ፮፻፹፭፡ ሺሕ፡ ብር፡ አደራ፡ ከተቀመጠው፡ ገንዘብ፡ ከፍሎ፡ ፬፻፮፡ ሺሕ፡ ፫፻፡ ብር።

አንድ፡ ላይ፡ ድምሩ፡ ፫፡ ሚሊዮን፡ ፫፻፴፱፡ ሺሕ፡ ፫፻፡ ብር።

እንሆ፡ በሥራ፡ በሠለጠኑ፡ ሕዝቦች፡ አገር፡ እንኳ፡ ብዙው፡ ገንዘብ፡ ሥራ፡ ሊፈታ፡ ጥቂቱም፡ ብር፡ ቢሆን፡ ስለ፡ ብዙ፡ ሆኖ፡ በሁለትና፡ በሦስት፡ ወገን፡ ሊሠራ ይችላል። በዚሁም፡ ሳብ፡ እንደምናየው፡ ብር፡ የለወጥ፡ መሣሪያ፡ ነው፡ እንጂ፤ሌላ፡ ብልኅት፡ የለውም። በተፈለገ፡ ጊዜ፡ የታመነ፡ ባንክ፡ ከመሰከረ፡ ዘንድ፡ ሰው፡ በምስክሩ፡ ወረቀት፡ ሲገበያይ፡ ይችላል። ከዚህም፡ እምነት፡ የተነሣ፡ ጥቂቱ፡ ብር፡ እንደ፡ ብዙ፡ ብር፡ እየሆነ፡ ያገሩን፡ ሕዝብ፡ ሲያገለግል፡ መንግሥት፡ ካወቀበት፡ ለሕዝቡ፡ ትልቅ፡ ጥቅም፡ ነው። በሥራ፡ የሠለጠነ፡ ሕዝብ፡ ባገሩ፡ ቼክና፡ ባንክ፡ ኖት፡ ሌላውም፡ የባንክ፡ ሥራ፡ ሁሉ፡ ሲታወቅ፡ ይጠቀምበታል። ባንድ፡ አገርም፡ የምድር፡ ባቡር፡ ወይም፡ ዐረብያ፡ ሲበዛ፡ ለሕዝቡ፡ ሀብት፡

ማስፈያ፡ እንዲሆን፤እንዲሁም፡ ብር፡ የሚያገለግልበት፡ መንገድ፡ ሲበዛ፡ የሕዝቡም፡ ሀብት፡ ያድጋል። ለተበዳሪውም፡ ወለድ፡ ያንስለታል። ያልሠለጠነ፡ ሕዝብ፡ ግን፡ ባገሩ፡ ምንም፡ እጅግ፡ ያማረ፡ የባንክ፡ ደንብ፡ ቢቆምለት፡ አንዳችም፡ ጥቅም፡ አያገኝበትም። ጥቅሙ፡ ከርሱ፡ ጋራ፡ ለሚገበያዩ፡ ለውጭ፡ አገር፡ ሕዝቦች፡ ነው።

# ፲፫ኛ፡ ምዕራፍ።

እንሆ፡ ከላይ፡ እንዳየነው፡ የባንኩ፡ ገንዘብ፡ ፩፡ ሚሊየን፡ ፱፻፶፡ ሺሕ፡ ብር፡ ነው። ባንክ፡ ኖት፡ ከተለመደ፡ በኋላ፡ ግን፡ ይህ፡ ገንዘብ፡ ቢያንስ፡ ቢያንስ፡ ስለ፡ ፫፡ ሚሊዮን፡ ፫፻፵፩፡ ሺሕ፡ ፫፻፡ ብር፡ ሆኖ፡ ያገለግላል። ባለአክሲዮን የሆኑትም፡ ማኅበረተኞች፡ መቼም፡ አክሲዮኑን፡ ለሌላ፡ ሰው፡ ሸጠው፡ ጥሬ፡ ብር፡ ሊያገኙ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ነው፡ እንጂ፤እንዲሠራበት፡ ብለው፡ ለባንክ፡ የሰጡትን፡ ብር፡ ከባንክ፡ መልሰው፡ ለመውሰድ፡ አይቻላቸውም። ማኅበሩም፡ ሲቆም፡ ለ፱፡ ዓመት፡ ይሠራል፡ ተብሎ፡ ነውና። ማኅበረተኞቹ፡ ሁሉ፡ ተሰብስበው፡ ከማናቸውም፡ አንድ፡ ምክንያት፡ የተነሣ፡ የባንኩ፡ ሥራ፡ ይቅር፡ ካላሉ፡ በቀር፤፶ው፡ ዓመት፡ እስኪያልቅ፡ ድረስ፡ ማኅበረተኛው፡ ለባንኩ፡ ሥራ፡ ያገባውን፡ ገንዘብ፡ መልሱልኝ፡ ቢል፡ አይሆንለትም። ችግር፡ ያገኘው፡ እንደ፡ ሆነ፡ ግን፡ ማኅበረተኛ፡ መሆኑን፡ የሚያስታውቅ፡ በእጁ፡ የያዘውን፡ የምስክር፡ ወረቀት፡ ለሌላ፡ ሰው፡ አሳልፎ፡ ሊሸጥ፡ ይችላል። ስለዚህም፡ ምክንያት፡ ሽያጩቴ፡ ማኅበረተኛ፡ መሆኑ፡ ይቀራል። አክሲዮኑንም፡ የገዛ፡ ሰው፡ ደግሞ፡ ጥሬ፡ ብር፡ ካስፈለገው፡ እንደ፡ ገና፡ ይሸጣል፡ እንጂ፡ ማኅበሩ፡ የመደበው፡ ኀምሳ፡ ዓመት፡ እስኪያልቅ፡ ድረስ፡ በአክሲዮኑ፡ ላይ፡ የተጻፈውን፡ ኀንዘብ፡ ከባንኩ፡ ሊቀበል፡ አይችልም። ስለዚህም፡ ኣክሲዮኑን፡ የያዙ፡ ሰዎች፡ የሰጠናችሁን፡ ገንዘብ፡ መልሱልን፡ ብለው፡ ያለጊዜም፡ ያስቸግሩናል፡ ብለው፡ የባንኩም፡ አለቆች፡ አይይጉበትም። ስለዚህም፡ ባንኩ፡ ይሠራበታል፡ ከተባለው፡ ፫፡ ሚሊዮን፡ ፫፻፷፩፡ ሺሕ፡ ፫፻፡ ብር፡ የአክሲዮኑ፡ ዋጋ፡ የሆነውን፡ ፩፡ ሚሊዮን፡ ፱፻፶፡ ሺሕ፡ ብር፡ ጊዜው፡ ሳይደርስ፡ መልሱ፡ እንባላለን፡ ብለው፡ የባንኩ፡ አለቆች፡

አይሥጉበትም፡ ካልነው፡ ገንዘብ፡ ስጡን፡ እንባላለን፡ ብለው፡ የሚሥጉበት፡ ቀጥሎ፡ የተጻፈውን፡ ገንዘብ፡ ብቻ፡ ነው።

የባንክ፡ ኖት፡ ፩፡ ሚሊዮን፡ ፱፻፵፡ ሺሕ፡ ብር፡ አደራ፡ ካስቀመጡት፡ ገንዘብ፡

ከፍለው፡ ያበደሩት፡ ፬፻፯፡ ሺሕ፡ ፫፻፡ ብር።

ድምሩ፡ ፩፡ ሚሊዮን፡ ፯፻፷፯፡ ሺሕ፡ ፫፻፡ ብር። ለዚሁም፡ መክፈያ፡ በባንክ፡ ቤት፡ ውስጥ፡ ስለ፡ ውስትና፡ የሚቀመጠው፡ ወደ፡ ፯፻፴፫፡ ሺሕ፡ ብር፡ ይሆናል። ስለዚህም፡ ባንኩ፡ ከሚሠራበት፡ ገንዘብ፡ ፩፡ ሚሊዮን፡ ፴፬፡ ሺሕ፡ ፫፻፡ ብር፡ ሕዝቡ፡ በእምነት፡ ሊሠራበት፡ ነው፡ እንጂ፡ ዋስ፡ የለውም።

በሥራ፡ ሠልጥኖ፡ የሚያስፈልገውን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ራሱ፡ የሚሠራ፡ ሕዝብ፡ በእንደዚህ፡ ያለው፡ ነገር፡ ይጠቀምበታል፡ እንጂ፡ አይጐዳበትም። ርስ፡ በርሱ፡ ሲለዋወጥ፡ መሣሪያ፡ ሆኖ፡ የሚረዳው፡ ብርና፡ ወርቅ፡ እንዳያንስ፡ እንደዚህ፡ ያለ፡ ብልኀት፡ ያወጣበታል። በዚህም፡ ብልኀት፡ ጥቂቱ፡ ብር፡ እንደ፡ ብዙ፡ ሆኖ፡ ያገለግለዋል። በሥራ፡ ያልሠለጠነ፡ ሁኖ፡ የሚያስፈልገውን፡ ነገር፡ ራሱ፡ ለመሥራት፡ የማይችል፡ ሕዝብ፡ ግን፡ ባገሩ፡ ባንክ፡ ኖት፡ ቢለመድ፡ የሚጠቅመው፡ መሆኑን፡ ያስጠረጥራል። የሚያስፈልገውን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ራሱ፡ ለመሥራት፡ የማይችል፡ ሕዝብ፡ መቼም፡ ልብሱና፡ የቤቱ፡ መሣሪያ፡ የሚመጣለት፡ ከውጭ፡ አገር፡ ነው፡ ደግሞ፡ ልብሱንና፡ የቤቱን፡ መሣሪያ፡ የሚሸጡለት፡ ሕዝቦች፡ ግን፡ የሚቀበሉት፡ ዋጋቸው፡ ጥሬ፡ ብር፡ ብቻ፡ ነው፤ባንክ፡ ኖት፡ ኣይቀበሉም። ባገራቸው፡ ዋጋ፡ ሳይጐድል፡ በገበያ፡ የሚሄደው፡ ያገራቸው፡ ባንክ፡ ያተመው፡ ባንክ፡ ኖት፡ ብቻ፡ ነው። ጥሬው፡ ብር፡ ግን፡ የትም፡ ቢሄዱ፡ ከዋጋው፡ የሚያጐድለው፡ ብዙ፡ አይደለም።

እንግዲህም፡ ባንድ፡ አገር፡ ባንክ፡ ኖት፡ ሲለመድ፡ አንዱ፡ ብር፡ ስለ፡ ሁለት፡ ሊሠራ፡ ነው። አንድ፡ ሰው፡ አንድ፡ ነገር፡ ሸጦ፡ ባንክ፡ ኖት፡ ሲቀበል፡ አንዱ፡ ሰው፡ በባንክ፡ ኖቱ፡ ላይ፡ የተጻፈውን፡ ጥሬ፡ ብር፡ ይቀበላል። ባንክ፡ ኖቱን፡ የሚቀበል፡ ሰው፡ መቼም፡ ብሩን፡ በፈለግሁ፡ ጊዜ፡ በባንክ፡ ተቀምጧልና፡ እወስዳለሁ። ብሎ፡ ከማመኑ፡ የተነሣ፡ ነው። ባንኩ፡ ግን፡ ብሩን፡ አያስቀምጥም፤ለሌላ፡ ሰው፡ ያበድረዋል፡ እንጂ።

ስለዚህም፡ አንዱ፡ ብር፡ ስለ፡ ሁለት፡ ብር፡ ሆኖ፡ ስለ፡ ሥራ፡ ባገሩ፡ ውስጥ፡ ያለው፡ ብር፡ ባንድ፡ ጊዜ፡ ዕጥፍ፡ የሆነ፡ ይመስላል፤ሕዝቡም፡ የሚያስፈልገውን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ራሱ፡ የሚሠራ፡ ከሆነ፡ በሕዝቡ፡ ውስጥ፡ ልብስና፡ ቤት፡ መሣሪያ፡ ለማስመጣት፡ የሚያስቡ፡ ሰዎች፡ ዕጥፍ፡ ሊሆኑ፡ ነው። ጥሬ፡ ብር፡ የያዙ፡ ሰዎች፡ መቼም፡ ለሚያስመጡት፡ ዕቃ፡ ዋጋ፡ ጥሬውን፡ ብር፡ ይሰጣሉ። ባንክ፡ ኖት፡ የያዙ፡ ሰዎች፡ ግን፡ ባንክ፡ ኖቱ፡ ወደ፡ ውጭ፡ ነገር፡ አይሄድላቸውምና፤ወደ፡ ባንኩ፡ አገር፡ ሄደው፡ በብር፡ ሊለውጡት፡ ነው።

በመዠመሪያ፡ ባንኩ፡ አይቸግርም፡ ይሆናልና፤ባንክ፡ ኖቱን፡ እየተቀበለ፡ ባንክ፡ ኖቱን፡ ለሚያመጡ፡ ሰዎች፡ ጥሬውን፡ ብር፡ ይሰጣል። ችግር፡ የሚያገኛቸው፡ ግን፡ በመዠመሪያ፡ ብቻ፡ ነው። ባንክ፡ ኖት፡ የያዘው፡ ሰው፡ ሲበዛ፡ ግን፡ ሳይቸገሩ፡ አይቀሩም። መቼም፡ ባንክ፡ ኖቱን፡ የያዘ፡ ሰው፡ ለኑሮው፡ የሚያስፈልገውን፡ ነገር፡ ካልገዛበት፡ ባንክ፡ ኖቱ፡ አይጠቅመውም። የሚያስፈልገውም፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ባገሩ፡ የሚሠራ፡ ቢሆን፡ ወደ፡ ባንክ፡ ቤት፡ ሄዶ፡ በባንክ፡ ኖቱ፡ ላይ፡ የተጻፈውን፡ ብር፡ በጥሬው፡ ስጡኝ፡ ሳይል፡ ባንክ፡ ኖቱ፡ ብቻ፡ ሁሉንም፡ ነገር፡ ለመግዛት፡ ይችላል። በሥራ፡ ያልሠለጠነ፡ ሕዝብ፡ ግን፡ አንዳች፡ ነገር፡ ባገሩ፡ አይሠራም። ሁሉም፡ ነገር፡ የሚመጣለት፡ ከውጭ፡ አገር፡ ነው። ስለዚህም፡ የተቀበለውን፡ ባንክ፡ ኖት፡ ከውጭ፡ አገር፡ የሚመጣውን፡ ዕቃ፡ ሊገዛበት፡ ሲፈልግ፡ ወደ፡ ባንክ፡ ሄዶ፡ በብር፡ ይለውጠዋል። ባንኩም፡ የራሱ፡ ብር፡ ቢያንሰው፡ አደራ፡ ከተቀመጠው፡ ጥሬ፡ ብር፡ ከፍሶ፡ ይሰጣል። ገንዘቡን፡ አደራ፡ ያስቀመጠ፡ ሰውም፡ ገንዘቤን፡ ስጡኝ፡ ሲል፡ ቢመጣም፡ ባንክ፡ ኖት፡ ይሰጡታል። ሰውዬውም፡ ገንዘብ፡ ያስፈለገው፡ ባገር፡ ውስጥ፡ ለሚፈጸም፡ ጉዳይ፡ ከሆነ፡ ባንክ፡ ኖቱ፡ በገበያ፡ እንዲሄድ፡ ያውቃልና፤ ሸክሙ፡ ስለ፡ ቀለለት፡ ከጥሬ፡ ብር፡ ባንክ፡ ኖት፡ ሊቀበል፡ ይወዳል። በጊዜም፡ ብዛት፡ ባገር፡ ባንክ፡ ኖት፡ እየበዛ፡ ይሄዳል። ጥሬው፡ ብር፡ ግን፡ ለተሠራ፡ ዕቃ፡ መግ[፡] ወደ፡ ውጭ፡ አገር፡ ይሄዳል። ይህም፡ ከሆነ፡ በኋላ፡ ባንክ፡ ኖት፡ በእጁ፡ የያዘ፡ ሰው፡ ከባንክ፡ ጥሬ፡ ብር፡ እንዳይፈልግ፡ ብልኀት፡ ካልተደረገ፡ በቀር፡ ባንኩ፡ በጣም፡ ሳይቸገር፡ አይቀርም። ባንኩ፡ መቼም፡ ራሱ፡ ወደ፡ ጭንቅ፡ እንዳይገባ፡ ይፈልግ፡ ይሆናል። ስለዚህም፡ ከርሱ፡ የተበደሩትን፡ ሰዎች፡ አስጨንቆ፡ ይይዛል። ተበዳሪዎቹም፡

የሚከፍሉትን፡ ገንዘብ፡ ሳያገኙ፡ ቢያዙ፡ ነጋዴዎች፡ እንደ፡ ሆኑ፡ በእጃቸው፡ ያለውን፡ ቆዳና፡ ቡና፡ ባላገሮችም፡ እንደ፡ ሆኑ፡ መሬታቸውን፡ በርካሽ፡ ለመሸጥ፡ የግድ፡ ይሆንባቸዋል። ቆዳውና፡ ቡናው፡ ሌላውም፡ ካገሩ፡ የሚገኘው፡ ዕቃ፡ በርካሽ፡ ሲሸጥ፡ የሕዝቡ፡ ድካም፡ በከንቱ፡ ስለ፡ ሄደ፡ ሕዝቡ፡ መክሰሩ፡ ነውና፤መንግሥት፡ ይጐዳል። ባሳገሩም፡ መሬቱን፡ በርካሽ፡ ለመሸጥ፡ የግድ፡ ሲሆንበት፡ ባገሩ፡ ውስጥ፡ ያለው፡ መሬት፡ በጥቂቶች፡ ሀብታሞች፡ ሰዎች፡ እጅ፡ ሊጠቀለል፡ ነውና፤ባገሩ፡ ውስጥ፡ የሚያርፍበት፡ ቦታ፡ ያጣ፡ ድኻ፡ ሊበዛ፡ መሆኑን፡ ያሳየናል። ከዚህ፡ ቀደምም፡ እንደ፡ ተረዳነው፡ ባገሩ፡ ድኻ፡ ሲበዛ፡ ለመንግሥት፡ ጐዳት፡ ነው፤መሠረቱ፡ ይነቃነቃል።

ስለዚህም፡ ሕዝቡ፡ በሥራ፡ ባልሠለጠነ፡ አገር፡ ባንክ፡ ኖት፡ ሲለመድ፡ ባገሩ፡ ላይ፡ ትልቅ፡ ጐዳት፡ ሊያወርድ፡ ይችላል። ባገሩ፡ ባንክ፡ ኖት፡ ሲለመድ፡ መንግሥት፡ ወዲያው፡ ሕዝቡን፡ በሥራ፡ ለማሠልጠን፡ ታጥቆ፡ ከተነሣ፡ ግን፡ ባንክ፡ ኖት፡ ቢለመድ፡ ጐዳት፡ የለበትም፤ ይልቁንም፡ ትልቅ፡ ጥቅም፡ ይገኝበታል። ባገሩ፡ ውስጥ፡ የሚበቃ፡ የለውጥ፡ መሣሪያ፡ የሌለው፡ ሕዝብ፡ ብዙ፡ ሀብት፡ እንዳያገኝ፡ ከዚህ፡ ቀደም፡ ተረድተነዋል። ስለዚህም፡ አንዱ፡ ብር፡ ስለ፡ ሁለት፡ ስለ፡ ሦስት፡ እየሆነ፡ እንዲያገለግል፡ የሚያደርግ፡ ባንክ፡ ኖት፡ ነውና፤ሁሉንም፡ ነገር፡ ራሱ፡ ሊሠራ፡ የሚችል፡ ሕዝብ፡ ይጠቀምበታል። የሚያስፈልገውንም፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ከውጭ፡ አገር፡ የሚያስመጣ፡ ሕዝብ፡ ግን፡ ጥሬው፡ ብር፡ በባንክ፡ የተቀመጠ፡ መስሎት፡ ርስ፡ በርሱ፡ በባንክ፡ ኖት፡ ሲለዋወጥ፡ ባገሩ፡ ያለ፡ ጥሬ፡ ብር፡ ሁሉ፡ ለዕቃ፡ መግዣ፡ ተብሎ፡ ወደ፡ ውጭ፡ አገር፡ ይሄዳል። በዚህም፡ ምክንያት፡ የተነሣ፡ ሕዝቡ፡ ባልሠለጠነ፡ አገር፡ ውስጥ፡ ባንክ፡ ኖት፡ ሲለመድ፡ ካላወቁበት፡ ጐዳት፡ ያመጣል።

# ፲ኛ፡ ምዕራፍ።

ዛሬ፡ በኢትዮጵያ፡ የቆመው፡ ባንክ፡ አፍ፡ አቢሲኒያ፡ ከቆመበት፡ ቀን፡ ዠምሮ፡ እስከ፡ ኀምሳ፡ ዓመት፡ ድረስ፡ በኢትዮጵያ፡ ሌላ፡ ባንክ፡ እንዳይቆም፡ ውል፡ ተቀብሏል። ከዚህ፡ ቀደም፡ እንደ፡ ተረዳነው፡ ግን፡ ማናቸውም፡ ነገር፡ በጥቂቶች፡ ሰዎች፡ እጅ፡ ገብቶ፡ ሞኖፖል፡ ሲሆን፡

ለሕዝብም፡ ለመንግሥትም፡ ጉዳት፡ ነው። ለዐፄ፡ ምኒልክ፡ አንድ፡ ሰው፡ መጥቶ፡ ባገርዎ፡ ከኔ፡ በቀር፡ ሌላ፡ ሰው፡ እንዳያርስ፡ ወይም፡ በቅሎ፡ ገዝቶ፡ እያከራየ፡ እንዳይነግድ፡ ወይም፡ እኔን፡ ሳይጠይቅ፡ በየቤቱ፡ ማንም፡ ወጥ፡ እየሠራ፡ እንዳይበላ፡ ፈቃድ፡ ይስጡኝ፡ ብሎ፡ ለምኗቸው፡ ቢሆን፡ የሚናገራቸው፡ ቃል፡ ምንም፡ ቢያምር፡ የሚሰጣቸው፡ ተስፋ፡ ምንም፡ ትልቅ፡ ቢሆን፡ ያለጥርጥር፡ ይቈጡት፡ ነበር።

አማላጅ፡ ሆኖ፡ ይህነን፡ ቃል፡ የነገራቸውንም፡ ሹማቸውን፡ ጉሶ፡ በልተን፡ መንግሥቴን፡ ልትሸጥ፡ አሰበኻል፡ ብለው፡ ሳይቈጡት፡ አይቀሩም፡ ነበር። የባንክ፡ ሥራ፡ ሞኖፖል፡ እንዲሆን፡ ግን፡ የዕውቀት፡ ባሕሪ፡ በሌላቸው፡ ሰዎች፡ ቃል፡ ተታለው፡ ዐፄ፡ ምኒልክ፡ ፈቃድ፡ ሰጡ። ያውም፡ ለጥቂት፡ ጊዜ፡ ነው፡ አይባል፡ ለኀምሳ፡ ዓመት፡ ነው። ሕዝቡም፡ በሥራ፡ ከሠለጠነ፡ ዝንድ፡ ያለባንክ፡ እንዳይሆንለት፡ ተመልክተነዋል። ደጉን፡ ንጉሥ፡ ዐፄ፡ ምኒልክን፡ ግን፡ ይህንን፡ ሁሉ፡ ነገር፡ ያስረዳቸው፡ ሰው፡ የለም። የባንክ፡ ሥራ፡ የገንዘብ፡ ሥራ፡ ነውና፤የሕዝብ፡ ትዳር፡ መሠረት፡ እንደ፡ ሆነ፡ የታወቀ፡ ነው። ብር፡ የማይገባበት፡ ጉዳይ፡ የለም፤ ማንኛውንም፡ ለኑሯችን፡ የሚያስፈልገንን፡ ሁሉ፡ በሩብ፡ ባላድ፡ በተሙን፡ በብር፡ ገዝተን፡ ነው። ስለዚህም፡ ይህ፡ ተሙን፡ ሩብ፡ አላድ፡ ብር፡ እስኪገኝ፡ ድረስ፡ የሚደከመው፡ ድካም፡ ጥቂት፡ ወይም፡ ብዙ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ኣንድ፡ ባንክ፡ እንዳወቀ፡ እንዲለየው፡ መንግሥት፡ በውል፡ መፍቀዱ፡ ትልቅ፡ ጉዳት፡ ነው። ሕዝቡ፡ በመላው፡ ብሩን፡ የሚያስቀምጥበት፡ ቦታ፡ አንድ፡ ብቻ፡ እንዲሆን፡ ቢደነባ፡ ደግ፡ ይሆናልን፤ባገሩም፡ ውስጥ፡ ካንዱ፡ ወረዳ፡ ወዳንዱ፡ ወረዳ፡ ብር፡ ሲላክ፡ መልክተኛው፡ አንድ፡ ብቻ፡ እንዲሆን፡ ቢደነገግ፡ ይበጃልን። የዚህንም፡ መልስ፡ በምሳሌ፡ እናስረዳለን።

ባንድ፡ አገር፡ ውስጥ፡ ባላንጣ፡ ተፎካካሪ፡ የሌለው፡ አንዳች፡ ነገር፡ ሲቆም፡ ሕዝቡ፡ ይጐዳበታል፡ እንጂ፡ አይጠቀምበትም። ስለዚህም፡ የጥይትንና፡ የባሩድን፡ ምስጢር፡ የሚያውቁ፡ ሰዎች፡ ጥቂቶች፡ ብቻ፡ ቢሆኑ፡ የቀረውን፡ ሰው፡ ሁሉ፡ ፈጅተው፡ የዓለምን፡ ሀብት፡ ሁሉ፡ ቀምተው፡ ለብቻቸው፡ ለመኖር፡ ማሰባቸው፡ አይቀርም፡ ነበር። በሌላውም፡ ነገር፡ ሁሉ፡ እንደዚሁ፡ ነው። በያዘው፡ ሥራ፡ ባላንጣ፡ እንዳይነሣበት፡ ርግጡን፡ ያወቀ፡ ሰው፡ ሁሉ፡ ሌላውን፡ ሰው፡ ደስ፡

የሚያሰኝበት፡ ወይም፡ የሚጠቅምበትን፡ መንገድ፡ አይፈልግም። ሐሳቡም፡ ሕልሙም፡ ለጥቅሙ፡ ብቻ፡ ነው። ሚዛን፡ የማይዘናበለው፡ በሁለቱም፡ ጫፍ፡ እኩል፡ የሚከብድ፡ ነገር፡ ሲደረግበት፡ ነው። የሰው፡ ባሕሪው፡ ሁለት፡ ነው። ኣንዱ፡ መልአካዊ፤ሁለተኛው፡ ግን፡ እንስሳዊ፡ ይባላል። ቀስቃሽ፡ ካላገኘ፡ ግን፡ ሰው፡ መልአካዊ፡ ባሕሪውን፡ ኣይከተልም። ወደ፡ እንስሳዊ፡ ባሕሪው፡ ያደላል፤ለሰው፡ ኣውራ፡ ቀስቃሽ፡ ግን፡ ባላንጣ፡ ነው። ተፎካካሪ፡ ባላንጣ፡ ያለው፡ ሰው፡ ክፉ፡ ሥራ፡ ለመሥራት፡ አይችልም። ለባለጋራውም፡ ቢሆን፡ እንዳይሳነው፡ ያውቃልና፤በደግነት፡ ለማሸነፍ፡ ይጣጣራል። ገንዘብ፡ ያለው፡ ሰው፡ አንድ፡ ብቻ፡ ሲሆን፡ ገንዘቡን፡ ሲያበድር፡ የፈለገውን፡ ያኽል፡ ወለድ፡ አምጡ፡ ቢል፡ ይሆንለታል። የተጨነቀውም፡ ሰው፡ አበድረኝ፡ ሊል፡ ቢመጣበት፡ አይራራለትም። ይልቁንም፡ የሰውዬውን፡ መጨነቅ፡ አይቶ፡ ከፍ፡ ያለ፡ ወለድ፡ ይፈልጋል። ገንዘብ፡ የሚያበድር፡ ሌላ፡ ባላንጣ፡ ሲነሣበት፡ ግን፡ ተበዳሪዎቹ፡ ወደባላንጣው፡ እንዳይሄዱበት፡ ርኅሩኅ፡ ነው፡ እንዲባል፡ ይጣጣራል። በተቸገሩትም፡ ሰዎች፡ ላይ፡ መጨከኑን፡ ይተዋል። ባለጋራውም፡ የሚቀበለው፡ ወለድስንት፡ እንደ፡ ሆነ፡ እየጠየቀ፡ ሰው፡ ወደ፡ ርሱ፡ እንዲመጣለት፡ የሚቀበለውን፡ ወለድ፡ ያሳንሳል፤ዝቅ፡ ያደርጋልም። ገንዘብ፡ የሚያበድሩት፡ ባላንጣዎችም፡ በብዙ፡ ቍጥር፡ የያንዳንዱ፡ ባላንጣ፡ ባሕሪ፡ እየተሻለ፡ ይሄዳል፤ወለዱም፡ ሁሉ፡ በጣም፡ ዝቅ፡ ይላል። ወለድም፡ ዝቅ፡ እያለ፡ ሲሄድ፡ ተበዳሪም፡ ይበዛል። ተበዳሪም፡ ሲበዛ፡ ባገርም፡ ያለው፡ ብር፡ ሁሉ፡ ሥራ፡ አይፈታምና፡ ሕዝብ፡ ይጠቀምበታል። ሕዝብም፡ ሲጠቀም፡ የመንግሥትም፡ ኀይል፡ እያደገ፡ ይሄዳል። ነገሩንም፡ እንድንረዳው፡ ቀጥሎ፡ የተጻፈውን፡ የሒሳብ፡ መንገድ፡ ሰንብረን፡ እንመልከት፤እሱም፡ አበዳሪው፡ ሲበዛ፡ የተበዳሪውም፡ ቍጥር፡ መብዛቱንና፡ የወለዱን፡ እያነሰ፡ መሄድ፡ ይገልጽልናል።

| ያበዳሪዎቹ፡ ቍጥር፡ | ከሺው፡ ብር፡ ወለድ፡ የሚያጎድሉት፡ ብር፡ ቍጥር፡ | ከሺው፡ ብር፡ የሚቀበሉት፡ ብር፡ የድርሻው፡ ቍጥር፡ | የተበዳሪች፡ ሰዎች፡ ቍጥር፡ |
|---|---|---|---|
| ፩ | ፲ | ፩፻ | ፪ |
| ፪ | ፳ | ፺ | ፬ |
| ፫ | ፴ | ፹ | ፰ |
| ፬ | ፵ | ፸ | ፲፮ |
| ፭ | ፶ | ፷ | ፴፪ |
| ፮ | ፷ | ፶ | ፷፬ |
| ፯ | ፸ | ፵ | ፻፳፰ |
| ፰ | ፹ | ፴ | ፪፻፶፮ |
| ፱ | ፺ | ፳ | ፭፻፲፪ |
| ፲ | | ፲ | ፲፻ ፳፬ |

ይኸው፡ በላይኛው፡ የሒሳብ፡ አካሄድ፡ እንደምናየው፡ ያበዳሪዎቹ፡ ባሕሪ፡ እየተሻለ፡ የሚሄድ፡ ወለድም፡ ዝቅ፡ የሚል፡ ተበዳሪም፡ የሚበዛ፡ አበዳሪዎች፡ ሲበዙ፡ ነው። ከዚህም፡ የተነሣ፡ ባገር፡ ያለው፡ ብር፡ ሥራ፡ አይፈታም። አበዳሪ፡ አንድ፡ ሲሆን፡ ግን፡ ወስዱ፡ ብዙ፡ ስለ፡ ሆነ፡ ተበዳሪም፡ እያነሰ፡ ይሄዳል። ባገሩም፡ ያለው፡ ብር፡ ሥራ፡ የሚፈታ፡ ስለ፡ ሆነ፡ መንግሥትንም፡ ይጐዳዋል። በሌላውም፡ የሕዝብን፡ ትዳር፡ የሚነካ፡ ነገር፡ ሁሉ፡ እንደዚሁ፡ ነው። ሞኖፖል፡ ለመንግሥትም፡ ለሕዝብም፡ ጉዳት፡ ነው። በያዘው፡ ሥራ፡ ባላንጣ፡ እንዳይነሣበት፡ ርግጡን፡ ያወቀ፡ ሰው፡ ከጥቅሙ፡ በቀር፡ ሌላ፡ አያስብም። ለሕዝቡም፡ ክፉ፡ መንገድ፡ ሆኖ፡ ሕዝቡ፡ ርስ፡ በርሱ፡ እንዳይራራና፡ እንዳይረዳዳ፡ ያደርጋል። ስለዚህም፡

ሞኖፖል፡ የበዛበት፡ አገር፡ ቀጣፊና፡ ሌባ፡ ወንበዴም፡ ይበዛበታል። ሞኖፖልም፡ ሁሉ፡ የሚጐዳ፡ ከሆነ፡ ዘንድ፡ ይልቁንም፡ የባንክ፡ ሥራ፡ ሞኖፖል፡ ሲሆን፡ እጅግ፡ ክፉ፡ ነው። ዐረቄና፡ ጠጅ፡ ሞኖፖል፡ ሆኖ፡ ያረቄውና፡ የጠጁ፡ ዐይነት፡ ለጤና፡ የሚጐዳ፡ ሲሆን፡ በመላው፡ ሕዝብ፡ ኣይጐዳበትም፤የሚጐዳው፡ ጠጭው፡ ብቻ፡ ነው። የሐር፡ ሞኖፖል፡ ሲሆን፤የሚጐዳው፡ ሐር፡ ለባሹ፡ ብቻ፡ ነው። ትንባኾም፡ ሞኖፖል፡ ሲሆን፤የሚጐዳው፡ የትንባኾ፡ ልማድ፡ ያለው፡ ሰው፡ ብቻ፡ ነው። እያንዳንዱ፡ ሰው፡ ትልቅም፡ ቢሆን፡ ትንሽም፡ ቢሆን፡ ሀብታምም፡ ቢሆን፡ ድኻም፡ ቢሆን፡ ለኑሮው፡ የሚያስፈልገውን፡ ነገር፡ ሞኖፖል፡ ማድረግ፡ ግን፤በሕዝብ፡ ድኽነት፡ በመንግሥትም፡ ጒዳት፡ እንዲወርድ፡ እንደ፡ መፈለግ፡ ያኽል፡ ነው። እንግዲህ፡ በማናቸውም፡ አገር፡ ከብር፡ አብልጦ፡ የሚፈለግ፡ ነገር፡ የለም፡ ብር፡ የለውጥ፡ መሣሪያ፡ ነው። ጎበሬ፡ ቢያርስ፡ ሸማኔም፡ ቢሠራ፡ ጸሓፊ፡ ቢጸፍ፡ ፈራጅ፡ ሲፈርድ፡ ቢውል፡ ነጋዴም፡ ቢነግድ፡ ሁሉም፡ የፈለጉትን፡ ነገር፡ የሚያገኙ፡ ስለ፡ ድካማቸው፡ ዋጋ፡ ኣስቀድመው፡ ብር፡ ከተቀበሉ፡ በኋላ፡ ነው፡ ብር፡ እስኪገኝ፡ ድረስ፡ ድካሙ፡ ጥቂት፡ የሚሆን፡ ግን፡ ወለዱ፡ ሲያንስ፡ ነው። ወለድም፡ የሚያንስ፡ አበዳሪዎቹ፡ ብዙ፡ ሲሆኑ፡ ነው። አበዳሪዎቹም፡ የሚበዙ፡ ሕዝቡ፡ በሥራ፡ ሲሠለጥን፡ ነው። ሕዝብም፡ በሥራ፡ የሚሠለጥን፡ በሥርዐት፡ ፊት፡ ርስ፡ በርሱ፡ እኩል፡ ሆኖ፡ የሚበቃ፡ ዐቅም፡ ካገኘ፡ ዘንድ፡ ልቡ፡ የመረጠውን፡ ሥራ፡ ለመሥራት፡ ሲችል፡ ነው። ስለዚህም፡ በኢትዮጵያ፡ የባንኩ፡ ሥራ፡ ሞኖፖል፡ በመሆኑ፡ ለኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ትልቅ፡ ጒዳት፡ ነው።

ዛሬ፡ በኢትዮጵያ፡ የቆመው፡ ባንክ፡ ኦፍ፡ አቢሲኒያ፡ ማኅበረተኞቹ፡ የውጭ፡ ሰዎች፡ ናቸውና፤የባንኩ፡ ውል፡ የተሰጠው፡ በማይገባ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ሰው፡ ሁሉ፡ ተረድቶት፡ በኢትዮጵያ፡ ባንኩን፡ ከልብ፡ የተቀበለው፡ ሰው፡ የለም። ስለዚህም፡ የባንኩ፡ አለቆች፡ ከኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡ ሹማምት፡ የሚበቃ፡ ርዳታ፡ እንዳያገኙ፡ ዐውቀውት፡ ለኢትዮጵያ፡ ሰው፡ ሲያበድሩ፡ እጅግ፡ ተጠንቅቀው፡ ነው፤የሚበዛውን፡ ገንዘባቸውን፡ እየተበደሩ፡ የሚጠቀሙበት፡ የውጭ፡ አገር፡ ሰዎች፡ ናቸው። እነዚህም፡ የውጭ፡ ኣገር፡ ሰዎች፡ በተበደሩት፡ ገንዘብ፡ ነግደው፡ ያገኙትን፡ ትርፍ፡ ገንዘብ፡ ወዳገራቸው፡ ይሰዳሉ፡ እንጂ፤ለኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ጥቅም፡

የሚሆን፡ ሥራ፡ አይሠሩበትም። የባንኩም፡ ጌቶች፡ የውጭ፡ አገር፡ ሰዎች፡ ስለ፡ ሆኑ፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝቦች፡ ባንኩን፡ አያምኑትም። ስለዚህም፡ ገንዘቡን፡ በባንክ፡ የሚያስቀምጥ፡ የኢትዮጵያ፡ ሰው፡ ጥቂት፡ ነው። ገንዘቡን፡ አደራ፡ የሚያስቀምጥበት፡ ሌላ፡ ቦታ፡ ስላጣ፡ የሚበዛው፡ የኢትዮጵያ፡ ሰው፡ ብሩን፡ በማሰሮ፡ እየከተተ፡ ከመሬት፡ በታች፡ ይቀብረዋል። ባለገንዘቦችም፡ የኢትዮጵያ፡ ሰዎች፡ ተባብረው፡ አንድ፡ የረባ፡ ባንክ፡ አቍመው፡ በገንዘባቸው፡ እንዳይሠሩበት፡ የባንኩ፡ ሥራ፡ ሞኖፖል፡ ሆኗልና፡ ፈቃድ፡ አያገኙም። ቢያገኙም፡ በማናቸውም፡ ትንንሽ፡ ምክንያት፡ እንዳይወረሱ፡ እየፈሩ፡ ገንዘብ፡ እንዳላቸው፡ ቢገለጽ፡ ኣይወዱም።

ከጥቂት፡ ዓመት፡ በፊት፡ ያገራችን፡ ሹማምት፡ በመንግሥት፡ ትእዛዝ፡ ተሰብስበው፡ አንድ፡ የባንክ፡ ዐይነት፡ ማኅበር፡ አቆሙ። ማኅበሩ፡ ግን፡ እስከ፡ ዛሬ፡ ድረስ፡ የረባ፡ ሥራ፡ አልሠራም። የረባ፡ ሥራም፡ አለመሥራቱ። ምናልባት፡ የኢትዮጵያ፡ ሰው፡ ለባንክ፡ ሥራ፡ የሚበቃ፡ አእምሮ፡ ስላጣ፡ አይደለም። ነገር፡ ግን፡ ማኅበረተኞች፡ የሆኑት፡ ሹማምቶች፡ ማኅበሩን፡ ያቆሙት፡ ስለ፡ ሹመታቸው፡ እንዳልሆነ፡ ባይገባቸው፡ በመንግሥት፡ ጒዳይ፡ ሁሉ፡ ባለጋራቸውን፡ ለማጥቃት፡ እንደሚጥሩ፤እንዲሁም፡ ስባንኩ፡ ጒዳይ፡ ለምክር፡ በተሰበሰቡ፡ ቍጥር፡ ርስ፡ በርሳቸው፡ ከመነቃቀፍ፡ አንዱ፡ ያንዱን፡ ሥራ፡ ከማስነወር፡ በቀር፡ ሌላ፡ የረባ፡ ሥራ፡ ለመሥራት፡ አልሆነሳቸውም። ይልቍንም፡ የባንኩ፡ ጒዳይ፡ ሲመከር፡ አንዳንድ፡ ጊዜ፡ ልዑል፡ አልጋ፡ ወራሽ፡ አብረው፡ ስለ፡ ተቀመጡ፡ እያንዳንዱ፡ ማኅበረተኛ፡ ብልኅ፡ ተብሎ፡ እንዲመሰገንና፡ ባለጋራውን፡ እንዲያጠቃ፡ ከሙግት፡ በቀር፡ ሌላ፡ ለማኅበሩ፡ ሥራ፡ የሚበጅ፡ እውነተኛ፡ ምክር፡ አላመጣም። ስለዚህም፡ የባንኩ፡ ሥራ፡ እስከ፡ ዛሬ፡ ድረስ፡ የኢትዮጵያን፡ ሕዝብ፡ ሳይጠቅምመቅረቱ፡ የሚገርም፡ ነገር፡ አይደለም። ለወደ፡ ፊትም፡ ሳይጠቅም፡ ቢቀር፡ አያስደንቅም። ማናቸውም፡ ማኅበር፡ ለያንዳንዱ፡ ማኅበረተኛና፡ ለመላው፡ ሕዝብ፡ ጥቅም፡ የሚሆን፡ ማኅበረተኞቹ፡ ወደው፡ ሲተባበሩ፡ ነው፡ እንጂ፤ንጉሠ፡ ነገሥቱ፡ የገቡበት፡ ማኅበር፡ ነውና፡ ሳንገባ፡ ብንቀር፡ እንነቀፋለን፡ እያሉ፡ ለግብር፡ ይውጣ፡ ነው፡ እንጂ፤ሲተባበሩ፡ አይደለም። እንደዚህ፡ ያሉትም፡ ማኅበረተኞች፡ ተስማምተው፡ ኣንዳች፡ የረባ፡ ሥራ፡ ለመሥራት፡

አይችሉም፤አይሳካላቸውም። የኢትዮጵያ፡ መንግሥትም፡ ሕዝቡ፡ እየተባበረ፡ የባንክ፡ ሥራ፡ እንዲያቆም፡ ከፈለገ፡ ዘንድ፡ እንደዚህ፡ ያለውን፡ ማኅበር፡ ማቆሙን፡ ትቶ፡ ሕዝቡን፡ በሥራ፡ ቢያሠለጥን፡ ይሻላል። የሰውም፡ ገንዘብ፡ እንዲታፈር፡ የተደላደለ፡ ሥርዐት፡ ያውጣ። እሱ፡ ራሱም፡ ማኅበረተኛ፡ እየሆነ፡ በያንዳንዱ፡ ማኅበር፡ መግባቱን፡ ትቶ፡ ማኅበር፡ ሲቆም፡ እንዴት፡ ባለ፡ ደንብ፡ እንዲያድር፡ በፍትሐ፡ ነገሥት፡ ለይቶ፡ ዐውቆ፡ ዜጎቹ፡ የወደዱትን፡ ሥራ፡ ለመሥራት፡ እንዲተባበሩ፡ ሙሉ፡ ፈቃድ፡ ቢሰጥ፡ ይሻላል። ይህነንም፡ ካደረገ፡ በኋላ፡ ከሕዝቡ፡ ውስጥ፡ አንድም፡ ሰው፡ ገንዘቡን፡ ከመሬት፡ በታች፡ ሊቀብር፡ አይወድም። ወደ፡ ባንክ፡ አግብቶ፡ እንዲወልድለት፡ ወይም፡ የተሻለ፡ ሥራ፡ እንዲሠራለት፡ ይፈልጋል፡ እንጂ። ሕዝቡም፡ በሥራ፡ ሠልጥኖ፡ አርነት፡ ሲያገኝ፡ ባገሩ፡ ውስጥ፡ ያለው፡ ገንዘብ፡ ሥራ፡ ይይዛልና፤መንግሥት፡ የሚያገኘው፡ ክብር፡ ይበዛል። በእንደዚህ፡ ያለውም፡ መንገድ፡ የሚያገኘው፡ ግብር፡ ማኅበረተኛ፡ እየሆነ፡ ከያንዳንዱ፡ ማኅበር፡ ከሚያገኘው፡ ትርፍ፡ ሳይበልጥ፡ አይቀርም። መንግሥት፡ ከሁሉ፡ በላይ፡ ነው፤ይህነን፡ በላይነቱን፡ ትቶ፡ ከዜጎቹ፡ ጋራ፡ በማኅበረተኛነት፡ መተባበር፡ አይገባውም፤እንደዚህም፡ ቢያደርግ፡ አይጠቀምም።

ዛሬ፡ በኢትዮጵያ፡ ደኅና፡ ባንክ፡ ከላይም፡ የተጠራው፡ ባንክ፡ ኦፍ፡ አቢሲኒያ፡ ብቻ፡ ስለ፡ ሆነ፤ይህም፡ ባንክ፡ ኦፍ፡ አቢሲኒያ፡ ለኢትዮጵያ፡ ሰው፡ ማበደር፡ የሚሠጋ፡ ስለ፡ ሆነ፤የኢትዮጵያ፡ ሰዎች፡ ገንዘባቸውን፡ እየሸሸጉት፡ ሥራ፡ ፈቶ፡ ስለ፡ ተቀበረ፡ ዛሬ፡ ባገራችን፡ ብር፡ ውድ፡ ነው። ስለዚህም፡ ብር፡ የሚበደር፡ የኢትዮጵያ፡ ሰው፡ ወለድ፡ ይበዛበታል። ጭንቅ፡ ካሳገኘው፡ በቀር፡ ሠርቼ፡ አትርፋለሁ፡ ሲል፡ አይበደርም። የኢትዮጵያም፡ ሰው፡ የሚበደረው፡ ሲጨነቅ፡ ብቻ፡ ስለ፡ ሆነ፡ ብዙ፡ የታመነ፡ ተበዳሪ፡ የለምና፡ ገንዘባቸውን፡ ሊያበድሩ፡ የሚፈልጉ፡ ሰዎች፡ ቢኖሩ፡ የሚያገኙት፡ ጥቅም፡ ጥቂት፡ ነው። ገንዘብ፡ ያለው፡ ሰው፡ መቼም፡ የታመነ፡ ዋስ፡ ለሌለው፡ ሰው፡ አያበድርም። ገንዘብ፡ የሌለው፡ ሰው፡ ደግሞ፡ በቶሎ፡ ዋስ፡ አያገኝም። የኢትዮጵያም፡ ሕዝብ፡ በሥራ፡ ስላልሠለጠነ ፥ አበዳሪዎችም፡ የሚፈልጉት፡ ወለድ፡ ብዙ፡ ስለ፡ ሆነ፤ ድንገተኛ፡ ችግር፡ ካላገኘው፡ በቀር፡ ሠርቼ፡ አተርፍበታለሁ፡ ሲል፡ የሚበደር፡ ሰው፡ በኢትዮጵያ፡ የለም። ይልቍንም፡ ዛሬ፡ በኢትዮጵያ፡

ውስጥ፡ ያለ፡ ብር፡ የሚበልጠው፡ ሥራ፡ ፈቶ፡ በመሬት፡ ውስጥ፡ ተቀብሯል። እንዲሠራ፡ ወደ፡ ገበያ፡ የሚወጣው፡ ብር፡ ግን፡ ጥቂት፡ ስለ፡ ሆነ፡ የሚገኝበትም፡ ጥቅም፡ አነሰ።

ከዚህም፡ ምክንያት፡ የተነሣ፡ በኢትዮጵያ፡ የቆመው፡ ባንክ፡ ኦፍ፡ አቢሲኒያ፡ ከቆመ፡ ዠምሮ፡ እስከ፡ ዛሬ፡ ድረስ፡ ያገኘው፡ ትርፍ፡ ጥቂት፡ ነው። ለወደ፡ ፊት፡ ትልቅ፡ ጥቅም፡ ማግኘቱን፡ ያጠራጥራል። ባንክ፡ የሚጠቀም፡ የታመነ፡ ተበዳሪ፡ ሲበዛለት፡ ነው። የታመነም፡ ተበዳሪ፡ የሚበዛ፡ ሕገቡ፡ ሥራ፡ ሲሠስጥን፡ ነው። ሕዝብም፡ በሥራ፡ የሚሠለጥን ፥ ባገሩ፡ ያለው፡ ብርና፡ ወርቅ፡ ሥራ፡ ያልፈታ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ነው። ባገርም፡ ያለው፡ ብር፡ ሥራ፡ የማይፈታ፡ መላው፡ ሕዝብ፡ በሥርዐት፡ ፊት፡ እኩል፡ ሆኖ፡ እያንዳንዱ፡ ሰው፡ ዐቅም፡ አግኝቶ፡ ልቡ፡ የመረጠውን፡ ሥራ፡ ሲሠራ፡ የሕዝቡ፡ ሀብት፡ ያድጋል። የሕዝበም፡ ሀብት፡ ካደገ፡ ዘንድ፡ ባንክ፡ ይጠቀማል። ስለዚህም፡ የኢትዮጵያ፡ ባንክ፡ የሚፈልገው፡ የገንዘብ፡ ጥቅም፡ ብቻ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ከሁሉ፡ በፊት፡ የባንኩን፡ ሥራ፡ ሞኖፖልነት፡ ለቆ፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ በሥራ፡ እንዲሠለጥን፡ እንደ፡ ተቻለው፡ መጠን፡ መርዳት፡ አለበት። ይህን፡ ካላደረገ፡ ግን፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ድኽነት፡ ላይለየው፡ ነውና፤ባንኩም፡ ለወደ፡ ፊት፡ የሚያገኘው ትርፍ፡ አይበዛም። ባንክ፡ ኦፍ፡ አቢሲኒያ፡ ከቆመ፡ ወዲህ፡ ይኸው፡ ፲፡ ዓመት፡ ሊሆን፡ ተቃርቧል። የባንኩ፡ ማኅበረተኞች፡ ግን፡ እስከ፡ ዛሬ፡ ድረስ፡ ለባንኩ፡ ሥራ፡ ካገቡት፡ ገንዘብ፡ ኣንድም፡ ወለድ፡ አልተቀበሉም። የማኅበሩም፡ አማካሪዎች፡ ባመት፡ ባመት፡ ለመቀበል፡ በማኅበሩ፡ ደንብ፡ የተፈቀደላቸውን፡ ደመወዝ፡ እስከ፡ ዛሬ፡ ድረስ፡ አልተቀበሉም። ነገሩም፡ እንዲህ፡ መሆኑ፡ አያስገርምም። ሕዝቡ፡ በሥራ፡ ባልሠለጠነ፡ አገር፡ ባንክም፡ ቢቆም፡ ትርፍ፡ ኣያገኝም። የባንኩም፡ ሥራ፡ ፈጸሞ፡ ሞኖፖል፡ በሆነበት፡ አገር፡ ሕዝበ፡ በሥራ፡ አይሠለጥንም።

የኢትዮጵያን፡ ነገር፡ የመሰለ፡ ሀብታም፡ መሬት፡ የትም፡ ብንሄድ፡ ብዙ፡ አናገኝም። ያገሩ፡ ሕዝብ፡ ሠልጥኖ፡ እንደሚገባ፡ ቢሠራ፡ እንኳን፡ አንድ፡ ባንክ፡ ሺሕ፡ ባንኮችም፡ ቢሆኑ፡ ብዙ፡ ትርፍ፡ ያገኙበት፡ ነበር። ሕዝቡ፡ በሥራ፡ ካልሠለጠነ፡ ግን፡ እንኳን፡ ብዙ፡ ትርፍ፡ እንዲያገባ፡ ተብሎ፡ የቆመው፡ ባንክና፡ ትንሽ፡ ትርፍ፡ ይበቃኛል፡ የሚለው፡ አንድ፡ አጣሪም፡ ሐሳቡ፡ አይሳካለትም።

# ፲፫ኛ፡ ምዕራፍ።

ዕውቀት፡ የሌለው፡ ሰው፡ የዝሆንን፡ ቍመትና፡ መብረቅ፡ ሲያይ፡ የትልቅም፡ ነጐድጓድ፡ ጩኸት፡ ሲሰማ፡ የፈጣሪውን፡ ሥራ፡ ያደንቀዋል። ኣስተዋይ፡ የሆነ፡ ሃይማኖተኛው፡ ግን፡ የንብንና፡ የጕንዳንን፡ ትጋት፡ የሥራቸውንም፡ ትክክልነት፡ የሥርዐታቸውን፡ ማማር፡ አይቶ፡ በዚህ፡ ዓለም፡ ፍጥረት፡ ይገረማል። ከመብረቅና፡ ከነጐድጓድ፡ ኀይልም፡ ይልቅ፡ የንብና፡ የጕንዳን፡ ተኣምር፡ ለፈጣሪው፡ የበለጠ፡ ምስጋና፡ ሁኖ፡ ይታየዋል።

እንሆ፡ ሰሎሞንም፡ በመጽሐፈ፡ ምሳሌው፡ ሁለት፡ ጊዜ፡ ያደንቃቸዋል፡ ምሳሌ፡ (ምዕራፍ፡ ፮፡ ቁ፡ ፮። ም፡ ፴፡ ቍ፳፭)። እንዲሁም፡ ዕውቀት፡ የሌለው፡ ሹም፡ የመንግሥቱ፡ ሀብት፡ ከሐርና፡ ከሻምፓኝ፡ የሚነሣው፡ ግብር፡ ሲበዛ፡ ቢያይ፡ ብዙ፡ ሀብት፡ የሚሰበሰብ፡ ይመስለዋል። አስተዋይ። የሆነ፡ ሰው፡ ግን፡ መንግሥቱን፡ ለመጥቀም፡ ዐይኑን፡ በሐርና፡ በሻምፓኝ፡ ላይ፡ አይጥልም፡ ፡ ሕዝብ፡ ሁሉ፡ የሚገዛውን፡ ዕቃ፡ አይቶ፡ በዚያው፡ ዕቃ፡ ላይ፡ ትንሽ፡ ግብር፡ ይጨምራል። በዚሁም፡ ለመንግሥት፡ ትልቅ፡ ጥቅም፡ ይገኝበታል።

አሁን፡ ለምሳሌ፡ የኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡ በያመቱ፡ ከሐርና፡ ከስጋጃ፡ የሚያገኘው፡ ቀረጥ፡ ጥቂት፡ ነው። ካቡጀዲድና፡ ከብርድ፡ ልብስ፡ የሚገባለት፡ ቀረጥ፡ ግን፡ ብዙ፡ ነው። መንግሥታት፡ ሁሉ፡ ጥቅማቸውን፡ የሚፈልጉ፡ ውድ፡ ከሆነ፡ ነገር፡ አይደለም። ሕዝብ፡ ሁሉ፡ ከሚፈልገው፡ ከትንንሹ፡ ዕቃ፡ ሁሉ፡ እንጂ፤ስለዚህም፡ ሐርንና፡ የኤሌክትሪክን፡ ማብሪያ፡ ሰው፡ ሁሉ፡ እንደ፡ ፈቀደው፡ ሲሸጥ፡ ሲለውጥ፡ ጨውና፡ ክብሪት፤ትንባኾም፡ በብዙ፡ መንግሥታት፡ አገር፡ ሞኖፖል፡ ሆነው፡ እናያለን። እነዚህም፡ ዕቃዎች፡ ከሌላው፡ ዕቃ፡ ሁሉ፡ ተመርጠው፡ ሞኖፖል፡ የሚሆኑበት፡ ከሚገዟቸው፡ ሰዎች፡ ብዛት፡ የተነሣ፡ ለመንግሥት፡ የሚገኝባቸው፡ ጥቅም፡ ተጠራቅሞ፡ ብዙ፡ ስለ፡ ሆነ፡ ነው። ከብርና፡ ከወርቅ፡ አብልጦ፡ የሚፈለግ፡ ግን፡ በማናቸውም፡ አገር፡ አይገኝም። እያንዳንዱ፡ ሰው፡ ለኑሮው፡ የሚያስፈልገውን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ በተሙን፡ በሩብ፡ ባላድ፡ በብር፡ ገዝቶ፡ ነው። ስለዚህም፡ ብዙ፡ ነገሥታት፡

መጥፎ፡ ብር፡ እያተሙ፡ እያወጡ፡ ባገራቸውም፡ ከርሱ፡ በቀር፡ በሌላ፡ ብር፡ ሕዝባቸው፡ እንዳይገበያይ፡ እያወጁ፤ደኅና፡ ብር፡ የያዘ፡ ሰው፡ ሁሉ፡ ብሩ፡ በገበያ፡ እንዳይሄድለት፡ እያየ፡ እንዲሸጥላቸው፡ ሲያደርጉ፡ እንደ፡ ነበሩ፡ የዓለም፡ ታሪክ፡ ይመሰክርልናል። ውቡ፡ ፊልጶስ፡ የሚባል፡ አንድ፡ የፈረንሳዊ፡ ንጉሥማ፡ ከነከታቴው፡ ከነገሥ፡ ዠምሮ፡ እስኪሞት፡ ድረስ፡ ሕዝቡ፡ የሚገበያይበትን፡ የብር፡ ዐይነት፡ የለወጠ፡ ከሙቶ፡ ጊዜ፡ ይበልጣል፡ ይላሉ።

የብር፡ ዐይነትም፡ ከመለዋወጡ፡ የተነሣ፡ ሕዝቡ፡ የሚያገኘው፡ ጕዳት፡ ምን፡ እንደ፡ ሆነ፡ እንዲረዳ፡ አንባቢው፡ ቀጥሎ፡ የተጻፈውን፡ ቃል፡ አስተውሎ፡ ይመልከት። ዛሬ፡ በኢትዮጵያ፡ ያለው፡ ብር፡ የነሳውና፡ ያፄ፡ ምኒልክ፡ ብር፡ ነው።

እንሆ፡ የነምሳውም፡ ብር፡ ክብደቱ፡ ፳፰፡ ግራም፡ ከ፮፻፷፰፡ ዐሥር፡ ሺሕኛ፡ ግራም፡ ነው። በውስጡ፡ ያለው፡ ንጹሕ፡ ብር፡ ግን፡ ፳፫፡ ግራም፡ ከ፫፻፹፱፡ ሺሕኛ፡ ግራም፡ ነው። ስለዚህም፡ በነምሳው፡ ብር፡ ውስጥ፡ ያለው፡ ብር፡ ያልሆነ፡ ነገር፡ ፬፡ ግራም፡ ፮፡ ሺሕ፡ ፯፻፸፰። ዐሥር፡ ሺሕኛ፡ ግራም፡ ነው። ያፄ፡ ምኒልክም፡ ብር፡ እንደዚሁ፡ ብር፡ ትክክል፡ ነው፡ ይባላል። ሁለቱም፡ የብር፡ ዐይነት፡ በገበያ፡ አይበላለጡም።

እንግዲህ፡ የኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡ ለወደ፡ ፊት፡ እነዚህን፡ ሁለቶቹን፡ የብር፡ ዐይነት፡ ሕዝቡ፡ እንዳይገበያይባቸው፡ ከልክሎ፡ በውስጡ፡ ፳፬፡ ግራም፡ ፭፻፬፡ ዐሥር፡ ሺሕኛ፡ ግራም፡ ጥሩ፡ ብር፡ ያለበት፡ ሌላ፡ አዲስ፡ የብር፡ ዐይነት፡ ቢያወጣ፤ብር፡ የያዝክ፡ ሰው፡ ሁሉ፡ ካሥር፡ ብር፡ አንድ፡ ብር፡ ፈሰስ፡ ጥዬብኻለሁ፡ እንደ፡ ማለት፡ ያኽል፡ ነው። ስለ፡ ምን፡ ቢሎ፡ ቀጥሎ፡ የተጻፈው፡ ቃል፡ ያስረዳል።

እንደዚህ፡ ያለ፡ ዐዋጅ፡ ተነግሮ፡ የዱሮው፡ ብር፡ በገበያ፡ መሄዱ፡ ሲቀር፡ የዱሮውን፡ ብር፡ የያዘ፡ ሰው፡ ሁሉ፡ መቼም፡ ብሩን፡ የሰበሰበው፡ ዕቃ፡ ሊገዛበት፡ ነው፡ እንጂ፡ ሊቈረጥመው፡ አይደለምና፤የያዘውን፡ ብር፡ በገበያ፡ ሰው፡ የማይቀበልለት፡ ሲሆን፡ ሳዲሱ፡ ብር፡ ሊለውጠው፡ ነው። በዚሁም፡ ምክንያት፡ የዱሮው፡ ብር፡ ሁሉ፡ ወደ፡ መንግሥት፡ ጓዳ፡ ሊገባ፡ ነው። ይህም፡ ሲሆንለት፡ የኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡ ዐሥር፡ ብር፡ ፳፬፡ ግራም፡ ፭፻፬፡ ዐሥር፡ ሺሕኛ፡ ግራም፡ የሚከብድ፡ ብር፡ ሰጥቶ። ዐሥር፡

ብር፡ ፳፫፡ ግራም፡ ፫የ፳፱፡ ሺሕኛ፡ ግራም፡ የሚከብድ፡ ብር፡ ሲገባለት፤ ባሥሩ፡ ብር፡ አንድ፡ ብር፡ ትርፍ፡ ሊያተርፍበት፡ ነው።

ከውጭ፡ አገር፡ የሚመጣው፡ ዕቃ፡ ሁሉ፡ ግን፡ የሚገዛው፡ በኤሮፓ፡ ነገሥታት፡ ብር፡ ሒሳብ፡ ነውና፤የኤሮፓ፡ ነጋዶች፡ ባዲሱ፡ ብር፡ ውስጥ፡ ያለው፡ ጥሬ፡ ብር፡ በዱሮው፡ ብር፡ ውስጥ፡ የነበረውን፡ እንደማያኽል፡ ይገምቱታልና፤የዕቃቸውን፡ ዋጋ፡ ከፍ፡ ሊያደርጉ፡ ነው። የዱሮውን፡ ዐሥር፡ ብር፡ ሲቀበሉበት፡ የነበረውን፡ ዕቃ፡ ሁሉ፡ ላዲሱ፡ ብር፡ ሲሸጡት፡ ዐሥራ፡ አንድ፡ ብር፡ ሊፈልጉ፡ ነው። እኸልና፡ ሌላውም፡ ባገራችን፡ የሚገኘው፡ ነገር፡ ሁሉ፡ የሚሸጠውም፡ ባላገር፡ ብር፡ የሚፈልገው፡ መቼም፡ አቡጀዲድ፡ ወይም፡ ሌላ፡ ከውጭ፡ አገር፡ ተሠርቶ፡ የመጣውን፡ ዕቃ፡ እንዲገዛበት፡ ነውና፤የሚፈልገው፡ ዕቃ፡ መወደዱን፡ ሲያይ፡ ርሱም፡ ከመሬቱ፡ ያገኘውን፡ እኸልና፡ ሌላውንም፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ዋጋውን፡ ሥር፡ አንድ፡ ከፍ፡ ሊያደርግ፡ ነው። ስለዚህ፡ ብር፡ የያዘ፡ ሰው፡ ዱሮ፡ ዐሥር፡ ብር፡ ሲሰጥበት፡ የነበረውን፡ ዕቃ፡ ለመግዛት፡ ሲፈልግ፡ ዐሥራ፡ አንድ፡ ለመስጠት፡ የግድ፡ ሊሆንበት፡ ነው። ከባሕር፡ ማዶ፡ ነጋዴ፡ የሚያመጣው፡ ዕቃ፡ ግን፡ ስለ፡ ተወደደ፡ ትርፍ፡ ብር፡ አያገኝበትም። አዲሱ፡ ብር፡ እንደ፡ ዱሮ፡ ብር፡ ጥሩ፡ ሳይሆን፡ ቀርቶ፡ ለሚያመጣው፡ ዕቃ፡ ስለ፡ ተወደደበት፡ ነው፡ እንጂ፤ከባሕር፡ ማዶ፡ የመጣው፡ ዕቃ፡ ሁሉ፡ ተወዶበት፡ ከዱሮ፡ የበለጠ፡ ዋጋ፡ መስጠት፡ የግድ፡ ስለ፡ ሆነበት፡ አይደለም። ባላገሩም፡ ቢሆን፡ እኸሉ፡ ስለ፡ ተወደደለት፡ አንዳች፡ ትርፍ፡ አያገኝም። ትርፉን፡ ያገኘ፡ መንግሥት፡ ብቻ፡ ነው። ደግሞም፡ ዋጋ፡ ስለ፡ ተጨመረባቸው፡ ብሩ፡ መጥፎ፡ በመሆኑ፡ እንደሆን፡ ዕቃ፡ የያዙ፡ ነጋዴና፡ ባላገር፡ አይጐዱም። የሚጐዳ፡ ዕቃ፡ ስለ፡ ተወደደ፡ ብር፡ የያዘ፡ ሰው፡ ብቻ፡ ነው።

በኢትዮጵያ፡ ያለው፡ ብር፡ ሕዝቡ፡ የሚገበያይበት፡ ያ፡ ሚሊዮን፡ ይሆናል፡ ተብሎ፡ ስለ፡ ተገመተ ፥ የኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡ ድንገት፡ ከላይ፡ ባሳየነው፡ ሒሳብ፡ አዲስ፡ ብር፡ አውጥቶ፡ በዱሮው፡ ብር፡ ሰው፡ እንዳይገበያይ፡ ቢከለክል፡ ባንድ፡ ጊዜ፡ ሁለት፡ ሚሊዮን፡ የሚሆን፡ ብር፡ ያገኝ፡ ነበር። ማለት፡ እንደ፡ ፈረንሳዊው፡ ንጉሥ፡ ውድ፡ ፊልጶስ፡ እየደጋገመ፡ በያመቱ፡ ቢለዋውጥ፡ የኢትዮጵያ፡ መንግሥትም፡ ቢሆን ማድረጉ፡ ይቻለው፡ ነበር። ሕዝቡ፡ ግን፡ በጣም፡ ይጐዳበታል። ነገር፡ ግን፡

እንደዚህ፡ ያለውን፡ ሥራ፡ ፈጽሞ፡ የቅጥፈት፡ ሥራ፡ ነውና፤ከላይ፡ የተጠራው፡ የፈረንሳዊ፡ ንጉሥም፡ ቢሆን፡ ሥራው፡ መሰደቢያ፡ ሆኖ፡ በዓለም፡ ታሪክ፡ ላይ፡ ተጻፈበት፡ እንጂ፤አልተመሰገነበትም። ስለዚህ፡ የኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡ እንደዚህ፡ ያለውን፡ ሥራ፡ እንኳን፡ መሥራት፡ ማሰብም፡ አይገባውም። ገንዘብ፡ ካስፈለገው፡ በእንደዚህ፡ ያለ፡ የቅጥፈት፡ መንገድ፡ ወይም፡ ሥራ፡ አውጥቶ፡ ብር፡ የያዘት፡ ዜጎችን፡ ሁሉ፡ ከመጐዳት፡ በግልጽ፡ እገሌ፡ ይህንን፡ ያኽል፡ ገንዘብ፡ አግባ፡ ወይም፡ አለው፡ ተብሎ፡ በያንዳንዱ፡ ዜጋው፡ ላይ፡ እንደ፡ ሀብቱ፡ መጠን፡ ፈሰስ፡ ቢጥልበት፡ ይሻላል። እያንዳንዱ፡ ዜጋ፡ የሚከፍለው፡ ግብር፡ እንደ፡ ገንዘቡ፡ ብዛት፡ እንደ፡ ሀብቱ፡ መጠን፡ ቢሆን፡ ፍርድ፡ ጐደለብኝ፡ ብሎ፡ የሚያዝን፡ ሰው፡ ከሕገቡ፡ ውስጥ፡ ባልተገኘም፡ ነበር። አሁንም፡ ለምሳሌ፡ ዛሬ፡ ገብረ፡ ማርያም፡ አቡጀዲድ፡ እገዛለሁ፡ ሲል፡ አንድ፡ ጋሻ፡ መሬት፡ ለወልደ፡ ማርያም፡ ሸጠለት። በመንግሥቱ፡ አዲስ፡ ብር፡ የወጣ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ገብረ፡ ማርያም፡ ስለ፡ መሬቱ፡ ዋጋ፡ የተቀበለው፡ ብር፡ በገበያ፡ የማይሄድለት፡ ሆኖ፡ ላዲሱ፡ ብር፡ መለወጥ፡ የግድ፡ ይሆንበታል። ገብረ፡ ማርያም፡ ሊገዛው፡ የፈለገው፡ አቡጀዲድ፡ ግን፡ አዲሱ፡ ብር፡ መጥፎ፡ ስለ፡ ሆነ፡ ዋጋው፡ ሊወደድበት፡ ነው። ነገሩ፡ እንደዚህ፡ ሲሆን፡ ቀላዱን፡ የገዛ፡ ወልደ፡ ማርያም፡ ሳይነካ፡ ቀላዱን፡ የሸጠ፡ ገብረ፡ ማርያም፡ ይጐዳል። ስለዚህ፡ ባንድ፡ መንግሥት፡ ውስጥ፡ እንደዚህ፡ ሆኖ፡ አንዱ፡ ዚጋ፡ ሲጐዳ፡ ሌላው፡ ሳይነካ፡ የቀረ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ፍትሕ፡ ጐደለ፡ ይባላል።

ጸሓፊው፡ የግድ፡ ባይሆንበት፡ ይህ፡ ከላይ፡ የተጻፈው፡ የቅጥፈት፡ ሥራ፡ በዚህ፡ መጻፉ፡ ኣይገባም፡ ነበር። ነገር፡ ግን፡ የሕዝብ፡ አስተዳደር፡ የሚባለውን። መጽሐፍ፡ ሲጻፍ፡ እንደዚህ፡ ያለ፡ ማስረጃ፡ በውስጠ፡ ሳያሳይ፡ ቢቀር፡ መጽሐፉ፡ ጐደሎ፡ ይሆንበታል። ደግሞም፡ ጸሓፊው፡ እንደ፡ ሰማው፡ ወሬ፡ አንድ፡ የውጭ፡ ሰው፡ ዛሬ፡ በኢትዮጵያ፡ ያለውን፡ ብር፡ እየከፈሉ፡ ሁለት፡ ብር፡ ቢያደርጉት፡ ይቻላል፡ ብሎ፡ ለኢትዮጵያ፡ ሰዎች፡ መክሯል፡ ኣሉ። እንደዚህ፡ ያለውን፡ ምክር፡ ሰምቶ፡ ፊት፡ ባሳየነው፡ ሒሳብ፡ እንዳይሆንበት፡ መጠንቀቅ፡ ነው። የኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡ ያንድ፡ ቀጣፊ፡ ምክር፡ ሰምቶ፡ ከላይ፡ የተጻፈውን፡ ስሕተት፡ ቢያደርግ፡ በቀሩት፡ ነገሥታት፡ ፊት፡ ውርደት፡ ይሆንበታልና፤ስለዚህ፡ ከንደዚህ፡ ያለው፡ ምክር፡ ይጠንቀቅበት። በዛሬው፡ አላድ፡ ሩብ፡ ተሙን፡

ሲሸረፍ፡ የሚያገኘው፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብና፡ መንግሥት፡ ጒዳት፡ ይበቀዋል። የዛሬው፡ አላድ፡ ሩብ፡ ተመን፡ ሲታተም፡ ላንድ፡ ብር፡ ሁለት፡ አላድ፡ አራት፡ ሩብ ፥ ፲፯፡ ተሙን፡ እየታሰበ፡ ነበር። ይህ፡ ስል፡ ሆን፡ እነዚህ፡ መሣሪያዎች፡ ላገራችን፡ ገበያ፡ እንደሚበቍ፡ ሆነው፡ አልተገኙም። ደግሞም፡ ብሩ፡ ለሁለት፡ አላድ፡ ላራት፡ ሩብ ፥ ፲፯፡ ተሙን፡ እንዲሸረፍ፡ የኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡ ምንም፡ ለሥርዐቱ፡ ቢያውጅ፡ ዐዋጁ፡ አረጋም፤ እንደ፡ ሥርዐቱ፡ ፩፡ ብር፡ ፲፯፡ ተሙን፡ ብቻ፡ ሊሸረፍ፡ አይገባውም።

ነገር፡ ግን፡ ፳፡ ተመን፡ ያንድ፡ ብር፡ ኻያኛ፡ ነውና፤የኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡ ፩፡ ብር፡ ፲፯፡ ተሙን፡ ይሸረፍ፡ ብሎ፡ ሲያውጅ፡ ብርኽን፡ ለትመን፡ የምትለውጥ፡ ሰው፡ ሁሉ፡ በያንዳንዱ፡ ብር፡ አራት፡ ተሙን፡ ገብርልኝ፡ እንደ፡ ማለት፡ ነው። ግን፡ ይመስገነው፤መንግሥታችን፡ ይህነኑ፡ ዐዋጅ፡ አላጠነከረምና፤ሕዝቡም፡ የተሙንን፡ ርካሽነት፡ ዱሮ፡ ተረድቶት፡ ብሩን፡ ባሽ፲፯፡ ተሙን፡ እስከ፡ ፲፰፡ ድረስ፡ ሲለዋወጥ፡ ይኖራል። ተሙኑም፡ ያገራችን፡ ገበያ፡ እንደሚፈልገው፡ መጠን፡ በብዙ፡ ታትሞ፡ ቢሆን፡ ያለጥርጥር፡ አንድ፡ ብር፡ ለኻያ፡ ተሙን፡ ይሸረፍ፡ ነበር። ነገር፡ ግን፡ እንደ፡ አላዱና፡ እንደ፡ ሩቡ፡ የታተመው፡ ተሙን፡ ጥቂት፡ ነውና፤ ያውም፡ የሚበዛው፡ አላድ፡ ተሙን፡ ሩብ፡ ታትሞ፡ የሚመጣልን፡ ከፈረንሳይ፡ አገር፡ ነውና፤ይህም፡ ሳይቀር፡ ቀጥሎ፡ የተጻፈውን፡ እንደሚያሳየን፡ ላገራችን፡ ትልቅ፡ ጒዳት፡ ነው። የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ የትንንሾቹ፡ የለውጥ፡ መሣሪያዎችን፡ ጣዕም፡ ለምዶ፡ ወዷቸዋልና፤ ሕዝቡም፡ በጣም፡ ድኻ፡ ስለ፡ ሆነ፡ ባገሩ፡ ውስጥ፡ ከትልቍ፡ የለውጥ፡ መሣሪያ፡ ይልቅ፡ ትንንሹ፡ የለውጥ፡ መሣሪያ፡ ይፈለጋል። ዛሬ፡ በድሬ፡ ዳዋና፡ በሐረር፡ ባዲስ፡ አበባም፡ ገበያዎች፡ አስተውለን፡ ብንመለከት፡ ሕዝቡ፡ ርስ፡ በርሱ፡ ሲገበያይ፡ ወይም፡ ሲገዛዛ፡ የሚበልጠው፡ ግርው፡ በተሙን፡ ነው። ከዚያ፡ በኋላ፡ ቀጥሎ፡ በሩብ፡ ባላድ፡ ነው፤ከፍ፡ ያለውም፡ በብር። የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ያገሩ፡ ሀብት፡ ጥቂት፡ ስለ፡ ሆነ፡ ሙሉ፡ ብር፡ በቶሎ፡ ለማግኘት፡ አይሆንለትም። ለኑሮው፡ የሚያስፈልገውን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ የሚገዛበት፡ ገበያ፡ ሩቅ፡ የሆነበት፡ ሕዝብ፡ ጒልበቱ፡ ሁል፡ ጊዜ፡ ርካሽ፡ ነው፤እንደዚህ፡ ባለ፡ አገርም፡ ሁል፡ ጊዜ፡ ብር፡ ይወደዳል።

አሁን፡ ለምሳሌ ፥ ኣንድ፡ ያዲስ፡ አበባ፡ ጒራጌ፡ ሠርቶ፡ አንድ፡ ሙሉ፡ ብር፡ እስቲያገኝ፡ ድረስ፡ ያራት፡ ቀን፡ ሥራ፡ ይውልበታል። አላድም፡ እስኪያገኝ፡ ድረስ፡ ሁለት፡ ቀን ፥ሩብም፡ እስኪያገኝ፡ ድረስ፡ አንድ፡ ቀን፡ ተሙን፡ እስኪያገኝም፡ ድረስ፡ የሚሠራው፡ ሁለት፡ ሰዓት፡ ያኽል፡ ነው። እንግዴህ፡ ከሙሉ፡ ብር፡ በቀር፡ ሌላ፡ የለውጥ፡ መሣሪያ፡ ባይኖር፡ ሙሉውን፡ ብር፡ እስኪያገኝ፡ ድረስ፡ ጒራጌ፡ አራት፡ ቀን፡ ሙሉ፡ በራብ፡ ይቸገር፡ ነበር። ሙሉውን፡ ብር፡ ካገኘ፡ በኋላ፡ ሊከፍለው፡ አይችልም፡ ነበርና፤በሙሉው፡ ብር፡ ሽንብራ፡ እንዲገዛበት፡ የግድ፡ ይሆንበታል። በሙሉው፡ የሚገዛው፡ ሽንብራም፡ በዝቶበት፡ በልቶም፡ በቶሎ፡ የማይጨርሰው፡ ነውና፤የሚጠብቅለት፡ እያጣ፡ ሽንብራውን፡ ታቅፎ፡ ሥራውን፡ ትቶ፡ ወይም፡ አስታጒሎ፡ ይቀራል። ወይም፡ ደግሞ፡ ሥራ፡ እንዳይታጐል፡ ከፈለገም፡ ሽንብራውን፡ የምትጠብቅ፡ ሚስት፡ ማግባት፡ የግድ፡ ይሆንበታል። ከዚሁ፡ ምክንያት፡ የተነሣ፡ በላተኞቹ፡ በዝተው፡ ያ፡ በብር፡ የተሸመተ፡ ሽንብራ፡ በጥቂቱ፡ ቀን፡ ያልቃል። ጒራጌም፡ ልፋቱና፡ ሥራው፡ ለሁለቱ፡ ሆድ፡ ብቻ፡ ሆኖ፡ ይቀር፡ ነበር።

ጉራጌም፡ ትርፍ፡ አልባ፡ ሆኖ፡ ይቅር፡ ነበር። ተሙን፡ ሳለ፡ ግን፡ ጒራጌም፡ ከላይ፡ እንዳየነው፡ የመሳሰለ፡ ችግር፡ አያገኘውም። ሽንብራውን፡ የምትጠብቅለት፡ ሚስትም፡ ማግባት፡ አያስፈልገውም። ለዕለት፡ ምግቡ፡ የሚያስፈልገውን፡ ያኽል፡ ሽንብራ፡ በእኩለ፡ ቀን፡ ከሥራው፡ ሲያርፍ፡ በተሙን፡ ሸምቶ፡ ለምሳው፡ የሚበቃውን፡ ያኽል፡ በልቶ፡ የተረፈውን፡ በጨርቍ፡ ቋጥሮ፡ በወገቡ፡ ታጥቆት፡ ወደ፡ ሥራው፡ ይመለሳል። ከሥራው፡ የማይተጓጐል፡ ስለ፡ ሆነ፡ በዕለት፡ በዕለቱ፡ እየሠራ፡ በጊዜ፡ ብዛት፡ ጥቂት፡ ብር፡ አጠራቅሞ፡ ወዳገሩ፡ ይመለሳል። በሌላውም፡ ነገር፡ ቢሆን፡ እንደዚሁ፡ ነው። ሕዝቡ፡ ድኻ፡ በሆነበት፡ አገር፡ ሁሉ፡ ትልቍን፡ የለውጥ፡ መሣሪያ፡ ከሚፈልገው፡ ይልቅ፡ ትንሹን፡ የለውጥ፡ መሣሪያ፡ የሚፈልገው፡ ይበዛል። ያንድ፡ ድኻ፡ ወታደር፡ ሚስት፡ ወደ፡ ገበያ፡ ብትሄድ፡ ብሩን፡ በተሙን፡ ሽርፋ፡ በተመን፡ ሽንኩርት፡ በተሙን፡ ጨው፡ በተሙን፡ ቀንዶ፡ በርበሬ፡ በተሙን፡ ጋዝ፡ በቀለሕ፡ ክብሪት፡ ገዝታ፡ ለመመለስ፡ ትችላለች። አንድ፡ ብር፡ ሙሉ፡ ይዛ፡ ወደ፡ ገበያ፡ የምትሄድ፡ ምናልባት እኽል፡ ለመሸመት፡ ነው። በድኻ፡ ቤት፡ እኽል፡ የሚሸመተው፡ ግን፡ ቢበዛ፡ በወር፡ አንድ፡ ጊዜ፡ ነው። ማለት፡ ነገሩ፡ ሁሉ፡ አጥብቀን፡

ከመረመርነው፡ ባዲስ፡ አበባና፡ ባውራጃው፡ ሁሉ፡ በሐረርጌ፡ አውራጃም፡ ያሉት፡ ገበያዎች፡ ሁሉ፡ ከለውጥ፡ መሣሪያ፡ ሁሉ፡ እንደ፡ ተሙን፡ ዘወትር፡ የሚፈለግ፡ የለምይህም፡ ምክንያቱ፡ ከሕዝቡ፡ የሚበዛው፡ ድኻ፡ ስለ፡ ሆነ፡ ነው። ያንድ፡ ድኻ፡ ባሻገር፡ ሚስት፡ የሚሸጥ፡ ዕቃ፡ ይዛ፡ ወደ፡ ገበያ፡ ብትወጣ፡ የያዘችውም፡ ዕቃ፡ ምናልባት፡ የተሙን፡ ጐመን፡ ወይም፡ ሽንኩርት፡ ወይም፡ ዶሮ፡ ወይም፡ የተሙን፡ ዳቦ፡ ወይም፡ ቄስ፡ እንደዚሁ፡ የመሰለ፡ ትንንሽ፡ ነገር፡ ይሆናል። አንዲት፡ ላም፡ ብትኖራት፡ ያንድ፡ ብር፡ ቅቤ፡ እስቲጠራቀምላት፡ ድረስ፡ ብዙ፡ ቀን፡ የሚያስፈልጋት፡ ነውና፤ ለዕለት፡ የሚሆነን፡ ትንንሹን፡ ጉዳይዋን፡ ለተሙን፡ ትሸጣለች። ተመን፡ ወደሌለባቸው፡ የኢትዮጵያ፡ አውራጃዎች፡ በተመን፡ ፈንታ፡ በጨው፡ ወይም፡ የጨው፡ ገሚስ፡ ወይም፡ የጨው፡ ኵርማን፡ በጥይት፡ በቀለሕ፡ ከፍ፡ ያለውም፡ በሸማ፡ ከብሩ፡ ይልቅ፡ በእንደዚህ፡ ያሉት፡ ትንንሾች፡ የለውጥ፡ መሣሪያዎች፡ ሲገበያዩ፡ እናገኛቸዋለን። እውነትም፡ የዛሬውን፡ ብር፡ የሚያኽል፡ ትልቅ፡ የለውጥ፡ መሣሪያ፡ እንደ፡ ኢትዮጵያ፡ ላለ፡ አገር፡ አይመችም። አንባቢው፡ ይህነኑ፡ በጣም፡ እንዲረዳው፡ ባገራችንም፡ ቢሆን፡ የሀብታምንና፡ የድኻን፡ ኑሮ፡ ይመልከት። አንድ፡ ራስ፡ ወይም፡ ደጃዝማች፡ አንዳች፡ ነገር፡ መግዛት፡ ሲፈልግ፡ በብዙ፡ ብር፡ እንጂ፡ እንደ፡ ድኻው፡ ባላድ፡ በሩብ፡ በተሙን፡ አይገዛም። በሌሎች፡ ሕዝቦችም፡ ትዳር፡ እንደዚሁ፡ ነው። ሀብታም፡ የሆነ፡ ሕዝብ፡ የሚፈልገው፡ የለውጥ፡ መሣሪያ፡ ትልቅ፡ ነገር፡ ነው። ድኻ፡ የሆነው፡ ሕዝብ፡ አገር፡ ግን፡ ትንሹን፡ የለውጥ፡ መሣሪያ፡ ይፈልጋል። ከእንደዚህ፡ ያለው፡ ምክንያት፡ የተነሣ፡ ይኸው፡ ባገራችን፡ እንደምናየው፡ ሕዝቡ፡ ከሙሉ፡ ብር፡ ይልቅ፡ አላድ፡ ሩብ፡ ተሙን፡ ስላስፈለገው። በገበያም፡ በብዙ፡ ስለ፡ ተወደደና፡ ስላስፈለገ፡ የማይበቃም፡ ስለ፡ ሆነ፡ ብሩን፡ ሲሸርፍ፡ ከሚገባው፡ ዋጋ፡ በላይ፡ ይሰጥበታል። ትሙንና፡ ሩብ፡ አላድ፡ ስለ፡ ተወደዱ፡ ግን፡ ለኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ እጅግ፡ ትልቅ፡ ጉዳት፡ ነው። ስለ፡ ምን፡ ቢሉ፡ ቀጥሎ፡ የተጻፈውን፡ አስተውለን፡ ብናነበው፡ ያስረዳናል። ፊት፡ እንደ፡ ተናገርነው፡ ባገራችን፡ ያለው፡ አላድ፡ ሩብ፡ ተሙን፡ ወደ፡ ኣገራችን፡ የሚመጣው፡ በነጋዶች፡ በኩል፡ ከውጭ፡ አገር፡ ነውና። እንደዚሁ፡ እነዚህ፡ ነጋዶች፡ ይህነን፡ ትንንሽ፡ የለውጥ፡ መሣሪያ፡ ባገራችን፡ መወደዱን፡ አይተው፡ ለብር፡ ሲለውጡት፡ ከፍ፡ ያለ፡ ዋጋ፡ ይቀበሉበታል። አንድ፡ ነጋዴ፡ በሺ፡ ብር፡ ተሙን፡ ገዝቶ፡ ወዳገራችን፡

ቢያመጣውና፡ ፲፪ቱን፡ ተመን፡ ላ፩፡ ብር፡ ቢሸርፈው፡ ፬፡ ሺ፡ ተሙን፡ ያተርፍበታል። በብር፡ ቤትም፡ ፪ኛ፡ ብር፡ ያገኝበታል። ማለት፡ እንደ፡ ሥርዐቱና፡ እንደ፡ ሚዛኑ፡ ፩፡ ብር፡ ፳፡ ተሙን፡ መሸረፍ፡ ይገባው፡ ነበር። ይኸው፡ ነጋዴም፡ ተሙኑን፡ የገዛው፡ ባ፩፡ ብር፡ ፳፡ ተሙን፡ ሒሳብ፡ ነበርና፤ስለዚህ፡ ወዳገራችን፡ አምጥቶ፡ ፲፪ቱን፡ ተሙን፡ ላ፩፡ ብር፡ ሲሸርፈው፡ በያንዳንዱ፡ ብር፡ ፬፡ ተሙን፡ ያተርፍበታል። እያንዳንዱ፡ የኢትዮጵያ፡ ሰውም፡ ፬፡ ፬፡ ተመን፡ ይገብርለታል። የብሩ፡ ትርፍም፡ ወደ፡ ውጭ፡ አገር፡ ይመለሳል። ነጋዴው፡ ብሩን፡ በጥሬው፡ ወዳገሩ፡ ባይመልሰው፡ ቆዳና፡ ቡና፡ ወይም፡ ሌላ፡ ነገር፡ ባገራችን፡ የሚገኘውን፡ ዕቃ፡ ይገዛበታል፤ማለት፡ ከውጭ፡ አገር፡ ሌላ፡ ብር፡ ሳያመጣ፡ በሸረፋ፡ ባገኘው፡ ትርፍ፡ የኢትዮጵያን፡ ሕገብ፡ ድካም፡ ወይም፡ ጉልበት፡ ይገዛበታል። ይህነኑም፡ ነገር፡ አጥብቀን፡ ከተመለከትነው፡ ያገራችን፡ ሕዝብ፡ አላድና፡ ሩብ፡ ተሙን፡ ለሚያመጡለት፡ ሰዎች፡ እንደ፡ ሸርፉ፡ ከፍታና፡ ዝቅታ፡ ከመቶው፡ ብር፡ ፲ና፡ ፳፡ ብር፡ ይገብርላቸዋል። አላዱና፡ ሩቡ፡ ተሙኑ፡ ሁሉ፡ ባገራችን፡ የሚሠራ፡ ቢሆን፡ ግን፡ ይህ፡ ግብር፡ ለመንግሥታችን፡ በገባለት። መንግሥቱም፡ ለሠራተኞቹ፡ በደመወዝ፡ ምክንያት፡ ሲያካፍላቸው፡ ጥቅሙ፡ ና፡ ትርፉ፡ አንድ፡ ጊዜ፡ ወደ፡ መንግሥት፡ አንድ፡ ጊዜም፡ ወደ፡ ሕዝቡ፡ እየተመላለሰ፡ ብሩ፡ ካገራችን፡ ሳይወጣ፡ በሕዝቡ፡ እጅ፡ ይቀር፡ ነበር፤ጉዳትም፡ ባልሆነበትም፡ ነበር።

መንግሥትም፡ ሕዝቡ፡ የሚለዋወጥበትን፡ የለውጥ፡ መሣሪያ፡ ሁሉ፡ ምንም፡ ርሱ፡ ራሱ፡ ቢያትም፡ ፊት፡ እንዳሰብነው፡ ይህን፡ ያኽል፡ የሸረፋ፡ ግብር፡ ሊወስድ፡ አይገባውም። እንደዚህ፡ ያለውን፡ ብር፡ ሊከፍል፡ የሚገባው፡ ግን፡ የሚሸርፈው፡ ሰው፡ ብቻ፡ ነው። መንግሥትም፡ ግብሩን፡ በሕዝቡ፡ ላይ፡ ሲጥል፡ ፍርዱን፡ አሳጐደለም፡ የሚባለው፡ በያንዳንዱ፡ ገባሩ፡ እንደየሀብቱ፡ መጠን፡ ሲያስከፍለው፡ ነበር። መንግሥት፡ አንድ፡ ብር፡ ፲፪፡ ተሙን፡ ይሸረፍ፡ ብሎ፡ ማወጁ፡ ደግ፡ ሥራ፡ እንዳልሠራ፡ ይህነን፡ ፊት፡ ግልጽ፡ ሆኖ፡ የተጻፈውን፡ አንብቦ፡ ነገሩን፡ ከተረዳው፡ ወዲያ፡ ዐዋጁ፡ ባለመርጋቱ፡ ደስ፡ ሳይለው፡ አይቀርም። አእምሮ፡ ያላቸው፡ ነገሥታት፡ ገንዘብ፡ አትመው፡ ሲያወጡ፡ ከየሥራቸው፡ ዋጋና፡ ከሕዝቡ፡ ግብር፡ የሚወስዱት፡ ባንድነት፡ ታስቦ፡ ቢሆን፡ ያንሳል፡ እንጂ፤ከመቶ፡ ፳፡ በላይ፡ አይበልጥም። እንግዲህ፡ ይህ፡ ከላይ፡ ያነበብነውና፡ ያየነው፡ ብቻ፡

አይደለም። ማለት፡ ጒዳቱ፡ ብሩ፡ ባ፲፮፡ ተሙን፡ ይሸረፍ፡ ተብሎ፡ የታወጀ፡ ብቻ፡ አይደለም። ሌላ፡ ጒዳት፡ ደግሞ፡ አለበት፡ እንጂ፡ ማለት፡ ዛሬ፡ ያዋጁን፡ ቃል፡ የተከተሉት፡ የኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡ ግምጃ፡ ቤትና፡ የኢትዮጵያ፡ ባንክ፡ ብቻ፡ ናቸው። በገበያው፡ ግን፡ ተሙኑ፡ እንደ፡ ተፈለገ፡ መጠንና፡ እንደ፡ ጊዜው፡ መወደድ፡ ሁል፡ ጊዜ፡ ከፍና፡ ዝቅ፡ ይላል። እንግዲህ፡ አንዳንድ፡ ጊዜ፡ ጒዳቱ፡ ያገራችን፡ መንግሥት፡ ሠራተኛ፡ ደመወዙን፡ በብር፡ ፈንታ፡ ተሙን፡ ባ፲፮፡ ሸረፋ፡ ሒሳብ፡ ሲቀበል፡ አንዳንድ፡ ጊዜ፡ በገበያው፡ ሸረፋው፡ ፲፯ና፡ ፲፰፡ ሆኖ፡ ያገኘዋል። ሠራተኛው፡ እንደዚሁ፡ ሆኖ፡ ሲያገኘው፡ ደመወዙን፡ የሚቀበል፡ ከመንግሥት፡ ሲሆን፡ ከሌላው፡ ሰው፡ ሁሉ፡ በተለየ፡ ከደመወዙ፡ ከሙቶ፡ ፫ና፡ ከሙቶ፡ ፲፩፡ መገበሩ፡ ነው። ስለዚህ፡ ከዚህ፡ በላይ፡ የተጻፈውን፡ ነገርና፡ ምክንያት፡ ሁሉ፡ እንዳየነውና፡ እንዳስተዋልነው፡ የኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡ ሕዝቡ፡ በሺረፋ፡ እንዳይጐዳበት፡ በመላው፡ ሥልጣኑ፡ ሊጥርበት፡ ይገባዋል። እንዲሁም፡ ለመጣር፡ ፈቃዱ፡ ከሆነም፡ አስቀድሞ፡ ቀጥሎ፡ የተጻፈው፡ ሦስት፡ ነገር፡ ያስፈልገዋል።

መዠመሪያ፤ሕዝቡ፡ የሚገበያይበት፡ ትንንሽ፡ የለውጥ፡ መሣሪያ፡ ሁሉ፡ እያንዳንዱ፡ ሕዝቡ፡ የሚፈልገው፡ ስንት፡ እንደ፡ ሆነ፡ እየተመረመረ፡ እንደሚበቃ፡ ሆኖ፡ ቢታተም፡ መልካም፡ ነው። እያንዳንዱም፡ ትንሹ፡ የለውጥ፡ መሣሪያ፡ በብር፡ ስንት፡ እንዲሸረፍ፡ መንግሥት፡ ባለቤቱ፡ ደንብ፡ ለይቶ፡ ሸረፋው፡ ከፍና፡ ዝቅ፡ እንዳይል፡ ቢጠበቅ፡ መልካም፡ ነው።

ሁለተኛ፤ከመንግሥት፡ በቀር፡ ማንም፡ ሰው፡ አሳድና፡ ሩብ፡ ተሙን፡ በሐሳበ፡ እያሳተመ፡ ከውጭ፡ አገር፡ እንዳያስመጣ፡ ቢከለከል፡ መልካም፡ ነው። የኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡ ያቆመውን፡ የብር፡ ማተሚያ፡ ወይም፡ ፋብሪካ፡ በያመቱ፡ ላገሩ፡ ሕዝብ፡ የሚበቃ፡ ትንንሽ፡ የለውጥ፡ መሣሪያ፡ ለማተም፡ የማይቻለው፡ እንደሆን፡ ፋብሪካውን፡ ያስፋው። ያለዚያ፡ ግን፡ ላገሩ፡ ሕዝብ፡ የሚበቃውን፡ ያኽል፡ አላድና፡ ሩብ፡ ተዐውን፡ መንግሥት፡ ራሱ፡ እየተዋዋለ፡ ከውጭ፡ አገር፡ በብር፡ ማተሚያ፡ ፋብሪኮች፡ እያሳተመ፡ ቢያስመጣ፡ መልካም፡ ነው።

ሦስተኛ፤ባንድ፡ መንግሥት፡ አገር፡ ሸረፋው፡ ከፍና፡ ዝቅ፡ እንዳይል፡ ዋናው፡ ነገር፡ ሕዝቡ፡ በቶሎ፡ እንዲገናኝ፡ በሁሉ፡ አገር፡ ደኅና፡ ደኅና፡

መንገድ፡ ማስበጀት፡ ነው። ደኅና፡ መንገድ፡ በሌለበት፡ አገር፡ ውስጥ፡ ግን፡ እያንዳንዱ፡ ሰው፡ የፈለገውን፡ ነገር፡ በቶሎ፡ እንዳይገበያይበት፡ የመንገዱ፡ ጕርፍ፡ እየከለከለው፡ በእጁ፡ ያገኘው፡ ሩብ፡ ተሙን፡ ብዙ፡ ጊዜ፡ ሥራ፡ ፈቶ፡ ይቀመጣል። የሚበዛው፡ ትንንሹ፡ የለውጥ፡ መሣሪያ፡ እንደዚሁ፡ በያለበት፡ ሥራ፡ ሲፈታ፡ መንግሥት፡ ያወጀው፡ ዐዋጅ፡ ምንም፡ ቢጠበቅ፡ የገበያው፡ ሽረፋ፡ ከፍና፡ ዝቅ፡ ማለቱ፡ አይቀርም።

# ፲፪ኛ፡ ምዕራፍ።

ከዚህ፡ ደም፡ እንዳየነው፡ ብርና፡ ወርቅ፡ ሳይለመዱ፡ ሰው፡ በከብትና፡ በጨው፡ ሲለዋወጥ፡ ሳለ፡ ከብቱ። ሲከሳበት፡ ወይም፡ በበሽታ፡ ሲሞትበት፡ ጨዉ.ም፡ በውሃና፡ በገናም፡ ሲመበት፤ልለወጥባቸው፡ ብሎ፡ ለገዛቸው፡ ሰው፡ ብዙ፡ ጕዳት፡ ነበረበት። ከዚህ፡ በኋላ፡ ቀጥሎ፡ ብረትና፡ መዳብ፡ የለወጥ፡ መሣሪያዎች፡ ሆኑ፡ ነገር፡ ግን፡ እነዚህም፡ ቢሆኑ፡ አንዳንድ፡ ጊዜ፡ ዋጋቸው፡ ዝቅ፡ ብሎ፡ ሽከማቸው፡ ግን፡ ከባድና፡ ባንድ፡ ሌሊት፡ ርጥበትም፡ ሲዝጉ፡ ለዘወትር፡ የለውጥ፡ መሣሪያ፡ ሆነው፡ ሊኖሩ፡ የማይመቹ፡ ሆነው፡ ተገኙ፤ከነዚህ፡ በኋላ፡ ቀጥለው፡ ብርና፡ ወርቅ፡ የለውጥ፡ መሣሪያዎች፡ ሆነው፡ በዓለም፡ ሁሉ፡ የታወቁ፡ ሆኑ።

ከምድር፡ ውስጥ፡ የሚገኘው፡ ብር፡ ከወርቁ፡ ይበዛልወዲያውም፡ ብር፡ ለመልቀም፡ የሚደከመው፡ ድካም፡ ያንሳል። ስለዚህም፡ ከወርቁ፡ ብር፡ በጣም፡ ይረከሳልና፤በያመቱ፡ እንደ፡ ተገኘው፡ ብር፡ ብዛት፡ መጠን፡ የብር፡ ዋጋ፡ ዘወትር፡ ከፍና፡ ዝቅ፡ ይላል። በምድር፡ ውስጥ፡ የሚገኘው፡ ወርቅ፡ ጥቂት፡ ስለ፡ ሆነና፡ ለመልቀመም፡ ቢሆን፡ የሚደከመው፡ ድካም፡ ብዙ፡ ስለ፡ ሆነ፡ የወርቅ፡ ዋጋ፡ እንደ፡ ብሩ፡ በቶሎ፡ ከፍና፡ ዝቅ፡ አይልም። የለውጥ፡ መሣሪያቸው፡ ብር፡ የሆነ፡ ሕዝቦች፡ ይህ፡ የብር፡ ዋጋ፡ ዘወትር፡ ከፍና፡ ዝቅ፡ በማለቱ፡ በብዙ፡ ይጐዳቸዋል።

አሁን፡ ለምሳሌ፡ አንድ፡ ነጋዴ፡ የሆነ፡ ሰው፡ ብር፡ በተወደደበት፡ ጊዜ፡ በእጁ፡ የነበረውን፡ ቆዳ፡ ለሺሕ፡ ብር፡ ቢሸጠው፤የሚሸጠው፡ ቆዳ፡ ኣቡጀዲ፡ ለመግዛት፡ ነበር። ነገር፡ ግን፡ ገና፡ አቡጀዲ፡ ሳይገዛ፡ ብሩ፡ ቢረክስ፡ በሺሕ፡ ብር፡ ሊገዛው፡ አስቦ፡ የነበረውን፡ አቡጀዲ፡ በሺሑ፡ ላይ፡

መቶ፡ ብር፡ ጨምሮ፡ ለመግዛት፡ ግድ፡ ይሆንበታል። ስለዚህ፡ ያ፡ ነጋዴ፡ በሺሕ፡ ብር፡ ብቻ፡ ሊገዛው፡ የነበረ፡ ዕቃ፡ ብር፡ ዋጋ፡ ስለ፡ ረከሰ፡ በሺሑ፡ ላይ፡ ጨምሮ፡ ሲገዛው፡ መቶ፡ ብር፡ መክሰሩ፡ ነው። በቀሩትም፡ ሕዝብ፡ ትዳር፡ እንደዚሁ፡ ነው። የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ በያመቱ፡ የሚሸጠው፡ ዕቃ፡ ዋጋ፡ ግምቱ፡ ወደ፡ ፫፡ ሚሊዮን፡ ብር፡ ይሆናል። በዚሁም፡ ገንዘብ፡ በያመቱ። ከውጭ፡ አገር፡ ዕቃ፡ ይገዛበታል። እንግዲህ፡ ባንደ፡ ድንገተና፡ ምክንያት፡ የብር፡ ዋጋ፡ ከመቶ፡ ፫፡ ዝቅ፡ ባለ፡ ቍጥር፡ ዱሮ፡ ባ፫፡ ሚሲዎን፡ ብር፡ ሲገዛው፡ የነበረ፡ የውጭ፡ አገር፡ ዕቃ፡ ሁሉ፡ በብር፡ ዋጋ፡ ቢታሰብ፡ ብሩ፡ ከመቶ፡ ፫፡ ከፍ፡ ባለበት፡ ጊዜ፡ ካ፫፡ ሚሊዮን፡ ብር፤፱፻፶፡ ሺሕ፡ ብር፡ ያስጨምራልና፤ከዚሁ፡ ምክንያት፡ የተነሣ፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ባንድ፡ ዓመት፡ ብቻ፡ ወደ፡ ፱፻፶፡ ሺሕ፡ ብር፡ ያኸል፡ ይከስራል።

ስለዚህ፡ ብዙ፡ ነገሥታት፡ የብር፡ ዋጋ፡ በያመቱ፡ ከፍና፡ ዝቅ፡ ሲል፡ ሕዝባቸው፡ እንደሚጐዳ፡ ተረድተውት፡ ባገራቸው፡ ውስጥ፡ ሰው፡ ሁሉ፡ በወርቅ፡ ሒሳብ፡ እንዲለዋወጥ፡ ደንብ፡ ደነቡ። እንደዚህ፡ ብለው፡ በደነቡት፡ ነገሥታት፡ አገር፡ ውስጥ፡ የብር፡ ወይም፡ የመዳብ፡ ገንዘብ፡ ቢኖር፡ የወርቍ፡ ምትክ፡ እየሆነ፡ ሥራውን፡ ይሠራል፡ እንጂ፤እንደ፡ ዋጋው፡ እያወጣ፡ አይደለም። ይህነን፡ ስላልነ፡ አንባቢው፡ እንዲረዳ፡ ቀጥሎ፡ የተጻፈውን፡ አስተውሎ፡ ያንብብ።

በ፲፱፻፲፯፡ ዓመተ፡ ምሕረት፡ በሰኔ፡ ፳፱፡ ቀን። የእንግሊዝ፡ መንግሥት፡ እንደ፡ ዐወጀው፡ ደንብ፡ ባገሩ፡ ውስጥ፡ ሰው፡ ሁሉ፡ ሲገበያይ፡ የዕቃው፡ ዋጋ፡ የሚለካበት፡ የለውጥ፡ መሣሪያ፡ ፓውንድ፡ እስተርሊንግ፡ ወይም፡ ጅኔ፡ የሚባል፡ ወርቅ፡ ነው። የዚህ፡ የጅኔ፡ ሚዛን፡ ፯፡ ግራም፡ ፺፫፡ ሺሕ፡ ፲፱፻፳፡ መቶ፡ ሺሕኛ፡ ግራም፡ ነው። በውስጡ፡ ያለው፡ ጥሩ፡ ወርቅ፡ ግን፡ ፯፡ ግራም፡ ፴፱፡ ሺሕ፡ ፱፻፴፱፡ መቶ፡ ሺሕኛ፡ ግራም፡ ነው። ስለዚህ፡ በጅኔው፡ ውስጥ፡ እንዲጠነክር፡ ተብሎ፡ ከወርቍ፡ ጋራ፡ የተደባለቀው፡ መዳብ፡ ፳፯፡ ሺሕ፡ ፯፻፳፯፡ መቶ፡ ሺሕኛ፡ ግራም፡ ነው። እንግዲህ፡ ባጭሩ፡ ብናመለክት፡ በያንዳንዱ፡ የእንግሊዝ፡ ጅኔ፡ ውስጥ፡ ፲፩፡ እጅ፡ ጥሩ፡ ወርቅ፡ ፩፡ እጅ፡ መዳብ፡ አለበት። ጅኔውም፡ ሲሠራ፡ ክፍሉ፡ ፫፡ ጅኔ፡ ፱፡ ጅኔ፡ ፩፡ ጅኔ፡ እኩሌታ፡ ጅኔ፡ እየሆነ፡ ይታተማል። ካ፩፡ ጅኔ፡ እኩሌታ፡ ያነሰ፡ የወርቅ፡ ገንዘብ፡ ለማተም፡ ግን፡ ወርቍ፡ እያነሰ፡ የማይመች፡ ስለ፡ ሆነ፤ሌላ፡ የብርና፡ የመዳብ፡ ተበጀ።

ጅኔው፡ በኻያ፡ ክፍል፡ ተከፍሎ፡ እያንዳንዱም፡ ኻያኛ፡ ክፍል፡ ሺሊንግ፡ ይባላል። ነገር፡ ግን፡ የወርቅ፡ ሺሊንግ፡ ከማነሱ፡ የተነሣ፡ እንኳን፡ ለማተም፡ በእጅም፡ ለመያዝ፡ አይመችምና፤የዚሁ፡ ትንሹ፡ ወርቅ፡ ምስል፡ እንዲሆን፡ ተብሎ፤የብር፡ ሺሊንግ፡ ታተመ። ስለዚህ፡ ዛሬ፡ በእንግሊዝ፡ አገር፡ አንዱ፡ ጅኔ፡ ለ፳፡ የብር፡ ሺሊንግ፡ ቢለወጥ፤ሺሊንጉ፡ የወርቁ፡ ወኪል፡ እንዲሆን፡ ስለ፡ ተደነባ፡ ነው፡ እንጂ፤በ፳ው፡ ሺሊንግ፡ ውስጥ፡ ያለው፡ ጥሬ፡ ብር፡ በእውነት፡ አንድ፡ ጅኔ፡ የሚያወጣ፡ ሁኖ፡ አይደለም። የብሩ፡ ሺሊንግ፡ ምልክት፡ ብቻ፡ ነው። ብርም፡ መሆኑ፡ ቀርቶ፡ መዳብ፡ ወይም፡ ነሐስ፡ ሆኖ፡ ቢሆን፤ያው፡ ነው። ሰውም፡ በእነዚህ፡ ገንዘብ፡ ሲለዋወጥ፡ ካሣ፡ ሺሊንግ፡ በላይ፡ ወርቅ፡ እንጂ፡ ብር፡ እንዳይቀበል፡ ሥርዐት፡ ተበጅቶለታልና፤ስለዚህ፡ በእንግሊዝ፡ አገር፡ አንዱ፡ ሰው፡ ከሌላው፡ ሰው፡ በማናቸውም፡ ምክንያት፡ የሚቀበለው፡ ገንዘብ፡ ቢኖረው፤በብር፡ ካ፵፡ ሺሊንግ፡ የበለጠ፡ መቀበል፡ የግድ፡ የለበትም። ሺሊንግም፡ ሲታተም፡ ፭፡ ሺሊንግ፡ ፪ተኩል፡ ሺሊንግ፡ ፪፡ ሺሊንግ፡ ፩፡ ሺሊንግ፡ እኩል፡ ሺሊንግ፡ የሺሊንግ፡ ፫ኛ፡ የሺሊንግ፡ ፬ኛ፡ የሺሊንግ፡ ፮ኛ፡ የሺሊንግ፡ ፲፪ኛ፡ እንደዚሁ፡ እየተከፋፈለ፡ ይታተማል። ባ፲፪፡ የሺሊንግ፡ ክፍል፡ ውስጥ፡ ያለው፡ ጥሩ፡ ብር፡ ግን፡ በጣም፡ አንሶ፡ ለመያዝ፡ የማይመች፡ ስለ፡ ሆነ፡ ወኪል፡ እንዲሆነው፡ ተብሎ፡ ቈርቈሮ፡ ዐይነት፡ አንድ፡ ገንዘብ፡ ለምስል፡ ታተመ። ስሙም፡ ፔኒ፡ ይባላል። ፔኒውም፡ ፩፡ ፔኒ፡ እኩል፡ ፔኒ፡ ሩብ፡ ፔኒ፡ እየሆነ፡ ይታተማል። ፲፪፡ ፔኒ፡ ባ፩፡ ሺሊንግ፡ ይለወጣልና፤ማንም፡ ሰው፡ ከዚሁ፡ ፔኒ፡ ከተባለው፡ የቈርቈሮ፡ ገንዘብ፡ ካ፩፡ ሺሊንግ፡ ዋጋ፡ በላይ፡ በግድ፡ መቀበል፡ የለበትም።

በጀርመንም፡ አገር፡ እንደዚሁ፡ ነው። ሰው፡ ሁሉ፡ ዕቃ፡ ሲገዛዛ፡ መተሳሰቢያው፡ በወርቅ፡ ነው። በዚያው፡ ነገር፡ ያለውም፡ የብርና፡ የነሐስ፡ ገንዘብ፡ ሁሉ፡ ለምልክት፡ ብቻ፡ ነው። የጀርመን፡ አገር፡ ገንዘብ፡ ማርክ፡ ይባላል። ከያንዳንዱ፡ ኪሎ፡ ግራም፤ጥሩ፡ ወርቅ፡ ፪፡ ሺሕ፡ ፯፻ኝ፡ አንዱ፡ ማርክ፡ ይታተማል። ማርኩም፡ ሲታተም፡ ፳፡ ማርክ፡ ፲፡ ማርክ፡ ፭፡ ማርክ፡ እየሆነ፡ ነው። ሲታተምም፡ ፱፡ እጅ፡ ጥሩ፡ ወርቅ፡ ፩፡ እጅ፡ መዳብ፡ እየሆነ፡ ነው።

ካ፳፡ ማርክ፡ በታች፡ ግን፡ ወርቅ፡ አንሶ፡ ለማተም፡ የማይመች፡ ስለ፡ ሆነ፡ ምስል፡ እንዲሆነው፡ ተብሎ፡ ከያንዳንዱ፡ ኪሎ፡ ግራም፡ ጥሩ፡ ብር፡ ሆኖ፡ ይታተማል። ይህም፡ ምስል፡ የሆነው፡ የብር፡ ገንዘብ፡ ፫፡ ማርክ፡ ፪፡ ማርክ፡ ፩፡ ማርክ፡ እኩል፡ ማርክ፡ የማርክ፡ ያ፡ ክፍል፡ እየሆነ፡ ይታተማል። ነገር፡ ግን፡ እያንዳንዱ፡ ሰው፡ ከሌላው፡ ሰው፡ የሚቀበለው፡ ገንዘብ፡ ቢኖረው፡ ከ፳፡ ማርክ፡ በላይ፡ በወርቅ፡ እንጂ፡ በብር፡ መቀበል፡ የግድ፡ የለበትም። ብር፡ ለሆነው፡ ገንዘብ፡ የለውጥ፡ መሣሪያ፡ ወኪል፡ እንዲሆን፡ የማርክ፡ አምስተኛ፡ ዐሥረኛ፡ ኻያኛ፡ ክፍል፡ ተብሎ፡ ነሐስ፤ የማርክ፡ አምስተኛ፡ የማርክ፡ መቶኛ፡ ተብሎም፡ የቈርቈሮ፡ ገንዘብ፡ ይታተማል። ነሐስና፡ ቈርቈሮ፡ የሆነውን፡ ገንዘብ፡ ሁሉ፡ ግን፡ ሰው፡ የሚቀበለው፡ እስካንድ፡ ማርክ፡ ብቻ፡ ነው። ከዚያ፡ በላይ፡ ግን፡ በብር፡ እንጂ፡ በነሐስና፡ በቈርቈሮ፡ የግድ፡ መቀበል፡ የለበትም።

እንሆ፡ በላይ፡ እንደ፡ ተጻፈው፡ እንደምናየው፡ የእንግሊዝ፡ መንግሥትና፡ የጀርመን፡ መንግሥት፡ ባገራቸው፡ ውስጥ፡ ሰው፡ በገንዘብ፡ ሲለዋወጥ፡ የለውጥ፡ መሣሪያ፡ ወርቅ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ደንብተውታል። ከወርቅ፡ በቀር፡ የለውጥ፡ መሣሪያ፡ የብርና፡ የነሐስ፡ የመዳብና፡ የቈርቈሮም፡ የወርቅ፡ ወኪል፡ ሆኖ፡ አስተሳስቦ፡ ሒሳቡ፡ ሲሞላ፡ ወርቅ፡ እንዲያሰጥ፡ ነው፡ እንጂ፤ርሱ፡ ራሱ፡ እንደ፡ ወርቅና፡ እንደ፡ ብር፡ ሆኖ፡ ዋጋ፡ ሊያወጣ፡ አይደለም።

እንግዲህ፡ ፊት፡ እንዳልነው፡ እያንዳንዱ፡ ሺሕ፡ ግራም፡ ጥሩ፡ ብር፡ ፪፡ ሺሕ፡ የብር፡ ማርክ፡ ይታተማል። በያንዳንዱ፡ የብር፡ ማርክ፡ በውስጡ፡ ያለው፡ ጥሩ፡ ብር፡ አምስት፡ ግራም፡ ብቻ፡ ነው። ባፄ፡ ምኒልክ፡ ብር፡ ውስጥ፡ ያለው፡ ጥሩ፡ ብር፡ ግን፡ ከ፳፡ ግራም፡ ይበልጣል። ስለዚህ፡ ማርክ፡ እንደውነተኛ፡ ዋጋው፡ የሚሸረፍ፡ ቢሆን፡ ለያንዳንዱ፡ ያፄ፡ ምኒልክ፡ ብር፡ ካ፬፡ ማርክ፡ ተኩል፡ በላይ፡ ይደርሰው፡ ነበር። ዛሬ፡ ግን፡ ያፄ፡ ምኒልክ፡ አንዱ፡ ብር፡ እጅግ፡ ቢበዛ፡ ለ፪፡ ማርክ፡ ብቻ፡ ይሸረፋል። እንደዚህ፡ የሆነበት፡ ምክንያት፡ ያፄ፡ ምኒልክ፡ ብር፡ በገበያ፡ ያለው፡ ዋጋ፡ የሚያወጣ፡ በውስጡ፡ ስላለው፡ ጥሩ፡ ብር፡ ነው። ማርክ፡ ግን፡ የወርቅ፡ ወኪል፡ ነውና፤፳፡ ሲሞላ፡ ፲፡ ግራም፡ ሺሕ፡ ፳፯፻፺፡ ዐሥር፡ ሺሕኛ፡ ግራም፡ ስሚከብድ፡ ጥሩ፡ ወርቅ፡ የሚለወጥ፡ ስለ፡ ሆነ፡ ነው።

ሽሊንግም፡ እንደዚሁ ባዬ፡ ምኒልክ፡ ብር፡ ሲለዋወጥ፡ ፪፡ ሽሊንግ፡ ፩፡ ብር፡ እየሆነ፡ ነው። በውስጡ፡ እንዳለው፡ ጥሩ፡ ብር፡ ሚዛን፡ ቢሆን፡ ግን፡ ለያንዳንዱ፡ ያዬ፡ ምኒልክ፡ ብር፡ ፬፡ ሽሊንግ፡ ተኩል፡ ሊሰጡበት፡ ይገባ፡ ነበር። ይህነን፡ ስላልነ ፥ አንባቢው፡ እንዲህ፡ ብሎ፡ ይጠይቅ፡ ይሆናል። በያንዳንዱ፡ ማርክ፡ ውስጥ፡ ያለው፡ ጥሩ፡ ብር፡ ጥቂት፡ ከሆነ፡ ስለ፡ ምን፡ ከፍ፡ ያለ፡ ዋጋ፡ ይሰጥበታል። የዚህ፡ ጥያቄ። መልሱ፡ ግን፡ እንዲህ፡ ነው። የብሩን፡ ማርክ፡ እያተመ፡ የሚያወጣ፡ የጀርመን፡ መንግሥት፡ ራሱ፡ ነው። ይህም፡ የጀርመን፡ መንግሥት፡ ባዋጁ፡ ፳፡ የብር፡ ማርክ፡ ይዞ፡ ለሚመጣ፡ ሰው፡ በፈለገው፡ ጊዜ፡ ፯፡ ግራም፡ ሺሕ፡ ጌየሣጌ፤ዐሥር፡ ሺሕኛ፡ ግራም ፥ በሚዛኑ፡ የሚከብድ፡ ጥሩ፡ ወርቅ፡ ከመንግሥት፡ ግምጃ፡ ቤት፡ እንዲቀበል፡ እዋሳለሁ፡ ብሏል። ስለዚህ፡ የጀርመን፡ መንግሥት፡ ስለ፡ ተዋሰ፡ እያንዳንዱ፡ የብር፡ ማርክ፡ የሚቀበል፡ ሰው፡ ፳፡ ማርክ፡ ሲሞላለት፡ ወርቅ፡ እንዲቀበል፡ ያውቃልና፤የብር፡ ማርክ፡ በገበያ፡ ዋጋ፡ ሲያወጣ፡ ስለ፡ ወርቅ፡ እየታሰበ፡ ነው። እንደዚሁም፡ በጀርመን፡ አገር፡ ውስጥ፡ ያለውን፡ የነሐስና፡ የቄርቄሮ፡ ገንዘብ፡ እያተመ፡ የሚያወጣ፡ የጀርመን፡ መንግሥት፡ ነውና፤ይህነን፡ የነሐስና፡ የቄርቄሮ፡ ገንዘብ፡ የሚቀበል፡ ሰው፡ ሒሳቡ፡ ሲሞላለት፡ የብር፡ ማርክ፡ ወይምየወርቅ፡ እንዲሰጠው፡ የጀርመን፡ መንግሥት፡ ተውሷል። ስለዚህ፡ በጀርመን፡ አገር፡ ያለው፡ የብርና፡ የነሐስ፡ የቄርቄሮም፡ ያለውን፡ መሣሪያ፡ ዕቃ፡ ሲገዛዛበት፡ ዋጋው፡ ዝቅና፡ ከፍ፡ የሚል፡ ወርቅ፡ ሲረክስ፡ ነው፡ እንጂ፤ የወርቅ፡ ዋጋ፡ ከፍና፡ ዝቅ፡ ካላለ፡ ዋጋው፡ አይነቃነቅም። ይህም፡ የሆነበት፡ ምክንያቱ፡ ወርቅ፡ እሰጣለሁ፡ ብሎ፡ የጀርመን፡ መንግሥት፡ ተውሷል፡ እያለ፡ ሰው፡ ሁሉ፡ ስላመነ፡ ነው።

የእንግሊዝ፡ መንግሥትም፡ ደንብ፡ እንደዚሁ፡ ነው። መንግሥት፡ ራሱ፡ እያተመ፡ ለሚያወጣው፡ የብርና፡ የነሐስ፡ የቄርቄሮም፡ ገንዘብ ፥ የእንግሊዝ፡ መንግሥት፡ ተውሷል። ፳፡ የብር፡ ሽሊንግ፡ ይዞ፡ ወደ፡ መንግሥት፡ ግምጃ፡ ቤት፡ የሚሄድ፡ ሰው፡ ሁሉ፡ ጅኔ፡ የሚባል፡ ወርቅ፡ በውስጡ፡ ፯፡ ግራም፡ ፴፪፡ ሺሕ፡ ፪የ፴፱፡ መቶ፡ ሺሕኛ፡ ግራም፡ ሚዛኑ፡ የሚከብድ፡ ጥሩ፡ ወርቅ፡ ያለውን፡ ገንዘብ፡ ይቀበላል። ፲፪፡ የቄርቄሮ፡ ፔኒ፡ ይዞም፡ ቢሄደ፡ የመንግሥቱ፡ ግምጃ፡ ቤት፡ አንድ፡ የብር፡ ሺሊንግ፡ ይሰጠዋል። ስለዚህ፡ የእንግሊዝ፡ መንግሥት፡ ከመታመኑ፡ የተነሣ፡

እያንዳንዱ፡ ሰው፡ የብር፡ ሽሊንግ፡ ወይም፡ ቈርቈሮ፡ ፔኒ፡ ሲቀበል፡ እንደ፡ ወርቅ፡ ይቈጥረዋል።

ስለዚህ፡ በእንግሊዝና፡ በጀርመን፡ አገር፤ሁሉ፡ ሲገዛ፡ የሚተሳሰብበት፡ በወርቅ፡ ነውና፤ከምድር፡ የሚገኘው፡ ወርቅ፡ ጥቂት፡ ሆኖ፡ የወርቅ፡ ዋጋ፡ የማይንቀሳቀስ፡ ስለ፡ ሆነ፡ ሰው፡ ሁሉ፡ የሚለዋወጥበት፡ የለውጥ፡ መሣሪያ፡ ከመርከሱ፡ የተነሣ፡ ሕዝቦቻቸው፡ አይጐዱባቸውም።

ስለዚህ፡ የኢትዮጵያ፡ መንግሥትም፡ ቢሆን፡ ሕዝቡ፡ እንዳይጐዳበት፡ ቢፈልግ፡ ያገሩን፡ ሕዝብ፡ የሚተሳሰብበት፡ የለውጥ፡ መሣሪያ፡ ወርቅ፡ እንዲሆን፡ ቢጥርበት፡ መልካም፡ ነበር። ይህነኑ፡ ለመጣር፡ ፈቃዱ፡ እንደ፡ ሆነ፡ እንዴት፡ ያለ፡ ደንብ፡ ለማውጣት፡ እንደሚገባው፡ ለይተን፡ በዚሁ፡ መጽሐፍ፡ ውስጥ፡ ለመናገር፡ ጊዜ፡ አይሰጠንም። ደግሞም፡ የደንብ፡ አውጮች፡ ሥራ፡ ነውና፤የሕዝብ፡ አስተዳደር፡ በሚባለው፡ መጽሐፍ፡ ውስጥ፡ ቢገባ፡ ትክክለኛ፡ ቦታው፡ አይደለም። ያገራችን፡ መንግሥት፡ ባገሩ፡ የለውጥ፡ መሣሪያ፡ መሠረቱ፡ ወርቅ፡ እንዲሆን፡ ቢፈልግ፡ ካንዳቸው፡ የኤሮፓ፡ ነገሥታት፡ የገንዘብ፡ ፍትሐ፡ ነገሥት፡ ኣስመጥቶና፡ አስተርጕሞ፡ መንገዱን፡ አይቶ፡ ላገሩ፡ የሚመቸውን፡ የገንዘብ፡ ደንብ፡ ማውጣት፡ ይቻለዋል።

**ተፈጸመ።**

# ላንባቢው፡ ማስታወሻ።



## ከባላምባራስ፡ አሸብር፡ ገብረ፡ ሕይወት፡ የተጻፉ፡

፩ኛ፤ የኪዳነ፡ ቃል፡ ቲያትር፡ ፲፱፻፵፫፡ ዓ፡ ም፡

በአርቲስቲክ፡ ማተሚያ፡ ቤት፡ ታተመ።

፱ኛ፤የንግሥተ፡ ኣዜብ፡ ታሪካዊ፡ ጕዞ፡ ፲፱፻፶፩፡ ዓ፡ ም፡
በንግድ፡ ማተሚያ፡ ቤት፡ ታተመ።
፲ኛ፤ፍቅር፡ አያረጅም፡ ፲፱፻፶፱፡ ዓ፡ ም፡
በንግድ፡ ማተሚያ፡ ቤት፡ ታተመ።



## ስለደራሲው በጥቂቱ

ነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ በ1879 ዓ.ም. በአድዋ አካባቢ ተወለዱ፡፡ ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ ኤርትራ ውስጥ በሚገኘው የሲዊድን ሚሽን ከተማሩ በኋላ ወደ ጀርመንና አውስትራሊያ በመሄድ የሕክምና ትምህርታቸውን አጠናቀቁ፡፡ ከጀርመን ሚሽን ጋር ወደ ኢትዮጵያ በመመለስ በዓፄ ምኒልክ ቤተመንግሥት ፀሐፊ በመሆን ሠርተዋል። የምኒልክ ሐኪም ለነበረው ጀርመናዊ ዶክተር አስተርጓሚ ሆነው ሲያገለግሉ ከእቴጌ ጣይቱ ጋር በነበራቸው አለመግባባት አገር ለቀው ወደ ሱዳን ተሠደዱ፡፡ ከዛም ለሱዳን መንግሥት የሀገር ውስጥ ደኅንነት ሲሠሩ ቆይተው ወደሀገራቸው በመመለስ በቤተመንግሥት ውስጥ ማገልገል ጀመሩ፡፡ በመቀጠልም የድሬዳዋ ጉምሩክ ኃላፊ ሆነው ተመድበው በራስ ተፈሪና በሌሎች ተቀናቃኞች ወገኖች ተፈጥሮ በነበረው ግጭት ራስ ተፈሪን ወግነሀል በሚል ከኃላነታቸው ተነሱ፡፡

እኚህ የኢኮኖሚ ፈላስፋና የሕክምና ምሁር በ1912 ዓ.ም. በኅዳር በሽታ ሕይወታቸው ቢያልፍም "መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር" በሚለው ዝነኛ መጽሐፋቸው የሀገሪቱን የውስጥ ጉዳይ አስተዳደርና ኢኮኖሚ እንዲሁም በትምህርት ላይ ፍጹም ለውጥ እንዲኖር አሳስበዋል፡፡ መጽሐፋቸው ለመጀመሪያ ጊዜ የታተመው በአቶ ጳውሎስ ኞኞ አማካይነት ነው፡፡

## የደራሲው ሥራዎች

1. ዐፄ ምኒልክና ኢትዮጵያ(ታሪክ)

2. መንግስትና የህዝብ አስተዳደር

# “ዐፄ ምኒሊክና ኢትዮጵያ”

ነጋድራስ ለመንግስትና ለህዝባቸው በርካታ ምክሮችን በመጀመሪያው “አጤ ምኒሊክና ኢትዮጵያ” በተሰኘው መጽሀፍ ላይ ያሰፈሩ ሲሆን በመጀመሪያ ምክሮቹ ለአጤ ምንሊክ የታቀዱ የነበሩ ቢሆንም በኋላ ግን ምክሮቹ ለልጅ እያሱ እንዲሆኑ በሚል ጽፈዋቸዋል። መጽሀፉ አጭር ሲሆን ትልልቅና ቁልፍ ጉዳዮችን አንስተዋል። ነጋድራስ ካነሷቸው ቁልፍ ምክሮች ውስጥ ጥቂቶቹን እናነሳለን።

ታላቁ ምሁር ነጋድራስ ገብረህይወት ከመቶ አመት በፊት በጻፉት በዚህ አስደናቂ መጽሀፋቸው ለአንድ ህዝብ ስርአት ወይም ሲስተም እንደሚያስፈልግ ሲገልጹ “የሀይል ምንጭ ሥርአት ነው እንጅ የሰራዊት ብዛት አይደለም” ብለዋል። ላለመሰልጠናችንና ላለማደጋችንም በአስተሳሰብ ባለመብሰላችን መሆኑን ሲገልጹ ደግሞ እንዳሉት “እኛ ኢትዮጵያውያን ካለመስማማታችን የተነሳ ሌሎች ህዝቦች በአእምሮና በጥበብ እየበረቱ ሲሄዱ እኛ ወደ ኋላ ቀረን” ነበር (ነጋድራስ ገ/ሕይወት 2003፣ 19)።

በሚገርም ሁኔታ ነጋድራስ ገብረህይወት ከመቶ አመት በፊት የጠቀሱት ጉዳይ ነገር ግን እኛን አሁን በደንብ የሚገልጸን የሚከተለው ገለጻቸው ነው።

በመላው አለም ላይ ሰላም ሲሰፋ አእምሮም ስትበራ እኛ በጨለማ እንኖራለን። እርስ በርሳችን መጠራጠራችንንም አልተውንም። ህዝቦቹም ሁሉ እርስ በርሳቸው በፍቅር ተቃቅፈው ስለልማታቸው ባንድነት ሆነው ሲደከሙ እኛ ግን ዘርና ወንድማማች መሆናችንን ገና አልተገለጸልንም። እርስ በርሳችን መፋጀትም እስከ ዛሬ ድረስ ጀግንነት ይመስለናል። ስለዚህ እግዚያብሄር ለብርታት የሚሆነውን ስጦታ ሁሉ ሰጥቶን ሳለ ባለቤቶቹ ሰነፍነ። ለሌሎቹም ነገስታት እንደ ሰነፎች ይቆጥሩናል፣ ይንቁናልም (ነጋድራስ ገ/ሕይወት ባይከዳኝ 2003፣ 19-20)።

ነጋድራስ ገብረህይወት የድህነታችንን ምክንያት ሲገልጹ የሚከተለውን አስቀምጠዋል።

ህዝቡም ሀብታም የሆነ መንግስት ብርቱ ነው። ህዝቡ የደኸየ እንደሆነ ግን ደካማ። እኛ ግን ስርአት የለንም። ስለዚህ ሰነፍን። በመሬታችን ውስጥ የተሸሸገውም ሀብት ፈላጊ አጣ፤ስለዚህም ደኸየን... ምነው የኢትዮጵያ ህዝብ ከእንቅልፍህ መቸ ትነሳለህ? (ነጋድራስ ገ/ሕይወት ባይከዳኝ 2003፣ 22)።

ጽሁፍ ለማህበረሰብ እድገት መሰረታዊ መሆኑን ሲገልጹ እንዳሉት "የተጻፈ ስርአት የሌለው መንግስት ብዙ እድሜ የለውም" (ነጋድራስ ገ/ሕይወት ባይከዳኝ 2003፣ 25)።

ከሁሉም በላይ ለዚህ ዘመን ነዋሪ እጅት በጣም የሚያስገርመው የነጋድራስ ገብረህይወት ሀሳቦች ውስጥ የሚጠቀሰው ስለሃይማኖት የጻፉት ነው። የሀይማኖት ነጻነት መኖር እንዳለበትና ሀይማኖት ከልብ የሆነ መሆኑንና ዳኛውም ፈጣሪ መሆኑን የገለጹበት መንገድ አስገራሚ ነው።

ደግሞም ባገራችን አንድ የድንቁርና ነገር አለ። ሃይማኖቱ ተዋህዶ ያልሆነ ሁሉ እንደ ርኩስ ይቆጠራል። ይህም እጅግ ያስቃል። አእምሮ የሌለው ህዝብ ሁሉ የእግዚያብሄርን ቃል ሳያውቅ የእግዚያብሄር ጠበቃ ሊሆን ይወዳል። ... ሀይማኖት የልብ ነው። ስለዚህ ሰማያዊው ንጉስ አንጅ የዚህ አለም ንጉስ አይቆጣጠረውም (ነጋድራስ ገ/ሕይወት ባይከዳኝ 2003፣ 28)።

ስለርእዮተ አለም ሲመከሩ ነጋድራስ ይህንን ብለው ነበር "ኢትዮጵያችን የኤሮጳን አእምሮ የተቀበለች እንደሆነ የሚደፍራት ጠላት የለም። ያልተቀበለች እንደሆነ ግን ትፈርሳለች፤ወደ ባርነትም ትገባለች" (ነጋድራስ ገ/ሕይወት ባይከዳኝ 2003፣ 28)።

በስተመጨረሻ የመጀመሪያውን መጽሀፍ ያገባደዱት "መንግስታችንም እንድትቀና የሚከተሉት አሥር ነገሮች በቶሎ ቢፈጸሙ ማለፊያ ነበር" (ነጋድራስ ገብረህይወት፣ 2003፡ 23-27) ያሉትን በማቅረብ ነበር።

1. ለመንግስት የሚሆን ገንዘብና ለንጉሱ የሚሆነውን ገንዘብ በሥርአት ይለይ። ሹሞቹም በደሞዝ ይደሩ። ካገር የሚወጣውም ግብር ለመንግስት ይግባ።
2. ሕዝቡ ለመንግስት የሚከፍለው ግብር እንደየሀብቱ መጠን ቁርጥ ሁኖ ይታወቅለት። የሕዝቡም ቁጥር በመዝገብ ይግባ። እንዲሁም በየአመቱ የሚወለደውና የሚሞተውም የሚጋባውና የሚፋታውም በመዝገብ ይታወቅ።
3. ሕዝቡም የሚከፍለው ግብር በብር እንጅ በእህል በማርም በፍሪዳም አይሁን። የመንግስት ስራ ሁሉም በባላገር አይሰራ፤ በባለ ደሞዝ እንጅ።
4. ያማርኛ ቋንቋ ገና ሰዋሰው አልተበጀለትም። ስለዚህ መንግስታችን ከያገሩ ሰዋሰው የሚያዉቁትን ሊቃውንት ሰብስቦ ያማርኛን ቋንቋ ሰዋሰው ቢያስወጣ ደግ ነው። … ያገራችን ሰው ፊደልን ለመማ ቢተጋ አገራችን ቶሎ በቀናች። ፊደልንም መማር እጅግ ቀላል ነገር ነው።
5. ፍትሐ ነገሥታችን (ህጋችን) ከዛሬው ያደባባይ ሥርአት ጋር አይስማማም። ስለዚህ መንግስት የሥርአት አዋቆችን ሰብስቦ ከኤሮጳ ሥርአት ጋር የተስማማ ፍትሐ ነገስት ያውጣ።
6. ያገራችን ሰራዊት ስርአት የለውም። ስለዚህ የኤሮጳን መኳንንት አምጥተው ሰልፍን ቢማር ማለፊያ ነበር። እንዲሁም የኤሮጳን መምህራን አምጥተው ባዲስ አበባ ላይ የጦር ትምህርት ቤት ይበጅ።
7. የዛሬው የመንግስታችን ብር የተበላሸ ነው። ሥርአት ውል የለውም። ስለዚህ መንግስት ለመላው ኢትዮጵያ የሚሆን የገንዘብ ሥርአት በቶሎ ያላወጣ እንደሆነ ንግድ ሊለማ አይችልም።
8. ላገራችን ነጋዴ ሥርአት እስኪወጣለት ድረስ መንግስታችን አይቀናም። በሩና (ኬላው) ቀራጩ ብዙ ነው። በአንድ መንግስት ውስጥ አንድ ነጋዴ በየበሩ መቀረጥ የለበትም።
9. ህዝቡ ባንድ መንግስት ውስጥ መሆኑን አጥብቆ እንዲታወቀው አገሩን የሚዞሩ ተቆጣጣሪዎች ይሾሙበት።

10. የሀይማኖት አርነት ይታወጅ። የሃይማኖት አርነት ቢታወጅ ሃይማኖት ይታወቃል እንጅ አያጠፋም። ሃይማኖት የልብ ነገር ነው። ስለዚህ ሰማያዊው ንጉስ እንጅ የዚህ ዓለም ንጉስ አይቆጣጠረውም።
11.

# "መንግስትና የህዝብ አስተዳደር"

ሁለተኛው መጽሀፍ "መንግስትና የህዝብ አስተዳደር" ሰፋ ያለ ሲሆን ደራሲው በርካታ ቁልፍ ጉዳዮችን አንስተዋል። ይህ መጽሀፍ ኢኮኖሚክስ፣ ገንዘብ፣ ንግድና የመሳሰሉ ጉዳዮችን ይዳስሳል። ለሁሉም ነገር ቁልፉ ትምህርት እንደሆነ ሲገልጹ ይህንን ብለዋል "መንግስት ሀይል ለማግኘት የፈለገ እንደሆነ ህዝቡ እንዲበለጽግና እንዲማር መጣር ያስፈልገዋል" (ነጋድራስ ገብረህይወት 2003፣ 36)።

ስለዋጋ ሲናገሩ "ዋጋ ማለት የስራ መለኪያ ማለት ነው" (ነጋድራስ ገብረህይወት 2003፣ 68)። የኑሮውድነትና ጫናን ለመቀነስ እውቀት ቁልፍ እንደሆነ ነጋድራስ እኛን የመከሩን ከመቶ አመት በፊት እንደዚህ ብለው ነው "እውቀት ሲበዛ ለኑሮ የሚያስፈልገውን ማናቸውንም ነገር ለማግኘት መሰናከሉ ያንሳልና የማናቸውም ዋጋ ሁሉ ዝቅ ይላል" (ነጋድራስ ገብረህይወት 2003፣ 71)። ትምህርት ለአንድ ህዝብ የጀርባ አጥንት መሆኑን ሲገልጹ "ህዝቡ እንዳይጎዳ የሚፈልግ መንግስት ሁሉ አውራ ጥረቱ ትምህርት እንዲበዛ ነው" (ነጋድራስ ገብረህይወት 2003፣ 75)።

ነጻነት በእውቀትና በትምህርት የሚገኝ መሆኑን ሲገልጹ "ሰው በአለም ላይ ጌታ የሆነው ግን በእውቀቱ ብቻ ነው። … እውቀት የሌለው ህዝብ ሁሉ ለብቻው መንግስት ቢኖረውም ባይኖረውም እውቀት ላቸው ህዝቦች ይገዙታል" (ነጋድራስ ገብረህይወት 2003፣ 75)። እውቀት ለሰው ልጅ መበልጸጊያና ማደጊያ መሰረታዊ መሳሪያ መሆኑን ሲያሰምሩ "እውቀት አለምን እንዲገዛ የማይነቃነቅ ዘላለማዊ ደንብ ነው" ብለዋል።

በተጨማሪም ደራሲው የሰው ልጅ ሲፈጠር ጌታና ሎሌ እንዲሆን እንዳልነበረ አጽንኦት ሰጥተው አብራርተዋል። ፈጣሪ የሰውን ልጅ በምድር ሲያስቀምጥ የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ አሟልቶለት እንደሆነም በሚመስጥ አገላለጽ ገልጸውታል "ለሰው የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ ምድር በሆዷ ይዛለች። ... ማናቸውንም ነገር ሲፈልግ አንቀሳቅሶ ማጋጠም ብቻ ነው ያለበት። ማንቀሳቀስና ማጋጠም የሚሆነው በስራ ነው። ስለዚህ የሰው እውቀቱና ገንዘቡ ስራ ብቻ ነው" ይሉናል (ነጋድራስ ገብረህይወት 2003፣ 80)።

በእውቀት፣ በስራና በጥረት ላይ የተመሰረተ ለውጥን የሚያቀነቅኑት አስገራሚው ነጋድራስ ገብረህይወት "ሰውም ምድርን የሚገዛበት ምክንያት በእውቀት ነው እንጅ በጉልበት አይደለም" ያሉን ከ100 አመት መሆኑ ነገር ግን እና እስካሁን አዲስ ነገር እየሆነብን መሆኑ ይገርማል። እሳቸው ግን አበክረው "እውቀት የሌለው ህዝብ ሀብታም ሊሆን አይችልም" ብለውናል (ነጋድራስ ገብረህይወት 2003፣ 83)።

የሰው ልጅ ምድርን ለመግዛት እንጅ በምድር ለመገዛትና የምድር ሎሌ ለመሆን እንዳልተፈጠረ ያስረዳሉ። ነገር ግን ደሀ ከሆንን ሌላ አማራጭ አይኖረንም። ይህንንም በአሳማኝ ሁኔታ ሲያቀርቡት እንደዚህ በማለት ነው "ድሀ የሆነ ህዝብ የምድር ሎሌ ነው። በረሀብና በበሽታ በሞት ስታንገላታው ትኖራለች። ሀብታም ህዝብ ግን የምድር ጌታ ነውና ምድር ሎሌ ሆኖ ታገለግለዋለች" (ነጋድራስ ገብረህይወት 2003፣ 84)።

ሌላው አስገራሚው የገብረሂወት ገለጻ ስለሀብት የሰጡት ነው። "ሀብት ማለት የተከማቸ ስራ ማለት ነው። ... እውቀት የሌለው ህዝብ ግን ሥራው አይከማችለትም። የፊት የፊቱ ወዲያው ያልቃል። ከድካሙም ፍሬ የሚያገኘው ጥቅም ጥቂት ነው። ስለዚህ እውቀት የሌለው ህዝብ ድሀና የሰው ሎሌ ነው" (ነጋድራስ ገብረህይወት 2003፣ 94)።

ከውጭ ስለሚመጡና ስለምንገዛቸው ቁሶች ሲገልጹ "እውቀት ያነሳቸው ህዝቦች እውቀታቸው ከፍ ካለ ህዝቦች ላይ እቃ ሲገዙ እየተበደሩ ነው። የሚበደሩትም ብድር እኩሌታው ከጉልበታቸው እኩሌታው

ከምድራቸው ነው" ይሉናል። ነጻነት ስላለው ህዝብ የሚከተለውን ማብራሪያ በመግለጽ ስለሀገራችን ነጻ መሆን ይጠይቃሉ

እስቲ አሁን እኛ የኢትዮጵያ ህዝብ አርነት አለን ነው? አርነት ያለው ህዝብ ማለት እውነተኛ ትርጉሙ ለብቻው መንግስት ያለው ህዝብ ማለት ብቻ አይደለም፤ራሱን የቻለ ህዝብ ማለት ነው እንጅ። የኢትዮጵያ ህዝብ እስከ ዛር ድረስ ገና ራሱን አልቻለም። እስቲ የለበስነውን እንይ፤ከወዴት የተሰራና ማን ያመጣው ነው? የቤታችንስ እቃ ራሱ ከወዴት የመጣ ነው? የምንለብሰውስ ልብስ የምንጠጣውስ የምንበላበት ምግባችንን የምናበስልበት እቃና መስሪያ ሁሉ ፈጽሞ ከውጭ አገር የመጣ አይደለምን?" (ነጋድራስ ገብረህይወት 2003፣ 102)።

የሀገር ሀብት የሚያንሰው ከሰሪው ይልቅ በላተኛው ሲበዛ መሆኑን ገልጸው ለሀገር ብልጽግና ሲባል እውቀት ብቻ ሳይሆን ሀብትም እንደሚያስፈልግ አበክረው እንደሚከተለው ይመክራሉ "የዚህ አለም ህዝቦች የለውጥ መሳሪያዎቻቸው ብርና ወርቅ ብቻ ስለሆኑ ብርና ወርቅ ያነሰበት ህዝብ ከፍ ወዳለው የእውቀት ደረጃ ደርሶ ሀብታም ሊሆን አይችልም" (ነጋድራስ ገብረህይወት 2003፣ 131)። በተጨማሪም መሰረታዊ ፍላጎቱን ያላሟላ ህዝብ የሀገር ፍቅር እንደማይኖረው በማሳሰብ የህዝብን ፍላጎት ማሟላት ለሀገር ደህንነት ቁልፍ ሚና እንዳለው በዚህ መልኩ ይነግሩናል "የሚበላውና የሚለብሰውንም ያጣ ድሀ የተወለደበትን አገር የሚወድበትን ምክንያት ያጣልና ያገሩ መንግስት ቢበረታ ወይም ቢጠፋ ግድ የለውም፤ስለዚህ መንግስት የሚጠቁም ያገሩ ሀብት በጥቂቶች ሰዎች እጅ ቢሰበሰብ አይደለም። ያገሩን ሀብት በመላው ህዝቡ ሊከፋፈል ነው አንጅ" (ነጋድራስ ገብረህይወት 2003፣ 142)።

ስርአት ወይም ሲስተም ከህዝብ ፍላጎት መመንጨት እንዳለበት ሲያብራሩ እንዳሉት "ስርአት የሚመች ይሆናል ተብሎ በብልሆች ሰዎች ልብ ውስጥ ተፈጥሮ አይጻፍም፤ከህዝብ ልብ ቀዳል እንጅ። ንጉስ ወይም ሹም በኋለኞች ትውልዶች የሚመሰገንም በልቡ ፈልስፎ ደንብ ሲያወጣ አይደለም። የህዝቡን አሳብ ተርጉሞ በትርጉሙ ሲሄድ ነው እንጅ" (ነጋድራስ ገብረህይወት 2003፣ 147)።

የህዝብና መንግስት መሰረት ትምህርት ቤት መሆኑን ያሰመሩበት ነጋድራስ ገብረህይወት "ትምህርት የሌለበት አገር አዲስ ደንብ ቢያወጣ ከሚጠቅመው የሚጎዳው ይበልጣል" ብለዋል (ነጋድራስ ገብረህይወት 2003፣ 148)።

ስራን በመስራት ሀብት ለማካበት በምንጥርበት ወቅት መተማመን ቁልፍ ሚና እንዳለው ገልጸዋል። ብር የለውጥ መሳሪያ እንጅ ሌላ ፋይዳ ያለው ነገር እንዳልሆነ አስገንዝበዋል። የሰው ልጅም መልካምና መጥፎ ባህሪ እንዳለው ሲገልጹልን "የሰው ባህሪው ሁለት ነው። አንዱ መለኮታዊ፤ ሁለተኛው ግን እንስሳዊ ይባላል። ቀስቃሽ ካላገኘ ግን ሰው መልአካዊ ባህሪውን አይከተልም። ወደ እንስሳዊ ባህሪው ያደላል። ለሰው አውራ ቀስቃሽ ግን ባላንጣ ነው" (ነጋድራስ ገብረህይወት 2003፣ 164)።

አንድ መንግስት አማካሪ እንደሚያስፈልገው የሚያመለክት አንድ ተጨባጭ ምክር በባንክ ዙሪያ የሚከተለው ተገልጧል

ዛሬ በኢትዮጵያ የቆመው ባንክ አፍ አቢሲን ከቆመበት ቀን ዠምሮ እስከ ሀምሳ አመት ድረስ በኢትዮጵያ ሌላ ባንክ እንዳይቆም ውል ተቀብሏል። ከዚህ ቀደም እንደተረዳነው ግን ማናቸውም ነገር የጥቂቶች ሰዎች እጅ ገብቶ ሞኖፖል ሲሆን ለህዝብም ለመንግስትም ጉዳት ው። ለአጼ ምኒሊክ አንድ ሰው መጥቶ ባገርዎ ከኔ በቀር ሌላ ሰው እንዳያርስ ወይም በቅሎ ገዝቶ እያከራየ እንዳይነግድ ወይም እኔን ሳይጠይቅ በየቤቱ ማንም ወጥ እየሰራ እንዳይበላ ፈቃድ ይስጡኝ ብሎ ለምኗቸው ቢሆን የሚያናግራቸው ቃል ምንም ቢያምር የሰጣቸው ተስፋ ምን ትልቅቢሆን ያለጥርጥር ይቆጡት ነበር (ነጋድራስ ገብረህይወት 2003፣ 163)።

መንግስትና የህዝብ አስተዳደርን በተመለከተ ሀሳባቸውን በሚከተሉት በአስር ነጥቦች አጠቃለው አስቀምጠዋል (ነጋድራስ ገብረህይወት 2003፡ 124-126)።

1. ሰው የተፈጠረ የምድር ጌታ ለመሆን ነበር፤ነገር ግን በመዠመሪያ ጥቂት እራሱን ስለ ሆነ የሚበቃ መሳሪያ የለውምና የምድር ተገዥ ሆነ።

2. በኋላ ግን እውቀት ስላገኘ ተባዛ ተባበረም።
3. በዝቶ ከተባበረም ዘንድ ሥራውን ተከፋፍሎ የሰራውን ሥራ እንደየስራው መጠን መለዋወጥ ዠመረ፣ ዋጋ ማለት የስራ መለኪያ ነው እንዳልነው ሁሉ።
4. ሀብት ማለት የአለም ጌትነት መለኪያ ነው። ማንቀሳቀስና ማጋጠም የሚሆነው በስራ ብቻ ነውና ሀብት ማለት የተከማቸ ስራ ማለት ነው።
5. ማንኛውም የተሰራ ስራ ከኋላ የሚከተለውን ስራ ያቀላል። ማንኛውንም ሀብት የበለጠ ሀብት ይከተለዋል።
6. የህዝብ ሀብት የሚሰፋው ህዝቡ የሚያስፈልገውን ሁሉ ለመስራት ስራውን በብዙ ተካፍሎ የተለዋወጠ እንደሆነ ነው።
7. የድካማቸውን ፍሬ የሚለዋወጡ ሰራተኞች እንዲቃረቡ መንገስት መጣር ይገባዋል።
8. መንገድና የምድር ባቡርም ጥቅም ሚሆነው የስራ ማሰልጠኛ የትምህርት ቤቶች በያይነቱ ሲሰራና ማናቸውም እቃ ሁሉ እንደሚቻል መጠን ባገሩ ውስጥ እንዲበጅ መንግስትም ሲጥርበት ነው።
9. መሬቱ በጥቂቶች ሰዎች እጅ የገባ ህዝብ በጣም ይደኸያል። የባላገሩ ጥቅም እያነሰ ይሄዳል፣ መሬትም ይረከሳል።
10. የመንግስት መሰረት እርሻ ነው። ባለእርሻ የሚያገኘው ጥቅም ሲያንስ የመንግስት መሰረት አይጠናም። ባለእርሻ ሺፀቀም ግን መንግስትም ይጠነከራልና ይበረታል።

ነጋድራስ ገብረህይወት ባይከዳኝ ከመቶ አመታት በፊት ያስቀመጧቸው እነዚህ ቁልፍ ቁልፍ ሀሳቦች በአሁኑ ሰአት ብንተገብራቸው ራሱ ብዙ እናተርፋለን። በጣም መነበብ ያለበት ምርጥ መጽሀፍ ነው።



# ስለደራሲው በጥቂቱ

ነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ በ1879 ዓ.ም. በአድዋ አካባቢ ተወለዱ፡፡ ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ ኤርትራ ውስጥ በሚገኘው የሲዊድን ሚሽን ከተማሩ በኋላ ወደ ጀርመንና አውስትራሊያ በመሄድ የሕክምና ትምህርታቸውን አጠናቀቁ፡፡ ከጀርመን ሚሽን ጋር ወደ ኢትዮጵያ በመመለስ በዓፄ ምኒልክ ቤተመንግሥት ፀሐፊ በመሆን ሠርተዋል። የምኒልክ ሐኪም ለነበረው ጀርመናዊ ዶክተር አስተርጓሚ ሆነው ሲያገለግሉ ከእቴጌ ጣይቱ ጋር በነበራቸው አለመግባባት አገር ለቀው ወደ ሱዳን ተሠደዱ፡፡ ከዛም ለሱዳን መንግሥት የሀገር ውስጥ ደኅንነት ሲሠሩ ቆይተው ወደሀገራቸው በመመለስ በቤተመንግሥት ውስጥ ማገልገል ጀመሩ፡፡ በመቀጠልም የድሬዳዋ ጉምሩክ ኃላፊ ሆነው ተመድበው በራስ ተፈሪና በሌሎች ተቀናቃኞች ወገኖች ተፈጥሮ በነበረው ግጭት ራስ ተፈሪን ወግነህል በሚል ከኃላነታቸው ተነሱ፡፡

እኚህ የኢኮኖሚ ፈላስፋና የሕክምና ምሁር በ1912 ዓ.ም. በኅዳር በሽታ ሕይወታቸው ቢያልፍም “መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር” በሚለው ዝነኛ መጽሐፋቸው የሀገሪቱን የውስጥ ጉዳይ አስተዳደርና ኢኮኖሚ እንዲሁም በትምህርት ላይ ፍጹም ለውጥ እንዲኖር አሳስበዋል፡፡ መጽሐፋቸው ለመጀመሪያ ጊዜ የታተመው በአቶ ጳውሎስ ኞኞ አማካይነት ነው፡፡

## የደራሲው ሥራዎች

1. ዐፄ ምኒልክና ኢትዮጵያ(ታሪክ)
2. መንግስትና የህዝብ አስተዳደር

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY